# የቤተክርስቲያን ቅድሜ  መከራ ንጥቀት

# አስተምህሮ በቃለ እግዝአብሔር ስመዘን

ቅጽ.1

እድሉ ዮሐንስ ጋምሳ

# ምስጋና

በውነት ታናሽነቴን ሳይንቅ የእርዳታ ጥሪዬን ተቀብሎ የረዳኝን የደገፈኝን የመከረኝን ወንድም ዛድግ ብርሃኑን ከልብ አመሰግናለሁ ፤ለምልምልኝ። ለመተባበር ፈቃደኛ ኾናችኹ ጊዜ በማጣታችኹ ልትተባበሩኝ ስላልቻላችኹ ወንድሞቼ] ታላቅ አክብሮት አለኝ፤ ክበሩልኝ። ደገሞም የፊደል አጠቃቀም ግድፈትና የንባብ ፍሰትን ችግሮችን ተረድታችኹ በትዕግሥት አንብባችሁ ሃሳቡን ስለሚትይዙ አንባቢያን ልባዊ ምስጋና አለኝ። ከኹሉም በላይ ይህችንም የሰጠኝ ጌታ ለዘላለሙ ይባረክ።

ለሃሳብ ለአስተያየት

email፡- ediluyohannes16gmail.com

ቴለግራም ገጼን፡- በአማርኛ ״ቀጥተኛ እምነት״ በማለት ይጎበኙ

**ማውጫ** **ገጽ**


መግቢያ ......................................................................................4

ምዕራፍ አንድ

1. የራዕይ መጽሐፍ ይዘት ...............................................................6

1.1 አኹን ያለው ...............................................................................7

1.2 ከዚህ በኋላ የሚኾነው ...............................................................30

1.2.1 አንደኛው መግለጫ ...............................................................37

1.2.2 ኹለተኛው መግለጫ ...............................................................40

1.2.3 ሦስተኛው መግለጫ ...............................................................50

1.2.4 አራተኛው መግለጫ ...............................................................60

1.2.5 አምስተኛው መግለጫ ...............................................................64

1.2.6 ስድስተኛው መግለጫ ...............................................................66

1.2.7 ሰባተኛው መግለጫ ...............................................................71

መደምደሚያ ...............................................................................74

ምዕራፍ ሁለት

2. ለንጥቀት አስተምህሮ ስባል የተጨነገፉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ................77

2.1 የክርስቶስ ስውር ዳግም መምጣትና ስውር ንጥቀት .................................93

2.2 ከመከራው በስውር የተነጠቁ ቅዱሳን ሰርግ . ........................................95

ምዕራፍ ሦስት

3. በታላቁ መከራ ጊዜ ቅዱሳን እንዴት በመከራው ያልፋሉ? ......................97

3.1 የ144,000 ሺህ ቅዱሳኖች ትርጓሜ ................................................97

3.2. እስራኤል ...............................................................................100

3.3. ሴቲቱና ዘሯ ...............................................................................105

ማጠቃለያ ...............................................................................119

ዋቢ መጻሕፍት ...............................................................................126

## መግቢያ

የትኛውም ዶክተር ክርስቲያን ከኾነ የጌታ ተማሪ ነው፤ ፍደል ያልቆጠረውም የጌታ ምርጥ ነው። ጌታን ለሥራዉ የኛ ትምህርት ልህቀት አይረዳውም ፤ አለመማራችንም እንዳይሠራብን አያገግደውም ። እርሱ የእውቀት ሙላት ነው። ስሰጥ የማያልቅበት ባዶውን ጋን ብቻውን የሚሞላ ። በባዶ ሸለቆ ምንም በሌለበት ውኋ የሚሞላ፤ ባዶ ጋኖችን ንፁህ፣ ጣፋጭና ማራኪ የሚያደርግ ድንቅ አምላክ ነው። ያለ መሄንዲስና እውቀት ትልቁን መርከብ የሚሠራ ። ታዲያ ይኽ ጌታ በእኛ እውቀት እየተደገፈ "ይሠራል?" ብለን እንዴት እናስባለን !? በፊደል ከመራቀቅ ብቻውን ወደሚሠራ አምላክ ፊታችን ማዞር አለብን? ከተናገርኩት ዋናው ነገር; እንዲህ የሚል ነው፡- እንደ ሳውል በታዋቂ አስተማሪ ፣አንቱ በተባለ ሰው ተምሬን ልኾን እንችላለን። ነገርግን ሳውል እንዲህ ያለ ብኾንም ፣ እዚህ ግባ በማይባል አስተዳደግ ወዳደገው ወደ ሐናንያ ተልኳል ። ሳውልም አልናቀውም። አንተም አንባቢ ኾይ ሳታውቅ የክብርን ጌታ እያሳደድክ እንዳይሆን ከገባህበት አዘቅት፣ ከያዘህ ጭፍን ፈረሳውነት ተላቀቅህ ወደ ጳውሎስነት በእግዚአብሔር እውቀት እንዲትሻገር ወደ ቃሉ ልብህን እንዲታቀና እመክራለሁ ።

የራዕይ መጽሐፍ ደብቀን ሸሽገን እንዲንጠብቀው ሳይኾን፣ ጌታ እንድናነበው የተሰጠ መልእክት ነው። ይኽንን መጽሐፍ እንደ ሌሎቹ የእግዚአብሔር መልእክታት በማንበብ በማጥናት በምሪቱ የመልእክቱ ተጠቃሚ ልንኾን ይገባናል። ይሁን እንጂ እኛ መጽሐፉን ከመግለጥ ይልቅ መደበቁን አማራጭ አድርገናል ። እንነሳና እናጥና፤ እንወቀው፤ ትውልዱን ለመመገብም እንዘጋጅ ። በማህተም ያልተዘጋውን መጽሐፍ በመዘጋታችንም ንስሓ እንግባ ። በእውቀታቸው አንቱታን ያተረፉ አስተማሪዎች ፣አንዷንና ወጧን መልእክት ፤ "እንዲህም ወይም እንዲያም ልኾን ይችላል" በማለት በመተርጎም ፣ ትክክለኛውን የእግዚአብሔርን መልእክት ባለመናገር መንጋውን ከመጥቀም ይልቅ ፥እንዲፈሩና እንዳይጠጉ በማድረግ ግራ አጋብተዋል። የእግዚአብሔር መልእክት ግን አንድና አንድ ብቻና ብቻ ነው። አልገባኝም ማለት እየተቻለ እንዴት "በልኾን ይችላል" በግምት ይተረጎማል?

አስተማሪዎች ለአንዲቷ መልእክት ሁለትና ከዚያ በላይ የኾነ የአማራጭ ትርጓሜ በመስጠት፤ ማፈርና መሸማቀቅ ሲጋባቸው እንዴ ባለአዕምሮ እንደ ልቤ ሰፊነት መቆጠሩ ይደንቃል ። እንዴት ተደርጎ የሁሉም ሃሳብና የሁሉም የተለያየ መልእክቶች ትክክል ልኾኑና እውነት ልኾን ይችላሉ? አይችልም ።ይኽ የሚያሳየው ለአስተማሪዎችም መለኮታዊ ግልጠት አለመኖሩን ነው፤ በጉድለታቸው ሳያፍሩ እንደ አዋቂ እንደ እግዚአብሔር ቃል መጋቢ መናገራቸው ይደንቃል ። ስለዚህም ከፍደል ብቻ ያልኾነ በቃልም በመንፈስም **በሥልጣን** የሚናገሩና የሚያስተምሩ የሚዘልፉ መምህራን ያስፈልጉናል ። መልእክቱን በቀጥታ አለማስተማር ትርፉ መንታ ልብን መፍጠር ነውና።

የራዕይ መጽሐፍ ምዕራፍ አራትን ስመለከቱ "እኛን አይወክልም" ለእስራኤል ዘሥጋ ነው፥ "እኛ ቀድመን በስውር ከመከራው እንነጠቃለን" በሚል የእግዚአብሔርን ቃል የሸቀጡና የመረዙ አስተማሪዎችም አሉ። ራዕይ መጽሐፍ ለአማኞች ኹሉ ዘወትር እያስተዋሉ እንድኖሩ የተሰጠ ትንቢታዊ መጽሐፍ [መልእክት] እንጂ በሥጋ እስራኤላውያን ለኾኑ የተነገረ ብቻ አይደለም ። እነዚህ የጌታን መምጣትን ቤተክርስቲያን አስተውላ ተገቢውን ዝግጅትና ምላሽ እንዳትሰጥ ለማድረግ ጭፍን ፈረሳውያን [ለራሳቸው ወግና ዕሳቤ የሚቀኑ] የፈጠሩት ስብከት ነው፡፡ መጽሐፉን እንዳንረዳ ተቋማዊ ትርጓሜዎች መብዛታቸው ቀላል የማይባል ጉዳትን አድርሰዋል ።" ምዕራፍ 1" ብለን ሳናነብ ከመሃሉ እየነጠልን በድፍረት መተርጎማችንም የድፍረታችንን ጥግ ይገልጣል።

በዚህ አጭር ጽሑፍ ላይ ፥ የራዕይ መጽሐፍ ይዘት፣ ለንጥቀት አስተምህሮ ስባል የተጨነገፉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን፣ የክርስቶስ ስውር ዳግም መምጣትና የቤተክርስቲያን ስውር መነጠቀቅ ፣ከመከራው በስውር የተነጠቁ ቅዱሳን ሰርግ ፥ ይዳሰሳሉ፤ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተነሳውን የሰውን ሃሳብ ስውሩን የሰይጣን ሥራ በቃሉ አስረጂነት ይፈርሳል ። ደግሞም በታላቁ መከራ ጊዜ ቅዱሳን እንዴት በመከራው ያልፋሉ? የ 144,000 ሺህ ቅዱሳኖች ትርጓሜ ፣ስለ እስራኤል እና ስለሴቲቱና ዘሯ በዝርዝር የምናይ ይኾናል ።አንባቢ መጽሐፍ ቅዱስን ይዘው ብያነቡ ይመከራል ። መጽሐፉ ስለቤተክርስቲያን ቅድሜ መከራ ንጥቀት አስተምህሮ ኑፋቄ መልስ ለመስጠት ይጥራል ።የትምህርቱ ኑፋቄነቱ እንዲገለጥ እና ትምህርቱ ሕይወትን ልያሳጣ እንደሚችል ለማስታወቅ ይጥራል ። የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ የቅድሜ መከራ ንጥቀት አስተምህሮ ከእግዚአብሔር እንዳልኾነና "ኑፋቄ" እንደኾነ ያምናል ። ብዙ መጽሐፍትን አገላብጠው ብዙ ምንጭ አግኝተው ለትምህርቱ ኹኔኛ ፍተሻ እንዲያደርጉ ታላቆችን ይማጸናል። ደግሞም የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ይኽንን አስተምህሮ እንዲትመረምር ጥሪ ያደርጋል ። መልካም ምንባብ ።

ዳግም በስውር ሳይኾን በግልጥ በሚመጣ ፣ኹሌተ ሳይኾን አንድ ጊዜ ብቻ ልወስደን በሚመጣ፣ከመከራው በፊት ሳይኾን ከመከራው በኋላ፤ድል ነሺዎችን ለመቀበል በሚመጣ፣በመምጣቱም ለሙታን ትንሳኤ በሚሰጥ፣ጌታ አምናለሁ ። በሕይወት ያሉትን ደግሞ ከመቅጽበት በሚለውጥ መነጠቅ አምናለሁ፤ በክብር ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌሉ በግልጽ እንደተቀመጠው አምናለሁ ።

# ምዕራፍ አንድ

## 1. የራዕይ መጽሐፍ ይዘት

ራእይ መጽሐፍን ለማስተማር ኾነ ለማወቅ በአብዛኛው አንፈልግም ደግሞም እንዲሁ ሳናውቀው እንፈራለን ።ከመፍራታችንም የተነሳ ልታወቅ የማይችል አድርገን እናስባለን ። በትክክልና በስልጣን የሚተረጉም ሳይኖር እንዴት እናውቀዋለን !? ካላወቅን እንዴትስ የትንቢቱን ቃል እንጠብቃለን ? እንዴትስ ለመልእክቱ ተገቢውን ምላሽ እንሰጣለን ? በይመስለኛል ትርጓሜ የሚያስተምሩ አስተማሪዎች ቀላል የማይባል ጉዳት አድርሰዋል ። የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ ጥናት የማታደርግ ቤተክርስቲያን ያንቀላፋች ናት፤ ልቧ በሌላ የተያዘና በዚህ ዓለም ነገር የከበደችባት፣ ከመቆሸሿም የተነሳ ከላይ በሚያማምሩ ሕንፃዎች [መቃብሮች] ውስጥ ያለች ናት፤ ብል ማጋነን አይኾንብኝም።

የዮሐንስ ራዕይ እንደሌሎቹ መጽሐፍት ብቻውን ልጠና ልንማረው የሚገባ መጽሐፍ ነው። ስለመጨረሻው ዘመን የብሉይ ነቢያትም ተናግረዋል ፤ኢየሱስም ሐዋሪያቱም። ስለመጨረሻው ዘመን በተለያየ አቅጣጫ መመልከት ግልጽና የተደላደለ መረዳትና ዝግጅት እንድኖረን ያደርገናል ። ራዕዩን ከዓለም ተነስተን ሳይኾን ከመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከላዊ ሃሳብ ተነስተን በተለይ የዐዲስ ኪዳን መጽሐፍ ስለኾነ በዐዲስ ኪዳን መንፈስ ለመተርጎም ለመረዳት ፈቃደኛ ስንኾን ይገባናል ።አልያ አንኳር ሃሳቡን አንይዝም ። የመልእክቱ ተጠቃሚም አንኾንም። ስለዚህም በሌሎች መጻሕፍት ክፍሎች የተገለጠውን በዝርዝር የምናይ መጽሐፍ ስለኾነ ደስ እየተሰኘን ልናጤነው ይገባናል ።

መጽሐፉ ስለ ተጻፈበት ጊዜ የተለያየ ሃሳብ ይኖራል ፤"በርካታ ሊቃውንት ግን በ95 ዓ.ም ገደማ እንደኾነ ያምናሉ"[1]። መጽሐፉ በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተገለጡ እውነቶችን በልዩ አቀራረብ በሥዕላዊ መልክ እንደ ትይንት እያዋዛ ያብራራል ። ቊጥሮች ፣ እንስሳት ፣ ተፈጥሮዎች፣ ከተማዎች ፣ስሞች ..በምሳሌያዊ መንገድ የተብራሩ ናቸው ።በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጡ ስለኾኑ ከመጽሐፉ ቅዱስ በመነሳት እንረዳዋለን ። [ከዋክብት መላእክት ናቸው ፣መቅረዞች አብያተክርስቲያናት ናቸው ፤ታላቂቷ ጋለሞታ ባቢሎን የተባለች ሃያል ሀገርን ወክላለች፤ ሙሽርት የበጉ ሚስት ቤተክርስቲያን በመባል፣ በቊጥሮችም በ7 ቁጥር የሙሉነት የፍጹምነት፣ 4 ቊጥር የዓለምን አራቱን [አቅጣጫ]፣12 ቊጥር ነገድን /የእግዝአብሐር ሕዝብን/ ለማመልከት የዋለ ስኾን፣ ቀስት አዕምሮ የሚይዝ የሚቆጣጠር ሃይል በማመልከት ውሏል። ፈረሶችም የነገሮችን ፍጥነትና በመልካቸው የያዙትን መልእክት ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል ..። ወደ ውስጥ እየገባን ስለምንመለከት ከመጽሐፍ በቀጥታ ለጥናት አፈታይት እንዲከፈት በወፍ በረር ለማየት እንሞክራለን ።

"ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባውን ነገር ለባሪያዎቹ ያሳይ ዘንድ እግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው በእርሱም የተገለጠው ይህ ነው፥ ኢየሱስም በመልአኩ ልኮ ለባሪያው ለዮሐንስ አመለከተ፥" ራእይ *1፥1*

ከዚህ ቃል በግልጽ እንደምንረዳው ለዮሐንስ የመጣው መልእክት "ቶሎ ይኾን ዘንድ የሚገባ" እንደኾነ ነው። ራዕዩ አፋጣኝ ምላሽ የሚሻ ነው። ይኽንን መልእክት የተቀበለና የሰማ ኹሉ መልእክቱን ወደ መፈጸም እንዲገባ የሚያሳስብ ነው። ከዚህ በፊት የኾነውን ለመተረክ የቀረበ መልእክት አይደለም ። የመልእክቱ ምንጭ እግዚአብሔር [አብ] ስኾን መልእክቱን ለማድረስ የመጀመሪያው ተቀባዩም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው /ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ከመኾኑ በፊትም እንደሚላክና ሰው ከኾነ በኋላም እንደሚላክ ደግሞም ከትንሳኤው በኋላም እንደሚላክ እንገነዘባለን/።ይኽ የሚያሳየው የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይነት ፤ የአብ ደስታ መኾኑ፤ ሰው ስኾን አለመጀመሩን ነው። *(ይህንን በይበልጥ ለመረዳት ትምህርተ ሥስትነት-በአንድነት pdf ይመ]*። መልእክቱ ከእግዚአብሔር ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ በቀጥታ ብመጣም ኹሉም መልእክቶች ግን በቀጥታ ከኢየሱስ ወደ ዮሐንስ አልወረዱም ።ኢየሱስ በፉጡር መላአክ በኵል ወደ ዮሐንስ መልእክቱን እንዳስተላለፈ "ኢየሱስም በመልአኩ ልኮ ለባሪያው ለዮሐንስ አመለከተ.." የሚለው ቃል ያስረዳል።

ዮሐንስ በእስር በፈጽሞ ደሰት ላይ ኾኖ [ራዕ1፥9]፣ራዕዩን ከተመለከተበት ግዜ አንስቶ ገና እና ቶሎ የሚኾነውን ተመለከተ እንጂ [ከዚህ በፊት የኾነውን አይደለም]።“እንግዲህ ያየኸውን <u>አሁንም ያለውን</u> <u>ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን</u> ጻፍ።” ራእይ 1፥19/ እንደምል። በዚህ ቃል ላይ "አኹንም ያለውን" የሚለው በሰዓቱ ለነበሩት አብያተክርስቲያናት በቀጥታ የተሰጠ አስቸኳይ ምላሽ የሚያስፈልግ መልእክት ስኾን፣ ለቀሩት ዓለም አብያተክርስቲያናት ግን የየዕለት እራስን መመልከቻና መፈተሻ መማርያ የእግዚአብሔር መልእክት ነው። በሰዓቱ የነበሩት 7ቱ አብያተክርስቲያናት የመጀመሪያ ተደራስያን ናቸው ። “..፥ ሰባቱም መቅረዞች ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው።” ራእይ 1፥20። ስለዚህም ራዕይ መጽሐፍ ዓላማው ይዘት ኹለት ነው ማለት ይቻላል፦ **1**ኛው. "አኹን ያለው" የተባለው የ7ቱ አብያተክርስቲያናት ወቅታዊ ሁኔታ የያዘ መልእክት ስኾን፣ ከምዕራፍ ኹለት እስከ ሦስት የተገለጠው መልእክት ነው፣ **2**ኛው. "..ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን ጻፍ" እንደሚል ወደፊታዊ ተፈጻሚነት መልእክት ያዘለ እንደኾነ እንረዳለን ። ከዚህም መባሉ ዮሐንስ ራዕዩን አይቶ ከጨረሰ በኃላ መፈፀም የሚጀምሩት የያዘ እንደሆነ ያስረዳል ፤ ይኽም ከምዕራፍ አራት ጀምሮ ያለው ነው።

## **1.1** አኹን ያለው

በዚህ ላይ አኹን ያለውን የተባለውን የሰባቱ አብያተክርስቲያናት መንፈሳዊ ኹኔታና የእግዚአብሔር አስቸኳይ መልእክት ከምዕራፍ 2-3 ያለውን የያዘውን፣ ለኛም እራሳችንን እንድንፈትሽ የተሰጠውን መልእክት ለማየት እንሞክራለን ፦

<u>፩</u>." በኤፌሶን ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፦ በቀኝ እጁ ሰባቱን ከዋክብት የያዘው በሰባቱም የወርቅ መቅረዞች መካከል የሚሄደው እንዲህ ይላል፦ *ሥራህንና ድካምህን ትዕግሥትህንም አውቃለሁ፤ ክፉዎችንም ልትታገሥ እንዳትችል፥ እንዲሁም ሳይሆኑ፦ ሐዋርያት ነን የሚሉቱን መርምረህ ሐሰተኞች ሆነው እንዳገኘሃቸው*

አውቃለሁ፤ ታግሠህማል፥ ስለ ስሜም ብለህ ጸንተህ አልደከምህም። ዳሩ ግን የምነቅፍብህ ነገር አለኝ የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃልና። እንግዲህ ከወዴት እንደ ወደቅህ አስብ ንስሐም ግባ የቀደመውንም ሥራህን አድርግ፤ አለዚያ እመጣብሃለሁ ንስሐም ባትገባ መቅረዝህን ከስፍራው እወስዳለሁ። ነገር ግን ይህ አለህ፤ እኔ ደግሞ የምጠላውን የኒቆላውያንን ሥራ ጠልተሃልና። መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ። ድል ለነሣው በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይወት ዛፍ እንዲበላ እሰጠዋለሁ።" [ራእይ 2፥1-7] ።

በስሙ በተጠሩ መቅረዞች [ማህበረ ቅቡዓን] መካከል የሚገኘው፣ የሚመላለሰው ፥ ደግሞም ለኹሉም መልእክተኞች ባለሥልጣን የኾነው፣ ለኤፌሶን ቤተክርስቲያን መልእክተኛ አገልጋይ ባሪያ እንዲህ ይላል፦ የቤተክርስቲያንቱ መልእክተኛ ባሪያና አገልጋይ አስቀድሞ ፣ ሳይታክት፣ ሳይደክም፣ በትዕግሥት የሚሠራ ስኾን፥ ክፉዎችን ሃሰተኞችን አይምራቸውም፤ አይታገሳቸውም ነበር። መንጋውን ለመጠበቅ የተሰጠውን አደራ በአግባቡ ይወጣ ነበር፤ መንፈስን የሚመረምር ነበር። በዚህም ሃሰተኛ ሐዋርያትን እንኳን እንዳጋለጠ ተመስክሮለታል ።

ምንም እንኳን የኤፌሶን ቤተክርስቲያን አገልጋይ ቀድሞ እንዲህ የሚለፋ ብኾንም፣ አኹናው ሁኔታው ስታይ እንደበፊቱ እንዳይደለ ጌታ ይገልጻል ። እንደበፊቱ አይሠራም ።ትቶታል ።ጌታም ይኽንን መንጋውን የመጠበቅን፣ እምነትን የመጠበቅን ተግባርን "የፍቅር መገለጫ " እንደኾነ መስክሮለታል ። የቤተክርስቲያንቱም እረኛ ይኽንን ትጋት ስተው፣ "እንደ ቀድሞው አትወደኝም፤ትተሄኛል" በማለት ማዘኑን ይገልጻል ።

ከዚህ መልእክት ተነስተን ለቤተክርስቲያኒቱ መልእክተኛ /አገልጋይ/ መንፈስን መመርመር ፣መንጋውን መጠበቅ፣ ያለመታከት በዚህ መትጋት የተሰጠው ሥራው ነው ማለት እንችላለን ። ይኽንን የሚያደርጉ ዛሬ ላይ በእግዚአብሔር የተሾሙ ስኾኑ፣ ተቋማት የማያውቋቸው ባሪያዎች ናቸው ። ለዚህም ነው መልእክቱን ለእረኛው ብቻ እንደተጻፈ "ጆሮ ካለህ ስማ" ያልተባለው። ምክንያቱም ባሪያ ፣መልእክተኛ፣ አገልጋይ ምዕመናት ኹሉ እምነትን የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው ። ስለ ጤናማው ሕይወት ስለሚገኝበት ትምህርት አብዝተን ልንተጋ ልንጋደል ይገባናል ።ምክንያቱም ጌታን መውደዳችን የሰው ኾነ የሰይጣን ሃሳብ ፣በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተነሳውን በመቃወም ይገለጣልና ።

ዛሬ ላይ ግን የኤፌሶን አገልጋይ የተመሰገነበት አገልግሎት የጥላቻ፣ የቅንዓት ፣ የወሬኛ፣ የሥራ አልባነት ፣ የክርስቶስ ተቃዋሚነት ፣ ወዘተ. ያስብላል እንጂ እንደ አገልግሎት አይቈጠርም ። ለማንም ፊት ሳያደሉ መለኮታዊ ጅራፍ የሚያነሱት "እንደ ፍርደኞች፣ ፍቅር የራቃቸው ጥለኞች" ተደርገው ይቆጠራሉ ። ይኽ የሚያሳየው የኢትዮጵያ አብያተክርስቲያናት መንጋነት; ጀማ መከተልን ብቻ ሳይኾን፣ እንደ ሕዝብ መጥፋታችንን ነው።

ለቤተክርስቲያኒቱ አገልጋይ የቀደመውን ሥራውን እንዲተው ምክንያቱ የጌታ ፍቅሩ መቀዝቀዙ ነው። ይኽንን ሳስተውል አንዳንዴ መቃወም የሚገባንን ነገር አለመቃወምን እንደ አዋቂነት መቈጠሩ ይደንቀኛል ፤ እንደ እርጋታ ሰው መቈጠሩ።

ግን አይደለም ።ቤቱን ስያቆሽሽ ዝም ማለት መተባበር ነው። ስለዚህም አንዳንዴ አዲስ እረኛ ከፍት አያስተኛውም በሚል በመነቃቃት፣ ኹሌም በጥበብና በማስተዋል በመመርመር ሥራችንን ልንሠራ ይገባናል እላለሁ ። ይኽ በዋነኝነት ለቤተክርስቲያኒቱ መጋቢ ብኾንም፣ በወረቀት ተሹሞ ይኹን ወይም በእግዚአብሔር እንደተሾመ የማይታወቅ በዛሬይቱ አገልጋይ አሳከን፣ "የእርሱ ሥራ ነው" ብለን ዝም በማለት ልንጥለውና ልንተወው አይገባንም ።

የቤተክርስቲያኒቱ ባሪያ [መልእክተኛ] ነቀፌታ የተቀበለው ፣ መንፈስን መመርመርን በመተው እንጂ ከሃሰተኞች ጋር ሕብረት በማድረጉ አይደለም። እግዚአብሔር የጠላውን ሕብረት "የኒቆላውያንን "የሚጠላ ነበር ። በዚህም ተቀይጦ ከሃሰተኞች ጋር ባለማምለኩ ተመስግኗል። የእኛስ አምልኳአችን ከማን ጋር ነው? በውኑ ጌታዬ በሕብረቴ ደስተኛ ይኹን? ብለን አስበን እናውቀዋለን ? እንዲሁም ሃሰተኞችን ተቃውመን እናውቀዋለን ? ወይስ ኢጋፋሪአቸው ኾነን አለን? የኢትዮጵያ አብያተክርስቲያናት መንፈስን መመርመር አለመቻልን ፅድቅ አድርገው በምቄጥሩ ምዕመናት የተሞላች ናት። የከሰመች እንደኾነች መናገር እንችላለን ።

ይኽ የቤተክርስቲያን መጋቢ ሃሰተኞችን አልተከተለም ፣ ከእነርሱም ጋር አልተተባበረም ወይም በኃጢአት አልተወቀሰም ።ነገርግን ፍቅሩ ስለቀዘቀዘ ወይም ቸል ስላለ ብቻ ጌታ "እመጣብሃለሁ" ብሎታል። በሐዲስ ኪዳን የሰጠውን ሥራ ቸል ማለት በራሱ ፍርድን የሚያመጣ ነው፤ ሐዲስ ኪዳን ከሙሴ ሕግም ይልቃል ። አንዳዶች ወስላቶች 'በዝሙት በመጠመድም መዳኔን አላጣም' እንደሚሉ አይደለም ። እነኚህ ሃሰተኞች ንስሐም አይወዱም ። ስለ ሁሉ ኃጢአተ ጌታ ኃጢአትን እንደሚሠራ አስቀድሞ አውቆ፣ ታሳቢ አድርጎ አንዴ ሞቷል ይላሉ። በዚህም ሞቱ የኃጢአትን ምንጩን ለማድረቅ እንደኾነ ይክዳሉ፤ ያስክዳሉ። ምክንያቱም ኢየሱስ ለኃጢአት እንዳትገዛና በኃጢአት እንዳትኖር ለማድረግ እንጂ በቀጣይ ለሚትሠራቸው ኃጢአቶች ታሳቢ አድርጎ አልሞተም ።ወንጌልም ይኽንን አይመሰክርም።

የመዳንን ዋስትና እርግጠኛነት; በኃጢአት ብመላለስም ብጠመድም አልጠፋም ብሎ ማመን ሳይኾን እርሱን እየመሰልን በእርሱ ችሎታ መኖርን በመለማመድ መተማመን ነው። ለዚህ ቤተክርስቲያን መጋቢ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ እንደገለጸው ቸልተኝነቱ መጥፋትን እያመጣለት ይገኛል ፣"በመላእክት የተነገረው ቃል ጽኑ ከሆነ፥ መተላለፍና አለመታዘዝም ሁሉ የጽድቅን ብድራት ከተቀበለ፥ እኛስ እንዲህ ያለውን ታላቅ መዳን ቸል ብንለው፥ እንዴት እናመልጣለን?" ዕብ 2፥2 ።ስለዚህም አንዴ ድኛለሁ አልጠፋም ብለህ እራስህን ከማታለል ውጣና፣ መጽሐፍ እንደሚል ’’.. እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ።" [1ኛ ቆሮ 10፥12 ]፣ እንደሚል እንዳንወድቅ ስለመዳናችን እንጠንቀቅ ። ሕይወት ተከፍሏልና።

ይኽ የቤተክርስቲያኑ መጋቢ የእግዚአብሔርን ልጅ ቸል አለ እንጂ አልካደም ወይም በኃጢአት አልወደቀም ወይም ከሃሰተኞች ጋር ሕብረት አላደረገም ። ግን እግዚአብሔር በታላቅ ቍጣ መጥቶበታል። እንደ ቀድሞ አትወደኝም በማለት ።በዚህም "መቅረዙን" እወስዳለሁ ብሎታል። ከላይ እንዳየነው መቅረዝ ቤተክርስቲያንን የሚያመለክት ቃል ነው። ቤተክርስቲያንን "ቤተክርስቲያን" የሚያስብለው የክርስቶስ መኖር እንጂ የአምልኮ አዳራሽ ማማር አይደለም ።ወይም የሰው ብዛት። ቤተክርስቲያንን ቤተክርስቲያን ያስባለው በመካከሏ የሚሄደው ክርስቶስ ነው። መቅረዙን እወስዳለሁ ማለቱ ሕልውናውን መገኘቱን መንፈሱን እወስዳለሁ ማለቱ ነው። ንስሐ ካልገባ ። የኢትዮጵያ አብያተክርስቲያናት ኢካቦድ ከኾነች ቆየች፣ ለአውሬው ብሮ ይባስ ብላ ክብሯን ሰጥታለች፤ ለካውንስሉ። አይደለም እንደዚህ እንደ ኤፌሶን ቤተክርስቲያን ሃሰተኞችን መቃወም ቀርቶ፣ ከእነርሱ ጋር "ወንጌል" ካልሰበኩ ብላለች። ስለዚህም ሕንፃ እንጂ አካል የላትም።ከጌታም የሚጠብቃት መለኮታዊ ሰይፍ ነው። ጆሮ ካለህ ስማና ተለይ። ለእድር ብለህ ነፍስህን አታጥፋት። በጌታ ፊት ያለህበት እምነት ተቋም አይቆምልህምና ፤ ወስንና ተለይ ። ጌታ ለድል ነሺዎች የሚሰጠውን አክሊል ለመቀበል ተዘጋጅ። ንስሐ በመግባት ብቻ እንደ ቀድመው መከራ እየተቀበለ የሚያገለግል ከኾነ "ድል ነሺ" ይኾናል ፥ “.. ድል ለነሣው በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይወት ዛፍ እንዲበላ እሰጠዋለሁ።” ራእይ 2፥7 ። አገልጋይ ለምድራዊ ዝናና ብልጽግና ባለመስራቱ ፣ ለማይጠፋው ለዘላለሙ ሙብል በማገለገሉ ፤የዘላለምን ሕይወትን ያገኛል ።ጌታም ለማይጠፋው ለዘላለም ለሚኖረው ሙብል ሥሩ ብሏልና። “ለሚጠፋ ሙብል አትሥሩ፤ ነገር ግን ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር ሙብል የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ሥሩ፤ እርሱን እግዚአብሔር አብ አትሞታልና።” ዮሐ 6፥27 ። ስለዚህም ምዕመናት ቸል ባለማለት በቤቱ ቅናት እየተቃጠሉ ካገለገሉ የዘላለምን ሕይወት ያገኛሉ፤ቀድሞ በአዳም ያጡትን ክብር ሕብረት ያገኛሉ ፤ይበላሉ። በንስሐ የማይመለሱና በቸልታ እንደቀድሞው ሳይኾኑ ከቀጠሉ የዘላለምን ሙብል አያገኙም ። አስተዋላችሁ? አይደለም ኃጢአት; ቸልታ የሚያሳጣውን ?ደግሞም በንስሐ ብቻ የሚያገኘውን ? ታማኝ አገልጋይ ድኖ የነበረ በቸልታ እንደሚወድቅ መጽሐፍ ስመሰክር ሃሰተኞች ግን ኃጢአት እየሠራችሁ ብኾንም የዘላለም ሙብል [የዘላለም ሕይወት] አላችሁ አትጠፉም ይላሉ። ጆሮ ያለው ማንን ማዳመጥ እንዳለበት ይወቅ።

፪." በሰምርኔስም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ። ሞቶ የነበረው ሕያውም የሆነው ፊተኛውና መጨረሻው እንዲህ ይላል፦መከራህንና ድህነትህን አውቃለሁ፥ ነገር ግን ባለ ጠጋ ነህ፤ የሰይጣንም ማኅበር ናቸው እንጂ አይሁድ ሳይሆኑ፦ አይሁድ ነን የሚሉት የሚሳደቡትን ስድብ አውቃለሁ። ልትቀበለው ያለህን መከራ አትፍራ። እነሆ፥ እንድትፈተኑ ዲያብሎስ ከእናንተ አንዳንዶቻችሁን በወኅኒ ሊያገባችሁ አለው፥ አሥር ቀንም መከራን ትቀበላላችሁ።

እስከሞት ድረስ የታመንህ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ። መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ። ድል የነሣው በሁለተኛው ሞት አይጐዳም።" ራእ 2፥8-11።

ለዚህች ቤተክርስቲያን ጌታ በሞት ላይም ስንኳ ባለስልጣናን እንደኾነ ይገልጻል ። ሞትን እንዳይፈሩ በእርሱ ቊጥጥር ያለ መኾኑን ለማስታወቅ ። የቤተክርስቲያኒቱ መልእክተኛ በመከራና በስቃይ ውስጥ ያለ ስኾን፣ በኢኮኖሚም ድሃ ነው፤ በጌታ ጸጋ ግን ባለጠጋ ነው። ለመልእክተኛው መከራውን ያበዙት የመጀመሪያ ጠላቶች በቤት ውስጥ ያሉቱ ናቸው ፣ የአውሬው ተወካዮች ፤ስመ አማኞች። እነኚ አይሁድ ነን ይላሉ። በሥጋ እስራኤላዊ ልኾኑም ላይኾኑም ይችላሉ ። ምክንያቱም በሐዲስ ኪዳን አይሁድ ተብለው የሚጠሩት በክርስቶስ ያሉቱ ብቻ ናቸው ። እግዚአብሔር የሥጋዊ አይሁዳውነትን ብልጫ አስወግዷል ። ቃሉም " ከፍጥረቱም ያልተገረዘ ሕግን የሚፈጽም ሰው የሕግ መጽሐፍና መገረዝ ሳለህ ሕግን በምትተላለፈው በአንተ ይፈርድብሃል። በግልጥ አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ አይደለምና፥ በግልጥ በሥጋ የሚደረግ መገረዝም መገረዝ አይደለምና፤ ዳሩ ግን በስውር አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ ነው፥ መገረዝም በመንፈስ የሚደረግ የልብ መገረዝ ነው እንጂ በመጽሐፍ አይደለም፤ የእርሱ ምስጋና ከእግዚአብሔር ነው እንጂ ከሰው አይደለም።" ሮሜ 2፥27-29።

ጌታ የሚያውቀው መገረዝ [አይሁዳዊነት] በመንፈስ መገረዝ ነው። በመንፈስ ያልተገረዘ በሥጋ አይሁዳዊ ብኾንም አይሁዳዊ አይደለም በማለት ጳውሎስ ያስረዳል ። እነኚህ "አይሁዳዊ ነን" የሚሉት በመንፈስ ሳይገረዙ ፣ የእግዚአብሔር ልጆች ነን፣ በእምነት ከክርስቶስ ተወልደናል የሚሉ ናቸው ። ውሸታሞች አማኞች ስለኾኑ ለቤተክርስቲያኒቱ አገልጋይ መከራውን አብዝተዋል ። ይባስ ብለውም በውሸት ይከሳሉ ያስወራሉ። ስሙን አገልግሎቱን ለማጠልሸት የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም። ጌታ እነዚህ የሰይጣን ዘር የኾኑ ስለሚያውቅ ፣ የሰይጣን ማህበሮች ናቸው በማለት ይገልጻቸዋል ። የነገረስራቸው ተንኮል፣ ክፋት ፣በቅዱሱ ላይ የሚያሰሩት ሰራ ፍሬአቸውን ይገልጻል ። ሰይጣን አማኝ መስሎ ቅዱሳንን ቀርቦ መዋጋቱ ይደንቃል ። ከአሕዛብ ብኾን በቀላሉ ይታወቅ ነበር። ነገርግን የበግ ለምድ ለብሶ "አማኝ ነኝ" በማለት በቤተክርስቲያን ጉባዔ ውስጥ ኾኖ ስያታልል፣ ምስክኖችን ገለባ ስያደርግ ይኖራል ። በዚህ ሁኔታ ያሉትን  መቃወምን በጌታ ወንድም የኾነውን እንደ ተቃወማችሁ አትቊጠሩ። ሰይጣን በመካከላችኹ የዘራቸው ሃሰተኞች ወንድሞች አማኞች የሰይጣን ማህበሮች ፍሬዎች እንደኾኑ እወቁ።

በዚህ መከራና ስቃይ በኢኮኖሚ ድኽነት ተማቆ የሚኖረውን ጌታ ፣ "ሃብታም አደርጋለሁ" አላለውም ። እንደ ዛሬ ሃሰተኞች ; መኪና ያዝ፣ የቤት ቁልፍ ያዝ፣ .. አላለውም ። የምድርን ብልጽግና አልሰበከም ። ጸጋ አልጎደለለትምና የሚልቀውን፣ የዘላለሙን፣ የማይጠፋውን ለመስጠት እንዲዘጋጅ አለው። መከራ እንደሚቀበል አበሰረ፤ በመከራውም እንዲጸና ። ይኽ መከራ እንቅርት ላይ ጆሮ ድግፍ እንዲሉ በውስጥ በተነሳው መከራ ላይ ተደራቢ ነው። መከራው እስከሞት ድረስ መታመንን የሚጠይቅ ነው። በነፍሱ ተወራርዶ ማገልገል ያለበት ኃላፊነት ነው። ከዚህ የምንረዳው

ለመልእክተኞች መከራ በስሙ ከምዋሹ አገልጋይ ነን ፣ ነቢይ ነን ወይም አማኝ ነኝ ከሚሉት እንደሚመጣ ፣ደግሞም ከውጪ በመንግሥት በኩል ለአካላዊ ጥቃት እስር ቤት ከመጣል እስከ መሞት እንደሚመጣ እንረዳለን ። የጤናማ አማኞች ፈተና ከውስጥና ከውጭ እንደሚመጣ እንረዳለን ፤የኹለቱም ፈተና ምንጭ አንድ ነው፤ ዲያብሎስ ።

ሰይጣን አንዱን ዳንኤልን ለማሳሰር በራሱ መንግሥት በኩል ሕግ አውጥቶ እስር ቤት እንደወረወረው፣ደግሞም እነ አናንያን አዛሪያን .. እስር ቤት ለመጣል በሕግ ከስሶ ለሞት ፍርድ እንዳበቃ፣ ጳውሎስ ሳውል በነበረበት ጊዜ በሕጋዊ እስር ፈቃድ አማኞችን እንደሚያሳድድ [ሐዋ 9]፣ በሰምርኔስ ቤተክርስቲያንም ታማኝ ምስክሮች የኾኑትም በሃገርቱ ገዥ በኩል በሰይጣን ሃሳብ የሚወጣውን ሕግን በመቃወም ይታሠራሉ፤መከራውን ይቀበላሉ። በዚህም በፈተናው መሞት ካለባቸውም መሞት አለባቸው ። ድል በመንሳት ማለፍ አለባቸው ። ተባለላቸው ።

ሰይጣን በሃገራችንም በቅርቡ በደርግ ግዜ እንኳን ፣እግዚአብሔር የለም የሚለውን ሕግ የሚቃወሙትን እንዳያመልኩ በማሰር በማሰቃየት አሳልፏል ። ዛሬ ላይ እንዲህ ያለ መከራ እንደገና እያቆጠቆጠ ይገኛል ። በኢኮኖሚ ሰበብ ኢትዮጵያ ሃገራችን የግብረሰዶም ተባባሪ እንዲሁም ለሕፃናት በመጽሐፍ ቀርፃ እንዲታስተምር ፣ ጠቅላይ ሚንስቴር አቢይ አሕመድ ተስማምቶ ተፈራርሞ መጥቷል ። ይኽንን ተከትሎ የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባዔ; በላይ ጠባቂዎች የተቃውሞ ድምጻቸውን አሰምተዋል ። የፎቶ ማስረጃ ይመልከቱ ፦

## የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ የበላይ ጠባቂ አባቶች

### በአውሮፓ ኅብረት እና በአፍሪካ፣ በካሪቢያንና በፓስፊክ ሀገራት መካከል የተፈረመውንና የሳሞአ ስምምነት በመባል የሚታወቀውን የንግድና የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት አስመልክቶ የተሠጠ መግለጫ

የተወደዳችሁ በሀገር ውስጥና በውጪው ዓለም የምትኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ኢትዮጵያዊያት ልጆቻችን ከሁሉ በማስቀደም መንፈሳዊ ሰላምታችንን እናቀርባለን።

ባሳለፍነው የህዳር ወር በ5ኛው ቀን 2016 ዓም የተወሰኑ የአፍሪካ የካሪቢያንና የፓሲፊክ ሀገራት ለሚቀጥሉት 20 ዓመታት ጸንቶ የሚቆይ የንግድና ኢኮኖሚ አሳሪ የአጋርነት ስምምነትን ከአውሮፓ ኅብረት ጋራ ሳሞአ በምትባል ሀገር በተከናወነው የስምምነት የፊርማ ሥነ ሥርዓት ወቅት ሀገራችን ኢትዮጵያም ይህንኑ ስምምነት መፈረሟን በብራሰልስ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ይፋ ማድረጉ ይታወሳል።

ይህ በአውሮፓ ኅብረት እና በአፍሪካ፣ በካሪቢያንና በፓስፊክ ሀገራት መካከል ለ20 ዓመታት እንዲዘልቅ ታሳቢ ተደርጎ የተከናወነው የንግድና የኢኮኖሚ ትብብር የአጋርነት ስምምነት በዋናነት የሰብአዊ መብቶች፣ የዲሞክራሲና የአስተዳደር፣ የሰላምና ደኅንነት፣ የሰብአዊና ማኅበራዊ ልማት፣ አካታች የሆነ ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገትና ልማት፣ የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ፣ እና የሰዎች ፍልሠትና የመዘዋወር ጉዳዮች ላይ በጋራ መርኅና የየሀገራቱን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ተፈፃሚ እንደሚሆን የስምምነት ሰነዱ ያትታል።

በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ በትብብርና በአጋርነት ለመስራት የሚያስችል ሕጋዊ የስምምነት ማዕቀፍ መኖሩ መልካም ቢሆንም የስምምነቱ ዝርዝር ጉዳዮችና ነጥቦች ሲፈተሹ ግን ከየሃይማኖታችን ሕግጋትና አስተምህሮ ጋር በእጅጉ የሚቃረኑ ሀሳቦችና አቅጣጫዎች የያዘ ሰነድ በመሆኑና በዚህም ምክንያት በህዝባችን ውስጥ ከፍተኛ ድንጋጤን፣ መረበሽንና ስጋትን እንደፈጠረ በማጤን እና ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት በመስጠት የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ አስፈላጊውን ማጣራት ሲያደርግ ቆይቷል።

በዚህም መሠረት የትብብርና የአጋርነት ስምምነቱ በውስጡ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የሃይማኖትና የባህል እሴቶች ጋር የሚፃረሩ ጾታዊ ሀሳቦችና ትርጉሞች ያላቸውን ይዘቶች ያካተተ ስለመሆኑና ይህም በዓለም አቀፍ ድርጅቶችና መድረኮችም ጭምር የሚታወቁ ሐረጎችንና አንቀፆችን እንደያዘ ጉባኤው ካገኘው መረጃ ማረጋገጥ ተችሏል። ለአብነት ያህል፦

**ሀ)** በስምምነቱ አንቀፅ 36.2 ላይ የተጠቀሰው "የወሲብና የተዋልዶ ጤናና መብቶች" ("Sexual and Reproductive Health and Rights") የሚለው ሐረግ በቀጥታ ከግብረሰዶም መብቶች፣ ከፆታ መቀየር፣ ከውርጃ፣ ሁሉን አቀፍ የወሲብ ትምህርትና ግልሙትናን ሕጋዊ ከማድረግ ጋራ

የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ
INTER-RELIGIOUS COUNCIL OF ETHIOPIA

1

በቀጥታ የተያያዘ መሆኑ በአውሮፓ ፓርላማና በዓለም የጤና ድርጅት የመረጃ ምንጮች ላይ በግልፅ መቀመጡ ፤

ለ) በስምምነቱ የአፍሪካ ፕሮቶኮል አንቀፅ 40.6 ላይ በአህጉራቱ ለሚገኙ ልጆችና ታዳጊዎች ሁሉን አቀፍ የወሲብ ትምህርት (Comprehensive Sexuality Education) የተባለ እጅግ አደገኛ አቀፍ የወሲብ ትምህርት እንዲማሩ አስገዳጅ መሆኑ ለዚህም በዩኔስኮ የተዘጋጀውና ኢግብረገባዊና ልቅ የወሲብ ትምህርት እንዲማሩ የተረጋገጠው መተግበርያ "International Technical Guidance on Sexuality Education" በስም ተጠቅሶ መቀመጡ ፤ እጅግ አደገኛ ይዘት እንዳለው

ሐ) ይህም "ሁሉን አቀፍ የወሲብ ትምህርት" በሚል የሚታወቀውና በዚህ ስምምነት ውስጥ "Comprehensive Sexual and Reproductive Health Information and Education" የሚል ስያሜን ይዞ የሚገኘው ዕድሜንና ባህልና ያማከለ እንደሆነ የሚነገርለት ኢግብረገባዊ የትምህርት ዓይነት በዓለማችን በበርካታ ሃገራት ተተግብሮ በታዳጊዎችና በወጣቶች ላይ በከፍተኛ ደረጃ የሞራል ውድቀትንና ወሲባዊ ልቅነትን ማስከተሉ በብዙ ሳይንሳዊ ምርምሮች የተረጋገጠና በተለይም በአፍሪካ ካሁን በፊት በተተገበረባቸው ሃገራት 84% ጊዜ ውድቀት ያስከተለ መሆኑ መረጋገጡ

መ) በዚህ ደረጃ ያለ ዓለም አቀፋዊ ስምምነትን የያዘው ዶኩመንት በውስጡ የቃላት መፍቻ (Glossary) አለመካተቱ, እንዲሁም ሃገራት ያልተስማሙባቸውን አንቀፆች የሚቃወሙባቸው ዕድሎች (reservation clause or interpretive declaration) ሆን ተብለው እንዲወጡ ወይም እንዳይኖሩ መደረጋቸው፤

ሠ) በስምምነቱ አንቀፅ 40. 6 ውስጥ እንደተመለከተው ሀገራችንን ካሁን በፊት ተካሂደው በነበሩና ገና ወደፊት በሚካሄዱ ውጤታቸውም በማይታወቅ ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች የሚወጡ አደገኛ ይዘት ያላቸው የጋራ መግለጫዎችን እንዲህ በሚሉ አንቀጾች ("The Parties shall commit to the full and effective implementation of the Beijing Declaration and Platform for Action and the Programme of Action of the International Conference on Population and Development and the outcome documents of their review conferences.") ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ ውስጥ የሚያስገባት መሆኑ እየታወቀ መፈረሙ ፤

ረ) እንዲሁም ኢትዮጵያ ፈራሚ ባልሆነችባቸው አካባቢያዊና አህጉራዊ ስምምነቶች አካል የሚያደርጋት መሆኑና የሀገር ሉዓላዊነትን በግልፅ ተቀምጦ እያለ የተፈረመ መሆኑ፤

ሰ) የፆታ ጥንክሳን (gender based violence) ማስቀረት በሚል በጣም አሻሚ የሆኑ ግብረሰዶማዊ እስተሳሰቦችን ለማስረፅ እንዲረዳው በሰነዱ በበርካታ ክፍሎች ውስጥ "አካታች" ("inclusive") በሚሉ ቃላት ተሸፍኖ እንዲገባ የተደረገ መሆኑ፤

ሽ) በተጨማሪም በበርካታ ሥፍራዎች የተጠቀሰው "Gender" የሚለው ቃል ወንድና ሴት ተብሎ እንደሚተረጎም በስምምነቱ በግልጽ ባለመቀመጡ ይልቁንም በርካታ ጾታዎች እንዳሉ በማስመሰል ሀገራትን የሚያደናግሩባቸው እንደ (sexual orientation እና gender identity)ን የመሳሰሉ ግብረሰዶማዊ እስተሳሰቦችን የያዙ ዶክመንቶች በስም ተጠቅሰው በስምምነቱ ውስጥ መካተታቸው፤

የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ
INTER-RELIGIOUS COUNCIL OF ETHIOPIA

2

ፀ) ስምምነቱ የወላጆችን መብት የሚጥስና የኢትዮጵያዊ ቤተሰብ እሴቶችን አደጋ ላይ የሚጥሉ አንቀፆችን የያዘ ስለመሆኑ በሰነዱ ላይ ከተደረገ የኤክስፐርቶች ጥልቅ ጥናት ተረድተናል፡፡

በአጠቃላይ ይህ አዲስ የአጋርነት ስምምነት ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡና ትውልድንና ብሎም ሀገርን አጅግ የሚጎዱ በርካታ አንቀጾች የተካተቱበት በመሆኑ ለሀገራችን ህዝብ ዕድገትን ሳይሆን ውድቀትንና ከፍተኛ የሞራል ዝቅጠትን የሚያስከትል የሀገራችንንም ሉዓላዊነት አደጋ ላይ የሚጥል መሆኑን በሚገባ ተረድተናል፡፡ ስለሆነም እኛ የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ የበላይ ጠባቂ አባቶች የአጋርነት ስምምነቱ አስገዳጅና አሳሪ እንዲሆን ተደርጎ የተዘጋጀ ከመሆኑ አንፃር መንግስት ከዚህ በታች ያቀረብናቸውን ምክሮችና ተግሳፆችን በመቀበል የሀገርን ሉዓላዊነትና ትውልድን የመጠበቅ ሕጋዊ፣ ሞራላዊና ታሪካዊ ኃላፊነቱን እንዲወጣ ከታላቅ አባታዊ አደራ ጋር በአጽንኦት እናሳስባለን፡፡

1. መንግስት የአዲሱን የሳሞአ የንግድና የኢኮኖሚ የአጋርነት ስምምነትን በርካታ ጎጂ ጎኖች እንዳሉት በማመን ከዚህ ስምምነት ኢትዮጵያ ራሷን እንድታገልል በማድረግ መንግስታዊ ኃላፊነቱንና አደራውን በተግባር እንዲወጣ በአጽንኦት እንጠይቃለን፡፡

2. የሀገሪቱ ከፍተኛው የሥልጣን አካል የሆነው የተከበረው የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና በሥሩ ያሉ የሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች የስምምነት ሰነዱ ውስጥ በዝርዝር የቀረቡትን በተለይም ከሰብአዊ መብቶች፣ ከወሲባዊና የተዋልዶ ጤናና መብቶች፣ ሁሉን አቀፍ የወሲብ ትምህርት፣ አካታችነት እና መሰል በሰነዱ የተካተቱ አንቀጾች ወይም ይዘቶች ከግብረሰዶማዊነትና ጾታን ከመቀየር እንዲሁም ከልቅ ወሲብና ከውርጃ ጋራ በቀጥታ ተያያዥነት ያላቸው ጽንሰ ሃሳቦች መሆናቸውን በመረዳት ይህንን እጅግ አደገኛ ስምምነት ባለማጽደቅ ህዝባዊና ታሪካዊ አደራውን እንዲወጣ በአጽንኦት እንጠይቃለን፡፡

3. መንግስታችን ከህዝብ አደራን ተቀብሎ ሀገርን የሚያስተዳድር እንደመሆኑ ከዚህ በኋላ በሚያደርጋቸው ተመሳሳይ የትብብር ስምምነቶች ከላይ የዘረዘርናቸውን ዓይነት የሀገራችንን ኃይማኖት፣ባሕልና ነባር እሴቶችን የሚጎዱ ጽንሰሃሳቦችን ያዘሉ አሳሳች ሀረጎች ያሉባቸውን ስምምነቶች ፈጽሞ እንዳይፈርም እያሳሰብን፣ ስምምነቶችንም ለመፈራረም በሚደረጉ ድርድሮች ወቅትም የሚፈርማቸው ዶክመንቶች ውስጥ የምንወዳት ሀገራችን ኢትዮጵያ እንደሀገር የማትስማማባቸውን ወይም የማትቀበላቸውን አንቀጾች የምትቃወምበት (reservation clause or interpretive declaration) ዕድልና መብት እንዲኖራት ሊሠራ እንደሚገባ በአጽንኦት እንመክራለን፡፡

4. በመጨረሻም የአጋርነት ስምምነቱ ማዕቀፍ ውስጥ በሰብአዊ መብት፣ በንግድና የኢኮኖሚ ትብብር ሽፋን ከሃይማኖታችን መሠረታዊ አስተምህሮ የወጡና የሀገራችንን ባሕልና ነባር እሴቶችን የሚጎዱ ጸያፍ ልምምዶች ቀጥተኛ ባልሆነ አግባብ በሰነዱ ውስጥ የተካተቱ መሆናቸውን ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም በየትኛውም ሁኔታና አግባብ የሰነዱ ዋናና ዝርዝር አንቀጾች ወይም ይዘቶች ትርጓሜ ከሃይማኖቶቻችን መሠረታዊ አስተምህሮ፣ ከዶግማዊና

3



ቀኖናዊ ጉዳዮች ጋር የሚቃረኑና የማይስማሙ ወይም ተቀባይነት የሌላቸው አንቀጾች ወይም ይዘቶች/ሀሳቦች በሀገራችን ኢትዮጵያ በየትኛውም ሁኔታና ደረጃ በምንም መልኩ ፍፁም ተፈፃሚ ሊሆኑ እንደማይችሉ ከወዲሁ በአጽንኦት እያስገነዘብን 98% የሚሆነውን ህዝቦችን እንደመወከላችን ይህን ቁርጠኝነታችንን የአውሮፓ ኅብረት፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት፣ ምዕራባውያኑ ሀገራት እና የአፍሪካ ኅብረት ከወዲሁ እንዲገነዘቡ በአጽንኦት እናሳስባለን።

የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ
INTER-RELIGIOUS COUNCIL OF ETHIOPIA

ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይባርክ!

ይህ እንዲህ ብኾንም የወንጌላውያን አማኞች ካውንስል ተጠርነቱ ለጠቅላይ ሚንስቴሩ ነውና ከመቀበል ውጪ ሌላ ምርጫ የለውም። ምክንያቱም ወንጌላውያን በይፋ ክብራቸውን ለአውሬው አስረክበዋል ። የአውሬው ብሮ ካንስሉ ነውና። በዚህ ሰዓት ይኽ ሕግ ወደታች ስወርድ ፣ ተመሳሳይ ጾታ በቤተክርስቲያን አላጋባም፣ ጾታ የቀየሩትን አናስተናግድም ፣ ለሕፃናት የልቅ ወሲብ ትምህርት አንሰጥም .... የሚሉቱ ታማኞች አገልጋዮች አማኞች ለእስር ይዳረጋሉ ። ልረሸኑም ይችላሉ ። አውሬው እየጠረገ ያለውን መንገድ ተመልከቱ ። የራሱ የውሸት አገልጋይ እና የራሱ አገልጋይ መንግስት መሳሪያዎቹ ናቸው። ታምናችኹ እየተከተላችኹ ያላችሁ ውሸቱን በግልጽ በመቃወም መከራን ትቀበላላችሁ ። ተመሳስላችሁ ለመኖር ካሰባችሁ ኪዳችኋልና ከጌታ ጋር እድል ፈንታ የላችሁም ።ዛሬ ላይ ሰይጣን በኹለቱም ተወካዮቹ [በመንግስትና በሃሰተኛ አስተማሪዎች ] በኰል በመኾን ዘመኑን ማወቅ ያልቻሉትን ብርሃን በመምሰል እያታለለ ይገኛል ። ድል ነሺ በመኾን ብቻ

የዘላለም ሕይወት አሸናፊነት ማረጋገጫ፤ በኹለተኛው ሞት [በእሳት ባሕር አለመጣልን] የአለመጎዳት ምልክት [አክሊልን] ይወስዳል ፥ልጆቼ ወይም ቤተ ወይም እናቴ ወይም አባቴ ሳትል መስቀሉን [መከራውን ] ለመቀበል ተዘጋጅ። ጆሮ ያለው ይስማ።

፫." በጴርጋሞንም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፦ በሁለት ወገን የተሳለ ስለታም ሰይፍ ያለው እንዲህ ይላል፦ የሰይጣን ዙፋን ባለበት የምትኖርበትን አውቃለሁ፤ ስሜንም ትጠብቃለህ፥ ሰይጣንም በሚኖርበት፥ በእናንተ ዘንድ የተገደለው የታመነው ምስክሬ አንቲጳስ በነበረበት ዘመን እንኳ ሃይማኖቴን አልካድህም። ዳሩ ግን ለጣዖት የታረደውን እንዲበሉና እንዲሴስኑ በእስራኤል ልጆች ፊት ማሰናከያን ሊያኖርባቸው ባላቅን ያስተማረ የበልዓምን ትምህርት የሚጠብቁ በዚያ ከአንተ ጋር ስላሉ፥ የምነቅፍብህ ጥቂት ነገር አለኝ። እንዲሁ የኒቆላውያንን ትምህርት እንደ እነዚህ የሚጠብቁ ሰዎች ከአንተ ጋር ደግሞ አሉ። እንግዲህ ንስሐ ግባ፤ አለዚያ ፈጥኜ እመጣብሃለሁ፥ በአፌም ሰይፍ እዋጋቸዋለሁ። መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ። ድል ለነሣው ከተሰወረ መና እሰጠዋለሁ፥ ነጭ ድንጋይንም እሰጠዋለሁ፥ በድንጋዩም ላይ ከተቀበለው በቀር አንድ ስንኳ የሚያውቀው የሌለ አዲስ ስም ተጽፎአል። " [ራእ 2፥ 12-17] ።

ጌታ እራሱን ለቤተክርስቲያኒቱ ስገልጽ ለማንም ሳያዳላ እንደ ሥራው የሚፈርድ እንደኾነ ያስታውቃል ፤ ምክንያቱም አማኞች የራሳቸውን ኃላፊነታቸውን በመተው ፣ ጌታ የሚጸየፈውን ትምህርትና ሕይወት ችግር እንደ ለሌበት ቈጥረው ተመቻችተው ተቻችለው በመኖራቸው ነው። ይኽ አማኝ እንደ ኤፌሶኑ አገልጋይ ጌታ የጠላውን መጥላት ያልቻለ ነው። ነገርግን ለራሱ የእነርሱን ትምህርት አይከተልም ። ሰይጣን መከራውን በሚያበዛበት ጊዜ እንኳን አልካደም ነበር ።

ሰይጣን ከውጭ ኾኖ ስዋጋቸው ማሸነፍ ያልቻሉትን ለመዋጋት ፣ ወደ ቤቱ ውስጥ [አማኝ መስሎ] በመግባት ፣መልኩን ቀይሮ ልዩ ትምህርትን ይመግባል ። ሕይወት የማይገኝበትን ትምህርት፣ ስውር የኾነ፣ ቃሉን እያጣመመ ያስተምራል ። በሃገራችን ላይ ትምህርትን መመዘን አስቸጋሪ ኹኔታ ላይ ደርሷል ።ሰይጣን ለሃሳዊያን በሰጣቸው ዝና በቀላሉ የሰውን አዕምሮ ይቆጣጠራል ። በአንደኛው ትምህርት ብያጣ በሌላኛው ያገኛል ። በበለዓም ትምህርት ብያጣ በኒቆላውያን ትምህርት ይይዛል ፤ ዘወር አሉ እንጂ አልሸሹም ያደርጋቸዋል ። ለእያንዳንዱ ትምህርት የራሱ ምርጥ ባሪያ አለው ። ባላቅ በለዓምን ያስተማረው ትምህርት ተብሎ የተመሰለው፣እግዚአብሐር ወደ አሰበው ስፍራ ማድረስ ስወስዳቸው በመንገድ እንድቂሩ የሚያደርግ ማሰናከያ ትምህርት ነው። ዘኍ 6።

እነዚህ አስፈላጊ ስኾን ስነታረኩ ከሰውነት ስወርዱ ፣ በአሕዛብ ዘንድ ስሙን ስያስሰደቡ ፣ የአማኝነትን ትርጕም በቀላሉ ያጠፉሉ ።በዚህም እምነት ከንቱ ይኾናል ። በውስጥ በተከላቸው ‘አገልጋዮቹ’ ከውጭ ሰው እንዳይመጣ ያደርጋል ፤ እውስጥ ያሉት መንታ ልብ ላይ በመኾን እውነት ደብዝዛ እንድትጠፋባቸው ያደርጋል ። በዚህም ይኸም ትክክል ነው፣ያም

ትክክል ነው በማስባል ፣ ብርቱ ተቃውሞ እንዳይመጣ ያደርጋል ። የዚህ ቤተክርስቲያን መጋቢም መቃወም መጠየፍ ስገባ በዝምታና በመቻቻል ከራሱ ጋር እንዲኖሩ አድርጓል ። የእግዚአብሔር ድምጽ ለአገልጋዩ "መታገስ ሳይገባ ታገሰሃል" የሚል ስኾን፣ ከመሃከል በማውጣት እንዲለያቸው መልእክትን ሰጥቷል ። ነገ ወይም ከነገ ወዲያ ይለወጣሉ ብሎ መታገስን ጌታ አማራጭ አድርጎ አላቀረበም ። ምናልባትም እንዲህ ማድረግ ዛሬ ላይ የዋህ የፍቅር ሰባኪ የሚያስብል ይኾናል ። በጌታ ፊት ግን አይደለም ። ጽዩፍ ነው።

የዚህ ቤተክርስቲያን አገልጋይ ወደ ሃሳዊያን አልሄደም ፤ ከማዕዳቸው አልተጋራም፤ በምስክርነት ሰበብ መቀየጥን አልወደደም ። ነገርግን እራሱ ጋ አቅፎ ይዞአቸዋል። ያውቃቸዋል ። ግን አልተናገራቸውም ። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ዛሬ ላይ የራሷ መንጋ ኾነ መልእክተኛ የላትም፤ የጋራ አገልጋይ እና ምዕመናት አሏት ።ታሽገው ስለሚሰጠው ፖስታው ስሉ አገልጋዮች "መስክሩ ይላል" በሚል ሰበብ ተቀይጠው ጠፍተዋል ። ምዕመናትም በጌታ የወጣውን ቃል ስለማያውቁ አዲስና ልዩ ቃል አውጣብኝ እያሉ፣በምድራዊ ብልጽግና ምኞት ተታልለው ጠፍተዋል ። እግዚአብሔር ይናገራል በማለት በማንም ወስላታ ስነገር፣ ሞኝ መኾን፣ ሳይጠይቁ መቀበልን ትህትና አድርገው ተታልለው ወድቀዋል ። በአድነትም ረክሰዋል ።

በቅርቡ ራሱ የወንጌላውያን አማኞች የብልጽግና ወንጌል የሚሰብኩትን "እንቃወማለን ከእነርሱ ጋር ሕብረት የለንም" በማለት በ32ኛው ጉባዔ መግለጫ አውጥተውም ነበር ፤ብያወጡም ግን ጸንተው አልቆዩም ።ወይም ተግባራዊ አላደረጉም። ኹሉንም ቀይጦ የሚይዘው አቃፊው ካንስል መጣና ቀዩን መስመር አጠፋው ። ብዙም ሳይቆይ የጉባኤው ውሳኔው ተቀልብሶ፣ ከታች በምስሉ ላይ እንደምታዩት እርኩሳን በቤተክርስቲያኒቱ ቆመዋል፣ወርሰዋል ።






ይኽ የኾነው ሰይጣን በራሱ ግብረአበሮቹ [በደርግ ዘመን እንኳን] የውጭ ተግዳሮት ተቋቁመው የቆሙትን ለመጣል፣ መልኩን ቀይሮ ሰርጎ በገባቸው አገልጋዮቹ ነው። እነዚህን ተጠቅሞ ቤተክርስቲያንን ቦርቡሮ ስለጨረሰ አኹን ልነግስ

መጥቷል ። ከመሠረቱም በብልጽግና ወንጌል ሰባኪ ኮንፈረሶቻቸው የሚያደምቁት ኢጋፋሪዎቻቸው የወንጌላውያን አማኞችና አገልጋዮች ናቸው ። በእግዚአብሔር ፊት ስታዩ ክብር የተወሰደባቸው ናቸው ። ለዚህም ነው በቀላሉ ስለምድራዊ ቦታ ብለው ለመቀየር የተጣደፉት። [ካንስሉ ውስጥ የገቡትና የአውሬው አገልጋይ የኾኑት] ።

ኢየሱስ ስፈርድ ለሃሰተኞችና ለተባባሪዎች ደግሞም ሕብረት ከእርሱ ጋር ላደረጉት እኩል ይፈርዳል ። ስይፉ በኹለት በኩል የተሳለ ነውና ኹለቱንም ይቀጥፋል። ስለዚህም ከሐሰተኞች ጋር አሸሸገዳሜ እያላችኹ፣ እየባረካችሁ ፣እየተሞጋገሳችኹ ፣ "በምስክርነት" ሰበብ ዝና እና ሃብት አሰልታችኹ የሚትሮጡትን ሩጫ ጌታ ያውቃል ፣ ተመልሳችሁ ተለይታችሁ ፣ ጌታ የጠላውን ጠላታችሁ ኑሩ። መለኪያ የሌለው መሪና ምዕመናት ስለበዙ፣ ጌታ የተጸየፈውን"፥ የተቀባ ነው" እያሉ፣ የሚቃወሙትን የሚያሳድዱ የዲያብሎስ ግበረአበሮች ማመካኛ የላችውም ። ንስሓ ካልገባችኹ መንግሥተ ሰማይ መግቢያ ትኬት፤ አዲስ ማንነት ክብር[ስም] አይሰጣችኹም፤ ድል አልነሳችኹምና። ምክንያቱም መንግስቱ ለድል ነሺዎች ብቻና ብቻ ናት ። ጆሮ ያለው ይስማ።

፬."በትያጥሮንም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፦ እንደ እሳት ነበልባል የሆኑ ዓይኖች ያሉት በእቶንም የነጠረ የጋለ ናስ የሚመስሉ እግሮች ያሉት የእግዚአብሔር ልጅ እንዲህ ይላል፡-ሥራህንና ፍቅርህን እምነትህንም አገልግሎትህንም ትዕግሥትህንም ከፊተኛውም ሥራህ ይልቅ የኋለኛው እንዲበዛ አውቃለሁ።ዳሩ ግን፡- ነቢይ ነኝ የምትለውን ባሪያዎቼንም እንዲሴስኑና ለጣዖት የታረደውን እንዲበሉ የምታስተምረውንና የምታስተውን ያችን ሴት ኤልዛቤልን ስለምትተዋት የምነቅፍብህ ነገር አለኝ፤ ንስሐም እንድትገባ ጊዜ ሰጠኋት ከዝሙትዋም ንስሐ እንድትገባ አልወደደችም። እነሆ፥ በአልጋ ላይ እጥላታለሁ፥ ከእርስዋም ጋር የሚያመነዝሩትን ከሥራዋ ንስሐ ባይገቡ በታላቅ መከራ እጥላቸዋለሁ፤ልጆችዋንም በሞት እገድላቸዋለሁ፤ አብያተ ክርስቲያናትም ሁሉ ኵላሊትንና ልብን የምመረምር እኔ እንደ ሆንሁ ያውቃሉ፥ ለእያንዳንዳችሁም እንደ ሥራችሁ እሰጣችኋለሁ። ዳሩ ግን ይህን ትምህርት ለማትይዙ ሁሉ የሰይጣንንም ጥልቅ ነገር እነርሱ እንደሚሉት ለማታውቁ ለእናንተ በትያጥሮን ለቀራችሁት እላለሁ፤ ሌላ ሸክም አልጭንባችሁም፥ነገር ግን እስክመጣ ድረስ ያላችሁን ጠብቁ። ድል ለነሣውና እስከ መጨረሻም ሥራዬን ለጠበቀው እኔ ደግሞ ከአባቴ እንደ ተቀበልሁ በአሕዛብ ላይ ሥልጣንን እሰጠዋለሁ፥ በብረትም በትር ይገዛቸዋል፥ እንደ ሸክላ ዕቃም ይቀጠቀጣሉ፤የንጋትንም ኮከብ እሰጠዋለሁ። መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ።" ራእ 2፥18-29።

ለትያጥሮን ቤተክርስቲያን የቀረበው መልእክት በውስጧ ላሉት ለ4 ወገኖች ነው። አንደኛው. ለዋናው ለአገልጋዩ ስኾን፣ ኹለተኛው. ነቢይ ነኝ ለሚትለዋ ነው፣ ሦስተኛው. ነቢይ ነኝ በምትለዋ ለተሳሳቱት ለጌታ ባሪያዎች አገልጋዮች ስኾን፣ የመጨረሻው ነቢይ ነኝ በምትለዋ ላልተሳሳቱት አማኞች ነው። ኹሉንም አብጠርጥሮ ስለሚያውቅ የተሰወረ ነገር ስሌለው ጌታ ለእያንዳንዱ ይናገራል ። በዚህም ለዋናው መጋቢ ሃሰተኛይቱን እያወቀ በግልጽ መናገርና መቃወም ስገባው፣ መንጋውን

ስታሳስት ዝም በማለቱ ነቅፎታል ።ምንም እንኳን ለራሱ ደኅና ብኾንም ስለ ሌሎች ግድ ብሎት አለማድረጉን ጌታ አልወደደም።

ሌላኛይቱ መልእክት ተቀባይ ራሷ በጣኦት መንፈስ የምትሠራ ፣ውሸትን የምታስተምር ፣ የማያውቁትን በስህተት ትምህርት የምትበርዝ ነቢይ ነኝ የሚትል ናት። ኤልዛቤል የሃሰተኞች መገለጫ ስም ነው። በጌታ የተላኩህ ነኝ በማለት ሳትላክና ሳይናገራት በስሙ ውሸትን ለምታስተምረዋ ፣ የንስሐ ዕድል ተሰጦቷታል ። ይኹን እንጂ ልትመልስ አልወደደችም ። ጌታ ለሰው ልጆች ኹሉ ያለው ሃሳብ መልካምና መዳን እንደኾነ እንረዳለን ። ልትመለስ ስላልወደደች በመጨረሻም ቍጣውን ልገልጥባት ወደደ፤ አልጋ ላይ ልጥላትና ልያሰቃያት ። ማንም ከእጁ ልታደጋት ኾነ ሊቃወመው አይችለውምና። ትምህርቷ ከእርሱ ያልኾነ "በዝሙት" ነው የተመሰለው ። ዛሬም እኛም የተቀበልነው ትምህርት ከማን እንደኾነ ልናውቅ ይገባናል ።እርሷ ብትሞት እንኳን መልኩን ቀይሮ የሚሠራው ሰይጣን አለና። የክርስቶስን በሥጋ መምጣትና ሥላሴን የሚክዱ ደግሞም መዳን ሕግን በመጠበቅ ነው የሚገኘው የሚሉ ነበሩ ።1ዮሐ። አኹን ግን ይኽንን መሠረታዊ ትምህርት ሳይክዱ ልዩና መጥፊያ መንገድ አበጅተው መልኩን ቀይሮ መጥቶባቸዋል ።ዛሬም ሰይጣን ከዚህ በፊት በማይታወቁ ኑፋቄዎች ስያወናብድ ይኖራል ። ከበለዓም ትምህርት ያመለጠ በኒቆላውያን ትምህርት ይገኛል ወይም ነቢይ ነኝ በሚሉት ስር፣ ስለዚህም ትምህርት ቀላል ነገር አይደለም ፤ዘር ነው ፍሬ አለው ።ልንጠነቀቅ ያስፈልገናል ። ጤናማ ትምህርት ያልኾነ ኹሉ የዘላለምን ሕይወትን ያጠፋል ።

ደግሞም ሌላኛው መልእክት በትምህርቷ ለወደቁ፤ ለተከተሉ፤ አማኞች ነው ። ትያጥሮን ከውጪ መከራ አልነበራትም ። በውስጥ የገባው መርዝ ግን ሞገሷን ቀምቷታል፤ ብርሃኗንም አደብዝዞታል ። እነኚህ አማኞች ናቸው ፤ የጌታ ባሪያዎች ። አስተዋለቻችኹ? በደሙ የፀደቁ የዳኑ በክርስቶስ ያሉት ናቸው ። ነገርግን ይኽንን ከእግዚአብሔር ያለኾነውን ትምህርትን ተቀበሉ ተማሩ፤ ተከተሏት፤ ተባበሯት። ጌታም "ንስሐ ካልገቡ" የእርሷን ፍርድ እንደሚሰጥ አስታወቀ ። የእርሷ ፍርድ የሥራዋ ዋጋ ፣ ለአሰሪዋ ለዲያብሎስ የተመደበው ነው። እነዚህ አማኞችም ምንም እንኳን ሕይወትን ብቀበሉም፤ የዳኑ ብኾንም በትምህርት ንፋስ ተወስደዋልና በንስሐ ካልተመለሱ እሳት ባሕር ይጠብቃቸዋል ። በዝሙት ኃጢአት የተጠመደ መዳኑን አያጣም የሚሉት፣ በትምህርት ስህተት የኤልዛቤል ፍርድ እንደሚቀበሉ ብያስተውሉ እንዲያ አይሉም ነበር። ሳያውቁ ሳይኾን እንደ ኤልዛቤል "ነቢይ ነኝ"ብለው የሚያስተምሩ የሚያስቱ ስለኾኑ እንጂ ቃሉ በግልጽ ተጽፏል ። ከእግዚአብሔር እንዳልኾኑም እናውቃለንና ።

ሌላኛው መልእክት የተቀበሉት ንፁህ አማኞች ናቸው ። ኤልዛቤልን ያልተቀበሉ። እነዚህ የተሰጣቸው ጸጋ እንደ እረኛው ስላይደለ ጌታም ፣ ያላቸውን እስኪመጣ ድረስ እንዲጠብቁ ብቻ ነገራቸው ። ሌላ አልጭንም አላቸው። ምክንያቱም በዚህ ኹኔታ ይኽንን እያዩ መኖር በራሱ ስቃይ ነው። ደኅና የነበረው አማኝን እየጣሉ በትምህርት እየበረዙ ስያስቱ ፣

በመድረካቸው ስያጓሩ ታግሰው መኖር በራሱ መከራ ነው። ዛሬም ለኢትዮጵያ አብያተክርስቲያናት ጌታ ለእነዚህ ዓይነቶች የሚለው ይኸንኑ ነው። ያላችኹን ጠብቁ። የመጀመሪያውን እምነታችኹን አጥብቃችሁ ያዙ።

ደግሞም ለኹላቸው ለ4ቱም ወገኖች ጌታ ድምጹን ሰምተው ፣በፈጽሙ ፣ብመለሱ ፥ ትልቅ ነገር እንዳዘጋጀላቸው ይገልጻል ። ትልክ ክብር ትልቅ ከፍታና ስልጣን እንደሚጠብቃቸው ። ይህም ባልተመለሱ በውጭና በውስጥ ባሉት አሕዛብ ላይ መሰልጠንን ነው፤ ያውም እንደ ሙሴ እና እንደ ኤልያስ ። ሙሴ በአሕዛብ ላይ እንደ አምላክ እንዲኾን እንደተሾመ፣ ኤልያስ ከአፉ በሚወጣ እሳት እንደሚያጠፋቸው ፣ ድል ነሺ የኾኑ ቅዱሳን፣ እግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው አይነት ስልጣን ፥ ኢየሱስ ደግሞ ለእኛ  ለድል ነሺዎች ይሰጣል ። አሕዛብ እንደ [አምላክ] መቀጥቀጥ፣ ልቋቋሙት በማይችሉ መለኮታዊ መቅሰፍት [ብረት] መምታት የሚጠብቀን ክብርና ስልጣን ነው። ድል የሚነሳ ብቻ ይገዛቸዋል ይመራቸዋል ወይም እረኛ ይኾናቸዋል ወይም ያስተዳድራቸዋል እንደ በላይ ባለሥልጣን ። አስቡ ይኸንን ክብር የሚያገኙት በሃሰት ትምህርት ባለመያዛቸው ነው። የአገዛዛቸውም ሃይል ልደፈር የማያስችል መለኮታዊ ሃይል ነው። ይገዛቸዋል የሚለው ቃል

* Lexical: ποιμαίνω - Transliteration: poimainó- Part of Speech:  Verb-  Phonetic Spelling: poy-mah'-ee-no-

Definition: to  shepherd,  tend, herd; hence: to rule, govern.- Origin: From poim en; to  tend as a shepherd of (figuratively, superviser).- Usage: feed (cattle), rule. [Hebrew/Greek Interlinear Bible]

*4ቱም አብያተክርስቲያናት በምዕራፍ ኹለት ላይ ስንመለከት ሰይጣን የውጭና የውስጥ ተግዳሮት እንደሚያመጣ የተገናዘብን ይመስለኛል።ወይ በሃሰተኛ በውስጥ ኾኖ ወይም በሃገረ ገዥ መንግስት ኾኖ ወይም አማኞች ከጠነከሩበት ኹሉቱንም ሃይላት በመጠቀም ይሠራል፤ ይኸንንም ተግዳሮት ድል በመንሳት ብቻ የሚያገኙት ሕይወትና በረከት በግልጽ ተገልጿል ። ሰይጣን ከውስጥ በሃሰተኛ አስተማሪዎች ፣ሕይወት በማይገኝበት ትምህርት ቤተክርስቲያንን ስያምስ፣ እንደ ሚስጥ ቦርቡሮ ስጨርስ ፤ ከውጭ ደግሞ በዓለም መንግሥታት ሃገር ገዥ በኩል ሕግ በማውጣት እንደሚያሳድድ ፈተና እንደሚያመጣ እናስተውላለን ። ሰይጣን ኹለቱንም ሃይላት በመጠቀም በጣምራ የመጨረሻውን ፈተና፣ መከራ በቤተክርስቲያንን ላይ ያደርሳል ። ድል የሚነሱት ብቻ ግን ወደ ክብር ይደርሳሉ ።

፩. "በሰርዴስም  ወዳለው  ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፡- ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስትና ሰባቱ ከዋክብት ያሉት እንዲህ ይላል፡- ሥራህን  አውቃለሁ ሕያው እንደ መሆንህ ስም አለህ ሞተህማል።ሥራህን በአምላኬ ፊት ፍጹም ሆኖ አላገኘሁትምና የነቃህ ሁን፥ ሊሞቱም ያላቸውን  የቀሩትን  ነገሮች አጽና ። እንግዲህ እንዴት እንደ ተቀበልህና እንደ ሰማህ አስብ፥ ጠብቀውም ንስሐም ግባ። እንግዲያስ   ባትነቃ እንደ ሌባ እመጣብሃለሁ በማናቸውም ሰዓት

እንድመጣብህ ከቶ አታውቅም። ነገር ግን ልብሳቸውን ያላረከሱ በሰርዴስ ጥቂት ሰዎች ከአንተ ጋር አሉ፥ የተገባቸውም ስለ ሆኑ ነጭ ልብስ ለብሰው ከእኔ ጋር ይሄዳሉ። ድል የነሣው እንዲሁ በነጭ ልብስ ይጐናጸፋል፥ ስሙንም ከሕይወት መጽሐፍ አልደመስስም፥ በአባቴና በመላእክቱም ፊት ለስሙ እመሰክርለታለሁ። መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ።" ራእ 3፥ 1-6።

ይህቺ ቤተክርስቲያን "ሕይወተ የተሳከልኝ፣ አገልግሎቴም የቀናልኝ ነኝ" የሚትል ናት። ነገርግን በጌታ ፊት ስም የላትም ፤የምትለዋ እውቅናና ምስክርነት የላትም ። የሞተች ናት። መከራ በሌለበት መከራውን ባለመቀበል በመሸወድ በመመሳሰል ትኖራለች ። ብርሃኗ ልታይ ያልቻለ ነው። እያገለገልኩ ነኝ ብለህ እየደከምክ ፣በጌታ ፊት ግን የሞተ ሥራ እንደኾነ ስትሰማ ምን ይሰማሃል ? ጌታ ለምን እንደሚትሠራ የልብህን ያውቃልና ። በወንጌል ለመክበር /በወንጌል ለመኖር/ እንደኾነም ያውቃል ። ላይ ላዩ "አገልግሎት" ብባል እንኳን ጌታ፡- ሕብረትህን ፣ልብን፣ ዓላማን አብጠርጥሮ ያውቃል ። ከእርሱ የተሠወረ አንዳች ነገር የለምና ።ይህቺ ቤተክርስቲያን በቸልተኝነት ስለምትኖር፣ በድንዛዘ ውስጥ ስላሉ የሚቀበሉት መከራ የላቸውም ።ታማኝ ምስክሮች ብኾኑ ከውጪም ከውስጥም መከራው ያይል ነበር። በዚህ ሁሉ ግን ቅሬታዎች አሉት። ተጠብቀው ታምነው የሚኖሩ። በመከራ የደረሰውን ወንጌልን መከራውን በመቀበል በመታገስ በመቃተት የሚኖሩ ። በአገልግሎትህ አንቱ የተባልክ ብትኾን እንኳን "የሞተ ነው" የሚለው የጌታ ምስክርነት አስደንጋጭ ነው።

ውድ አንባቢ ኾይ;ይኼኔ በድካሜ ምክንያት መዳኔን አላጣም እያሉ እየተሞኙ ይኾናል ። በሕይወት መዝገብ ላይ ስሙ የሰፈረ አይነሳም፤አይፋቅም፤ አይደመሰስም እያሉ ይኾናል ።ጭራሽ ንስሐ ባልገባም "አልጠፋም" እያሉ ይኾናል ።እንዲያ የሚያስብለው ግን ሰይጣን እንጂ የእግዚአብሔር መንፈስ አይደለም ። ለእነዚህ አማኞች ጌታ የሰጠው መልእክት ግልጽ ነው። ታማኝ ምስክር ኾነው ለኖሩትና ንስሐ ለሚገቡት ፣ስማቸው በሕይወት መዝገብ ላይ ይኖራል ፤አይጠፋም ፤አይፋቅም። ነገርግን ንስሐ ለማይገቡት ስማቸው ከሕይወት መዝገብ ላይ ይነሳል ፤መጥፋት ይኾናል ።እንግዲህ እነኚህ ከሕይወት መዝገብ ላይ ስማቸው የሚደመሰሱት ንስሐ ባለመግባታቸው ብቻ ነው። የዳኑ ያመኑ ነበሩ። ሕያው የኾኑ፣ የፀደቁ፣ በሕይወት መዝገብ ላይ ስማቸው የተጻፈላቸው ነበሩ።ነገርግን ንስሐ ባለመግባታቸው ልደመሰሱ፤ስማቸው ልሠረዝ ደርሷል ። ከሕይወት ልጎድል።

በጌታ ፊት የሞተ የተባለ እንዴት ሕይወትን ያገኛል? አያገኝም። መልአኩም በሕይወት መዝገብ ላይ ስማቸውን አያገኝም። ተጽፈው ነበር ተፋቁ፤ ዕድል አግኝተው ነበር ተሰናክለውና ወደቁ፤ ድነው ነበር መዳናቸውን ባለመጠባቃቸው አጡ፤ ከዓለም ወጥተው ነበር ተመልሰው ገቡ፤ ከግብጽ ወጥተው ነበር ባለመታዘዛቸው በመንገድ ላይ ወድቀው ቀሩ፤ቸልተኛ በመኾኑ ከሕይወት ጎደሉ። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ስበዛ ግልጽ ነው።ሰው ግን የራሱንና የሰይጣንን እያስገባ ያወዛግባል። መዳንን የማታጣው ነጭ በመልበስ በመኖርና ንስሐ በመግባት በመታጠብ በመታደስ ነው። ስለዚህም አኹንም

ደግሜ ደጋግሜ እላለሁ ከእነዚህ ውጪ የሚገለጥ ሃሰተኛ አስተማሪ የለም። ከመርዛቸው ውጡ ከሕይወት እንዳትወጡ ። ከእነርሱ ራቁ ከሕይወት እንዳትጎድሉ። ከሚታሰቡት በላይ መልካቸውን ቀይረው በግ መስለው የመጡት ተኩላዎች ሃሰተኛ አስተማሪዎች እነዚህ ናቸው ። በጌታ "ከሕይወት መጽሐፍ ስማቸውን እደመስሳለሁ" የተባሉት ስለ ቸልተኛነታቸው ነው፥ በኃጢአት ምክንያት ከኾነ ወዳጄ ልጠይቅህ ; ሰይጣን ለምን በኃጢአት ምክንያት አትጠፉም ይልሃል ?በኃጢአት ምክንያት ከክብርህ እንዳወረደ እንዴትስ አታስተውልም? ሰይጣን ለምን ንስሐ ባትገባም አትጠፉም ይልሃል ? ከሕይወት መዝገብ መጽሐፍ ላይ አዕምሮህን በውሸት እውቀት በመሙላት እንድትደመሰስ ለማድረግ አይደለምን ? በውኑ የመዳን እግርግጠኝነት ፣አለመጠራጠር፣ ዋስተና ፥በኃጢአት ምክንያት ንስሐ ባለመግባት አልጠፉም ብሎ ማመን ነውን? አይደለም። የሰይጣንን ሃሳብን አንስተውም። አንባቢ ኾይ ከእነዚህ ሃስተኛ አስተማሪዎች ራቁ አልያ በውዴታ ነፍሳችሁን ለስኦል ሙሽርነት ታዘጋጃላችኹ! ይኽንን በብዙ ጭንቅ በምጥ ኾኜ በክርስቶስ ፍቅር እላለሁ ። መጨረሻውን ሳስብ ዓይነ በእንባ ይሞላል።

የእብራዊያን ጸሐፊ በሐዲስ ኪዳን ; አይደለም ኃጢአትን ሠርተ ፣ሥራውን መልእክቱን ቸል ብትል እንኳን የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚደርስ ይገልጻል ፦ “በመላእክት የተነገረው ቃል ጽኑ ከሆነ፥ መተላለፍና አለመታዘዝም ሁሉ የጽድቅን ብድራት ከተቀበለ፥ እኛስ እንዲህ ያለውን ታላቅ መዳን ቸል ብንለው፥ እንዴት እናመልጣለን**?**” [ዕብ 2፥2]፣ አናመልጥም ። በኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው ሕግ ከሙሴ ሕግ በላይ የሚቀጣ ነው።ምክንያቱም የነገረው ልጁ ነው፤የከፈለውም ሕይወቱን ነው። ሰይጣን ግን ስም በሰጣቸው ሃሰተኛ አስተማሪዎች ብዙዎችን እያሳተ ይገኛል ።በውሸት እውቀት እየመረዘ ይገኛል ።የተጻፈ አይነሳም ይላሉ። የማይነሱት ግን ሩጫቸውን ስፈጽሙ ነው፤መዳናቸው ጠብቀው ነጭ ለብሰው ስኖሩ ነው ። እነዚህ ሃሰተኞች ነገረስራቸው ሰውን ማወዛገብ ነው።አማኝ ኃጢአት ልሠራ አይችልም ይሉና፤በኃጢአቱ ምክንያት መዳኑን አያጣም ይላሉ፤ከዚህም ንስሐ ባይገባም መዳኑን አይጣም ይላሉ።እንዲሁም አንዳንዶቹ ንስሐ አያስፈልግም ማለት ብቻ ሳይኾን፣ ንስሐ የሚገቡትን እንደ አለማመን ይቆጥራሉ ። ሰው ግን የሰውና የሰይጣን አዕምሮ ውጤት ስኾን ያስፈራል ። ጭፍናምነቱና አለማስተዋሉ፤ድንዛዜው ያስፈራል ። አንተ ግን ይኽንን የመስማት የማንበብ ዕድል አግኝተኻል። ጆሮ ካለህ ስማ።ግድ የለህም ተላውሶ ተከሽኖ የቀረቡ እውነቶችን አትቁጠር። ዋናውን ከነጠቁ ምን ልረባ ከንቱ እውቀት ። ውጣ ተለያቸው ። ስምህ ከሕይወት መጽሐፍ እንዳይደመሰስ የእግዚአብሔርን ድምጽ በመስማት ድል ልትነሳ ይገባሃል።

፮. "በፊልድልፍያም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፦ የዳዊት መክፈቻ ያለው፤ የሚከፍት፥ የሚዘጋም የሌለ፤ የሚዘጋ፥ የሚከፍትም የሌለ፤ ቅዱስና እውነተኛ የሆነው እርሱ እንዲህ ይላል።ሥራህን አውቃለሁ፤ እነሆ፥ በአንተ ፊት የተከፈተ በር ሰጥቼአለሁ ማንምም ሊዘጋው አይችልም፤ ኃይልህ ምንም ትንሽ ቢሆን ቃሌን ጠብቀሃልና፥ ስሜንም አልካድህምና።እነሆ፥ አይሁድ ሳይሆኑ፦ አይሁድ ነን ከሚሉ ነገር ግን ከሚዋሹ ከሰይጣን ማኅበር አንዳንዶችን

እሰጥሃለሁ እነሆ፥ መጥተው በእግሮችህ ፊት ይሰግዱ ዘንድ እኔም እንደ ወደድሁህ ያውቁ ዘንድ አደርጋቸዋለሁ። የትዕግሥቴን ቃል ስለ ጠበቅህ እኔ ደግሞ በምድር የሚኖሩትን ይፈትናቸው ዘንድ በዓለም ሁሉ ላይ ሊመጣ ካለው ከፈተናው ሰዓት እጠብቅሃለሁ። እነሆ፥ ቶሎ ብዬ እመጣለሁ፤ ማንም አክሊልህን እንዳይወስድብህ ያለህን አጽንተህ ያዝ ። ድል የነሣው በአምላኬ መቅደስ ዓምድ እንዲሆን አደርገዋለሁ፥ ወደ ፊትም ከዚያ ከቶ አይወጣም፤ የአምላኬን ስምና የአምላኬን ከተማ ስም፥ ማለት ከሰማይ ከአምላኬ ዘንድ የምትወርደውን አዲሲቱን ኢየሩሳሌምን፥ አዲሱንም ስሜን በእርሱ ላይ እጽፋለሁ። መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ።" ራእ 3፥1-13 ።

ይህቺ ቤተክርስቲያንም እንደ ሴምርኔስ ቤተክርስቲያን ነቀፌታ አልተቀበለችም፤ እንደ ሴምርኔስ ቤተክርስቲያንም የውስ ጠላቶች "አይሁድ ነን" የሚሉ ሰዎች ነበሯት ። ነገርግን ይህቺ ቤተክርስቲያን ከውጭ እንደ ሰምርኔስ ቤተክርስቲያን መከራ እየመጣባት አይደለም ። የዳዊት ቤት የመንግስቱ ምሳሌያዊ ገላጭ ቃል ነው። ክርስቶስ በዳዊት ቤት ለዘላለም ይነግሳል ተብሏልና።ሉቃ 1፥32-33። ለዚህች ቤተክርስቲያን ወደቤቱ ማስገባትም፣ከቤቱ ማስወጣትም ስልጣን ያለው ጌታ ፥ "የተከፈተ በር ሰጥቻለሁ" ይላቸዋል ። ይኸም በር የአገልግሎት የወንጌል በር ነው። ጳውሎስ “ሥራ የሞላበት ትልቅ በር ተከፍቶልኛልና ተቃዋሚዎችም ብዙ ናቸው።” [1ኛ ቆሮ 16፥9]፣እንዳለው ሃሰተኞች ወንድሞች "አማኝ ነኝ" የሚሉት እያሉ፣ ብዙዎችን የምወርሱበትና ለብዙዎች መዳንና መትረፍ ምክንያት የሚኾኑበትን፣ አገልግሎት እንዳላቸው፣ ማንም ልያስቆማቸው ኾነ ልቋቋማቸው እንደማይችል ጌታ ስልጣን መስጠቱን ይገልጻል ። ምክንያቱም ይህቺ ቤተክርስቲያን በትንሿ ኃይል [መክሊት] ታምና ጠብቃ አትርፋ ተገኝታለች፤ ስለዚህም ጨመረላት።

በሰዎች ዘንድ አማኝ የሚመስሉ ስያናውጡም፣ በትንሿ መክሊት ታምና ጸንታ ኖራለች ።የናቁትን በክፉ የተናገሩትን ፣ የሸነገሉትን፣ በእግሩ ሥር እንደሚጥላቸው ገልጿል; በጌታ የተወደደ ሞገሳም እንደኾነ ያውቁ ዘንድ አደርጋለሁ ብሏል። እንግዲህ ይኽንን ድምጽ የሚሰሙት ባላቸው ጸጋ ጸንተው በትምህርት ንፋስ ሳይወሰዱ የኖሩ፣ የጠበቁ ብቻ ናቸው ። ጌታ በሃሰተኞች ላይ ለመፍረድ የልጆቹን ንፅህና ይፈልጋል ። ምክንያቱም ለእነርሱ የመጣው እሳት ይዞ እንዳይሄድ በማሰብ ። ሃሰተኞች ላይ ይኽ መለኮታዊ ፍርድ የሚዘገይ ከኾነ; የእግዚአብሔር ልጆች እራሳቸውን ይፈትሹ። ጌታ መለኮታዊ ፍርዱን በልጆቹ በኩል ያስፈጽማል፤ በእጃችሁ ጥሎ ክብራችሁን ያሳያል ። ያለነቀፌታ እንዲንገኝ በጸጋው እንበርታ።

ጌታ ለዚህች ቤተክርስቲያን የሰጠው ተስፋ የሚደንቅ ነው፤ አስተውለን እንመልከት ። በእግዚአብሔር ትዕግሥት መከራውን ታግሰዋልና ጌታ፣ በዓለም ላይ ሰዎችን ልፈትን ከሚልከው መከራ "እጠብቃችኋለሁ" ብሎአቸዋል።ማለትም ፈተናው በሕይወት ሥጋ ላሉት ሁሉ የሚመጣ ስሆን በሕይወት ሥጋ ላሉት አማኞች ግን ጌታ ከመከራው ወይም በመከራው ይጠብቃል ። በዓለም ያሉት መከራውን ስቀበሉ ጌታ "የመጀመሪያው መከራ በቂ ነውና" በማለት ከሚመጣው ታላቁ መከራ ይጠብቃቸዋል ። ክፍሉ የሞቱ ቅዱሳንን አያካትትም ፤ በሕይወት ሥጋ ያሉ አማኞችን ከመከራው

ስለመጠበቅ እንጂ ።የክፍሉ ሃሳብ ቅዱሳንን ከመከራው የምጠበቁት "በመነጠቅ ነው" ለማለት አያስደፍርም ። በምድር እያሉ በመለኮታዊ ጠባቆት ስር በመኾን ኢንደሚጠበቁ ያስረዳል። ምክንያቱም የፊላድልፍያም ቤተክርስቲያን የመጀመሪያ የዚህ ትንቢት አካል ናት። ከመከራው የተጠበቁት ተነጥቀው አይደለም ። ተነጥቀው ነው ካልን ንጥቀት "ያኔ ኾኗል" ወደ ሚል ትምህርት ይወስደናል። ከቅድሜ መከራ ንጥቀት አስተምህሮ ጋርም ይጋጫል ።ስለዚህም ከመከራው በመከራው በምድር ላይ በመለኮታዊ ሃይል ተጠብቀው ነው የሚያልፉት የሚለው የማያሻማ አግባብነት ያለው ትክክለኛ ምላሽና አስተምህሮ ይኾናል። ወደ ውስጥ ስንዘልቅ እናየዋለን ።

አንባቢ ይኽንን ስያጠኑ መልእክቱ በቀጥታ በስም ለተጠቀሰችው አጥቢያ ብኾንም ፣ መንፈስ ቅዱስ "ጆሮ ያለው ለዚህች ቤተክርስቲያን የተነገረውን መልእክት ይስማ" ብቻ አይልም፤ "ለአብያተክርስቲያናት ኹሉ የሚለውን" እንጂ። ስለዚህም ለአብያተክርስቲያናት የሚለውን የመስማት ግዴታ አለብን። አይደለም እኛ እነኚህ ሰባቱ አብያተክርስቲያናትም አንዳቸው የሌላውን የመስማት ግዴታ አለባቸው ።መንፈስ ጆሮ ያለው ይስማ ኹሉንም በማለት ስያጠቃልል፤ የምንሰማው ደግሞ ለአብያተክርስቲያናት የተነገረውን ኹሉንም ነው። ስለዚህም ጌታ መጠነኛ ፈተና በየጊዜው እንደሚልክ መረዳት እንችላለን ።በመጨረሻም ከመምጣቱ በፊት በሚልከው በታላቁ መከራ፣ ከሚያበጥረው መከራ ልጠብቀን እንደኾነ እንረዳለን ። አዎን ለእኛ ያልተገባ ያልተፈቀደ መከራ አለ። የተፈቀደውን በማለፍ ያልተገባውን በጠባቆቱ ተጠብቀን እንሻገራለን። ምክንያቱም ለእኛ ስለእምነታችን የሚመጣ መከራ ትዕግሥትን የሚያስተምር ፈተና ስኾን፣ የማያምኑትን ለመቅጣት የሚመጣ ፈተና ግን መቅሰፍት ነው። ከመቅሰፍቱ በምድር እያለን ይጠብቀናል [ይሰውረናል] በመለኮታዊ ሃይል። ይኽ ተሰፋ አለንና በዚህም ደግሞ እንጽናናለን። ሃሌ ሉያ ።

ስለዚህም ጌታ ለፊላደልፍያ የሰጠው ተስፋ ቃል ለፊላደልፍያ ብቻ አይደለም እንላለን ።ምክንያቱም መከራው ራሱ በምድራቸው ላይ ብቻ ሳይኾን ከሰማይ ለሰው ልጆች ኹሉ የተዘጋጀ ፈተና ነው። በዚህ ፈተና ዓለም ምድር ኹሉ ሞላዋ ታልፋለች። ነገርግን ድል የነሱ አማኞች ፈተናቸውን በድል የተወጡ፣ እምነታቸውን የጠበቁ በዚህ መከራ መሃል አያልፉም ።ከመከራው በመከራው ተጠብቀው ይሻገራሉ ። ይኽ በዓለም ኹሉ የሚመጣ የአየር መበከል ወይም ወረሽኝ ወይም የአንበጣ ወይም ጦርነት ..ልኾን ይችላል ። ግን እነኚህ አማኞች በእግዚአብሔር ጠባቆት ውስጥ በዚያ ሳይጠቁ ያልፋሉ። ጌታ በፊላደልፍያ የመጣውን ወደሌላ ሃገር በመውሰድ ወይም በመንጠቅ እንደሚጠበቅ አልገለጸም ። ግን ከመከራው እጠብቃለሁ እንዳለው ባሉበት ቦታ ከሚመጣው ታላቁ ዓለም አቀፋዊ መቅሰፍት እንደሚጠብቅ አስታውቋል ። ይኽም በዚያ ረሃብ ሰዓት ኤልያስን እንደተጠበቀውና እንደመገበው ፣ በታላቁ መከራ ጊዜም በዓለም ከሚመጣው መቅሰፍት ኹሉ ልጠብቅ እንደኾነ ያስታውቃል ። እንግዲህ በንጥቀት ወይም ከመከራው መጥቼ እወስዳለሁ አላለም ።ከመከራው እጠብቃለሁ ብቻ ነው ያለው። እንዳለውም ከመከራው በመከራው ይጠብቃል ። ምን ይሳነዋል ? ምንም ።

ጌታ በዓለም ከሚመጣው መከራ ሰዓት እጠብቃለሁ ፤ካለህ በኋላ "ቶሎ እመጣለሁ አክሊልህን ጠብቅ ማንም እንዳይወስድብህ ተጠንቀቅ "በማለት አስጠንቅቆታል። አክሊል የሌለው ደኅንነት የለም። አክሊል ተወሰደበት ማለት ሽልማት አጣ ማለት ብቻ አይደለም፣ ድል አልነሳም ተሸንፏል ወድቋል ማለት እንጂ። አክሊልን ራስ ላይ እንደሚደረግ ነገር ብቻ ልናስብ አይገባንም ። አክሊል ክርስቶስ ድል ለነሱት የሚሰጠው ክብር ስልጣን ሕይወት ነው። ድል በመንሳት ለፍላደልፍያ ቤተክርስቲያን ምን ታገኛለች? "ድል የነሣው በአምላኬ መቅደስ ዓምድ እንዲሆን አደርገዋለሁ፥ ወደ ፊትም ከዚያ ከቶ አይወጣም፤ የአምላኬን ስምና የአምላኬን ከተማ ስም፥ ማለት ከሰማይ ከአምላኬ ዘንድ የምትወርደውን አዲሲቱን ኢየሩሳሌምን፥ አዲሱንም ስሜን በእርሱ ላይ እጽፋለሁ።" ራእይ 3፥12 ። ታዲያ ይኽንን ኹሉ ያጣ የወርቅ ሽልማት ነው ያጣው ወይስ ደኅንነቱን ? ከሕይወት መዝገብ መጽሐፍ ስሙ ተደመሰሰ ወይስ አለ? አክሊል የሚያገኙት ኹሉም ድል የሚነሱት ናቸው ። ድል ያልነሳ ድኖ አልቀረም፤አክሊል የለውም ። ለእያንዳንዱ ቤተክርስቲያን ድል ለሚነሱት የሚሰጠውን ተመልከት፤ ወደ ቀድሞው ሕብረት መመለስ፥ ወደ ክብር መግባት፤ የዘላለም ሕይወት ዋስተና ፤ ስልጣን ወዘተ.ኹሉም ድል ለሚነሱት ብቻ ነው። ምክንያቱም መንግስቱ ለድል ነሺዎች ብቻ ናት። አክሊል ማጣት ሕይወትን ማጣት ነው፤ አክሊል የሌለው ወራሽ የለምና ።ስለዚህም መዳን በእምነት ማለት በአፋዊ ንግረት፣ አምኛለሁ ድኛለሁ በመባል የሚረጋገጥ አይደለም ። መዳን በሥራ የሚገለጥ ፤ በጸጋው ጉልበት ድል በመንሳት የሚወረስ ነው። ጆሮ ያለው ይስማ።

፯. " በሎዶቅያም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፡- አሜን የሆነው፥ የታመነውና እውነተኛው ምስክር፥ በእግዚአብሔርም ፍጥረት መጀመሪያ የነበረው እንዲህ ይላል፡-በራድ ወይም ትኩስ እንዳይደለህ ሥራህን አውቃለሁ። በራድ ወይም ትኩስ ብትሆንስ መልካም በሆነ ነበር። እንዲሁ ለብ ስላልህ በራድም ወይም ትኩስ ስላልሆንህ ከአፌ ልተፋህ ነው። ሀብታም ነኝና ባለጠጋ ሆኜአለሁ አንድም ስንኳ አያስፈልገኝም የምትል ስለ ሆንህ፥ ጎስቋላና ምስኪንም ድሀም ዕውርም የተራቆትህም መሆንህን ስለማታውቅ፥ ባለ ጠጋ እንድትሆን በእሳት የነጠረውን ወርቅ፥ ተጐናጽፈህም የራቁትነትህ ኃፍረት እንዳይገለጥ ነጭ ልብስን፥ እንድታይም ዓይኖችህን የምትኳለውን ኵል ከእኔ ትገዛ ዘንድ እመክርሃለሁ። እኔ የምወዳቸውን ሁሉ እገሥጻቸዋለሁ እቀጣቸውማለሁ፤ እንግዲህ ቅና ንስሐም ግባ። እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ፥ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል። እኔ ደግሞ ድል እንደ ነሣሁ ከአባቴም ጋር በዙፋኑ ላይ እንደተቀመጥሁ፥ ድል ለነሣው ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ። መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ።" ራእ 3፥14-22።

ለሎዶቅያ ቤተክርስቲያን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እራሱን ስያስተዋውቅ ፣ "በእግዚአብሔርም ፍጥረት መጀመሪያ የነበረው" በማለት ገልጾላታል። መጀመሪያ የሚለው ቃል ሐዲስ ኪዳን በተጻፈበት [በግሪክኛው] ኹለት ትርጉም የምሰጥ ቃል ነው። ልክ ባማርኛችን "ማለደ" የሚለው ለመነ ወይም በጧት ገሰገሰ የሚል ትርጉም እንደሚይዝ ። ይኽ የቋንቋ ባሕርይ ነውና ያለ ተቋምተኝነት ለመረዳት ጥረት ካደረግን፣ እንደ አውዱ የተኛውን ትርጉም ልወክል ይችላል የሚለውን መረዳት ከባድ አይኾብንም ። ግሪክኛ የሚሞክር ባልኾንም ፣ መዝገበ ቃላቱን በመመልከት መረዳት ያስችለናል ። እናም Bible Interlinear Dictionary "መጀመሪያ" ተብሎ በነባሩ ትርጉም የተተረጎመውን Greek: ἀρχή Transliteration: archḗ Pronunciation: ar-khay'። "አርካይ" ሥልጣንን፣ ወይም ገዥነትን[ግዛትን] ወይም ጅምርን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የሚውል ቃል በማለት አስቀምጧል። ለምሳሌ :- "በኋላም፥ መንግሥቱን ለእግዚአብሔር ለአባቱ አሳልፎ በሰጠ ጊዜ አለቅነትንም ሁሉና ሥልጣንን ሁሉ ኃይልንም በሻረ ጊዜ፥ ፍጻሜ ይሆናል።" 1ኛ ቆሮ 15፥24። አለቅነት ተብሎ የተተረጎመው "አርካይ" የሚለው የግሪክ ቃል ነው፤ እንዲሁም በሮሜ መጽሐፍ ላይ ግዛትን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል፣ "ሞት ቢሆን፥ ሕይወትም ቢሆን፥ መላእክትም ቢሆኑ፥ ግዛትም ቢሆን፥ ያለውም ቢሆን፥ የሚመጣውም ቢሆን፥ ኃይላትም ቢሆኑ፥" ሮሜ 8፥38 ። ቲቶ 3፥1፤ ኤፌ 1፥21፣3፥10፣ 6፥12፤ ..።

አርከይ እንግዲህ እንዲህ የተለያዩ ትርጉሞችን የሚሰጥ ቃል ከኾነ እንደ አውዱ ማየት አስፈላጊ ይኾናል ። መደበኛ ትርጉም በዚህ ክፍል ላይ "ገዥ" ብሎ ተረጉመዋል ። ሃሳቡ የቀረበው ከጊዜ አንፃር ከኾነ፣ "በመጀመሪያ" በማለት መጠቀም ይቻላል፤ ከማዕረግ አንፃር ከኾነ "ገዥ" ተብሎ ልተረጎም ይቻላል ። ስለዚህም በእግዚአብሔር ፍጥረት መጀመሪያ የነበረው የሚለውን ፣ ከጊዜ አንፃር አይተን ከተረጎምነው፣ ኢየሱስ ከፍጥረት መጀመሪያ የነበረ መኾኑን እንደሚገልጽ እንረዳለን። "ያው" እንደኾነ የሚገልጽ ነው። ኢየሱስ በጊዜ ውስጥ እንደተገኘ ከአብ በኋላ እንደተገኘ የሚናገር አይደለም ። እርሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለ አምላክ ነውና፤ዮሐ1፥2። የቃሉን ትርጉም ከማዕረግ አንፃር ካየን የፍጥረታት ገዥ መኾኑን እንረዳለን ። በዚህም በዚያም ኢየሱስ ፍጥረታት ውስጥ የማይመደብ እንደኾነ እንገነዘባለን ።

ሎዶቅያ ቤተክርስቲያን ወይ አትሠራ፣ ወይ አትተው፣ ተኝታ ወይ አልሞተችም፣ ወይ አልተንቀሳቀሰችም በቸልተኝነት ውስጥ ተውጣ ፣ለእግዚአብሔር ሥራ ጊዜ ያጣች ሳታውቅ ቀርታ ወይም ትምህርት ቀይራ አይደለም ። እያወቀች ደንታ ቢስ በመኾን ትኖራለች ። ይባስ ብላም እንደ ዛሬዋ ብልጽግና ወንጌል አማኞች በኢኮኖሚ ሃብቷ መንፈሳነቷን እያማጠነች፣ በከፍታ ላይ እንደወጣችና ምንም የሚጎድላት እንደሌላት በመታበይ ከጸጋው ወድቃ ርቃ ትናገራለች ።

ጌታ ለሎዶቅያ አማኞች ልክ ዓለማዊ የኾነ ሰው እንድቀበለው; ደጅ እንደሚጠና፣ ጌታ በደጇ ቆሞ እንዲታስገባ ይማጠናታል። ያንኳኳል፣ የድሮውን እንዲታስብና የከፈለውን ዋጋ እንዲታስታውስ ይደክማል ። ግን በጠማማ መንገድ

ስለቀጠለች የመጨረሻውን የንስሐ ዕድል ይሰጣታል ። ንስሐ ካልገባች ልተፋት ያውም ልመልሳት እንደኾነ ያስጠነቅቃታል። ዛሬ ሃሰተኛ ነቢያት አስተማሪዎች እንደሚሉት አይደለም ። የንስሐ እድል እንቢ ያሉትን ጌታ ይተፋል፤ ይተዋል። ጌታ በተወው ላይ መንፈስ ቅዱስ አለበት የሚለው ዛሬ አወቅን፣ ፊደል ቆጠርን፣ አሰብን፣ ተራቀቅን ብለው የፈጠሩት የሰዎች ትምህርት ነው። ሰው በንስሐ እንዳይመለስ የእንደገና አምላክ እንደገና እንዳያቆመው ፣ በድካማችሁ ምክንያት አትጠፉም እያሉ ለድፍረት ኃጢአት በተከሸኑ ቃላቶች የእባቡን ትምህርት ይግታሉ። ከእግዚአብሔር ስላልተላኩ በትምህርታቸው የተጠመደ ከኃጢአት ከመመለስና ከመበርታት ይልቅ በድካሜ ምክንያት አልጠፋም በሚል መርዝ አዕምሮን አሳውሮ፣ የመንፈስ ቅዱስን ወቀሳ ቸል ስል ይኖራል ። ጌታ የትውልዱን አዕምሮ ይፈውስ እንጂ እንክርዳዱ ብዙ ነው። በዝሙት የተጠመደውን እንኳን መዳኑን አያጣም እስከማለት ርቀው ይሄዳሉ ። ጤናማ አስተማሪዎችም ይኸንን አይቃወሙም።ምክንያቱም ዕሳቤ ነው መረዳት ነው ብዙ ሙሁራን ይቀበላሉ በማለት የእባቡን ትምህርት ለማጽደቅ የሚከጅሉ ናቸው ።

ካስተዋልን ሎዶቅያ ቤተክርስቲያን ከጌታ ጋር ያላት ሕብረት የቆመ ነው። ወደልባቸው ልገባና እራት ልበላ በራቸውን የሚንኳንኳ ኾኖ የተገለጠላት ቤተክርስቲያን ናት። መንፈስ ቅዱስ ከመክሱሙ የተነሳ ከጹጋ ከመራቃቸው ከመራቆታቸው የተነሳ ሕልውና ያልነበራት መንፈስ ቅዱስ የተዳፈነባት ቤተክርስቲያን ናት። ምን ዋጋ አለው በአንድ ጥቅስ ቲዮሎጂ መሥራት ያምረናልና መልእክቱን መቀበልን አንወድም፤ግልጽ ነበር። እግዚአብሔር ለዘላለም በእኛ ውስጥ እንዲኖር መንፈስ ቅዱስን ልኮልናል።ነገርግን ሰዎች ካልሰሙ የሚያሳዝኑ ከኾኑ ይዳፈናል። በመጨረሻም ከውስጣቸው ይጠፋል ። ኪዳኑን ስላልጠበቅን ባለመታዛችን ፍርድን እንቀበላለን ።እንጣላለን ። እስኪ አስቡ ጌታ የተፋች ቤተክርስቲያን ማነው መንግስቱን የሚያወርሳት? እርሱ ከዘጋ ማን ይከፍታል? እሱ ከአስወጣስ ማንስ ያስገባል ። መንፈስ ቅዱስ እንዴት ከተተፋች በኋላ ይኖራታል ብለን እናስባለን ? ሽንታችንን ገትረንም ለሃሳባችን እንሚገታለን!? በኢየሱስ ስም ከእናንተ ይኸ ይራቅ ። እንግዲህ ድል ለሚነሳው ጌታ ከራሱ ጋር በዙፋኑ ዙሪያ እንዲቀመጥ ያደርጋል ። ድል ላልነሳ ይኸ ክብር አይኾንለትም።

*አኹን ያለውን የተባለውን መልእክት ስናጠቃልል ይኸንን እናሰላስል፣ ድል ያልነሳ አማኝ ምን ያጣል!?

*እንደ ኤፌሶን ቤ/ክን መልእክት ድል የነሳ፣ወደ ቀድሞ ክብሩ ይመለሳል፣"..። ድል ለነሣው በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይወት ዛፍ እንዲበላ እሰጠዋለሁ።" ራእይ 2፥7። ድል ያልነሳ ይኸንን ያጣል።

*እንደ ሴምርኔስ ቤ/ክ ን መልእክት ድል የነሳ፣የሞት ሞትን አይሞትም፤".. ድል የነሣው በሁለተኛው ሞት አይጐዳም።" ራእይ 2፥11። ድል ያልነሳ ይከንን ያጣል።

*እንደ ጴርጋሞን ቤ/ክን መልእክት ድል የነሳ፣ሰማያዊ ሙብልን ያገኛል፤ ወደመንግሥቱም መግቢያ ትኬት።".. ድል ለነሣው ከተሰወረ መና እሰጠዋለሁ፥ ነጭ ድንጋይንም እሰጠዋለሁ፥ በድንጋዩም ላይ ከተቀበለው በቀር አንድ ስንኳ የሚያውቀው የሌለ አዲስ ስም ተጽፎአል።" ራእይ 2፥17።ድል ያልነሳ ይኽንን ያጣል።

*እንደ ትያጥሮን ቤ/ክን መልእክት ድል የነሳ፣ በአሕዛብ ላይ እንደ አምላክ ይኾናል "ድል ለነሣውና እስከ መጨረሻም ሥራዬን ለጠበቀው እኔ ደግሞ ከአባቴ እንደ ተቀበልሁ በአሕዛብ ላይ ሥልጣንን እሰጠዋለሁ፥ በብረትም በትር ይገዛቸዋል፥ እንደ ሸክላ ዕቃም ይቀጠቀጣሉ፤" ራእይ 2፥26-27።ድል ያልነሳ ይኽንን ያጣል።

*እንደ ሰርዴስ ቤ/ክ መልእክት ድል የነሳ፣ ከሕይወት መዝገብ ላይ ስሙ አይፋቅም፤አይነሳም ፤ "ድል የነሣው እንዲሁ በነጭ ልብስ ይጐናጸፋል፥ ስሙንም ከሕይወት መጽሐፍ አልደመስስም፥ በአባቴና በመላእክቱም ፊት ለስሙ እመሰክርለታለሁ።"ራእይ 3፥5። ድል ያልነሳ ይኽንን ያጣል?

*እንደ ፊላደልፍያ ቤ/ክን መልእክት ድል የነሳ፣የአምላክ ባሕርይ በሙላት ይኖረዋል፤ "ድል የነሣው በአምላኬ መቅደስ ዓምድ እንዲሆን አደርገዋለሁ፥ ወደ ፊትም ከዚያ ከቶ አይወጣም፤ የአምላኬን ስምና የአምላኬን ከተማ ስም፥ ማለት ከሰማይ ከአምላኬ ዘንድ የምትወርደውን አዲሲቱን ኢየሩሳሌምን፥ አዲሱንም ስሜን በእርሱ ላይ እጽፋለሁ።" ራእይ 3፥12። ድል ያልነሳ ይኽንን ያጣል!

*እንደ ሎዶቅያ ቤ/ክ መልእክት ድል የነሳ፣ ከአምላክ ጋር በዙፋን [ዙሪያው] ይቀመጣል፤"እኔ ደግሞ ድል እንደ ነሣሁ ከአባቴም ጋር በዙፋኑ ላይ እንደተቀመጥሁ፥ ድል ለነሣው ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ።" ራእይ 3፥21። ድል ያልነሳ ይኽንን ያጣል! * ድል የሚነሳ አማኝ ብቻ ይኽንን ኹሉ ካገኘ፥ ድል የማይነሳ ይኽንን ኹሉ ያጣል ማለት ነው።

*ምን አስተላችሁ? "አማኝ ነኝ" ማለት በራሱ የትክክለኛነት ማረጋገጫ እንዳይደለ፣ ያመኑት በአሸናፊነት ስወጡ ድነው እንደሚቀሩ፣ ሩጫቸውን በአግባቡ ካልጨረሱ [ቸል ካሉ ከደከሙ] ድል እንደማይነሱ ፣ከሕይወትም እንደሚጎድሉ፣በድካማችሁ በኃጥአታችሁ ምክንያት እንደማይጠፉ እውቅና አልተሰጠም ፤ ይልቁንም ከድካማቸው ወጥተው በአሸናፊነት በማለፍ ድል እንዲነሱና፣ ድል ለሚነሳው ብቻ እንደሚሰጥ ተገለጸ። ስለዚህም ለዘላለም ሕይወት ዋስትና ድል መንሳት አማራጭ የሌለው ብቸኛው ምርጫ ነው፣ድል ባለመንስት ሽልማትን [ብቻ] ሳይኾን ሕይወት ይታጣል ፣ ስለዚህም በድካማችሁ ተቆራምዳችሁ እንዲትኖሩ የሚያስተምሩት ትምህርት; ለምን እያዘጋጁ እንደኾነ ያስተውሏል፣

*ኢየሱስ የሞተው ዓለምን እንዳሸነፈ እኛም እንዲናሸንፍ ነው፤ ድል ለማይነሱት ከእግዚአብሔር ዘንድ አንዳች ስፍራ የላቸውም ። በብርታቱ ብርቱዎች እንዲንኾን እንጂ በድካማችን [በኃጢአታችን] እንድንቀጥል ኢየሱስ አልሞተም ።

*ታዲያስ ድል ያልነሳ ምን ያገኛል? ከመጥፋት በስተቀር።ስለዚህም ዘመኑን ዋጁ። ጌታ በጸጋው ድል ለመንሳት ያብቃን።ስለዚህም "ለሚናገረው እምቢ እንዳትሉ ተጠንቀቁ፤ እነዚያ በምድር ላስረዳቸው እምቢ ባሉ ጊዜ ካላመለጡ፥ ከሰማይ ከመጣው ፈቀቅ የምንል እኛስ እንዴት እናመልጣለን? ... አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ እሳት ነውና።" ዕብ 12፥25-29።

## 1.2 ከዚህ በኋላ የሚኾነው

ይኸንን የራእዩን መጽሐፍ ዮሐንስ ራዕዩን በተመለከተበት መንገድ መረዳት ማየት መቻል ያስፈልጋል ።ዮሐንስ የተመለከተው በመንፈስ ኾኖ ነው፤ ካለመንፈስ ቅዱስ ምሪት በያዝናቸው አመለካከቶች ተይዘን ለመረዳት ከሞከርን የመልእክቱ ተጠቃሚ አንኾንም፤ በትክክል አለማወቃችንም ከፍርድ ነፃ አያደርገንም ። እንድናውቅ በልግስና የሚሰጠውን፣ መጻሕፍትን እንድናስተውል አዕምሮን የሚከፍተውን ጌታን አጥብቀን ልንለምነው ይገባናል ፤ያስፈልገናል ። የመረዳት ባለጠግነት እንድበዛ ጸጋ እንድጨመረልን:: ማንም በሥራው ዕሳቤና አስተምህሮ መሠረት ሳይኾን መጽሐፍ ልገልጽ በወደደው መንፈስ ፣ የጥበብና የእውቀት መንፈስ እንድረዳን ሙሉ እገዛ ልንቀበለው ይገባናል ።

አንድ ልብ አንድ መንፈስ አንድ ሃሳብ ያለው እንዴት የተለያዩ የማይገናኙ ትርጓሜዎችን ይሰጣል ? ይኽ የአገልጋዮች በመንፈስ አንድ አለመኾን አለመግባባት ለሰይጣን ትልቁን በርን ከፍቷል ። አዎን የቋንቋቸው መደበላለቅ ለሥራው ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል። ኹሉም ትክክል ነው፤ ይኸም ትክክል ነው፤ያም ትክክል ነው የሚሉ 'አዋቂ' አስተማሪዎች እንዲበረካቱ አድርጓል ። ምዕመናትንም አወናብዶ አወዛግቦ እንዳያነቡ አድርጓል ። አንባቢ ኾይ በተወሰነ ደረጃ፣ የተገለጡ ምሳሌዎች ፍንጭ ይዘህ በግልህ መጽሐፉን በተደጋጋሚ እንዲታጠናው አበረታታሉ ፤ከላይ በምዕራፍ አራት ላይ ዮሐንስ ራዕዩን ከተመለከተበት ጊዜ /በኋላ/ ጀምሮ እስከ ፍጻሜ ያለውን የሚኾኑ የሚከሰቱ የሚፈጸሙ ነገሮችን እንደሚገልጽ ገልጩ ነበር። “ከዚያ በኋላም አየሁ፥ እነሆም በሰማይ የተከፈተ ደጅ፥ እንደ መለከትም ሆኖ ሲናገረኝ የሰማሁት ፊተኛው ድምፅ፦

**ወደዚህ ውጣና ከዚህ በኋላ ሊሆን የሚያስፈልገውን ነገር አሳይሃለሁ አለ።**” ራእይ 4፥1።

ዮሐንስ መጀመሪያ ድምጹን ሰምቶ ደንግጦ እንደሞተ ሰው የኾነለት [ራዕ1፥12]፣ "ያ" የፊተኛው ድምጽ ኢየሱስ ክርስቶስ "ከዚህ በኋላ ሊኾን የሚያስፈልገውን አሳያለሁ" አለው። “ ከዚህ በኋላ ሊሆን የሚያስፈልገውን ነገር አሳይሃለሁ” ማለቱ ዮሐንስ ከተመለከተ በኃላ ጀምሮ የሚፈጸሙ ትንብቶችን እንደ ሆነ እንጂ የመጨረሻ መጨረሻው ፍጻሜ ላይ ያለውን ብቻ የሚያመላክት አይደለም፡፡ ከዚህ መባሉ አሁን ጀምሮ ያለውን እንጂ የወደፊቱን ብቻ አያሳይም፡፡ ደግሞም መጽሐፍ

“እንግዲህ ያየኸውን አሁንም ያለውን ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን ጻፍ።” ራእይ 1፥19/፤ ስል ፟ከዚህም ፞ መባሉ አሁን ጀምሮ ተፈጻምነት ያለውን ትንቢት መገለጡን ያስረዳል ፡፡ ስለዚህም ከዚህ ክፍል ተነስተው ቤተክርስቲያን ከተነጠቀች በኃላ ያለውን የመጨረሻ ጊዜ ላይ ያለውን መልእክት /ብቻ/ ያመለክታል መባሉ አያስኬድም እልለሁ፡፡

ከዚህ በኋላ ያሉት መልእክቶች የተፈጸሙትን ሳይኾኑ ግና የሚፈጸሙ ናቸው ።ዮሐንስም ግና የሚፈጸሙትን እንደ ተመለከተ በቀላሉ እንገነዘባለን ። ዮሐንስ የሰማይ ደጅ ተከፍቶ ኹሉንም በግልጽ ተገልጦለት ማየቱን ፡-በዚህ ዓለም ላይ የሚኾነውን ኹሉንም ፣ አንድንም ሳያስቀር ወገግ ብሎለት ፣ ያለ ድንግዝግዝታ በማያጠራጥር መልኩ በግልጥ እንደተመለከተ ይገልጻል ።በእውነት ማስዋወሉን ይስጠን። በብልሃት በተፈጠረ ፍልስፍና ተረት እንዳንያዝ ይጠብቀን ። ለእግዚአብሔር እራሳችንን አሳልፌን እየሰጠን ዮሐንስ ራዕዩን በጻፈበት መንፈስ ኾነን ለመረዳት ልባችንን እንክፈት ። የሰማይ ደጅ ተከፍቶ [እግዚአብሔር ያለበት] የልባችን ደጅ ተዘግቶ ጠማማ; አግድም አደግ ኵርንችት እንዳናፈራ እንጠንቀቅ ።

በመልኩ የሰው ልጅ የሚመስለው ፣ በምድር በነበረበት ግዜ ወደ ደረቱ ተጠግቶ /ቀርቦ/ ይነጋገረው የነበረ፣ አኹን ዮሐንስ ተመልክቶ እንደሞተ ሰው የኾነለት ፣ የፊተኛው ደምጽ; ሞቶ የነበረው፤ከሞትም የተነሳው አምላክ፣ ዮሐንስ ከነበረበት ስፍራ ከፈጽሞ ደሴት ወደላይ ወጥቶ እንዲመለከት አመለከተው ፤ ወደዚህ ውጣና በማለት ። ከዚህም ዮሐንስ ከፍ ወዳለበት ስፍራ ወጥቶ በግልጽ ተገልጦለት እንደተመለከተ እንረዳለን ። ያልተጻፈውን የሚያነቡ ፣በግምት እየፈጠሩ ውሸትን የሚያስተምሩ ሃሰተኞች አስተማሪዎች ይኽንን ቃል በመያዝ "ቤተክርስቲያን የለችም፣ተነጥቃለች ፣ ከዚህ በኋላ ያለው የሚያመለክተው እስራኤል ዘሥጋ ለኾኑትንና ያልተዘጋጁ አሕዛቦችን ብቻ ነው በማለት የውሸት የፈጠራ ስብከታቸውን ያሰራጫሉ ፣ትውልዱ እግዚአብሔር ከመኖሪያው የገለጠውን መልእክት ተቀብለው እንዳይለወጡ ያደነዝዛሉ፤ ያስተኛሉ።

የራዕይ ዮሐንስ መጽሐፍ ምዕራፍ 4 እስከ 22 ያለው በሙሉ.. ቤተክርስቲያን ከተነጠቀች በኋላ ያለውን ያመለክታል[1] የሚሉ << "ከዚህ በኋላም" ስል ከቤተክርስቲያን መነጠቅ በኋላ ያለውን ያመለክታል >>[2] በማለት የክፍሉ ሃሳብ ዮሐንስ ከተመለከተው ራዕይ እየቀጠለ በተከታታይ ሌላ እየተመለከተ የቀጠለውን ለማመልከት "ከዚህ በኋላም" የተባለውን ከአውዱ በመነጠል ፣በመገንጠል የክፍሉን ሃሳብ በማስጨነቅ "መነጠቅን" ያመላክታል ይላሉ ። ከላይ እንዳልሁት ራዕዩ የያዘው ዓላማ ከይዘቱ ስንመለከት ኹለት ነው ብዬ ነበር። በሰዓቱ ለነበሩት ለ7ቱ አብያተክርስቲያናት ልክ እንደ ገላትያ መልእክት ፣እንደ ቆሮንቶስ መልእክት ..በሰዓቱ የነበሩበትን ኹኔታ ጌታ አሳይቶ በመልእክቱ አኹን [በሰዓቱ]

---

[1] መጋቢ ተኩ ከበደ፣ የቅዱሳን በአየር ላይ መነጠቅ፣የመጀመሪያው ዕትም 1999ዓ.ም

[2] ዝኒህ ከማሁ

እየኾነ ያለውን ከገለጠ በኋላ ፣ ወደፊት ደግሞ ገና  ልኾን  ያለውን መግለጥ ስጀምር [የ7ቱ አብያተክርስቲያናት አኹናዊ መልእክት እንደጨረሰ] ፣ "ከዚህ በኋላ" በማለት በቀጣይ የሚሆኑትንና የወደፊቱን ብዙ ዓመታት ወደፊት በመንፈስ መጥቶ የተመለከተውን ፣ "መነጠቅ ነው" ይላሉ ። ማነኛውም ሰው ከፍም ዝቅም ብሎ መጽሐፉን በአግባቡ የሚያነብ ማስተዋሉ አይቀርም ።

<<"ወደዚህ ውጣና"ስል ዮሐንስ ወደ ሰማይ የወጣው በዚህ አካሉ አይደለም፤በመንፈስ ነው። በመንፈስ ከኾነ ይኽ ለምን ተፈጸመ ስንል የቤተክርስቲያንን የቅዱሳንን ወደ ሰማይ መሻጋገር የሚተነብይን [የሚገልጽ] እውነት በውስጡ እንደያዘ እናገኛለን ።>> [3] ይላሉ ፣ ክብር ምስጋና ይግባውና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፣ዮሐንስ ራዕዩን ካለበት ከፍ ብሎ ቀርቦ በግልጥ እንድመለከት ስለፈለገው ከነበረበት ፈጽሞ ደሰት "ወደዚህ ውጣ በማለት በከፍታ ኾኖ እንድመለከት መናገሩን እንጂ የቤተክርስቲያን መነጠቅ የሚያመላክት በፍጹም አይደለም ። ከመሠረቱ ወደዚህ ውጣ የተባለው ዮሐንስ እንጂ ቤተክርስቲያን አይደለችም ። ዮሐንስም ራዕዩን የተመለከተው ብቻውን ነው ። በመንፈስ የሆነውም ገና በዚህ ብቻ ሳይሆን ራዕዩንም ማየት ስጀምር ጭምር ነው፡፡ በመንፈስ መሆን ማለት በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ውስጥ ስለመሆን እንጂ የትንሳዔ አካል ስለመልበስ የሚናገር አይደለም፡፡

የዮሐንስ ኃላፊነቱም በግልጽ በራዕይ መጽሐፍ እንደ ተቀመጠው መልእክቱን በጽሑፉ ማስተላለፍ ነው። “ .**የምታየውን. በመጽሐፍ ጽፈህ .ላክ አለኝ**።... እንግዲህ ያየኸውን አሁንም ያለውን ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን **ጻፍ**። /ራዕ 1፥11-19/። የራዕዩን መልእክት ለእኛ ለተደራስያኑ ደግሞ የተጻፈውን እንድንጠብቀውና እንድንፈጽመው የተሰጠ ነው። “ዘመኑ ቀርቦአልና የሚያነበው፥ የትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና በውስጡ የተጻፈውን የሚጠብቁት ብፁዓን ናቸው። ”ራእይ 1፥3።

አይደለም እኛ ዮሐንስ እራሱን ከመከራው ተካፋይ አድርጎ በመግለጽ በመከራው በእግዚአብሔር ሃይል ደሴት ታስሮ ፣ እኛ መከራውን እንደሚንቀበል በማመልከት; ከእኛ ጋር የመከራው ተካፋ አድርጎ እራሱን በመቁጠር እየመጣ ላለው ዓለማዊ አገዛዝ እጅን ሳንሰጥ ፣ድል በመንሳት እንድንሻገር “**እኔ ወንድማችሁ የሆንሁ ከእናንተም ጋር አብሬ መከራውንና መንግሥቱን የኢየሱስ ክርስቶስንም ትዕግሥት የምካፈል ዮሐንስ** ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ኢየሱስ ምስክር ፍጥሞ በምትባል ደሴት ነበርሁ።” [ራእይ 1፥9]፣ በማለት በእሳቱ በመከራው ማለፋችንን በመግልጽ ስያዘጋጀን፣ ሃሰተኛ አስተማሪዎች ግን ብዙዎችን በሚያማምሩ ቃላትና ስብከት ፣በውሸት በማታለል "መከራ አያገኛችኹ" እንነጠቃለን በማለት

[3] ዝኒህ ከማሁ

ቀጣዩን መልእክት ትውልዱ አንብቦ ድል በመንሳት እንዳይነግስ፣ በዲያብሎስ እንድረግጥ ሃይል አልባ እያደረጉ ይገኛሉ ።"ብዙዎችን ያስታሉ" እንደተባለው አስተዋል። ጆሮ ያለው ይስማ።

ከምዕራፍ አራት ጀምሮ ያለው ከቤተክርስቲያን መነጠቅ በኋላ ያለውን ያመለክታል ፣ ለማለት ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል ከምዕ 6 -19 የለም [4] የሚል ሙግት ያነሳሉ ። ይኽ ሃሳብ በትዝብት ላይ የሚጥል ነው። ለምን ከምዕራፍ 4 ጀምረው አጠቃላዩን እስከ 22 አልተጠቀሰችም አይሉም ? ቤተክርስቲያን እስከ 22 ድረስም የለችም ተነጥቃለች ብለው ይለ? ከተነጠቀች እንደትስ "ናልን" ትላለች በምዕራፍ 22 ላይ? ለማነኛውም የግድ ቤተክርስቲያን በሚል ቃል ካልተጻፈ አያመለክተንም ማለት ነው? እንዲያ ማለትስ እንችላለን ? ቤተክርስቲያን በመጽሐፍ ቅዱሳችን ፣ በመንገዱ ያሉ [ሐዋ9] ፤ የበጉ ሚስት ፣አካሉ፣እስራኤል ፣ሴትቱ ፣ ሙሽሪት ወዘተረፈ በመባል ተገልጻለች ።ስለዚህም በዚህ ስም ብትጠራ አያመለክትም ማለት እንችላለን ? አንችልም ። በሥጋ ሳይኾን በክርስቶስ መንፈስ "ወንድማችሁ የኾንኩ ከእናንተ ጋር መከራውን የሚቀበል " በማለት መልእክቱ የተጻፈው; ለኾነ ለሥጋ ወገን ለኾኑት እንዳይደለ ዮሐንስ በግልጽ አስቀምተጧል ፡፡

“በዚህም ሥርዓት በሚመላለሱ ሁሉ ላይ **በእግዚአብሔር እስራኤልም** ላይ ሰላምና ምሕረት ይሁን።” ገላትያ 6፥16 ። በራዕይ መጽሐፍ እስራኤል አይሁዳውያን የሚያመለክት አይደለም ። በክርስቶስ የአብርሃምን በረከት ተካፋይ የኾኑትን ቤተክርስቲያንን እንጂ። “እኛ በመንፈስ እግዚአብሔርን የምናመልክ በክርስቶስ ኢየሱስም የምንመካ በሥጋም የማንታመን እኛ የተገረዝን ነንና።” [ፊል 3፥3]፣እንደሚል ። በዚህ ርዕሰ ላይ በቀጣይ "እስራኤል" ማንን ትወክላለች በራእይ መጽሐፍ ላይ የሚለውን በሰፊው እንሞግታለን።

ክርስቶስ የሥጋ እስራኤላውያን አካል ሳይኾን የቤተክርስቲያን አካልና ራስ ነው። በእጁ በፍጹምነት ያለችው ቤተክርስቲያን የኾኑቱ እንጂ እስራኤል ዘሥጋ አይደለችም ። የመጽሐፉን ለእኛ ያለውን መልእክት በማጣመም የሥጋ መገረዝን አለመገረዝ በማድረግ በመንፈስ ከክርስቶስ በመወለድ መገረዝን [አይሁዳውነት] ያወጀውን እውነት በማዳፈን ፣ በጭፍን ተነስተው የሚትረጉሙ የሥጋ ልእልና የሚሰብኩ ፣ በ7ቱ አብያተክርስቲያናት መካከልም በሴምርነስና በፊላደልፊያ ቤተክርስቲያን ተነስተው ነበር። አይሁዳውያን ሳይኾን አይሁዳውያን ነን የሚሉ ፤ የሚሳደቡና የሚዋሹ የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ። "**በግልጥ አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ አይደለምና፥ በግልጥ በሥጋ የሚደረግ መገረዝም መገረዝ አይደለምና፤ ዳሩ ግን በስውር አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ ነው፥ መገረዝም በመንፈስ የሚደረግ የልብ መገረዝ ነው እንጂ በመጽሐፍ አይደለም፤ የእርሱ ምስጋና ከእግዚአብሔር ነው እንጂ ከሰው አይደለም** ። [ሮሜ 2፥28-29]። ጌታ በሥጋ በግልጥ አይሁዳውያን የኾኑትን አይሁዳዊ አይደሉም በማለት በመንፈስ በመገረዝ ብቻ አይሁዳውያን የኾኑትን አይሁዳዊ

[4] ዝኒህ ከማሁ

አድርጎ ይቆጥራቸዋል ። እግዚአብሔር አይሁዳውያን በክርስቶስ በኩል በግልጽ በሥጋ ዘራቸው የተመጻደቁትን በሥራቸው "የዲያብሎስ ልጆች ናቸው" በማለት ከአሕዛብ ለራሱ መንፈሳዊ አይሁዳውያን "እስራኤላውያን" እንደሚያስነሳ ገልጿል ። “በልባችሁም፡- አብርሃም አባት አለን እንደምትሉ አይምሰላችሁ፤ እላችኋለሁና፡- ከነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣለት እግዚአብሔር ይችላል።” ማቴዎስ 3፥9 ፤እንደሚል። እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው የእነርሱን በመቊረጥ ሌላ ልዩ ከእምነት የኾኑት ለመትከል ነው ። ማቴ 3፥10።

በግልጽ ለዓለም አብያተክርስቲያናት የተላከውን መልእክትን በመቃወም ፤ ለሥጋ እስራኤላውያን በማድረግ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የሚዋሹ ተንኮለኞች እረኞች ናቸው ።**“እኔ ኢየሱስ በአብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ይህን እንዲመሰክርላችሁ መልአኬን ላክሁ። እኔ የዳዊት ሥርና ዘር ነኝ፥ የሚያበራም የንጋት ኮከብ ነ**ኝ።”ራእይ 22፥16፣ እንደሚል መልእክቱ ለዮሐንስ ወንድሞች ለመከራው ተካፋዮች ለአለም አብያተክርስቲያናት የተላከ ነው። በግልጽ የተቀመጠውን በመቃወም ፥ ትውልዱ አንብቦ እንዳይጠቀምና እንዳይተርፍ በማደንዘዝ ፣እንዳያስተውል በማድረግ ስንቱን በገፍ አሳቱ? አንባቢ ኾይ; "ከምዕራፍ አራት በኋላ ከተነጠኩ በኋላ ያለው ነው የተጻፈው " በማለት አኹንም ያስባሉ ? የእግዚአብሔርን መልእክት ችል ትላለህ ? እኔ የሚናገረው ለሚሰሙት ነው። ጆሮ ያለው ይስማ።

“መንፈሱና ሙሽራይቱም፡- ና ይላሉ። የሚሰማም፡- ና ይበል። የተጠማም ይምጣ፥ የወደደም የሕይወትን ውኃ እንዲያው ይውሰድ።” ራእይ 22፥17 ። ስለዚህም በምድር ያለችው የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሙሽርት [የበጉ ሚስት] ተናፍቃ ውዷን ትጣራለች፤ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር፤ ኾና። አያችኹ? መንፈስ ቅዱስም አለ፤ ምክንያቱም መልእክቱ ከምዕራፍ አንድ ጀምሮ ያለው ለእርሷ ነውና፤ ገብቷታል። ከምዕራፍ አራት ጀምሮ ያለው ከቤተክርስቲያን ንጥቀት በኋላ ያለውን የሚያመለክት ነው ካልን፣ ቤተክርስቲያን ተነጥቃ እያለች "ማራናታ ጌታ ኾይ" እያለች ነውን? በጌታ በኢየሱስም ። ውሸት ከእናንተ ይራቅ። በእግዚአብሔር ቃል ላይ መቀለድ መድፈር ከእናንተ ይራቅ ። ይኽንን የትንቢቱን ቃል "ቤተክርስቲያን" ተነጥቃ እያለች ነው የሚተጠብቀው ? በምድር በመከራው እያለች አይደለችምን ? ነው። ከእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ የመጣውን መልእክት ስትሰማ ፣ልትጠብቅ እንደሚገባት አውቃ፣ ባለችበት ቦታ ኾና በዓለም በምድር ላይ፣ ውዷን ትጣራለች ። መልእክቱ የተጻፈው ለአንተ/ለአንቺ ለእኛ ነውና።

ይኽንን እውነት እንድታነብ እንድታውቅ ጌታ ዕድል ሰጥቶሃል፤ ኹሉም በአፍህ ቀርቧል። እያወቃችሁ ተራ መረዳት ነው ወይም ችግር የለም በማለት ቀለል እና ለዘብ አድርጋችሁ ፣ ቈጥራችኹ የምታልፉ መምህራን፣ ከማስመሰል እንድትወጡ የበጉን መልእክት በግልጽ እናገራለሁ ።ምክንያቱም የትንቢቱ ቃል ስመጣ ከሰው አዕምሮ የመጣ አይደለም ።እንደገዛ ፍላጎታችን እንድንተረጉመው እንድንራቀቅበት የተሰጠ አይደለም ። ያለ ልዩነት ለሁሉ ለሰው ልጆች በሙሉ የተላከ

የተሰጠ መልእክት ነው።ጌታም ለእስራኤል ዘሥጋ ብቻ ሳይኾን ለሰው ልጆች ኹሉም ምስክር እንደኾነ ገልጿል ።ምክንያቱም መልእክቱ ሁላችንም ሰምተን ተገቢውን ምላሽ እንድንሰጥ የተጻፈ ነው። ጆሮ ያለው ይስማ።

ለእኛ በፍጻሜ ዘመን ላይ ላለነው መልእክቱ አንብበን እንጠቀም ዘንድ፣ ከሺህ ዓመት በፊት በጌታ ቶሎ ልኾን የሚያስፈልገው የተገለጠው; በክርስቶስ መንፈስ በማንበብ፣ በክርስቶስ ፊት በመኾን የበለጠ ለመረዳት በግልም በጽሞና እንድያነቡ አበረታታለሁ ። መጋቢዬ ያስተምረኛል ብለህ አትቦዝን። የኾነ እሳቤ ውስጥ ተጨቃይቶ ለሠራው አስተምህሮ በመጠንቀቅ እየተረጎመ እንዳያወዛግብኽ በመንፈስ ምሪት ፣ ከኹሉም በላይ በኾነው አስተማሪ በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ እንድታነብ አበረታታለሁ ። የራዕይ መልእክት በነቢያት ኾነ በኢየሱስ ወይም በሐዋርያት ከተገለጠው ዘመን ፍጻሜ መልእክት ልዩና ዐዲስ የኾነ አይደለም ። ራዕዩ ራሱ ወደፊት የሚኾነው በተለያየ መንገድ በተለያየ አተያይ የሚያብራራ ነው። እንደ ካሜራ 5 ከተለያየ አቅጣጫ እንደተቀረጸ ክስተት ፣አንዲን ነገር በዝርዝር ሙሉ መረዳት እንድኖረን ለማስረዳት የተገለጠ መጽሐፍ ነው። ከዚህ ቀጥሎ ባለው ፍንጭ እንመለከታለን ።አንድን ሰው ከፊለፊት፣ ከወኋላ፣ ከላይ፣ ከጎን ፣ ከተለያየ አቅጣጫ በተቀረጸው ካሜራ ብንመለከት ፣ነገሩን ራሱን በሚሉአት መረዳትና ማየት እንደሚቻል የተገለጸ ነው ፤እንዲያ የተገለጠና ያለ የትንቢት ቃል ነው።ከምዕራፍም አራት ጀምሮ ያለው" የቤተክርስቲያን መከራ መቀበልን"የሚያመለክተውን መልእክት የያዘ ነው። አስተውሉ ከላይ እንዳልሁት ዮሐንስ እየተመለከተ ያለው ያለፈውን፥ **የተፈጸመውን ታርክን አይደለም ፤ገና መኾንና መፈጸም ያለበትን ነገር እንጂ ።**

ዮሐንስ አብን በዙፋኑ ተቀምጦ ይመለከተዋል ።ራዕ 4፥2-3። ደግሞም በዙፋኑ ዙሪያ 24 ሽማግሌዎች ነበሩ።ቊ.4። እነዚህ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ አንስቶ በስውር የተነጠቁ ሳይኾኑ፣ በብሉይ መሠረት 12 እስራኤል ዘሥጋ ነገድ ቅዱሳንና 12 የሐዲስ ኪዳን ቅዱሳን በሐዋርያት መሠረት የተመሠረቱ ቅዱሳን የሚገልጹ ናቸው ። ደግሞም ግና የሚኾነው እየተመለከተ እንጂ የኾነ ዘመን የተከሰተውን ክስተት እንደሚመለከት ፣መፈላሰፍ አስፈላጊ አይደለም ። "እነዚህ 24ቱ ሽማግሌዎች የመከራው ዘመንና 144,000 እስራኤላውያን ሳይነጠቁ በፊት የተነጠቁት ቅዱሳን አማኞች ጉባዔ ተወካዮች ልኾኑ ይችላሉ። ኾኖም መቼና የት እንደነበሩ ፣እነማን እንደኾኑ ለማወቅ ይቸግራል ።" 6 ይላሉ። እነዚህ በሰማይ የነበሩ ሳይኾኑ እንዲያ እንደሚኾን ዮሐንስ እንደተመለከተ ብገነዘቡ 'ኮ “እኔ ደግሞ ድል እንደ ነሣሁ ከአባቴም ጋር በዙፋኑ ላይ እንደተቀመጥሁ፥ ድል ለነሣው ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ።” [ራእይ 3፥21] ማለቱን በተረዱ ነበር።በዙፋኑ ዙሪያ ከብበን እርሱን ብቻውን እያመሰገንን እያመለክን እንደምንኖር የሚገልጽ መኾኑ ባልጠፋባቸው ነበር። ደግሞም ገና ምዕራፍ አራት ስንጀምር ልኾን የሚገባውን ዮሐንስ እንደሚመለከት ገልጠን ነበር። ታዲያ እንዴት ከዚህ በፊት የተነጠቁ 24 ቅዱሳንን

---

[5] የራእይ ዮሐንስ ጥናት መጽሐፍ ፤አ.አ 2013 ዓ.ም

[6] መጋቢ ተኩ ከበደ፣ የቅዱሳን በአየር ላይ መነጠቅ፤የመጀመሪያው ዕትም 1999ዓ.ም

በሕሳብ አሃዝ እንረዳለን? እንተረጉመዋለን? ጆሮ ያለው ይስማ። በነጭ ልብስና [በቅድስናና] በተጋድሎአቸው አክሊል ደፍተው ያሉት ደግሞም በክብር ለእርሱ ስለኾኑ የተቀመጡት፣ ቅዱሳን የኾኑ ሁሉ ናቸው እንጂ መላእክት ኾነ፣ በስውር የተነጠቁ 24 ሰዎች [ብቻ] አይደሉም ።

"በዙፋኑም ፊት ብርሌ የሚመስል የብርጭቆ ባሕር ነበረ። በዙፋኑም መካከል በዙፋኑም ዙሪያ፥ በፊትና በኋላ ዓይኖች የሞሉአቸው አራት እንስሶች ነበሩ።" ራእይ 4፥6 ።እነዚህ ቅዱሳን በቤተመቅደስ የነበሩ ያኔ እርሱ ስገለጥ፣ ተከፍሎ የነበረው ኹሉ እንደሚሻር፣ ሙሉ እውቀትና ሙሉ መረዳት እንደሚኖረን ሐዋርያው በመልእክቱ እንደገለጸው ፣ "ከእውቀት ከፍለን እናውቃለንና፥ ከትንቢትም ከፍለን እንናገራለንና፤ ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፤ ዛሬስ ከእውቀት ከፍዬ አውቃለሁ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደ ታወቅሁ አውቃለሁ።" 1ቆሮ 13፥9-12። የዓይኖች ትላልቅና በዓይኖች የተሞሉ መኾን፣ ኹሉም ነገር ግልጽ እንደኾነላቸው የተሰወረ ነገር እንደሌለባቸው የሚያሳይ ነው። እግዚአብሔርን ፊትለፍት በክብሩ እንደሚመለከቱ ፣ ጌታ በሐዋርያው ጳውሎስ የገለጠውን ተስፋ፣ ዮሐንስ ተመልክቶ ትዕይንቱን በማብራራት በዝርዝር አስቀምጧል ። **24** ሽማግሌዎች የተነጠቁ ቅዱሳን ብኾኑ ጌታ የሚወደው አገልጋይ ከእነርሱ መሃል እንጂ ተመልካች አይኾንም ። ደግሞም"**12**ቱ የሐዲስ ኪዳን ቅዱሳን **/**ሐዋርያት**/** ናቸው **(**ማቴ **19**፥**28 )**[7] ለማለት የሚጠቀሰው አያስቀድም እላለው። ምክንያቱም ለ**12** ሐዋርያት ስነገር ይሁዳም አለ፡፡ የጌታችን ቃል ለይሁዳም ነው ለማለት ክፍሉ አያስደፍርም፡፡ ነገርግን በደሴቲቱ ለሥቃይ ለመከራ ተሰጥቶ የተጣለ ብኾንም፣ ብዙ ወገንና ብዙ እረፍት ደስታ እንደሚጠብቀውም በመመልከት እየተጽናና ተቀምጧል ። አራት እንስሶች አራቱን የምድር ማዕዘን የሚያመለክቱ የፍጥረታት ወክል ልዩ ፍጥረታት የተባሉ ናቸው /በሮሜ 8/፣ የማይታየው የእግዚአብሔር መለኮታዊ ባሕርይ የተገለጠባቸው ናቸው፤ሮሜ 1፥19-20። ልዩ ፍጥረታትም እግዚአብሔር ስያመልኩ፣ 24 ሽማግሌዎችም /ጥበብ የሞላባቸው ቅዱሳንም/ ተቀብለው ስያመሰግኑ እንመለከታለን ።

በምዕራፍ አምስት የዓለም እንቁቁልሽ የያዘውን መጽሐፍ እግዚአብሔር እንደያዘውና ቁ.1፤ የእንቁቅልሽ ፍቺ ለመስጠት ስልጣን ያለውና ፍጻሜውን ልቆጣጠረው የሚችለው የታረደው በግ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደኾነ ቁ.5 ያስገነዝበናል ። ስለዚህም ምክንያት በጉን መላእክቱ፣ ፍጥረታቱና ቅዱሳኑ ኹሉም አመለኩ አወደሱ ።ቁ.8-12። ምስጋናቸውን በጉ ያደረገውን የሚያሳስብ ነው፥ "መጽሐፉን ትወስድ ዘንድ ማኅተሞቹንም ትፈታ ዘንድ ይገባሃል፥ ታርደሃልና፥ በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው፥ በምድርም ላይ ይነግሣሉ እያሉ አዲስን ቅኔ ይዘምራሉ።"ራእይ 5፥9-10። በጉ ሰዎቹን

[7] ያሬድ ዮሐንስ፣ ድንቅ ፍጻሜ፣ ክፍል 1ና2፣ ገጽ 55-56፣ዕትም መስከ 2014 ዓ.ም

በደሙ ዋጅቶ ምን አደረጋቸው ? ካህናት ፣መንግሥትና በምድር እንዲነግሱ አደረጋቸው ። ኢየሱስን የተቀበሉት; የተዋጁ ስለኾኑ በምድር የነገሱ ናቸው ። ሺህ ዓመት [ብዙ ዓመት] ቤተክርስቲያን በመስቀሉ ሥራ የነገሰች ናት እያልሁ ነው። የተወሰነ ማብራሪያ በዚህ ርዕሰ ላይ ለመጨመር እሞክራለሁ ።

## 1.2.1 አንደኛው መግለጫ

ከምዕራፍ ስድስት ጀምሮ እስከ ምዕራፍ 8፥1 ድረስ ያለው የመጀመሪያው የፊለፊት ካሜራ የተቀረጸው ምስል ያሳየናል ።በዚህ መግለጫ ላይ እየመጣ ባለው ሥራዓት ቤተክርስቲያን በመከራው እንደሚታልፍ እንደሚትሻገር ይገልጻል ። በዓለም ላይ የሚኾኑ ክርስቶስ የገለጻቸው ምስጥራትን!

1. "አየሁም፥ እነሆም፥ አምባላይ ፈረስ ወጣ፥ በእርሱም ላይ የተቀመጠው ቀስት ነበረው፥ አክሊልም ተሰጠው፥ ድልም እየነሣ ወጣ ድል ለመንሣት።" ራእይ 6፥2

፨ ይኽ ፈረስ ገዳይ ቀስት አለው፣ አክሊልም ጥበብና እውቀት አለው፣ ድልም ያደርጋል ። በሃሰተኛ ትምህርት ወደ እልቂት ያመራል ። የሰውን አዕምሮ በሃሰተኛ ትምህርትና ፍልስፍና በመበረዝ መቆጣጠርን ያመለክታል ። ነጭ ፈረስ ላይ ስተቀመጠ ኢየሱስ ነው ማለት አይደለም፡፡ ምክንያቱም ኢየሱስ ከአጥፊ ፈረሶች ጋር አይሰለፍም ፡፡ደግሞም ሰይጣንም ድል የሚነሳቸው ሰዎች አሉ፡፡

2. "ሌላም ዳማ ፈረስ ወጣ፥ በእርሱም ላይ ለተቀመጠው ሰላምን ከምድር ይወስድ ዘንድ ሰዎችም እርስ በርሳቸው እንዲተራረዱ ሥልጣን ተሰጠው፥ ታላቅም ሰይፍ ተሰጠው።" ራእይ 6፥4

፨ ቀዩ ፈረስ የወንድማማቾች [የአንድ ወገን] ጦርነት እንደሚደረግ ያመላክታል ። በዚህም ምክንያት ሰላም ይጠፋል ።

3." ሦስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ ሦስተኛው እንስሳ፦ መጥተህ እይ ሲል ሰማሁ። አየሁም፥ እነሆም፥ ጐራቻ ፈረስ ወጣ፥ በእርሱም ላይ የተቀመጠው በእጁ ሚዛን ያዘ። በአራቱም እንስሶች መካከል ድምፅ፦ አንድ እርቦ ስንዴ በዲናር ሦስት እርቦ ገብስም በዲናር፥ ዘይትንና ወይንንም አትጕዳ ሲል ሰማሁ።" [ራዕ 6፥5-6]

፨ ይኽ ጥቁር ፈረስ የኑሮ ውድነት በከባድ ሁኔታ እንደሚከሰት የሚገልጽልን ነው።ነገርግን በዘይትና በወይን ላይ የዋጋ ንረት እንዳይመጣ የተወሰነ ገደብ ከኢየሱስ ተጥሏል ። ሰው እህል ለመግዛት ወርቅ እንደሚገዛ የሚቸገርበት ነው። የኑሮ ውድነት በማምጣት ሰይጣን እንደሚሠራ ያስረዳል ።

4. "አየሁም፥ እነሆም፥ ሐመር ፈረስ ወጣ፥ በእርሱም ላይ የተቀመጠው ስሙ ሞት ነበረ። ሲኦልም ተከተለው፤ በሰይፍና በራብም በሞትም በምድርም አራዊት ይገድሉ ዘንድ ከምድር በአራተኛዋ እጅ ላይ ሥልጣን ተሰጣቸው።" ራእይ 6፥8

፨ ይኽ ግራጫ ፈረስ ሞትን የሚያመጣ ነው። ከምድር አንድ አራተኛ (1/4) ያህልን ልያጠፋ የሚችል ነው።ሰዎችንም እንስሳትንም፤ በተፈጥሮ አደጋ ፣ በራብ ፣በጦርነት በተለያዬ ግዜ በተለያየ ሃገር ላይ የሚከሰት ነው። [ይህ ጦርነት የእርስበርስ ጦርነት አይደለም] ። የዓለም ጦርነት ዓይነት ፥ ትልቅ እልቅት የሚያስከትል ነው ።

5."አምስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ፥ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ጠበቁት ምስክር የታረዱትን የሰዎች ነፍሳት ከመሠዊያ በታች አየሁ። በታላቅ ድምፅም እየጮኹ፡- ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ፥ እስከ መቼ ድረስ አትፈርድም ደማችንንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከ መቼ አትበቀልም? አሉ። ለእያንዳንዳቸውም ነጭ ልብስ ተሰጣቸው፥ እንደ እነርሱም ደግሞ ይገደሉ ዘንድ ያላቸው የባሪያዎች ባልንጀራዎቻቸውና የወንድሞቻቸው ቍጥር እስኪፈጸም ድረስ፥ ገና ጥቂት ዘመን እንዲያርፉ ተባለላቸው።

፨ በግፍ የተገደሉ አማኞች የእግዚአብሔር "ፊትህ" ይጠይቃሉ ፤ ጌታም እንደ እነርሱ ታምነው የሚሞቱ ስላሉ ትንሽ ግዜ ጠብቁ አላቸው ።

6." ስድስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ አየሁ፥ ታላቅም የምድር መናወጥ ሆነ፥ ፀሐይም እንደ ማቅ ጠጕር ጥቁር ሆነ፥ ጨረቃም በሞላው እንደ ደም ሆነ፥...ሰማይም እንደ መጽሐፍ ተጠቅልሎ አለፈ፥ ተራራዎችና ደሴቶችም ሁሉ ከስፍራቸው ተወሰዱ።...ታላቁ የቁጣው ቀን መጥቶአልና፥ ማንስ ሊቆም ይችላል? አሉአቸው።" [ራዕ 12፥6-12]

፨ በመጨረሻም እግዚአብሔር ለዚህች ምድር ታላቅ እልቂትን ያደርጋል ። የትኛውም የቴክኖሎጂ ዋሻቸው አያስመልጥም። ለእኛ ለአማኞች ግን መሸሸጊያ አለ። ኖኅ በመርከብ እንደተረፈ በዚያን ሰዓት በኢየሱስ እንሸፈናለን ።

7. “ሰባተኛውንም ኅተም በፈታ ጊዜ እኩል ሰዓት የሚያህል ዝምታ በሰማይ ሆነ።” ራእይ 8፥1

፨ ዝምታ ሆነ፣ ለቅሶም አብቅቷል።

*የውስጥ ሰላም ያገኛችችሁ ፣ የመጸለይ አቅም ይስጣችሁ ፣ ተስፋችን የታመነ ነው፣ ዘመኑን እወቁ፣ በእውቀት ጎልምሱ ፣

**1ኛው መግለጫ ስለ ዘመን ፍጻሜ ምን ፍንጭ ይሰጣል ⁉ ስናጠቃልል ፡-**

*በዚህ ፊለፊት ካሜራ የተቀረጸውን የዓለምን መጨረሻ ክስተት ተመልክተናል፤ ከዚህ በመቀጠል ያሉትንም ይኽንን ክስተት በዝርዝር ከተለየየ አቅጣጫ እንደተቀረጸ ካሜራ ያሳዩናል ።ስለዚህም ሙሉ መረዳት እንድኖረን ጌታ ከሚያሳየው አቅጣጫ እየተመለከትን እንቀጥላለን ።እነዚህ አራቱ ፈረሶች የጨለማ ሃይል ምሳሌ የኾኑ መቅሰፍትን የሚያመጡ ናቸው ። ቤተክርስቲያን በዚህ እየታረደች እየተሰቃየች ታልፋለች ። የተዘጋጀችው ቤተክርስቲያን በመከራ ውስጥ በምድር ብትኾንም ጌታ ይሸሽጋታል፤ መቅሰፍትንም የሚያመጡ ጨለማ ሃይሎች በእግዚአብሔር መላእክት ቊጥጥር ውስጥ ናቸው ።“የአምላካችንን ባሪያዎች ግምባራቸውን እስክናትማቸው ድረስ ምድርን ቢሆን ወይም ባሕርን ወይም ዛፎችን አትጉዱ

አላቸው።” ራእይ 7፥3 ። ከዚህ በላይ ጉዳት እንዳይደርስ እግዚአብሔር የራሱ የኾኑትን ልለያቸው ፈልጓል።ልያትማቸው።ምክንያቱም በስድስተኛው ማህተም ዮሐንስ የተመለከተው መልእክት የዓለምን ፍጻሜ የሚሰጥ መቅሰፍት ስለኾነ፣ እንዱሁም ከመከራው የተነሳ ለዮሐንስ ጥያቄ ኾኖ በታል ̋ማንስ ልድን ይችላል ብሏል ።

በዚህ መከራ ውስጥ ቤተክርስቲያን ብትኾንም የመጨረሻው እልቅት እንዳያገኛት ጌታ ፣የእርሱ የኾኑት እስኪለዩ ድረስ [እስኪሞሉ ድረስ] የስድስተኛው ማህተም መቅሰፍቶች አይመጡም ። እግዚአብሔርም 144,000 እስራኤላውያን እንደዳኑ እነዚህም የሥጋ እስራኤላውያን እንዳይደሉ ፣ ከሕዝብ ኹሉ የወጡ መኾናቸውን መጽሐፉ ይገልጻል ፦“ከዚህ በኋላ አየሁ፥ እነሆም፥ አንድ እንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል ከሕዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ፤ ነጭ ልብስም ለብሰው የዘንባባንም ዝንጣፊዎች በእጆቻቸው ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆሙ፤” [ራእይ 7፥9] ። እነዚህ የራዕይ መጽሐፍ ቊጥሮች በህሳብ አሃዝ ልንተረጉመው የተገባ አይደለም ። ዮሐንስ ማንስ ይድናል ስል ራሱን ጭምር በጥያቄ ውስጥ አካትቶ ነው።ሺህ "አንድ ሺህ" የሕሳቡን ቊጥር የሚወክል ሳይኾን እጅግ በጣም ብዙ ብዙውን ለመግለጽ የዋለ ቃል ነው። እነዚህም እስራኤል ዘሥጋ ሳይኾኑ እስራኤል ዘነፍስ በመንፈስ የተገረዙ የእግዚአብሔር እስራኤሎች የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሙሽሪት ናቸው ። ከነገድና ከቋንቋ የወጣች የአንድ ዘር ሥጋ ያይደለች፤ በጌታ መንፈስ ግን አንድ የኾነች ፤ አካሉና ሙላቱ ናት። እነዚህ የታተሙት በያዕቆብ እስራኤል ምሳሌ የቀረቡ በእምነት የተወለዱ የእግዚአብሔር እስራኤሎች ናቸው ።በዚህ ጉዳይ በቀጣይ ክፍል እንደ ጌታ ፈቃድ በሰፊው እናያለን ።

እናም ኹሉም በበጉ ቊጥጥር ስር እንደኾነ፤ ሃሰተኛ ትምህርት ብዙዎችን እንደሚያሸንፍ ፤ የእርስበርስ ጦርነት እንደሚኖር፤ የኑሮ ውድነት እንደሚያይል ፤ ታላላቅ ሃገራዊ ጦርነቶች እንደሚደረጉ፤ የሞቱ ሰዎች የእግዚአብሔርን ፍትህ እንደሚጠይቁ ፤ በ6ተኛው ማህተም የሰማይ ከዋክብት መውደቅና ታላቁን መከራ ጅማሮ ስያሳይ፣ በዚያ መከራ ብዙዎች እንደሚታተሙ፤ የሚታተሙትም በዙፋኑ ፊት ልያመሰግኑ እንዳላቸው ይጠቊማል፤ በ7ተኛው ማህተምም; መናወጡ ኹሉ አልፎ ፤ሰላም ነግሶ ፤ዝምታ መኾኑን በማብሰር ይዘጋል ። የሚታተሙት ታትመው እንዲያልቁ ታላቁ መከራ ገታ ተደርጎ ነበር። በዚህ መግለጫ መሠረት እነዚህ የሚታተሙት ፣ገታ በተደረገው መቅሰፍት መሃል መታተማቸውን ይገልጻል። እንዴትስ ታተሙ? ከታተሙት በኋላ እንዴትስ ኖሩ በምድር ላይ የሚለውን አያሳይም ። ነገርግን ስለማንነታቸው እና ወደፊት ስለሚጠብቃቸው ሕይወት በሰፊው ያብራራል ። ራእ.7።

ደግሞም በዚህ መግለጫ መሠረት በዚያ በታላቁ መከራ መሃል የታተሙትን፣ በቅዱሳን መላእክት በኩል የሚመጣው መቅሰፍት አያገኛቸውም፤ “የአምላካችንን ባሪያዎች ግምባራቸውን እስክናትማቸው ድረስ ምድርን ቢሆን ወይም ባሕርን ወይም ዛፎችን አትጉዱ አላቸው።” [ራእይ 7፥3] ።144ሺህ ሰዎች በመከራ መሃል ያለፉ ድል የነሱ ሰማዕታት ስለኾኑ ጌታ

የገባውን ተስፋ ቃል ይፈጽምላቸዋል፤ “ድል የነሣው በአምላኬ መቅደስ ዓምድ እንዲሆን አደርገዋለሁ፥ ወደ ፊትም ከዚያ ከቶ አይወጣም፤ ..።”ራእይ 3፥12፣እንዳለውም እነዚህ ድል በመንሳት አለምን ስለ አሸነፉ ከእርሱ ጋር ለዘላለም በክብር ለመኖር ይበቃሉ።

የሚታተሙት ሰዎች ቊጥር ሂሳባዊ ቊጥር እንዳልኾነ አይተናል ፤ ማንም ሊቈጥራቸው የማይቻል መኾኑን ። ብዛታቸውን ፉጡር ማወቅ እንደማይቻል ተገልጿል ።ነገርግን ዮሐንስ ቊጥራቸውን ከመላአኩ ሰምቶ 144 ሺህ ናቸው በማለትም ገልጿል ።እያንዳንዱ ነገድ 12 ሺህ እንደኾነም አስቀምጧል ።ይኽ ቊጥር በሂሳብ ካየን ጊዜ ብወስድ እንጂ የሚቆጠር ነው። የተገለጡት በሂሳባዊ ስለት ስላልሆነ ምሳሌውን መያዝ እንችላለን ። እያንዳንዱ ነገድ 12 ሺህ መኾኑ፣ ሺህ 1000 ቊጥርን ሳይኾን እጅግ ብዙ የኾነውን ለመግለጽ የሚውል ቃል ስለኾነ፣ ብዙ ብዙ ያሉትን ሰዎችን እንደሚወክል እናስባለን ፤ 12 ደግሞ በመጽሐፍ የእግዚአብሔር ሕዝብ መሠረት የሚገልጽ ነው።መጽሐፉ የሐዲስ ኪዳን ስለኾነ 12 ሐዋርያትን እናስባለን ። ስለዚህ በ12ቱ ሐዋርያት መሠረት የተመሠረቱ እጅግ በጣም ብዙ ብዙ የኾኑት ነገድ እንደሚድኑ እንረዳለን ።ነገዱ የተገለጠው የዘር ሃረግ ለመግለጽ አይደለም። የብሉይ የእግዚአብሔርን ሕዝብ መሠረት ምሳሌ አድርጎ ለማስረዳት እንጂ። ደግሞም በአጠቃላይ ኹሉምን ስያባዛ 12*12 *ሺህ 144 ሺህ ኾኗል። ምሳሌም እጅግ በጣም ብዙ ብዙ የኾኑት ይድናሉ የሚል ነው። ሰው ወይም የትኛውም ፉጡር በሂሳብ ሊቈጥራቸው አይችልም ። ደግሞም ከነጭም ከጥቁርም የተውጣጡ ቅዱሳን ናቸው ። በታላቁ መከራ ጊዜ የሚድኑት ።

## 1.2.2 ኹለተኛው መግለጫ

ከምዕራፍ 8፥2 ጀምሮ እስከ 11፥17 ያለው ለዓለም በጌታ የሚሰጡ ማስጠንቀቂያዎች ናቸው [የዮሐንስ ራዕይ ጥናት ይመ.] ። በዚህኛው ካሜራ በዓለም የሚኾኑ ነገሮችን በጎን እንደተቀረጸ ካሜራ ብንመለከት ለመረዳት ይረዳናል ። ዓለምን ከማጥፋቱ በፊት በተለያየ ጊዜ የተለያየ የማስጠንቀቂያዎችን እንደሚያስተላልፍ [እንደሚሰጥ] እንገነዘባለን ። “በእግዚአብሔርም ፊት የሚቆሙትን ሰባቱን መላእክት አየሁ፥ ሰባትም መለከት ተሰጣቸው።” ራእይ 8፥2። ሰባቱ መለከቶች በእግዚአብሔር ለዓለም የቀረቡ ማስጠንቀቅያዎች ናቸው ። ማስጠንቀቂያ በራሱ የምህረት እድልን የሚያመለክት ነው ።ምክንያቱም እንዲመለሱ ስለሚፈልግ ነው የሚያስጠነቅቀው ፤የሚያስታውቀው ።

ዮሐንስ ለመለከቶች መነፋት ምክንያት የኾነውን ክስተት እንዲህ ያትታል ፣ ራእይ 8፥3 ሌላም መልአክ መጣና የወርቅ ጥና ይዞ በመሰዊያው አጠገብ ቆመ፤ በዙፋኑም ፊት ባለው በወርቅ መሰዊያ ላይ ለቅዱሳን ሁሉ ጸሎት እንዲጨምረው ብዙ ዕጣን ተሰጠው። 4 የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር ከመልአኩ እጅ በእግዚአብሔር ፊት ወጣ።5 መልአኩም ጥናውን ይዞ የመሰዊያውን እሳት ሞላበት ወደ ምድርም ጣለው፤ ነጐድጓድና ድምፅም መብረቅም መናወጥም ሆነ።

ይኸ መላእክ ሊቀ ካህናት ይመስላል፤ ጥና ይዟል ፤የሌሎች ጸሎት ለማቅረብ ወደ መሠዊያው ቀርቧል፤ ጸሎቱም ተሰምቷል ፤ ወደ እግዚአብሔር ፊት ቀርቧል። ከዚያም  መላአኩ ጸሎትና እጣን በሚኾንበት ጥና ላይ የመሠዊያ እሳት ሞላው ። በመሰዊያ እሳት ላይ የቀረበው መሰዋዕት የሚበላ እሳት ነው፤ የመለኮት ምሳሌ ። ደስ የሚል መዓዛ ያለው ዕጣንና ጸሎት ያለበት ጥና [መላአኩ እሳት ስሞላው] ሙሉ በሙሉ እሳት ብቻ ኾነ፤ ያውም የሚቃጠለውን መሰዋዕት የሚበላ እሳት ። ይኸ እሳት ወደ ምድር ስጣል በምድር መናወጦች ኾኑ። ይኸ ክስተት ሰባቱ መላእክት መለከት ለመንፋት እንዲዘጋጁ አደረገ።

የቅዱሳን ጸሎት ምን የሚል ልኾን ይችላል !? መላአኩ ያቀረበው ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ፊት ቀርቦ ምድር ላይ መቅሰፍቶችን የሚያመጣ ከኾነ፥ ካስተዋልን በ1ኛው መግለጫ እንደተመለከትነው የቅዱሳን ጸሎት "በምድር በሚኖሩት ላይ ፍረድልን" የሚል ነው የሚኾነው ።ራዕይ 5። መላአኩም ያቀረበው የቅዱሳን ጸሎት ይኸንን ያረጋግጥልናል ። ጸሎታቸው መቅሰፍትን እንዳቻኮለ። የቅዱሳን ጸሎት ከዕጣን ጋር ለመላአኩ መሰጠቱ፣ ዕጣን ደስ የሚል የሚወደድ ሽታ ያለው እንደኾነ ስናስተውል ፣ በምድር ቤተመቅደስ ምሳሌ የቀረበው ዕጣን አብ ደስ ብሎት የሚሸተው መዓዛ ኢየሱስን አመላካች ነው።ምክንያቱም በሐዲስ ኪዳን ጸሎት ከስሙ ጋር [በማንነቱ በኩል] የሚቀርብ ነው ። ይኸንን እንዲህ መረዳታችንን በሌሎች ክፍሎችም ተመርኩዘን ትርጓመአችንን ማጠናከር እንችላለን፡፡ መላእክት ድኅነትን እንዲነወርስ ያገለግላሉ፡፡ ዕብ ፤፤ ማቴ 4፡፡ ይኸንን እንዲህ ከያዝን ፣ ሰዎች ደወ መዳን እንዲመጡም እንደሚያገለግሉ መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም ጌታ ጠባቂ አድርጎ ሾሞአቸዋል፡፡ ፍሬ በማጣቱ ጌታችንን ልፈርድ ስል እንዲታገስና፤ወደ መዳን እንዲመጣ ልዩ እንክብካቤ እንደሚያደርግ በመጽሐፍ ተገልጧል፡፡  ሉቃ 13፥6-9፡፡ ስለዚህም ከክፍሉ መንፈሳዊ ትርጓሜ ስንነሳ፣ የሰዎች ጠባቂዎች መላእክት ናቸው፡፡በክፍሉ እንደተገጸው ጠባቂው ፍሬ ካላፈራ ጌታ መቁረጥ እንደሚችል አሳውቆታል፡፡ የሰማዕታት ፍረድልን ጥያቄ በመላአኩ መቅረቡ መላአኩ ፍሬ ባለማግኘቱ ፤የይቆረጥ ጥያቄ ማቅረቡን እንረዳለን፤ የሰማዕታትም ጥያቄ ነውና ፡፡ ስለዚህም እግዝአብሔር ስለሰማዉ ይኸም የመቅሰፍቶች መውረድ  ጅማሬ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ /መላአኩን ኢየሱስ ነው ለማለት ክፍሉም መጽሐፉም አይፈቅድምና/፡፡

ከዚህ በመቀጠል ለዓለም የቀረቡ **7** ማስጠንቀቅያዎችን እንመልከት ፡-

፨ በፊተኛው መለከት “ፊተኛውም መልአክ ነፋ፤ ደምም የተቀላቀለበት በረዶና እሳት ሆነ፥ ወደ ምድርም ተጣለ፤ የምድርም ሲሶው ተቃጠለ የዛፎችም ሲሶው ተቃጠለ የለመለመም ሣር ሁሉ ተቃጠለ።” ራእይ 8፥7 ። ምድርን የሰውን አከባቢ የሚመታ መቅሰፍት ስኾን ከምድር አንድ ሦስተኛው ተጠቂ ይኾናል ።

፡፡ሁለተኛውም መልአክ ነፋ፤ በእሳት የሚቃጠል ታላቅ ተራራን የሚመስል ነገር በባሕር ተጣለ፤ የባሕርም ሲሶው ደም ሆነ ፣በባሕርም ከሚኖሩ ሕይወት ካላቸው ፍጥረቶች ሲሶው ሞተ የመርከቦችም ሲሶው ጠፋ። ራዕ 8፥8-9። የመርከቦች መመታት ዋናው የንግድ ትሥሥር በማጥቃት የኢኮኖሚያዊ ጥቃት የሚያመጣ እንደኾነ ስያመለክት፣ በዚህም ሲሶው [⅓] ይመታል። በባሕር ውስጥ ያሉ እንስሶች በከፍል ይመታል ። በዚህ መቅሰፍት ዋናው ጥቃት የሚያርፈው በንግድ ላይ ነው።

፡፡ ሦስተኛውም መልአክ ነፋ፤ እንደ ችቦም የሚቃጠል ታላቅ ኮከብ ከሰማይ ወደቀ፥ በወንዞችና በውኃም ምንጮች ሲሶ ላይ ወደቀ። የኮከቡም ስም እሬቶ ይባላል። የውኃውም ሲሶ መራራ ሆነ መራራም ስለተደረገ በውኃው ጠንቅ ብዙ ሰዎች ሞቱ። ራዕ 8፥10-11። ለመጠጥ የሚኾነው የተፈጥሮ ሃብትን [ውኃውን] በመመረዝ ጥቃት የሚያደርስ ስኾን፣በዚህም ⅓ኛው ብቻ ከምድር ይመታል ።

፡፡ "አራተኛውም መልአክ ነፋ፤ የፀሐይ ሲሶና የጨረቃ ሲሶ የከዋክብትም ሲሶ ተመታ፥ የእነዚህ ሲሶ ይጨልም ዘንድ፥ የቀንም ሲሶው እንዳያበራ፥ እንዲሁም የሌሊት።" ራእይ 8፥12 ። " እግዚአብሔርም ሙሴን፦ እጅህን ወደ ሰማይ ዘርጋ፥ በግብፅም አገር ላይ ሰው የሚዳስሰው ፅኑ ጨለማ ይሁን አለው። ማንም ወንድሙን አላየም፥ ሦስት ቀንም ሙሉ ከስፍራው ማንም አልተነሣም፤ ለእስራኤል ልጆች ሁሉ ግን በተቀመጡበት ስፍራ ብርሃን ነበራቸው።" ዘጸ 10፥21-22። ልክ እንደዚሁ ከምድር ⅓ኛው በጨለማ ስዋጥ፣በሌሎች አከባቢዎች ብርሃን ይኖራል ። ብርሃን ያለበት ቅዱሳን ስለኾኑ አይደለም ።ጌታ የዘመኑን ፍጻሜ ለማስታወቅ የሚጠቀመው ምልክት ስለኾነ እንጂ።

"አየሁም፥ አንድም ንስር በሰማይ መካከል እየበረረ በታላቅ ድምፅ፦ ሊነፉ ያላቸው የሦስቱ መላእክት መለከት ስለሚቀረው ድምፅ በምድር ላይ ለሚኖሩት ወዮላቸው፥ ወዮላቸው፥ ወዮላቸው ሲል ሰማሁ።"ራእይ 8፥13 ። ከአራቱ መለከቶች ማስጠንቀቅያዎች በኋላ የሚመጣው የቀረው **3**ቱ ማስጠንቀቂያ፣ ጥቃቶች አደገኞች ስለኾኑ፣ በምድር ላይ ለሚኖሩት የወዮታ ድምጽ ያሰማል ።

፡፡"አምስተኛውም መልአክ ነፋ፤ **ከሰማይም ወደ ምድር ወድቆ የነበረ ኮከብ** አየሁ፥ የጥልቁም ጕድጓድ መክፈቻ ተሰጠው።" ራእይ 9፥1 ። በዚህ መለከት ላይ ሰማይ በሰማያዊ ስፍራ የነበረ ኮከብ መውደቁ ፣ የሰይጣንን ከሰማያዊ ስፍራ መጣልን ያመለክታል ። በዚህም ከጥልቁ ያሉትን የራሱ ጭፍራዎችን ይዞ ታላቅ ስቃይ መከራ እንደሚያመጣ ያስረዳል ።ይኽንን መጽሐፉ የመጀመሪያው ወዮ ይለዋል ።ቊ.12። በዚህም ሰዎች መሞት ብፈልጉም አይሞቱም፤ አይገድልም ያሰቃያል፤ ለ5ወራት ።"በዚያም ወራት ሰዎች ሞትን ይፈልጋሉ አያገኙትምም፥ ሊሞቱም ይመኛሉ ሞትም ከእነርሱ ይሸሻል።" ራእይ 9፥6 ። ምንም እንኳን ሰይጣን ከሰማይ በመውደቁ ስቃይ ለማብዛት ብታትርም የታተሙ ቅዱሳንን ድል የሚነሱ ኃይልን የተላበሱትን ልጎዳ አይችልም፤ለታተሙት የተፈቀደ መከራ አይደለም ። "የእግዚአብሔርም ማኅተም በግምባራቸው

ከሌለባቸው ሰዎች በቀር በምድር ያለውን ሣር ቢሆንም ወይም ማናቸውንም የለመለመ ነገር ወይም ማናቸውንም ዛፍ እንዳይጐዱ ተባለላቸው።"ራእይ **9፥4**። ከላይ የሚታተሙት እንዳሉትና ለእነርሱ ተብሎ መቅሰፍቶች እንዳይመጡ መከልከሉን ተመልክተናል ። በራእይ ምዕራፍ ሰባት ትርጉም ።

፨ ስድስተኛውም መልአክ ነፋ፤ በእግዚአብሔርም ፊት ካለ በወርቅ ከተሠራ መሠዊያ ቀንዶች አንድ ድምፅ ሰማሁ፥መለከትም ያለውን ስድስተኛውን መልአክ፦ በታላቁ ወንዝ በኤፍራጥስ የታሰሩትን አራቱን መላእክት ፍታቸው አለው። ... ከአፋቸውም በወጡት በእሳቱና በጢሱ በዲኑም በእነዚህ ሦስት መቅሰፍቶች የሰዎቹ ሢሶ ተገደለ። ራእ 9፥13-18። የምድር ⅓ኛው በታላቅ ጥፋት ተመታ ።የሰው ልጅ ግን እስካሁን ንስሐ አልገባም ። ልገባም አልወደደም ። የመጨረሻው ማስጠንቀቂያ ነበር ።"ስለ መግደላቸውም ቢሆን ወይም ስለ አስማታቸው ወይም ስለ ዝሙታቸው ወይም ስለ ስርቆታቸው ንስሐ አልገቡም።" ራእይ 9፥21 ።

፨ ከስድስተኛው መለከት በኋላም የሰው ልጅ በደል እየባሰ በመሄዱ በዚያ ጊዜም ጌታ ሰባተኛ መለከት ከመነፋቱ በፊት የንስሐ እድል ይሰጣል። "ወደ ፊት አይዘገይም፥ ዳሩ ግን ሰባተኛው መልአክ ሊነፋ ባለው ጊዜ ድምፁም በሚሰማበት ዘመን፥ **ለባሪያዎቹ ለነቢያት የምስራች እንደ ሰበከላቸው የእግዚአብሔር ምሥጢር ይፈጸማል** አለ።" ራእይ 10፥7 ። እስካሁን እየኾነ ያለውን የተረዱት ባሪያዎቹ ነቢያት ምስጢሩን ገልጠው እንዲያስተምሩ ጌታ ያደርጋል፤አስቀዲሞ አስታውቆአቸዋልና ። "በብዙ ወገኖችና በአሕዛብም በቋንቋዎችም በነገሥታትም ላይ እንደ ገና ትንቢት ትናገር ዘንድ ይገባሃል ተባለልኝ።" ራእይ 10፥11 ። ዮሐንስንም የትንቢቱን ቃል መግለጥና ማስተማር እንዳለበት ያዝዛል ። ይኸ እንዲኾን ለዮሐንስ የተሰጠው መልእክት ቃሉን በሥልጣን እንዲያስተምር ነው። ታዲያስ ለባሪያዎቹ ለእኛ አኹን በፍጻሜ ላለነው እንዴታ ?

※ለሁለቱም ምስክሮቼ ማቅ ለብሰው ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን ትንቢት ሊናገሩ እሰጣለሁ።እነዚህ በምድር ጌታ ፊት የሚቆሙ ሁለቱ ወይራዎችና ሁለቱ መቅረዞች ናቸው።ማንምም ሊጐዳቸው ቢወድ እሳት ከአፋቸው ይወጣል ጠላቶቻቸውንም ይበላል፤ ማንም ሊጐዳቸው ቢወድም እንዲሁ ሊገደል ይገባዋል። እነዚህ ትንቢት በሚናገሩበት ወራት ዝናብ እንዳይዘንብ ሰማይን ሊዘጉ ሥልጣን አላቸው፥ ውኃዎችንም ወደ ደም ሊለውጡ በሚፈልጉበትም ጊዜ ሁሉ በመቅሠፍት ሁሉ ምድርን ሊመቱ ሥልጣን አላቸው።ምስክራቸውን ከፈጸሙ በኋላ ከጥልቁ የሚወጣው አውሬ ይዋጋቸዋል ያሸንፋቸውማል ይገድላቸውማል። ራዕ 11፥3-7።

ሰይጣን ከወደቀ በኋላ ያለውን እየተመለከትን እንገኛለን ።ሰዎች በበደል እየረከሱ እየባሰባቸው በመሄዳቸው ጌታ ምስጥሩን የተረዱትን ባሪያዎቹን ፣ በኃይል የተሞሉትን ክብሩን የሚገልጡ ነቢያትን ፣ እንደ ወይራ ጠንካራ እንደ መቅረዝ ብርሃን የኾኑትን፣ በዚያ በታላቁ መከራ ዘመን እንዲያገለግሉ ያደርጋል ። እነዚህ ለሰይጣን በተሰጠው ጊዜ በስልጣን የሚመላለሱ ፣ ማንም ልቋቋማቸው የማይቻሉ ጌታ ምስጥሩን ያሳወቃቸው የፍጻሜው አገልጋዮች ናቸው ። ዮሐንስ መጥምቁ አገልግሎቱን ጨርሶ እንደ ሞተ፣ አገልግሎታቸውን ስጨርሱ እነዚህ ባሪዮችም ያርፋሉ፤ ይሞታሉ። ዮሐንስ መጥምቁ የኢየሱስ በሥጋ ወደ ምድር መግባትን መንገድ ጠራጊ አገልጋይ እንደኾነ ፣ እነዚህም ደግሞ የኢየሱስ ዳግም መምጣት የሚያውጁ የሚሰብኩ የመምጣቱ ፣ የቤተክርስቲያን የመጨረሻ አገልጋዮች ሃይልን የታጠቁ ቅዱሳን ናቸው ።

እነዚህ ቅዱሳን ብርቱዎች የፍጻሜው አገልጋዮች ፣ ሰይጣን ሴቲቱን በሚያሳድድበት ጊዜ [1260 ቀን] የሚያገለግሉ ፣እንደ ሙሴ በአሕዛብ ላይ እንደ አምላክ የሚኾኑ ፣በሥልጣን በአፋቸው ቃል መቅሰፍትን የሚያወርዱ በሰይጣን ጥቅት ጊዜ ሰይጣንን የሚያሸብሩ፣ የበላይ የኾኑ ብርቱ ወንድ ልጆች የጌታ ምርጦች ናቸው ።“ለሁለቱም ምስክሮቼ ማቅ ለብሰው ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን ትንቢት ሊናገሩ እሰጣለሁ።”ራእይ 11፥3።

እነዚህ ወይራዎች መቅረዞች የአውሬው ማህበረሰቦች ልቋቋማቸው ያልተቻሉ በአሕዛብ ላይ እንደ አምላክ የኾኑ ባልሥልጣኖች ናቸው ።“እነዚህ ትንቢት በሚናገሩበት ወራት ዝናብ እንዳይዘንብ ሰማይን ሊዘጉ ሥልጣን አላቸው፥ ውኃዎችንም ወደ ደም ሊለውጡ በሚፈልጉበትም ጊዜ ሁሉ በመቅሠፍት ሁሉ ምድርን ሊመቱ ሥልጣን አላቸው።” ራእይ *11፥6* ። እነዚህ የፍጻሜው ዘመን የገባቸው የተረዱ ምስጢርን ከጌታ የተማሩ ትላልቅ መንፈሳዊ ዓይኖች ያሏቸው ፣ ማንም ልቋቋምና ልጎዳቸው የማይቻሉ ፣ በአፋቸው ቃል መቅሰፍትን የሚያመጡ እንደ ኤልያስ ያሉ ብርቱዎች ናቸው ። “ማንምም ሊጐዳቸው ቢወድ እሳት **ከአፋቸው** ይወጣል ጠላቶቻቸውንም ይበላል፤ ማንም ሊጐዳቸው ቢወድም እንዲሁ ሊገደል ይገባዋል።” ራእይ 11፥5። እነዚህ ከብዙዎቹ ለዚህ ክብር የተለዩ የተዘጋጁ የኖሩ ናቸው ።የዚህን መልእክት ትርጓሜ በቀጣይ ካሜራ ስንመለከት በይበልጥ ይገባናል ። እነዚህ ብርቱዎች በቍጥር ኹለት ብቻ እንዳይደሉና እንመለከታለን ።

እነዚህ ቅዱሳን ካገለገሉ በኋላ የሚሰው ናቸው፤“ምስክራቸውን ከፈጸሙ በኋላ ከጥልቁ የሚወጣው አውሬ ይዋጋቸዋል ያሸንፋቸውማል ይገድላቸውማል።” ራእይ 11፥7 ።ኢየሱስን እንደሰቀሉ ብዙዎችን ነቢያትና አገልጋዮችን እንደገደሉ እነዚህንም ቅዱሳንንም ያን ጊዜ ገድለው ይሰቅሏቸዋል። እነዚህን ከመስቀል አውርደው አይቀብሩም በመሞታቸው; ብዙ ያሉ ስቃዮችን ስላመጡ ስጦታ እስከመሰጣጠት ይደሰታሉ፤ ራዕ 11፥፥8-10። ይኹን እንጂ ከሦስት ቀን በኋላ ይነሳሉ ፣

ተነስተውም ዳግን ምጽአት ስለሆነ ይነጠቃሉ ።"ከሦስቱ ቀን ተኩልም በኋላ ከእግዚአብሔር የወጣ የሕይወት መንፈስ ገባባቸው በእግሮቻቸውም ቆሙ፥ ታላቅም ፍርሃት በሚመለከቱት ላይ ወደቀባቸው።" ራእይ 11፥11 ። "በሰማይም፦ ወደዚህ ውጡ የሚላቸውን ታላቅ ድምፅ ሰሙ፤ **ጠላቶቻቸውም እየተመለከቱአቸው ወደ ሰማይ በደመና ወጡ።"** ራእይ 11፥12።

አስተውሉ ከመከራው በኋላ በሥልጣን ያገለገሉ ቅዱሳን በክብር ስነጠቁ ፦ስሞቱ የተደሰቱት አሕዛቦች ይመለከታሉ ። ንጥቀታቸውም በግልጽ ለኹሉም የሚታይ ነው። ንጥቀቱም ከመከራው በኋላ ነው። "በዚያም ሰዓት ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፥ ከከተማይቱም አሥረኛው እጅ ወደቀ፥ በመናወጥም ሰባት ሺህ ሰዎች ተገደሉ፥ የቀሩትንም ፍርሃት ያዛቸው፥ ለሰማዩም አምላክ ክብር ሰጡ።" ራእይ 11፥13 ።አሕዛብ ሳይፈልጉ በግድ ንስሐ ሳይገቡ እነርሱ ከፍ ከፍ ስሉ ይንበረከካሉ ፤ ለአምላክ ይገዛሉ። እነዚህ እነማን ናቸው? አኹንም ግልጽ አልኾነም አይደለ ? የራዕይ መጽሐፍ በመንፈስ ከተረጎምን ጌታ እየመጣ ላለው ነገር ከሚያዘጋጁት አገልጋዮች አንዱ እንኾናለን። ከምታተሙት በመከራው ውስጥ ኾነው መከራ ከማያገኛቸው አንዱ ትኾናለህ። ሰይጣን እርሱን የሚያስጨንቅ አገልግሎት የሚኖራቸውን ቅዱሳንን ማየት አይፈልግም ።መልእክቱ የእናንተ አይደለም ለእስራኤል ዘሥጋ ነው እያስባለ እያስተኛ ይገኛል። ምክንያቱም በቀላሉ ያደቅቃቸዋል በመከራው ጊዜ ። ጆሮ ያለው ይስማ ።

፡፡በእነዚህ መለከቶች የእግዚአብሔር ማስጠንቀቂያ ለዓለም እንደሚሰጥ እየተመለከትን ነበር። **የመጨረሻው የ7ኛው መለከትም "3ኛ ወዮ" ተብሏ**ል። ምክንያቱም የዓለምንና ዓለማዊያን መጨረሻ ነው። ለበጉ ታምነው የታረዱትና የታተሙት ደግሞ፣ ቅዱሳን ኹሉም በእግዚአብሔር ፊት በዓለም ፍጻሜ መጠቅለልና፣ ማለፏ ደስታቸውን ይገልፃሉ ። "ሰባተኛው መልአክ ነፋ፤ በሰማይም፦ የዓለም መንግሥት ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ ሆነች፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣል የሚሉ ታላላቅ ድምፆች ሆኑ። በእግዚአብሔርም ፊት በዙፋኖቻቸው የተቀመጡ ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች በግምባራቸው ተደፍተው ለእግዚአብሔር እየሰገዱ እንዲህ አሉ፦ ያለህና የነበርህ ሁሉን የምትገዛ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ **ትልቁን ኃይልህን ስለ ያዝህ ስለ ነገሥህም እናመሰግንሃለን፤ አሕዛብም ተቈጡ፥ ቍጣህም መጣ፥ በሙታንም ትፈርድ ዘንድ ዘመን መጣ፥ ለባሪያዎችህም ለነቢያትና ለቅዱሳን ስምህንም ለሚፈሩት ለታናናሾችና ለታላላቆችም ዋጋቸውን ትሰጥ ዘንድ፥ ምድርንም የሚያጠፉትን ታጠፋ ዘንድ ዘመን መጣ።**" ራእ 11፥15-18 ።

**2ተኛው መግለጫ ስለ ዘመን ፍጻሜ ምን ፍንጭ ይሰጣል !? ስናጠቃልል ፦**

ይኽ መግለጫ ስለታላቁ መከራ ተጨማሪ መረዳትን ይሰጣል። አምስተኛ መለከት የታላቁ መከራ ጅማሮ ስለኾነ ወዮታ ተብሏል፤ በሰይጣን ከሰማይ መጣል፣ የወረደውም ሰይጣን በጥልቁ የታሠሩትን መፍታት አዲስ እውቀትን የሚጨምር

ነው። ይኽ ለሰይጣን ጥቅት ጊዜ መፈታት ስለኾነ በደንብ ይሠራል። “ወደ ጥልቁም ሊሄዱ እንዳያዛቸው ለመኑት።”ሉቃስ 8፥31። ከሰማይ የወረደው ሰይጣን በምድር በጥልቁ የታሠሩትን እንዲፈታ ፈቃድ በመሰጠቱ፣ ሙሉውን ሃይሉን አሰባስቦ ጥቃት ያደርሳል ።ግን የታተሙትን [144 ሺህዎችን] ልነካ አይችልም ።ይኽም ቅዱሳን በታላቁ መከራ መሃል ጌታን ስቀበሉ; የእግዚአብሔር ጠባቆት በመከራው መሃል እንዳላቸው ያስረዳል ። እንዲሁም በማህተሞቹ [6ተኛው] ስንመለከት የታተሙበት ምክንያት ፣ መከራ ኹሉ እንዳይወርድባቸው ለመጠበቅ እንደኾነ አይተናል ። ይኽም እግዚአብሔር ከመከራው ለማሳለፍ "መንጠቅ" ግዴታ እንዳልኾነው ያስረዳል ።

6ተኛው መለከት ስነፋ ከመሰዊያ ቀንዶች የወጣው ድምጽ ቶሎ ንስሐ ግቡ የሚል ማስጠንቀቂያ ነበር፤ ሰዎች ግን ንስሐ አልገቡም ። የመስዊያ ቀንዶችን በደለኛ መጥቶ ከያዘው ምህረት ይደረግለታል፤ ከዚህ የወጣው ድምጽም ዓላማው "ንስሐ ግቡ፣ ኑ አምልጡ" የሚል ነበር ፤ ድሮ ሰዎች ሮጠው ምህረትን በመሻት የመሠዊያ ቀንድ ይይዛሉ ፤ አኹን ግን ሰዎች በሚሰጡ ማስጠንቀቂያዎች ልመለሱ ስላልቻሉ እራሱ [የመሠዊያ ቀንዶች] ለምህረት ይጣራል ። *1ኛ ነገ 1፥49 "አዶንያስም የጠራቸው ሁሉ ፈሩ፥ ተነሥተውም እያንዳንዳቸው በየመንገዳቸው ሄዱ። 50 አዶንያስም ሰሎሞንን ፈራ፥ ተነሥቶም ሄደ፥ የመሠዊያውንም ቀንድ ያዘ።51 ለሰሎሞንም፦ እነሆ፥ አዶንያስ ንጉሡን ሰሎሞንን ፈርቶ፦ ንጉሡ ሰሎሞን ባሪያውን በሰይፍ እንዳይገድለኝ ዛሬ ይማልልኝ ብሎ የመሠዊያውን ቀንድ ይዞአል አሉት።52 ሰሎሞንም። እርሱ አካሄዱን ያሳመረ እንደ ሆነ ከእርሱ አንዲት ጠጕር እንኳ በምድር ላይ አትወድቅም፤ ነገር ግን ክፉት የተገኘበት እንደ ሆነ ይሞታል አለ።53 ንጉሡ ሰሎሞንም ላከ፥ ከመሠዊያውም አወረዱት፤ መጥቶም ለንጉሡ ለሰሎሞን እጅ ነሣ፥ ሰሎሞንም፦ ወደ ቤትህ ሂድ አለው።"* ከመሰዊያው የሚወጣው ድምጽ ለአስቸኳይ ንስሐ የሚጣራ ብኾንም ክፉዎች ከክፋታቸው አልተመለሱም ። ንስሐም ልገቡም አልወደዱም ። በዚህም ጌታ ከመቅሰፍቱ የቀሩቱ;ተምረው ስላልተመለሱ፣ በዚያ በታላቁ መከራ ላይ በወንጌል ለመመለስ ዕድል ይሰጣል ፣ወንጌል እንዲሰበክ ያደርጋል ።

በዚህ መግለጫ ላይ ዮሐንስ ለግሉ የሚኾን ራእይ እንደተመለከተም እንረዳለን ፤ ለእኛ በጽሑፍም በቃልም እንዳያስተላልፍ የታዘዘው ።“ሰባቱ ነጐድጓድ በተናገሩ ጊዜ ልጽፍ አሰብሁ፤ ከሰማይም፦ ሰባቱ ነጐድጓድ የተናገሩትን ነገር በማኅተም ዝጋው አትጻፈውም የሚል ድምፅ ሰማሁ።” ራእይ *10፥4* ። ዮሐንስ የነጐድጓዶችን ድምጽ [ፍርድ] እንዳይጽፍ ለእኛ እንዳያስተላልፍ ታዙዋል፤ ይኽም ከተገለጠው /ከዚህ/ ውጪ አስፈሪ ፍርድ እንዳለ ያስረዳል ። ዮሐንስ ይኽንን ተረድቶ እንዲያገለግል ልዩ ተልዕኮም ተሰጥቶታል ፦

*ራእይ 10፥[8] ከሰማይም የሰማሁት ድምፅ እንደ ገና ሲናገረኝና፦ ሂድና በባሕርና በምድር ላይ ከሚቆመው መልአክ በእጁ ያለችውን የተከፈተችውን መጽሐፍ ውሰድ ሲል ሰማሁ።[9] ወደ መልአኩም ሄጄ፦ ታናሺቱን መጽሐፍ ስጠኝ አልሁት። እርሱም፦ ውሰድና ብላት፥ ሆድህንም መራራ ታደርገዋለች በአፍህ ግን እንደ ማር ትጣፍጣለች አለኝ።[10] ከመልአኩም እጅ ታናሺቱን መጽሐፍ ወስጄ በላኋት በአፌም እንደ ማር ጣፋጭ ሆነች፤ ከበላኋት በኋላም ሆዴ መራራ ሆነ።[11] በብዙ ወገኖችና በአሕዛብም በቋንቋዎችም በነገሥታትም ላይ እንደ ገና ትንቢት ትናገር ዘንድ ይገባሃል ተባለልኝ።"*

*ይህቺ መጽሐፍ የተከፈተች መጽሐፍ ናት፤ እንዲያስተምር የተፈቀደች ናት፤ መጽሐፉ ዮሐንስ ስበላ በአፉ ጣፍጣ በኾዶ መራራ ኾነች፤ የእግዚአብሔር ሃሳብ ስሰማ ጣፍጦ ስሰራ መራራ መራሪ እንደኾነ ያስረዳል ። ይኸንንም መራራ አገልግሎት እንዲያገለግል እንዲያስተምር [ትንቢት እንዲናገር] ታዘዘ ። ይኸ ለእኛም ነው። ዮሐንስ ራእዩን ከተመለከተበት ጊዜ አንስቶት ይኸንን ተረድቶ ስያስተምር ኖሯል። እኛም ይኸንን እውነት ስለመምጣቱ እንዲናስተምር ጌታ ይፈልጋል ። ዮሐንስ "ያኔ"ማስተማር ከጀመረ እኛስ እንዴታ !? ይኸ ተልዕኮ ለራእይ ተደራሲያን የተሰጠ ነው ። ትንቢት ተናገር የተባለው እንደ ሃሰተኞቹ ይኾንልሃል፣ ይሳካልሃል፣ ትጠረምሳለህ ወዘተ. የሚባለውን አይደለም ወይም ከዚህ በፊት ያልተሰበከ ቃል አይደለም ።ዮሐንስ የተባለው "እንደገና ልትናገር ይገባሃል " ነው፤ ስለዚህም አስቀድሞ የተናገረውን እንደገና በጭቃነ ይናገራል ። ዮሐንስ የሚናገረው ትንቢት በራእይ የተመለከተውን የፍጻሜ አገልግሎት ነው፤ይኸንኑን ይናገራል።ይኸም መራራ አገልግሎት ነው ።ምክንያቱም ያለ ፊት ማዳላት በነገስታቱ ፊት ቆሞ እንኳን ይመሰክራል ። ይኸንን የተረዱት መራራ አገልግሎት እንዲያገለግሉ ጌታ ይፈልጋል ። መጽሐፉን የበላ ያገለግላል። ሃሰተኛ አስተማሪዎች መጽሐፉ ለእስራኤላውያንን [ዘሥጋ] እና ለአሕዛብን ብቻ ያመለክታል ብሉም፣ ዮሐንስ ትንቢት እንደገና እንዲናገር የተነገረው ለኹሉ እንጂ ለእስራኤል ዘሥጋ ብቻ እንዳልኾነ ስናስተውል የሃሰት ትምህርት እንደኾነ በቀላሉ እንረዳለን ። ይኸም አገልግሎት ለእኛ ለአማኞች ነው። ዮሐንስ አኹን የለም። ንስሐ ልገቡ ላልወደዱ ለአሕዛብ ትንቢትን እንዲናገሩ የተባሉት የጌታ ምርጦች ናቸው።ዮሐንስ የፍጻሜ ዘመን ራእይ መልእክት ተቀባይ እንጂ ፈጻሚ አይደለም ። ፈጻሚዎቹ ባሪያዎቹ ኹሉ ናቸው ።*

*ደግሞም በዚህ መግለጫ ስር ፣የእግዚአብሔር መቅደስና በእዚያ የሚያመልኩት መለካቱ፣ ለ42 ወራት ተጠብቀው በአሕዛብ ሳይረገጡ እንዲኖሩ ነው። ነገርግን በዚያ ጊዜ ለ42 ወራት ሃይልን ታጥቀው የሚያገለግሉ አሉ፤ "እነዚህ በምድር ጌታ ፊት የሚቆሙ ሁለቱ ወይራዎችና ሁለቱ መቅረዞች ናቸው።" ራእይ 11፥4። እነዚህ ከላይ ንስሓ ልገቡ ባልወደዱት አሕዛብ ላይ ትንቢትን የሚናገሩ ናቸው።እነዚህ በስልጣን እንዲያገለግሉ ተሰቷቸዋል ፤ ከአፋቸው እሳት ይወጣል ፤ ልክ ለትያጥሮን ቤተክርስቲያን ጌታ; እንደገለጸው ፤ ድል የነሱት በአሕዛብ ላይ ስልጣን ይሰጣቸዋል ።*"**ድል ለነሣውና እስከ**

***መጨረሻም ሥራዬን ለጠበቀው እኔ ደግሞ ከአባቴ እንደ ተቀበልሁ በአሕዛብ ላይ ሥልጣንን እሰጠዋለሁ፥ በብረትም በትር ይገዛቸዋል፥ እንደ ሸክላ ዕቃም ይቀጠቀጣሉ፤" ራእይ 2፥26-27።*** እነዚህ ከቤተክርስቲያን ድል በመንሳት ለዚህ ለፍጻሜ፤ መጠቅለያ አገልግሎት የተመረጡ የጌታ ምርጦች ናቸው ። በታላቁ መከራ ጊዜ የሚያገለግሉ ።

አንድአንድ ሰዎች የሞቱና የተወሰዱ ታላላቅ ነቢያት [ሙሴና ኤልያስ] መጥተው የሚያገለግሉ አድርገው ይረዳሉ ።የዚህ ክፍል መግለጫ የሚናገረው ግን ጌታ ለድል ነሺዎች የሰጠውን ስልጣንን ነው። አኹን አስተውሉ ። እስካሁን ቅዱሳን በምድር ላይ እንዳሉ ከመከራው በፊት እንዳልተነጠቁ ።ተመከትን፡፡ ለ42 ወራት ተለይተው ተጠብቀው እንዲኖሩ በመቅደሱ የሚሰግዱት ተቈጥረው ተለዩ፤ አሕዛብ እንዳይገባ ተደረገ። ደግሞም ለ42 ወራት አሕዛብ ያልተለካውን ስፍራ ይረግጣሉ ፤ ደግሞም አሕዛብ በሚረግጡበት ስፍራ ለ42 ወራት በአሕዛብ ከተሞች በስልጣን የሚያገለግሉ አሉ። ምን አስተዋላችኹ!? ለትያጥሮን ቤተክርስቲያን የተሰጠው ቃል፣ በዚህ በታላቁ መከራ ጊዜ ለ42 ወራት በስልጣን የሚያገለግሉ አገልጋዮችን ለማስነሳት እንደኾነ፣ እነዚህም የፍጻሜ አገልጋዮች ስኾኑ፣ ደግሞም በመቅደሱ የሚሰግዱ የተቆጠሩ ለ42 ወራት የተሸሸጉ፤ በጌታ ተጠብቀው ባዘጋጀው ስፍራ የሚያሳልፉ መከራው የማያገኛቸው [ሴቲቱ የተባሉት] ናቸው ።

ከ5ተኛው መለከት ጀምሮ ያለው በታላቁ መከራ የሚኾኑት የሚያስረዳ ነው። በቀላሉ ለመረዳት ፡-

***ለ42 ወራት መከራ የማያዩ አማኞች [የተለኩ ቅዱሳን ]ሴቲቱ ስትኾን፣**

***ለ42 ወራት በአሕዛብ  ከተማ አሕዛብን ረግጠው በስልጣን የሚያገለግሉ ሴቲቱ የወለደቻቸው ወንድ ልጆች ናቸው ፤ ኹለቱ ምስክሮች የተባሉት ናቸው፣**

***144 ሺህ ቅዱሳኖች ደግሞ በታላቁ መከራ ጊዜ በመከራው አልፈው ግና የሚድኑቱ ናቸው ፣**

**[ይኽንን በቀጣዩ መግለጫ በደንብ እንረዳለን]**

ሴቲቱ ወይም በዚህ አውድ በመቅደሱ የሚሰግዱቱ የተሰጣትን መከራ በድል አልፋ ነጭ ለብሳ ያለ ነቀፋ እያመለከች ያለች ስትኾን ፣ለ42 ወራት አሕዛብ እንዲገባ እንዲረግጥ የማይፈቀድ ስፍራ ላይ ተጠብቃ ትኖራለች ።ምክንያቱም ጌታ በመከራ መሃል መከራው ሳያገኛት ለማሳለፍ ቃል ገብቷል እንደ ፊላደልፊያ አማኞች ላሉት ።"የትዕግሥቴን ቃል ስለ ጠበቅህ እኔ ደግሞ በምድር የሚኖሩትን ይፈትናቸው ዘንድ በዓለም ሁሉ ላይ ሊመጣ ካለው ከፈተናው ሰዓት እጠብቅሃለሁ።" ራእይ 3፥10። ጌታ ሳይነጥቀን ጠብቆ ሸሽጎ ለማሳለፍ ቃል እንደገባ; ያደርጋል ። አያችሁ; ሴቲቱ የወለደችው ወንድ ልጅ አሕዛብን በብረት ብትረ ገዝቶ እንደሚነጥቅ ?ራእ 12። አዎን መጽሐፉን በመንፈስ ስንረዳ ወደዚህ እንደርሳለን ። የቅድመ መከራ ንጥቀት አስተማሪዎች ሃሰተኞች ናቸው የሚለው ለዚህም ነው፥ ከሴቲቱ ኾነ ከወንድ ልጁ፣ ጌታ ላሰበላችኹ ላየላችኹ

ሕይወት እንዳትደርሱ ማድረግ ነው። ምክንያቱም በዚያ በታላቁ መከራ ብዙዎች አማኞች ይወድቃሉ ።እኹን እንዳትዘጋጁ በማድረግ በመከራው መንጠቅ ነው ሃሳባቸው ።ይኽንን አውቃችሁ ራቋቸው።

አስተውሉ ጌታ አሕዛብ ላይ ስልጣን የሚሰጠው ድል ለነሱት ምዕመናን እንጂ እናንተ ለሚታስቧቸው "አገልጋይ" ለሚባሉት ሰዎች [ብቻ] አይደለም ። ወዳጆቼ አሕዛብን እያስጨነቃችኹ ማገልገል አትፈልጉም ? ወይም ከመከራው በላይ መኾንን አትፈልጉም ? እኔ የሚሰብከው ለሚሰሙት ነው፤ ድል የሚነሱትን ለማፍራት ነው። ለራሴም ድል ለመንሳት ይኽንን ተረድቼ እመላለሳለሁ ። እነዚህ ወይራዎች ከሰበኩ በኋላ እንደዚህ መግለጫ መሠረት ፍጻሜ ይኾናል ማለት ነው። ስለዚህም በአጭር ቃል በ6ተኛው መለከት መነፋትም የሰው ልጅ ንስሐ ልገባ ስላልወደደ ጌታ በምህረት ልጎበኘው ወደደ ።“ሌላም ብርቱ መልአክ ደመና ተጐናጽፎ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ፤ በራሱም ላይ ቀስተ ደመና ነበረ፥ ፊቱም እንደ ፀሐይ እግሮቹም እንደ እሳት ዓምዶች ነበሩ፥” ራእይ 10፥1። ይኽ መላአክ ደመና የተጎናጸፈ [የእግዚአብሔር መገኘት ያለበት ]፣ ራሱ ቀስተ ደመና የኾነለት [ያለማጥፋት የምህረት ምልክት ያለው]፣ ፊቱ ፀሃይ [ጽድቅ የኾነ]፣ ነገርግን እግሮች እሳት የኾኑ ናቸው ፤የሚያቃጥሉ ። ይኽ መልአክ ምድርና ባሕርን የረገጠ ስኾን በእጁ የሚተረጎምና እንዲናውቀው እንዲናደርገው የተገባ መጽሐፍ [መልእክት] ይዟል ። ለዮሐንስ እንደገና የማስተማር ተልዕኮ ከተሰጠው በኋላ፣ 7ተኛው መለከት ከመነፋቱ በፊት ቤተመቅደሱንና መሰዊያ ለካ ፣በዚያ የሚሰግዱትን [አማኞችንም] ቈጠረ ። ምክንያቱም ትንቢቱ [ቃሉ] ለፍጻሜው ዘመን የሚያገለግልበት አገልግሎት ነው፤እጅግም በጣም ሃይል የተሞላበትና የሚያስጨክን መራራ አገልግሎት ነው።

ዮሐንስ ራእዩን ስመለከት በታላቁ መከራ ጊዜ እንደሚያገለግል ተልዕኮ ስሰጠው እናያለን ።አገልግሎቱ ስለ መጨረሻ ዘመን ስለ ፍጻሜው ስለ ማጠቃለያ አገልግሎት ለተመረጡት የተሰጠ ተልእኮ ነው። ይኽ የእግዚአብሔር ሃሳብ ነው።ዮሐንስም ይኽንን በመረዳት አገልግሏል ። ዛሬ ላይ ሰይጣን ከአስተማሪዎች ይኽንን እውነት ከራሱ ግብረአበሮቹ ጋር በመኾን ደብቋል። ከመከራው በፊት ትነጠቃላችኹ በማለት ራእይ ም.4 ጀምሮ ያለውን ቃል "አይመለከተንም" በማለት ጌታ የሰጠውን ተልእኮ እንዳያስተውሉ አድርጓል ። ይኽንን ተረድተው የሚመላለሱ አሉ ፤እግዚአብሔር ይመስገን ። ጆሮ ያለው ይስማ።

በስድስተኛው መለከት እንደተመለከትነው የእግዚአብሔር ታላላቅ ቍጣዎችን የሚያመጡት ለክብር ለመጨረሻው አገልግሎት የተለዩት ቅዱሳን ናቸው፤ደግሞም 1⅓ኛው ብቻ በአንድ መቅሰፍት ከምድር መመታቱ እግዚአብሔር አኹንም ምህረት ለማድረግ ፈቃኛ መኾኑንና የማስጠንቀቂያዎች ዓላማ ንስሐ እንደኾነ የሚያስገነዝብ ነው። ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ትይንት ለመመልከት አንባቢ በእግዚአብሔር ፊት ልበዎን እንድመረመሩ አበረታታለሁ ። ለማን ነው የሚትቀናው? ለሰው ወይስ ለእግዚአብሔር ቃል እውነት?

## 1.2.3 ሦስተኛው መግለጫ

ከምዕራፍ 11፥19 እስከ ምዕራፍ 15፥4 ያለው እስካሁን የተመለከትነው መልእክት በልዩ ልዩ መንገድ ከላይ ወደ ታች እንደተቀረጸ ካሜራ አንዷን ነገር /ዘመን ፍጻሜን/ የሚያሳዩ ናቸው ።በፊለፊት እና በጎን ካሜራ የተቀረጸ በማለት በምሳሌ በኹለት መንገድ አይተናል ።አኹን ደግሞ ከላይ ወደ ታች በተቀረጸው ካሜራ እንደቀረበ በማሰብ በዓለም የሚኾኑትን እንመለከታለን ።"በሰማይም ያለው የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ፥ የኪዳኑም ታቦት በመቅደሱ ታየ፥ መብረቅና ድምፅም ነጐድጓድም የምድርም መናወጥ ታላቅም በረዶ ሆነ።" ራእይ 11፥19 ። በዚህ ትይዕንት ከሰማይ ስፍራ ጀምረን የሚኾነውን እንመለከታለን ፤ እግዚአብሔር አኹንም ኪዳኑን እንደሚጠብቅ የኪዳኑ ታቦት መታየቱ ያስገነዝበናል ። ይኽ ካሜራ የሚያሳየው ከላይ ከፍ ብሎ የተቀረጸውን ስለኾነ ስለ መጨረሻው ዘመን ተጨማሪ መረዳት በመስጠት ይረዳናል ። አንባቢ ይኽንን ስያነቡ በምዕራፍ አራት ልኾን የሚያስፈልገውን እንጂ የኾነውን ያለፈውን ክስተት እየተመለከቱ እንዳይደሉ እያስተዋሉ ይኹን ። እንደ ታርክ ወይም እንደ ቅዱሳን ገድል ሳይኾን ዮሐንስ ራዕዩን ከተመለከተ ጊዜ ጀምሮ የሚፈጸሙ ምስጢራትን እንደሚገልጽ በልበዎ ይዘው ያንብቡ ። እስካሁን የተመለከትነው የማህተሙ ኾነ የመለከቱ ምስጥር **አንድ ነገርን በተለያየ አቅጣጫ እንደሚያሳይ** የተገነዘባችሁት ይመስለኛል ። ጀሮ ያለው ወደ ከፍታው መምጣቱ አይቀርም ። ከዮሐንስ ጋር እንቀጥል በወፍበረር ፍንጭ ለመስጠት ያህል እናያለን ።

"በሰማይም ያለው የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ፥ የኪዳኑም ታቦት በመቅደሱ ታየ፥ መብረቅና ድምፅም ነጐድጓድም የምድርም መናወጥ ታላቅም በረዶ ሆነ።" ራእይ 11፥19 ።

የእግዚአብሔር መቅደስ የሐዲስ ኪዳን ካህናት መኖሪያቸው ነው። ታቦቱ በመቅደሱ መኖሩ ፣ እግዚአብሔር በመቅደሱ መኖሩን ከሕዝብ ጋር መኾኑን የሚያመላክት ነው። እንግዲህ ይኽ ክስተት ለታላቁ ፍርድ ጅማሮ እንዲኾን ምክንያት እንደኾነው እንድንረዳ ያደርገናል ። በሌሎቹ መግለጫዎች በ1ኛው ኾነ በኹለተኛው የቅዱሳን የፍትሕ ጥያቄ ለምድር መናወጥ መነሻ እንደኾነ አይተናል ። በዚህ መግለጫ ስር ጌታ ከባሪያዎቹ ጋር በሙላት በክብር መኖሩ ለምድር መናወጥ ምክንያት ኾኗል። ጸሃይ የለበሰችው ሴት መታየቷ አብሮተ እግዚአብሔርን የሚያስረዳ ነው።

"ታላቅ ምልክትም በሰማይ ታየ ፀሐይን ተጐናጽፋ ጨረቃ ከእግሮችዋ በታች ያላት በራስዋም ላይ የአሥራ ሁለት ከዋክብት አክሊል የሆነላት አንዲት ሴት ነበረች።እርስዋም ፀንሳ ነበር፥ ምጥም ተይዛ ልትወልድ ተጨንቃ ጮኸች። ...አሕዛብንም ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ልጅ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ልጅዋም ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ። ሴቲቱም ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን በዚያ እንዲመግቡአት በእግዚአብሔር ተዘጋጅቶላት ወደ ነበረው ስፍራ ወደ በረሀ ሸሸች።" ራእ 12፥1-6።

አንባቢ ኾይ; ይኽ መጽሐፍ ዮሐንስ ራእዩን ከተመለከተ በኋላ የሚፈጸሙ ነገሮችን እንደሚይዝ በመገንዘብ ትንቢታዊ መጽሐፍ መኾኑን አምነው ያንብቡ። የታየው ታላቅ ምልክት ከዚህ በፊት ታይቶም ተሰምቶም የማይታወቅ አዲስ ነገር ነው። ፀሐይን ተጐናጽፋ ጽድቅን ለብሳ ፤ ያውም ብርሃን የኾነውን የእግዚአብሔር ባሕርይ ይዛ ተሞልታ፤ ደግሞም "ጨረቃ የራሱ ብርሃን ሳይኾን ከሌላው በወሰደው የሚያበራውን" ረግጣ ማለትም "ሃሰተኛውን ብርሃን መላአክ የመሰለውን ረግጣ"[ታላቁ መከራ በደጅ ነው ይመ.] የታየችው ሴት ፦ የፊት መጨማደድ ሳይኖርባት በቅድስና በጉን ለመቀበል የተዘጋጀችው የክርስቶስ እስራኤል ቤተክርስቲያን ናት። ይህች በ12ቱ ሐዋርያት መሠረት በክርስቶስ እንደራሴዎች ተውባ በዚያ ጊዜ በመጨረሻው ሰዓት የተገኘች ፣ ዘመኑን ያወቀች፣ የተዘጋጀች ሙሽሪት የበጉ ሚስት ናት። ቤተክርስቲያን በክብሯ በውበቷ በሙላቷ በመገለጧ በምዕራፍ 9 እንደ ተመለከትነው ሰይጣን ወደ ምድር ይጣላል ። በዚህም ይህቺን ቤተክርስቲያን ያስጨንቃታል ።

ሰይጣን ወደ ምድር ወርዶ በሃያላን ሃገራት እና በሐሰተኛው ሃይማኖት ይሠራል ።በዚህም ቤተክርስቲያንን ለመዋጥ ለማጥፋት ይተጋል ። ሌላም ምልክት በሰማይ ታየ፤ እነሆም ታላቅ ቀይ ዘንዶ፤ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶችም ነበሩት በራሶቹም ላይ ሰባት ዘውዶች ነበሩ፥ጅራቱም የሰማይን ከዋክብት ሲሶ እየሳበ ወደ ምድር ጣላቸው። ዘንዶውም ሴቲቱ በወለደች ጊዜ ሕፃንዋን እንዲበላ ልትወልድ ባላት ሴት ፊት ቆመ። ራእ12፥ 3-4። ዲያብሎስ ወደ ምድር ስጣል ከራሱ ጋር ከመላእክት ⅓ኛውን ወደ ምድር እንደሚጥል፣በዚህም ሃይል እንዳለው እንገነዘባለን ። የክርስቶስ ደም ባይሸፍነንና ስሙ ባይኖረን እንዴት ይጫወተብን ይኹን ? ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባውና ተጠብቀናል። ሰይጣን ከሰማያዊ ስፍራ ወደ ምድር የተጣለው በቤተክርስቲያን ሙላት መኾኑን እንገነዘባለን ።

ሰይጣን ወደ ምድር መውረዱ ቤተክርስቲያንን አስጨንቋታል። የፖለቲካ መሪዎች እና ሃሰተኛ መምህራን ይዞ ስለሚሠራ በመቃተት ላይ ትገኛለች ሃይልን ለመታጠቅ ።ጌታም እንዲታደጋት። የቤተክርስቲያን ጭንቀት ከፅንሰት ጋር ተመስሎ መገለጡ መከራ ውስጥ ታምና መቆሟን ያሳየናል ። በዚህ ጭንቀቷም የወለደችው ወንድ ልጅ አሕዛብን እያስጨነቀ ሚገዛ ፣ ደግሞም ከፍ ብሎ የሚነጥቅ ነው። አስተውሉ ሴቲት ልጁን ከወለደች በኋላ 1260 ቀን ወደ በረሃ ብቻዋን ስትሸሽ፣ልጁ ደግሞ አሕዛብን ገዝቶ ፣በመጨረሻም ወደ ሰማይ ይነጠቃል ። መጽሐፉን በትንቢት መንፈስ አንብቡ። ልጁ ኢየሱስ አይደለም ።ኢየሱስ ገና የሚወለድ አይደለም በዚያን ሰዓት ግና የሚገኝ አይደለም ። እርሱ የቤተክርስቲያን ራስ ነው። የእስራኤል አምላክ ነው።ሴቲቱ እስራኤልም ማርያምም አይደለችም ። የትንቢቱን መንፈስ አስተውሉ። ሴቲቱ ወልዳ ትሰደዳለች። ልጇም አሕዛብን ቀጥቅጦ ገዝቶ ይነጠቃል ።ሰይጣን ከሰማይ ስወድቅ፣ መቅደሱ [ቤተክርስቲያን] እንዳይነካ ስለካ ም.9 ፣ ያልተለካው ስፍራ ስረገጥ ፣ በዚያ ሰዓት እንደ ወይራ እንደ መቅረዝ ኾነው ፣ለአሕዛብ ጨንቀት የፈጠሩ የክርስቶስ ሠራዊቶች፣ በዲያብሎስ ጥቅት ጊዜ ዲያብሎስን የሚያስጨንቁ ወንድ ልጆች፣ እንደ አምላክ መቅሰፍት እያመጡ

እያሸበሩ አሕይዛብን የረገጡ ፣በመጨረሻም አገልግሎታቸውን ጨርሰው ወደ ሰማይ የሚነጠቁ የሴቲቱ ወንድ ልጆቿ ናቸው ። ጆሮ ያለው ይስማ።

"በሰማይም ሰልፍ ሆነ፤ ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉ። ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ፥ አልቻላቸውምም፥ ከዚያም ወዲያ በሰማይ ስፍራ አልተገኘላቸውም።ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፥ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፤ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ።" ራእ 12፥ 7-9።

የሰይጣንን ወደ ምድር መጣልን መውደቅን በተለያየ ካሜራ እንደተቀረጸ ምስል እየተመለከትን እንገኛለን ።ነገርግን ሰይጣን ወደ ምድር የሚጣለው ለዘላለምም በሰማይ ስፍራ የማይገኘው እንዴት ነው? የሚለውን አልተመለከትንም ። ኢሳይያስ ተረድቶ ስለ ሰይጣን መውደቅ፣ በዚያ ስፍራ ዳግም ስለአመገኘት እንዲህ ብሎ ተናግሮ ነበር ፡- "አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ፥ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ! አሕዛብንም ያዋረድህ አንተ ሆይ፥ እንዴት እስከ ምድር ድረስ ተቈረጥህ!አንተን በልብህ፡- ወደ ሰምይ ዐርጋለሁ፥ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፥ በሰሜንም ዳርቻ በመሰብሰቢያ ተራራ ላይ እቀመጣለሁ፤ከዳመናዎች ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ፥ በልዑልም እመሰላለሁ አልህ። ነገር ግን ወደ ሲኦል ወደ ጕድጓዱም ጥልቅ **ትወርዳለህ**።የሚያዩህ ይመለከቱሃልና፡- በውኑ ምድርን ያንቀጠቀጠ፥ መንግሥታትንም ያናወጠ፥ ዓለሙን ሁሉ ባድማ ያደረገ፥ ከተሞችንም ያፈረሰ፥ ምርከኞቹንም ወደ ቤታቸው ያልሰደደ ሰው ይህ ነውን? ብለው ያስተውሉሃል። ኢሳ 14፥ 12-17። ሐዋርያው ጳውሎስ ውጊያ ከእነዚህ በሰማይ ካሉት ሃይላት ጋር እንደኾነ መስክሮ ነበር፤[ኤፌ 6፥12]፤ መንፈሳዊ ነገር ተረድቶ። እነዚህ በሰማይ ያሉት ሃይላት የእግዚአብሔርን ሕዝብና መላእክቱን የሚያስጨንቁ የሚዋጉ ናቸው ። ወደ ዳንኤል መልእክት ይዞ የሚመጣው መልእክተኛው መላአክ፣ አየር ላይ በሰማይ እየተዋጉ በማቆየት የእግዚአብሔር መልእክት በጊዜው እንዳይደርስ ያደናቅፉ፣ያዘገዩ ፣ በምድር ኾነው እየጸለዩ ያሉትን ቅዱሳንን የሚያስጨንቁ ናቸው ።ዳን 10። ሰይጣን ወደ ምድር ስጣል ያላቸው ጊዜ 3 ዓመት ከ6 ወር ብቻ ነው።

አስተውሉ ሰይጣን ገና ወደ ምድር እንደሚጣል፤ የሰማይ መኖሪያ ለአንዴና ለዘላለም ስለቅ፣ በእርሱ መውረድ ሴቲቱ ስትሰደድ ፣ይኽ ገና የሚኾን የሚፈጸም ነው።ይህ ያለፈ ታርክ የሚያወሳ በፍጹም አይደለም፤ ከፈሪሳውያን እርሾ ተጠበቁ ። ከሃሰተኛ አስተማሪዎች ተጠበቁ።

“ዘንዶውም ወደ ምድር እንደ ተጣለ ባየ ጊዜ ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት አሳደዳት።” ራእይ 12፥13 ። ሴቲቱ ታትማ ተለይታ ተከልላ ፣ በጽድቅ ተሞልታ ሙላቷን ስትፈጽም ። እየመጣ ያለውን በመረዳት ብዙ በመቃተት ብርቱ ልጆቿን የመጨረሻው ዘመን አገልጋዮችን ስታዘጋጅ ፣ ሰይጣን ከሰማይ ወደ ምድር ተጣለ። ሴቲቱንም በራሱ ግብረአበሮቹ የፖለቲካ ሃይላትና ሃሰተኛ አስተማሪዎች ተጠቅሞ አሳደዳት ።ንፅሀት ቅድስት ሙሽሪት ኾና የተዘጋጀች ናትና ፣ጌታ ለዚህ ዓላማ

ይኾን ዘንድ ወዳዘጋጀው ስፍራ ሸሸች፤ ታላቁ መከራው አያገኛትም ።1260 ቀን በሰይጣን ጥቅት ጊዜም አትጎዳም። "ዘንዶውም ወደ ምድር እንደ ተጣለ ባየ ጊዜ ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት አሳደዳት።"ራእይ 12፥13 ።ሰይጣን ይኽንን እውነት እንዲታውቅ አይፈልግም ።ምክንያቱም እርሱን የሚያስጨንቁ ትውልዶች ፣ልጆች የሚታዘጋጁ እናንተ ናችሁ ። ጆሮ ያለው ይስማ።

" ከእባቡም ፊት ርቃ አንድ ዘመን፥ ዘመናትም፥ የዘመንም እኵሌታ ወደ ምትመገብበት ወደ ስፍራዋ ወደ በረሀ እንድትበር ለሴቲቱ ሁለት የታላቁ ንሥር ክንፎች ተሰጣት።እባቡም ሴቲቱ በወንዝ እንድትወሰድ ሊያደርግ ወንዝ የሚያህልን ውኃ ከአፉ በስተ ኋላዋ አፈሰሰ። ምድሪቱም ሴቲቱን ረዳቻት፥ ምድሪቱም አፍዋን ከፍታ ዘንዶው ከአፉ ያፈሰሰውን ወንዝ ዋጠችው።" ራእ 12፥14-16 ። ሴቲቱ [የተዘጋጀችው ቤተክርስቲያን] ለዚህ ጊዜ ይኾን ዘንድ ጌታ ወዳዘጋጀው ስፍራ ፣በረሃ [መንፈሳዊ ስፍራ] ትሸሻለች። በዚህም ታላቁ መከራ ሳያገኛት ታሳልፋለች። ከምድር ተነጥቃ ሳይኾን በምድር እያለች ። ሴቲቱ አስተማማኝ ታላላቅ ንስር ክንፍ አላት፤ በመለኮታዊ ሃይል የተሞላች ማንም ልነካትና ልደፍራት የማትቻል ናት። ዘንዶው ልሞክራት ብወድም የራሱን ግብረአበሮቹ [ወንዞችን] ብያስነሳባትም ተፈጥሮ ራሷ በተለያየ ምድራዊ መቅሰፍት በማምጣት ታደቅቃለች። ፍጥረት ራሱ ከጎኗ ኾኖ ውኃ እየተመረዘ በተለያየ ተፈጥሯዊ አደጋ አሕዛብን ይመታሉ።

ዘንዶው ፀሐይ ለበስ የኾነችውን ልይዛት አልቻለም ። በዚህም የእርሷ ዘር የኾኑትን ከእርሷ የተገኙትን ያልተሠወሩትን የቀሩትን ፣ነገርግን ሃይልን ታጥቀው ለፍጻሜው ለማገልገል የተዘጋጁትን፣ በነፍሳቸው ተወራርደው ያሉትን ለመዋጋት ዘወር ይላል። አያችሁ! ከመከራው ለመጠበቅ ከመከራው በፊት ትነጠቃላችኹ ብሎ ማስተማርና ማሰብ ግዴታ እንዳይደለ? የቅድሜ መከራ ንጥቀት አስተምህሮ በብልሃት የተፈጠረ ለሰው አዕምሮ ደስታን የሚሰጥ ትምህርት ነው።ነገርግን ከእግዚአብሔር አይደለም ።የእግዚአብሔር አይደለም ።ዋናው ዓላማው ከሴቷም ከዘሯ [ከልጇም] መሃል እንዳትኾኑ በማድረግ ማደንዘዝ ነው። ሴቲቱ ወደ ሰማይ ሳትነጠቅ በምድር ኾና ልክ እንደ ኤልያስ ተጠብቃ ተሰውራ ያንን ታላቁን መከራ **3** ዓመት ከ**6**ወር ታሳልፋለች ። የእርሷ ዘር ግን ለውጊያ ለጦርነት ይዘጋጃል ።"ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ ተቈጥቶ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትን የኢየሱስም ምስክር ያላቸውን ከዘርዋ የቀሩትን ሊዋጋ ሄደ፤" ራእይ 12፥17 ።

ከእነዚህ ቅዱሳን ጋር ለመዋጋት ባሕር ዳር [ሃያላን ሃገራት አጠገብ] የቆመው ዘንዶው በኹለት መንገድ ውጊያውን ያካሂዳል፤ ሃይሉን አሟጦ የመጨረሻ ጊዜው ስለኾነ፣ ቤተክርስቲያንም ሳትነካ ስለተረፈች በብስጭት እንደ ቆሰለ ውሻ ለመናከስ ይመጣል ።**1ኛው መንገድ**.ከባሕር የወጣ አውሬ መጠቀም ነው;በሃያላን ሃገራት ሌላውን ማስገደድ ከሚችሉት ጋር በግልጽ መሥራት ነው። "አንድም አውሬ ከባሕር ሲወጣ አየሁ፤ አሥር ቀንዶችና ሰባት ራሶች ነበሩት፥ በቀንዶቹም ላይ አሥር ዘውዶች በራሶቹም ላይ የስድብ ስም ነበረ።" ራእይ 13፥1። ብዙዎችን ይማርካል ። የእግዚአብሔር

ከተማ የነበሩ ሃይልን ያልታጠቁ ቅዱሳን የነበሩ ይጨፈለቃሉ። 2**ኛው መንገድ**. ከምድር የወጣ አውሬ መጠቀም ነው; "ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ፥ የበግ ቀንዶችን የሚመስሉ ሁለት ቀንዶችም ነበሩት እንደ ዘንዶም ይናገር ነበር።" ራእይ 13፥11 ። ከምድር የወጣው አውሬ ሃሰተኛ ነቢያት ስኾኑ የማይጎዱ የበግ ቀንድ ያላቸው ይመስላሉ ፣ ከአፋቸው የሚወጣው ግን ኑፋቄና መረን የኾነ እንደ ዘንዶ ያለ ነው። ለሃሰተኛ አስተማሪዎች ከባሕር የወጣው የመጀመሪያው አውሬ አቅሙ ነው። ብዙ ታላላቅ ምልክቶችን የሚያደርግ ስኾን ምልክት ፈላጊ ቅዠታም "አማኝ" ይጠፋል። ቍ.13። እነዚህ ምልክት ፈላጊ ልባቸው ያልሠሩትን ለማጨድ ገንዘብ አካውቷቸው ላይ "ገባ" ስባል የሚዘልሉ ይጠፋሉ፤ የሚሰብኩትም ለሰይጣን መንገድ ጠራጊዎች ናቸው ።ጆሮ ያለው ይስማ። ይኽ ሃሰተኛው አስተማሪ የራሱ ተከታዮችን ለመለየት በሰውነታቸው ምልክት ማህተም ያደርጋል፤ ስሙን ወይም 666 ምስጥራዊ ቍጡሩ ነው።በማህተሙም ማህተሙ የለሌው ሌላው እንዳይገዛ እንዳይጠቀም በማድረግ በማስጨነቅ ለመማረክ ይጠቀማል ።ጆሮ ያለው ይስማ።

በዚህ ሰይጣን ስያስጨንቅ፣ በዚህ ቤተክርስቲያን ተጠብቃ ስታመሰግን፣ እንደገና እድል ለተሰጣቸው ወንጌልን እንዲሰሙ ጌታ በወንዶች [በብርቱዎች] ከዘሯ በቀሩት እንዲሰበክ ያሳስባል፥"በምድርም ለሚኖሩ ለሕዝብም ለነገድም ለቋንቋም ለወገንም ሁሉ ይሰብክ ዘንድ የዘላለም ወንጌል ያለው ሌላ መልአክ ከሰማይ መካከል ሲበር አየሁ፤" ራእይ 14፥6 ። **አንደኛው ሰባኪ ፣ንስሐ እንዲገቡና ለእግዚአብሔር እንዲገዙ ያውጃል ።** "በታላቅ ድምፅም፦ የፍርዱ ሰዓት ደርሶአልና እግዚአብሔርን ፍሩ ክብርንም ስጡት፤ ሰማይንና ምድርንም ባሕርንም የውኃንም ምንጮች ለሠራው ስገዱለት አለ።" ራእይ 14፥7 ። **ሌላኛው ሰባኪ የነገሰችው ባቢሎን እንደሚትወድቅ ያውጃል፤ ይኽ መግለጫ ስለ አውሬው ሥራ አስፈፃሚ ከተማ መግለጫ ይሰጣል ።** "ሌላም ሁለተኛ መልአክ፦ አሕዛብን ሁሉ የዝሙትዋን ቍጣ ወይን ጠጅ ያጠጣች ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች፥ ወደቀች እያለ ተከተለው።" ራእይ 14፥8 ። አስተውሉ እነዚህ የመጨረሻው ፍጻሜ ላይ ከሰይጣን መውደቅ ተከትሎ የሚኾኑ ናቸው ። **ሌላኛው ሦስተኛው ሰባኪ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል** ።የአውሬ ቍጥር እንዳይቀበሉ ፣ የተቀበሉት እረፍት እንደማይኖራቸው ፣ ቅዱሳን የኾኑት በመከራው በትዕግሥት የሚያልፉት ድል እንደሚነሱ ፥ ""ሦስተኛም መልአክ ተከተላቸው፥ በታላቅ ድምፅ እንዲህ እያለ፦ ለአውሬውና ለምስሉ የሚሰግድ በግምባሩም ወይም በእጁ ምልክቱን የሚቀበል ማንም ቢኖር፥"ራእይ 14፥9 "ራእይ 14፥8፤9-12። አንባቢ ኾይ ጨኽተ ይሰማል።

በዚህ ስቃይ ውስጥ ከምማቁቅቱ እንዳትሆን ልክ እንዴ ሴቲቱ ሙሽሪት ቤተክርስቲያን ወይም እንደ ዘሯ ቅሬታዋ በስልጣን በአውሬው ላይ ከሚመላለሱት መሃል እንድትሆን እየነገርኩ ነው።የእግዚአብሔር ጥሪ ለኹሉ ነውና። አውሬው ዲያቢሎስ ከምማርካቸው ከሚያስታቸው እንዳትኾን ከተያዝክበት ወጥመድ እንድትወጣ እያሳሰብኩ ነው።ጆሮ ካለህ

አምልጥ። ዛሬ የተተማመንክባት እምነት ተቋም ማምለጫ አይትኾንም። ይኽንን እውነት ከተቀበልክ በሰማዩ አምላክ ፊት ኹን ። ተዘጋጅ የቅድስና ሕይወት ተለማመድ ። በእውቀት በጥበብ በመንፈሳዊ ነገር ዓይኖች ትላልቅ እስከሚኾኑ ድረስ በልግስና የሚሰጠውን ጌታ ተማጸን።

እነዚህ ብርቱዎች የመጨረሻው ማስጠንቀቂያ ከሰጡ በኋላ ፣ አስቀድሞ ኢየሱስ እንደገለጠው ተቀላቅለው ያሉት ስንዴውና እንክርዳዱ ስለዩ፣ ወቅቱ ስደርስ ከዓለም አሰናብታለሁ፤ ፍርድን እሰጣለሁ ፤ አጭዳለሁ ደግሞም በእሳት አቃጥላለሁ እንዳለው ያደርጋል ። በመላእክቱም ያሳጭዳል ።ምድር ፍጻሜዋን ታገኛለች። ተመሳስሎ ከቅዱሳን ጋር የኖሩትም በግልጽ የአውሬውን ቍጥር ተቀብለው ስያመልኩ፣ ታምነው ጨክነው የቆሙት ሲሰው ፣ ኹሉም በግልጽ ጻድቁም ኃጢኡም ስለይ፣ ኢየሱስ ምድር እንዲታጨድ ይፈቅዳል ።ራእይ 14፥[14] አየሁም፥ እነሆም ነጭ ደመና፥ በደመናውም ላይ የሰውን ልጅ የሚመስል ተቀምጦአል፥ በራሱም ላይ የወርቅ አክሊል በእጁም ስለታም ማጭድ ነበረው። … [16] በደመናውም ላይ የተቀመጠው ማጭዱን ወደ ምድር ጣለው ምድርም ታጨደች። ይህች ምድርም ተጠቅልላ ታልፋለች ። የትኛውም አስተማሪ ያከማቸኸው ልሽሽግህ የማይቻልበት ጊዜ ይመጣል ፤ ይህች ምድር ፍርዷን ትቀበላላችሁ ።ጆሮ ያለው ይስማ ።

በግልጽ በግልጥ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ቃልን እናገራለሁ ። በእግዚአብሔር ፍርድ በመጨረሻው በተገለጠው ፍትሕ ቅዱሳን በደስታ ይዘምራሉ ፡-“ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ፥ ሥራህ ታላቅና ድንቅ ነው፤ የአሕዛብ ንጉሥ ሆይ፥ መንገድህ ጻድቅና እውነተኛ ነው፤ ጌታ ሆይ፥ የማይፈራህና ስምህን የማያከብር ማን ነው? አንተ ብቻ ቅዱስ ነህና፥ የጽድቅም ሥራህ ስለ ተገለጠ አሕዛብ ሁሉ ይመጣሉ በፊትህም ይሰግዳሉ እያሉ የእግዚአብሔርን ባሪያ የሙሴን ቅኔና የበጉን ቅኔ ይዘምራሉ።” ራእይ 15፥3-4።አሜን ሃሌ ሉያ።

**3ኛውን መግለጫ ስናጠቃልል ፡-**

በሌሎች መግለጫዎች የመቅደሱ መለካትና በእዚያ የሚሰግዱትን መቍጠር፣ ከ42 ወራት ታላቁ መከራ ቀድሞ እንደሚደረግ አይተናል፤ ራእ.11። በዚህም መግለጫ ላይ በይበልጥ ስለዚህ እውነት ማብራሪያ ይሰጣል ። በምድር ያሉ ቅዱሳን በእግዚአብሔር ፊት በክርስቶስ ውስጥ ኾነው እንደተቀመጡ ጳውሎስ ያስረዳል፤ ኤፌ1። የመቅደሱ መለካት ያሉበት ስፍራ መለካትን ስያሳይ፣ በመቅደሱ የሚሰግዱት መቈጠር አብሮተ እግዚአብሔር ያለበትና ያሉባቸውን ከሌሎች መለየት እንደኾነ አይተናል ። በዚህ መግለጫ ላይ አብሮተ እግዚአብሔር ከባሪያዎቹ ጋር መኾኑ ይታያል ።ይኽም አማኞች ከእርሱ ጋር መኾናቸውን ያስረዳል ። እግዚአብሔር አብሮአቸው የኾነላቸው የተገለጡት የታዩት የእርሱን ባሕርይ ይለብሳሉ ፤በሙላት ። ምክንያቱም የእውነትም የሚያመልኩና ያለ ነቀፌታ በቤቱ በፊቱ ያሉቱ ናቸው ።

ጸሃይ ጽድቅ ነው፤ የመለኮት ባሕርይ የሚያመላክት ነው። በሙላት ለብሰው ያለነቀፌታ የተገኙት ድል የነሱ "አማኞች" ናቸው ። ደግሞም ጨረቃን ረግጣ ነው ያለችው ። ጨረቃ "ጨረቃ ጳጳስ" እንዲሉ የሃሰት ብርሃን የሃሰት ሃይማኖት /አስተማሪ/ ረግጣ ነው የተገለጠችው ። በእርሷ ዘንድ ለሃሰተኛ ስፍራ የላትም። እነዚህ አማኞች ከክብር ወደ ክብር ተሻግረው በመለኮታዊ ሃይል ተሞልተው ስለተገለጡ፣ የሰይጣንን መውደቅና ለጥቅት ጊዜ መፈታት ምክንያት ኾነዋል። በውስጧ የያዘቻቸው ልጆች "ለዲያብሎስ ፍራሃቶች" ናቸው ። ዲያቢሎስ በሴቲቱ መገለጥ ስለወደቀ፤ በውስጧ የያዘችውን ልጅ ለማስጨንገፍ ተጣጣረ። ጌታ ወዳዘጋጀው ስፍራ ወሰዳት፤ አንዳች ነገር ሳያደርግባት እንድትኖር አደረጋት ።ለ42 ወራት **በእንክብካቤ** እንድትኖር አደረጋት።

ሴቲቱ ማርያም ናት ያሉት ፣ ስለ ሴቲቱ በደንብ ጥናት እንዳላደረጉ ያስታውቃል ። የማርያምን የስደትን ታርክ ከቆይታዋ ጊዜ ብቻ ጋር በማነጻጸር ፣ ምንም እንኳን "ማርያም የተሰደደችው 3 ዓመት ተኩል ነው" የሚባለው በራሱ ጥያቄ የሚያስነሳ ብኾንም፣ እነርሱ እንደሚሉት፣ "ነው" ብለን ብንነሳ እንኳን የማርያም ስዴትና የሴቲቱ ሽሽት የሚገናኝ አይደለም ። ምክንያቱም ሴቲቱ የሸሸችው እግዚአብሔር ወደአዘጋጀው ስፍራ **በእንክብካቤ** ለ42 ወራት ለመኖር ስኾን፣ ማርያም ወደ ግብጽ የተሰደደችው "ትርክቱ" እንደሚለው ከኾነ እስከ ግብጽ በስቃይ ወርዳ፣ ከገብጽም መከራ አይሎባት ወደ ኢትዮጵያ እንደወረደች ያትታል [ተአምረ ማርያምን ይመ.] ። ባጠቃላይ ማርያም በሽሽቷ አይደለም እንክብካቤ; እረፍት እንኳን እንዳላገኘች ትርክቱ ያስረዳል ። ታዲያ ይኽ እንዴት ሴቲቱ ማርያም ናት ለማለት ያስደፍራል ? ስቃይና እንክብካቤ ለየቅል የኾኑ ናቸው ። ሽሽት ስለኾነ ብቻ የማይገናኘውን ለማገናኘት መጣር መልካም አይደለም ።

"ሴቲቱ" መባሉ በራሱ ደግሞ አንዲት እንሰትን ያመላክታል ለማለት የሚያስደፍር አይደለም ። ምክንያቱም ባቢሎንም[ከተማዋም] ሴቲቱ ተብላ ተገልጣለች፥ ራእይ 17፥[3] በመንፈስም ወደ በረሀ ወሰደኝ፤ የስድብም ስሞች በሞሉበት፥ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶችም ባሉበት በቀይ አውሬ ላይ አንዲት ሴት ተቀምጣ አየሁ።[4] ሴቲቱም በቀይና በሐምራዊ ልብስ ተጐናጽፋ በወርቅና በከበሩ ድንጋዮች በዕንቁችም ተሸልማ ነበር፥ በእጅዋም የሚያስጸይፍ ነገር የዝሙትዋም ርኵሰት የሞላባትን የወርቅ ጽዋ ያዘች፤[5] በግምባርዋም ምስጢር የሆነ ስም፦ ታላቂቱ ባቢሎን፥ የጋለሞታዎችና የምድር ርኵሰት እናት ተብሎ ተጻፈ።[6] ሴቲቱም በቅዱሳን ደምና በኢየሱስ ምስክሮች ደም ሰክራ አየኋት። ባየኋትም ጊዜ እጅግ ታላቅ ድንቅ አደነቅሁ።... [18] ያየሃትም ሴት በምድር ነገሥታት ላይ የምትነግሥ ታላቂቱ ከተማ ናት። ስለዚህ ሴቲቱ መባሉ አንዲት እንስትን የግድ እንደማይወክል ኹሉ ወንድ ልጁም አንድን አካል **[**ግለሰብን**]** ብቻ የሚያመላክት አይደለም ።

የወለደችው ወንድ ልጅ ለራሷ ከአሕዛብ ማህበረሰብ ስትሸሽ ያበረከተችው ልጇ ነው። “አሕዛብንም ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ልጅ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ልጅዋም ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ።” ራእይ 12፥5። ልጇ አሕዛብ ኹሉ በብረት በትር የሚገዛቸው ስኾን ደግሞም በክብር ወደ ሰማይ የሚነጠቅም ነው። አኹን ልጇ ኢየሱስ እንዳይደለ፣ በታላቁ መከራ ጊዜ ኢየሱስ ከቤተክርስቲያን አለመወለዱ[ወይም ሴቲቱ እስራኤል ዘሥጋ ናት እንደሚሉትም ከእስራኤላውያን እንደማይገኝ የተገለጠ ነው] ።በዚያ በታላቁ መከራ ኢየሱስ መጥቶ አሕዛብን ረግጦ አይነጠቅም።ከመሠረቱ እርሱ አስገኝ እንጂ ከሠራው የሚገኝ አይደለም ። ሴቲቱ የወለደችው ልጅ አሕዛብን የሚገዛና የሚነጠቅ ነው። ይኽም በሌሎች መግለጫዎች እንደተመለከትነው፣ በአሕዛብ ላይ በተሳጣቸው ስልጣን ለ42 ወራት የሚያገለግሉ ፣ኹለት ወይራዎችና ኹለቱ መቅረዞች የተባሉት ድል የነሱ አማኞችን የሚያመላክት ነው ።ጌታ ድል ለሚነሱት ይኽንን ስልጣን እሰጣለሁ ብሏል ድል የነሱ አገልጋዮችን የሚወክል ነው። ምክንያቱም እነኚህ ተወልዶ ወይም ተገኝቶ አሕዛብን ረግጦ አገልግለው ይነጠቃሉ። ኢየሱስ በውኑ በታላቁ መከራ ጊዜ ይኽንን ያደርጋል ? አያደርግም ። ስልጣን በሰጣቸው ባሪያዎች በኵል ይፈጽማል እንጂ።

ሰይጣን ከሰማያዊ ስፍራ መኖሪያ ዳግም ላይገኝ መጣሉ ፣ አማኞችን እንዳይከስ የሚያደርግ ስኾን ለሰማያዊያን ታላቅ ደስታ ነው። በ7ቱ ራሶች [ጥበብ የሚጠቀምባቸው ግብረአበሮቹ] እና በ10ሩ ቀንዶች [ሃይሉን በሚጠቀሚባቸው ግብረአበሮቹ] ምድርንና ባሕርን ያስጨንቃል ።ስለዚህ ለእነዚህ ወዮ ተብሎላቸዋል። ምክንያቱም ዲያቢሎስ ስለተሸነፈ በቍጣ ተሞልቶ ባሕርን [መንግስታትን] እና ምድርን [ሃሰተኛ ሃይማኖት የሚከተሉትን] ያስጨንቃል ፤ይገድላል ።ወዮ ተብሎላቸዋል። በእራሱ ጥቅት ጊዜ እንኳን የራሱን ወገኖቹን ከማስጨነቅ ሌላ የማያውቀው ክፉ ነው። ለራሱ ማህበረሰብ እንኳን አይኾንም። በሌሎች መግለጫዎች እንደተመለከትነው በታላቁ መከራ ጊዜ በሚድኑት ላይ ስልጣን የለውም፤ ወንዶች ልጆች ላይ ጭራሽ አቅም የለውም ፤ ሴቲቱ ደግሞ ትሰወራለች ።ስለዚህም በታላቅ ቍጣ ብወርድም አስፈሪ የሚኾነውን ለአሕዛብ እንጂ ኢየሱስን ለተቀበሉትና ለሚቀበሉት አይደለም ። አዎን ይኽንን አውቀው ድል ነስተው የሚኖሩት አውሬውን ለማሰቃየት ይናፍቃሉ እንጂ አይፈሩም ። የዲያብሎስ ፍራሃቶች ናቸውና።

እግዚአብሔር ሰይጣን ልደርስ በማይችል ስፍራ ላይ ቤተክርስቲያንን [አማኞችን] ለ42 ወራት ሙሉ በእንክብካቤ ሸሽጓታል። ኢየሱስ ዳግመኛ ለኹለተኛ ጊዜ ለምጽአቱ እስኪመጣ ድረስ በሕይወት እዚያው ኾኖ ትጠብቃለች ። እሷን ማግኘት ባለመቻሉ; መለኮታዊ ጠባቆት ባለቤት ስፍራ ላይ ያልተሸሸገችውን፣ የእርሷ ዘር ወይም ልጆች የኾኑትን ልዋጋ ፊቱን ይመልሳል ።

ከዘሯ የቀሩቱን ማለትም አማኝ የኾኑትን ልዋጋ በኹለት መንገድ ሃይሉን ያደራጃል ። አንደኛው የራሱን መንግሥት ይጠቀማል [ከባሕር የወጣ አውሬ] ። ኹለተኛው ሃሰተኛ አስተማሪዎች ነቢያትን ይጠቀማል [ከምድር የወጣ አውሬ]።

ሰይጣን በራሱ መንግስታት ቅዱሳንን ስያስጨንቅ ኖሯል፤ በግሪክ ፣ በሮም ፣በባቢሎን ወዘተ. ። በዚህ በመጨረሻ ውጊያ ላይ ሃይሉን አሟጦ ፍልሚያ ያደርጋል ። ለ42 ወራት በሃይል የሚሠራው አውሬ ፣ከዚህ በፊት በተለያየ መንግስታት በኩል ኾኖ የሠራውን ሃይል ጉልበት ጥበብ በጣምራ በመጠቀም የመጨረሻውን ውጊያ ያደርጋል ።"ያየሁትም አውሬ ነብር ይመስል ነበር፥ እግሮቹም እንደ ድብ እግሮች፥ አፉም እንደ አንበሳ አፍ ነበሩ። ዘንዶውም ኃይሉንና ዙፋኑን ትልቅም ሥልጣን ሰጠው።" ራእይ 13፥2 ። 10 ቀንድ [ሃይል]ና 7 ራሶች [ጠበብ] አለው። ሃይልና ጥበብ የኾኑ ማህበሮች አሉት። ስለዚህም ከዚህ ከአውሬው መንግሥት ጋር፣ ከእርሱ ወካይ፣ ስራ አስፈጻሚ ጋር ማንም ልዋጋ ኾነ ልገዳደረው አይችልም በማለት ፣ ብዙዎች ይቀበላሉ፤ ይሰግዳሉ ። "ለዘንዶውም ሰገዱለት፥ ለአውሬው ሥልጣንን ሰጥቶታልና፤ ለአውሬውም፡- አውሬውን ማን ይመስለዋል፥ እርሱንስ ሊዋጋ ማን ይችላል? እያሉ ሰገዱለት።" ራእይ 13፥4 ። ይኽንን ለመረዳት ዳንኤል ያየውን ራእይ ጋር ማስተያየት ይቻላል [7፣8 ]፤ በዳንኤል ራእይ ስለ አውሬ ትርጓሜ መደበኛ ትርጉም ማጥኛ ያቀረበውን ምስል መመልከት ነገሩን ግልጽ ያደርግልናል ፡-




በቀደም በመቅደሱ ያሉት ተቆጥረው መለየታቸውን አይተናል፤አሕዛብ ልገቡ ያልተፈቀደላቸው የቅዱሳን መቆያ እንደኾነ ተረድተናል ። እነዚህም ሴቲቱ የተባሉት በመቅደሱ እያመለኩ ያሉ አማኞች እንደኾኑ አይተናል ። ይኽ አውሬ ለ42 ወራት ብቻ ይሠራል ። እስከሚገለጥ መንገዱን በስውር እየጠረገ ብኾንም። ይኽ አውሬ መከራ እንዳያገኛቸው ተብለው

ያልተለዩትን ዘሮችኋን/ያልተዘጋጁ አማኞችን/ ልዋጋ ይኸንን ዘዴ ቀየሰው ።በዚህም ብዙ ቅዱሳንን ያገኛቸዋል ያስታቸዋል ያሸንፋቸዋል ።"ቅዱሳንንም ይዋጋ ዘንድ ድልም ያደርጋቸው ዘንድ ተሰጠው፥ በነገድና በወገንም በቋንቋም በሕዝብም ሁሉ ላይ ሥልጣን ተሰጠው።" ራእይ **13፥7**። የቅድሜ መከራ ንጥቀት አስተምህሮ ዓላማም ለዚህ ሽንፈት ማብቃት ነው። በመከራው ጊዜ መከራ የማያገኛትን እንዳታውቁ በማድረግ የራእይ መጽሐፍ ለራሴ ብላችሁ እንዳታነቡ በማድረግ ለጥፋት ያዘጋጃሉ። ይኸንን አውቃችሁ ተለዩ እያልሁ ነው። የእባቡ ትምህርት ነው። እነዚህ ወደተዘጋጀው ስፍራ ያልገቡ ዘሮችኋ ለአሕዛብ በተሰጠው ስፍራ የሚኖሩ ስለኾኑ በ42 ወራት ካለልክ ያሰቃያል ። አያችሁ; የሚዋጋው በታላቁ መከራ ጊዜ እንኳን ቅዱሳንን ነው።ድልም ያደርጋቸዋል ። ያልተዘጋጁ አማኞችን/ቅዱሳንን/ እንኳን ያስታቸዋል፤ ያሸንፋቸዋል ።

ቅዱሳን የዘሯ ቅሬታዎች፣ በተለያየ ነቀፌታ ምክንያት ልሰወሩ ያልቻሉት፣ በትዕግሥት በዚያ በታላቁ መከራ ጊዜ ብጸኑ ይድናሉ። አየህ ቅዱሳን ከመከራው በፊት ሳይነጠቁ በመከራው እንደሚያልፉ !? "ይማረክ ዘንድ ያለው ማንም ቢኖር ወደ ምርኮነት ይሄዳል፤ በሰይፍ የሚገድል ማንም ቢኖር ራሱ በሰይፍ እንዲገደል ይገባዋል። የቅዱሳን ትዕግሥትና እምነት በዚህ ነው።"ራእይ 13፥10 ። በሰይፍ በታላቁ መከራ አልፈው የሚድኑት በመንፈስ የተገረዙ እስራኤላውያን 144 ሺህዎች የተባሉት ቅዱሳን ናቸው ።ጆሮ ያለው ይስማ!

ከሰማይ የተጣለው ሰይጣን የሚዋጋበት ኹለተኛው መንገድ ለሃሰተኛ አስተማሪዎች አቅም በመኾን ነው። እነዚህ ሃሰተኞች የሚጎዱ የማይመስሉ የበግ ቀንድ ያላቸው ነገርግን በመንግሥታቱ ላይ ኾኖ በሚሠራው አውሬ ስልጣን በመቀናጀት እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚሠሩ ናቸው ። ከሰማይ የተጣለው ዘንዶ ለራሱ መንግሥት ሃይሉን ስልጣኑን ይሰጣል ፤ መንግስት ደግሞ ከዘንዶው በተቀበለው ሃይል ለሃሰተኛ አስተማሪዎች አቅም ይኾናል ። በሴምርኔስ ቤተክርስቲያን እንደተመለከትነው ለቤተክርስቲያንቱ ፈተና የኾኑት ሃሰተኛ ወንድሞች አማኝ የሚመስሉና መንግሥት ነበሩ። ሰይጣን በመንግሥት በኩል ኾኖ ለእግዚአብሔር ሕግ የማይመች ሕግ በማውጣት ፣ ቅዱሳንን "ሕግ ተላልፋችኋል" በማለት ለእስር ይዳርጋል ። ለራሱ ሕግ አልመች አልታዘዝ ያሉትን በመለየት ለመቅጣት፣ ምስጥራዊ ቍጥር ይጠቀማል 666 ።ይኽ ቍጥር ለአማኞች መንፈስ ቅዱስ ማህተም ኾኖላቸው ከሌሎች እንደሚለያቸው የሚለይ ስኾን ፣ በእጅ ወይም በግንባር በሰውነት ላይ የሚቀበር ምልክት ነው። ሌላ ምስጢር የለውም። እንግዲህ ይኽ ምልክታቸው ለአባሎቻቸው በሰውነታቸው ውስጥ የሚቀበር እንጂ በቍስ ላይ የሚኾን አይደለም ። አዕምሮ ያለው አውሬው ሃሰተኛ ነቢዩ የሚጠቀመውን ምስጥራዊ ኮድ ይወቀው ፤ይቍጠረውና ይለየው። ምክንያቱም በግ ስለሚመስል የመሸወድ አቅሙ; የሚናቅ አይደለም ። ጆሮ ያለው ይስማ!

ዮሐንስ አውሬው በጥምረት የሚሠሩትን ከተመለከተ በኋላ ፣ የሚደቅቁ ቅዱሳን በታላቁ መከራ ጊዜ እንደሚኖሩ አስተዋለ። የቅዱሳን ትዕግሥት በዚህ ይታወቃል በማለት ቅዱሳን በመከራው አልፈው እንደሚጸድቁ

አሳሰበልን። በዚያ በታላቁ መከራ ኹሉም ቅዱሳን አይስቱም ፤ እንዲሁም በትዕግሥት በመጽናት በመከራው የሚያልፉ ተቆጥረው የማያልቁ እንዳሉ፤ በክብር በሰማይ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ፊት ቀርበው እያሉ ይመለከታቸዋል ፤ በ6ተኛው ማህተም በም.7 እንደተመለከተው ። እነዚህ ቅዱሳን በታላቁ መከራ በምስክርነታቸው ሰማዕት ኾነው ያለፉ ናቸው ። እናም በዙፋኑ ፊት ቀርበው ማንም የማያውቀውን አዲስ ቅኔ ይቀኛሉ። ጌታ በታላቁ መከራ ስለማለፋቸው የሰጠው ውዳሴ ነው። በጉ ከእነርሱ ጋር ኾኖ በጽዮን ተራራ መታየቱ፣ ምድራዊ ቦታን የሚያመላክት አይደለም ።አውዱም እነዚህ ቅዱሳን በአርያም እንደኾኑ ያስታውቃል ። አዎን ጽዮን ሰማያቷ ኢየሩሳሌም በመወከል ተገልጣለች። ምንም እንኳን ሰይጣን በሃይል በቍጣ ብሠራም ቅዱሳንንም ብያስትም ፥ጌታ ተቈጥረው የማያልቁትን ያድናቸዋል ።

እንደሌሎቹም በዚህም መግለጫ ላይ በታላቁ መከራ ጊዜ ወንጌል እንደሚሰበክ ተጨማሪ ግንዛቤ ይሰጣል ።የዘላለሙን ወንጌል በአሕዛብ ላይ ስልጣን የተሰጣቸው ወይራዎችና መቅረዞች ያገለግላሉ ። “በምድርም ለሚኖሩ ለሕዝብም ለነገድም ለቋንቋም ለወገንም ሁሉ ይሰብክ ዘንድ የዘላለም ወንጌል ያለው ሌላ መልአክ ከሰማይ መካከል ሲበር አየሁ፤”ራእይ 14፥6። እነዚህ ሰዎች ንስሐ እንዲገቡ ያስተምራሉ ፤ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ያስተምራሉ ። ታላላቅ ቍጣዎች እንደሚደረጉ ያስታውቃሉ ። በዚያ በታላቁ መከራ በስልጣን የሚያገለግሉትን ሰምተው የሚመለሱ የሚጸኑ ፈተናቸው ይኽ ነው። “የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁት ኢየሱስንም በማመን የሚጸኑት ቅዱሳን ትዕግሥታቸው በዚህ ነው።” ራእይ 14፥12።

አስተውሉ ከመከራው በፊት ወደ ሰማይ ቤተክርስቲያን ስላልተነጠቀች በዚህ እንዲታልፍ እያሳሰበ ነው። በዚያ መከራ ጸንተው በትዕግሥት መከራውን ታግሰው የሚያልፉ ድል በመንሳት መንግስቱን ስወርሱ፣ የሚክዱት ደግሞ ድል ባለመንሳታቸው ከሕይወት መዝገብ ላይ ስማቸው ይደመሰሳል፤ ወደ እሳት ባህርም ይጣላሉ። ምክንያቱም ጀምረው መጨረስ አለባቸው ። ድነው ለመቅረት በጌታ ኾነው እንደጀመሩት መጨረስ አለባቸው ። “ከሰማይም፡- **ከእንግዲህ ወዲህ በጌታ የሚሞቱ ሙታን ብፁዓን ናቸው**። መንፈስ፡- አዎን፥ ከድካማቸው ያርፉ ዘንድ፥ ሥራቸውም ይከተላቸዋል ይላል ብለህ ጻፍ የሚል ድምፅ ሰማሁ።” ራእይ 14፥13። በዚያ በታላቁ መከራ ቅዱሳን ሳይክዱ መስክሮ ሰማዕት መኾን ይገባቸው ነበረና ይኽ ፅድቅ ሥራቸው ይከተላቸዋል፤ እረፍትንም ይሰጣቸዋል ።**የመዳን ዋስትና በድል መጨረስ ነው**። መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው ይኽኑኑ ነው። ጆሮ ያለው ይስማ።

### 1.2.4 አራተኛው መግለጫ

በዚህኛው ካሜራ በዝርዝር የሚገለጹት በመጀመሪያ በጨረፍታ በሌሎች ካሜራዎች የተገለጡ ፍርዶች ናቸው ።" ከምዕራፍ 15፥5 ጀምሮ እስከ ምዕራፍ 16" ። በመጨረሻው ዘመን ሰይጣንም በግልጽ ስሰራ፣በራሱ ሕብረተሰብ ስያሰራ፣

በጉም ከዘሯ በቀሩት ስያናውጥ፣ መላእክቱም ስሳተፉ በሰፊው በሌሎች መግለጫዎች አይተናል ።በዚህም በመጨረሻ ፍርድ ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚያጭድ እንደሚያቃጥል ተገንዝበናል ።በዚህ የምንመለከተው **የእግዚአብሔር ቍጣ ማጭድ በምድር ላይ የተገለጠውን ዝርዝር ሃሳቡን ነው።** "ከዚህ በኋላ አየሁ፥ የምስክርም ድንኳን መቅደስ በሰማይ ተከፈተ፥ሰባቱንም መቅሠፍት የያዙ ሰባቱ መላእክት ከመቅደሱ ወጡ፤ ከተልባ እግርም የተሠራ ጥሩ የጌጥ ልብስ ለበሱ ደረታቸውንም በወርቅ መታጠቂያ ታጠቁ።" ራእ 15 ፥5-6፤8። የእግዚአብሔር መላእክት ከመቅደሱ የወጡት ለማዳን ሳይኾን ለፍርድ ለፍትህ ነው፤ቍጣውን እስከሚጨርሱ ድረስ ተመልሰው አልገቡም፤ቍ.8። በዚህ ክፍል የምናየው በመጨረሻው ዘመን ላይ በእግዚአብሔር መላእክት በኵል ስለሚገለጡ ቍጣ፤ ምድር ከእግዚአብሔር ስለምትቀበለው ፍርድ ነው። በሰይጣን ጥቅት ዘመን ለሰይጣን ማረፍያ መደሰቻ ሳይኾን፣ መጨነቅያ መጥፍያ ነው።በዚህ በብርቱዎች ሃይልን በታጠቁ አገልጋዮች ስያሰቃያቸው ፥በዚህ ደግሞ በቅዱሳን መላእክትን ሰይጣንን ማሰቃየቱን ማሳደዱን መቀጠሉን እንመለከታለን ።መላእክቱ “ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፥ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፤ ወደ ምድር ተጣለ **መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ።**” ራእይ 12፥9 ። ቁጣዎችን በወፍ በረር እንመለከታለን :-

፨ **1ኛው ቍጣ**; ምድር ተመታች ፤“ፊተኛውም ሄዶ ጽዋውን በምድር ውስጥ አፈሰሰ፤ የአውሬውም ምልክት ባለባቸው ለምስሉም በሚሰግዱ ሰዎች ክፉኛ የሚነዘንዝ ቍስል ሆነባቸው።” ራእይ 16፥2 ። በዚህ ፍርድ የሚሞቱት የአውሬውን ምልክት የተቀበሉ የካዱ ናቸው ። "ብልጽግና ይኾናል" ስሉ ስቃይ ይኾናል። ይኽ ፍርድ ስለኾነ ቀጥታ የሰዎችን ሕይወት የሚጎዳ ነው።ከላይ እንዳየነው እንደ ማስጠንቀቂያ መለከቶች ተፈጥሮን ብቻ አይመታም።ደግሞም ⅓ኛውን ብቻም የሚመታ አይደለም ። በ3 ዓመት ከ6 ወር የሚገልጽ ፍርድ ነው።

፨ **2ኛው ቍጣ**; ባሕር ተመታች፤“ሁለተኛውም ጽዋውን በባሕር ውስጥ አፈሰሰ፤ እንደ ሞተም ሰው ደም ሆነ፥ በባሕርም ከሚኖሩት ሕይወት ያለበት ነፍስ ሁሉ ሞተ።”ራእይ 16፥3 ። ባሕርይ መዝናኛና የመንፈስ ማሪኪያ ስፍራ ሳትኾን የሚትገማ ትኾናለች።

፨ **3ኛው ቍጣ**;ወንዞች ተመቱ፤ "ሦስተኛውም ጽዋውን በወንዞችና በውኃ ምንጮች ውስጥ አፈሰሰ፤ እነርሱም ደም ሆኑ። … **የቅዱሳንና የነቢያትን ደም ስላፈሰሱ ደምን ደግሞ አጠጥተሃቸዋል**፥ የሚገባቸው ነውና ብሎ ሲናገር ሰማሁ።"ራእ 16፥4-6። ጌታ ፍርዱን በመግለጡ በመጀመሪያው ካሜራ የተመለከትናቸው ፍርድን ይጠይቁ የነበሩ ቅዱሳን ምላሽ በማግኘታቸው ደስታቸውን በምስጋና ይገልፃሉ ።የሞቱት የተሰዉት ቅዱሳን ስለ ደማቸው ፍርድን ይማጸናሉና ።

“ከመሰዊያውም፡- አዎን፥ ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ፥ ፍርዶችህ እውነትና ጽድቅ ናቸው ብሎ ሲናገር ሰማሁ።” ራእይ 16፥7 ።

፨ **4ኛው ቊጣ**; ፀሐይ ተመታች፤“አራተኛውም ጽዋውን በፀሐይ ላይ አፈሰሰ፤ ሰዎችንም በእሳት ልታቃጥል ተሰጣት።” ራእይ 16፥8 ።በዚህ ፍርድ ላይ ፀሐይ ጨለማ ሳትኾን የሚትኾነው ወይም ⅓ኛ ብቻ ሳይኾን የሚጠቃው እንደ ማስጠንቀቂያዎቹ፣ ሙሉ በሙሉ ፀሐይ ለሕይወት አስፈሪ በመኾን ታቃጥላለች ፤ ቤት ልከለክል አይችልም በሙቀት ግለት ትገድላለች።

፨ **5ኛው ቊጣ**;ሃያሏ ከተማ ባቢሎን ትመታለች፤; “አምስተኛውም ጽዋውን በአውሬው ዙፋን ላይ አፈሰሰ፤ መንግሥቱም ጨለማ ሆነች ከስቃይም የተነሳ መላሶቻቸውን ያኙኩ ነበር፥”ራእይ 16፥10 ። ከደረሰባቸው ስቃይ የተነሳ ጥርሳቸውን ያኙካሉ ማለትም ንስሐ አልገቡም ብቻል ምላሽ ለመስጠት ይዘጋጃሉ ። “ከስቃያቸውና ከቍስላቸውም የተነሳ የሰማይን አምላክ ተሳደቡ፥ ከስራቸውም ንስሐ አልገቡም።” ራእይ 16፥11

፨ **6ኛው ቊጣ;** የሚያርፈው በሰይጣን አገልጋዮች ነገስታት ሃያላን ሃገራት የዘንዶው ሥራ አስፈጻሚዎች ላይ ነው“ስድስተኛውም ጽዋውን በታላቁ ወንዝ በኤፍራጥስ ላይ አፈሰሰ፤ ከፀሐይም መውጫ ለሚመጡ ነገሥታት መንገድ እንዲሰናዳላቸው ውኃው ደረቀ።” ራእይ 16፥12። እነዚህ የፖለቲካ ሃያላን ሃገራት ስሙቱ፣ ሰይጣን በግልጽ ጦርነት ለማድረግ ሃይልን ለመሰብሰብ ሌሎችን ሃገራት ነገስታትንም ይዞ ይወጣል፤፣“ከዘንዶውም አፍና ከአውሬው አፍ ከሐሰተኛውም ነቢይ አፍ ጓጉንቸሮች የሚመስሉ ሦስት ርኵሳን መናፍስት ሲወጡ አየሁ፤” ራእይ 16፥13 ። የርኩሳን መናፍስት ራስ የኾኑና ቀንዶቹ ሥራው አስፈፃሚ የፖለቲካ ሃያል ሃገራት በተደጋጋሚ ስለተሙቱ፣ የመጨረሻውን ሃይሉን አሟጦ የመጨረሻውን ጦርነት ለማድረግ ወደ ዓለም ነገስታት ይወጣል ። “**ምልክት እያደረጉ የአጋንንት መናፍስት ናቸውና**፥ በታላቁም ሁሉን በሚገዛ በእግዚአብሔር ቀን ወደ ሚሆነው ጦር እንዲያስከትቱአቸው ወደ ዓለም ሁሉ ነገሥታት ይወጣሉ።” ራእይ 16፥14 ። አንድ ላይ አንድ ኾነው የዓለም ነገስታት በጉን ለመዋጋት ይወጣሉ።“በዕብራይስጥም አርማጌዶን ወደሚባል ስፍራ አስከተቱአቸው።”ራእይ 16፥16 ። በጉን መውጋት ወይም ኢየሱስን መውጋት በኢየሱስ ያሉትን የእርሱን ማህበረሰብን መውጋት ማለት ነው።

ስለዚህም አንባቢ ያስተውል ፣“እነሆ፥ እንደ ሌባ ሆኜ እመጣለሁ፤ ራቁቱን እንዳይሄድ እፍረቱንም እንዳያዩ ነቅቶ ልብሱን የሚጠብቅ ብፁዕ ነው።” ራእይ 16፥15 ።

፨ **በ7ኛው ቊጣ**; የመጨረሻ ፍርድ በዓለም ላይ፣"ሰባተኛውም ጽዋውን በአየር ውስጥ አፈሰሰ፤ ከመቅደሱም ውስጥ፦ ተፈጽሞአል የሚል ታላቅ ድምጽ ከዙፋኑ ወጣ።"... ታላቂቱም ከተማ በሦስት ተከፋፈለች፥ የአሕዛብም ከተማዎች ወደቁ። ታላቂቱም ባቢሎን የብርቱ ቍጣው ወይን ጠጅ የሞላበትን ጽዋ እንዲሰጣት በእግዚአብሔር ፊት ታሰበች። ደሴቶችም ሁሉ ሸሹ ተራራዎችም አልተገኙም። በሚዛንም አንድ ታላንት የሚያህል ታላቅ በረዶ በሰዎች ላይ ከሰማይ ወረደባቸው፤ ሰዎቹም ከበረዶው መቅሰፍት የተነሳ እግዚአብሔርን ተሳደቡ፥ መቅሰፍቱ እጅግ ታላቅ ነውና።" ራእ 16፥19-21 ። በዚህ ፍርድ ሰይጣን በጉን ለመውጋት የሰበሰባቸው እንዳልነበረ ስኾኑ ፣ ታላቅ የበረዶ ግግር ዝናብ ምድርን እንዳልነበረች ያደርጋል ።በዚህ 7ቱ ፍርዶች ይፈጸማሉ ።

**አራተኛው መግለጫ ስናጠቃልል ፦**

ከላይ ወደታች በተቀረጸ ካሜራ ብለን በምሳሌ በተመለከትነው በቊ.3 እይታ ላይ ዮሐንስ በሰይጣን መውደቅ ፣በቤተክርስቲያን በሙላት በፍጹምነት መገለጥ፣በብርቱዎች መወለድ እንደጀመረ አይተናል። ራእ12። እነዚህም ክስተቶች የመጨረሻው መጨረሻ ሰዓት የሚኾኑ ለዓለም ፍጻሜ 3ዓመት ከ6ወር ስቀር የሚኾኑ እንደኾኑ ተገንዝበናል ።ይኸኛው ቊጣም በዚህ ጊዜ እንደሚጀመር የእግዚአብሔር ፍርድ ከቅዱሳን መታተም በኋላ እንደሚጀመር ፣ የምድር ማጭድ የተላከው ቅዱሳን የታመኑቱ ከተለዩ በኋላ እንደኾነ ከቃሉ መገንዘብ ይኖርብናል ። ለታላቁ መከራ የምጥ ጣዕር ጅማሮ የሚኾኑ መከራና ማስጠንቀቂያዎችን ፣ ከታላቁ መከራ ጋር ደባልቄን መረዳት የለብንም ።

በዚህኛው መግለጫ በሰፊው ስለ እግዚአብሔር ፍርድ ስያስረዳ፣የፍርዱ ጊዜ በታላቁ መከራ [በ42 ወራት] ውስጥ የሚኾን ነው። ከእግዚአብሔር ፍርድ የተነሳ አሕዛብ ስሳደቡ ቅዱሳን ስደሰቱ፣የቅዱሳን የፍትህ ጥያቄአቸው ስለተመለሰላቸው ስያመሰግኑ ይታያል ።ደግሞም እግዚአብሔር ትኩረት አድርጎ በመላእክቱ ፍርዱን ስያስፈጽም ያሳያል ። በፍርዱ ወደ ምድር እንደ ጣሉት እስከወዲያኛው ወደ ጥልቁ እንዲያወርዱ ያደርጋል ። ሰይጣን ሙሉ ኃይሉን ሰጥተዋት የሚትጠቀመውን ሃያሏን ሃገር ፣ ነግሳ እንደማትቀር በፍርዱ እንደሚጥላት ያስረዳል ። በእርግጥ ስለ ዘንደው ሥራ አስፈፃሚ ሃያሏ ሃገር በምሳሌ ባቢሎን የተባለችው መውደቅ፣ [በ3ኛው] ላይ መውደቋን ስያበስር አይተናል ።ይኽም ሰይጣን በሃያሏ ሃገር ኾኖ እንደሚሠራ ያስረዳል ። ሃያሏ ሃገርም በመጨረሻም የተጣለች ከተማ እንደሚትኾን ያስረዳል ። ሰይጣን የባቢሎን ፣የግሪክ ፣ የመዴና፣ የሮም መንግሥት አማኞችን ለማሰቃየት እንደተጠቀመ ታርክም መጽሐፍ ቅዱስም ይመሰክራል ።እንደዚሁ ደግሞ በአኹኑ ሰዓት USA እየተጠቀመ እንዳለ እናስተውላለን ። ነገስታቱ በእርዳታ ሰበብ ሕጋቸውን እንዲቀበሉ ሃይልና ጥበብ እንደሚጠቀሙ ይታወቃል ። ሴቲቱ ብትገለጥ አኹን በስውር በሃይልና በጥበብ የሚትሠራው ታላቅ ሃገር ፣ዘንዶው ከሰጠው ስልጣን የተነሳ ስራውን የሚታስፈጽም ትኾናለች ብንል ግምት አይኾነብንም። ምክንያቱም ዛሬ ላይ ሴቱቲ እስከሚትገለጥና እስከሚትሰወር ድረስ በስውር ይሠራል ፤ጥንትም እንደሚሠራ። ይህቺ ከተማ

ባቢሎን ተብላለች ብንል በመጨረሻው ዘመን እንዳለን ሰዎች ስህተት አይኾነብንም። ነገርግን ግን ራእዩን ሃሳብ ኹሉም እሺ የሚልላት ሃያል ሃገር እንዳለ እና እንደሚትወድቅ ተረድተን ብንዘጋ መልካም ነው። ይኹን እንጂ ራእዩ የተጻፈው ሃሳቡን ለመረዳት ብቻ ሳይኾን የሚኾነውን እንዲናውቀው ስለኾነ መመርመራችን መልካም ነው። አዎን ከኾነ ወይም አይደለም ከኾነም የውይይት ጭብጣችን ከቃሉ ሃሳብ የተፋታ ልኾን አይገባም ። በቃሉ ሃሳብ ከተስማማን በቂ ነው።

## 1.2.5 አምስተኛው መግለጫ

እስካሁን የእግዚአብሔርን ማስጠንቀቂያ ቍጣ ፣ የታተሙ ቅዱሳን የሚያልፉበት ሁኔታ የሰይጣን መውደቅና መንፈራፈርን ተመልክተናል ። **በዚህኛው እይታ ሰፊ ማብራሪያ የሚሰጠው የሰይጣን ሃሳብ አስፈፃሚ ከተማ ስለኾነች ስለ ሃያሏ ሃገር ነው።** ስለምደርስባት ፍርድና ያቺን ከተማ ሃገር እንዲናስተውል መግለጫ ይሰጣል ። ከምዕራፍ 17 እስከ 19፥10 ድረስ በሰፊው ያትታል ። "ሰባቱንም ጽዋዎች ከያዙ ከሰባቱ መላእክት አንዱ መጥቶ፦ ና በብዙም ውኃዎች ላይ የተቀመጠችውን የታላቂቱን ጋለሞታ ፍርድ አሳይሃለሁ፤ ... በመንፈስም ወደ በረሀ ወሰደኝ፤ የስድብም ስሞች በሞሉበት፥ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶችም ባሉበት በቀይ አውሬ ላይ አንዲት ሴት ተቀምጣ አየሁ። ... ያየሃትም ሴት በምድር ነገሥታት ላይ የምትነግሥ ታላቂቱ ከተማ ናት።" ራእ 17። ይህቺ የሚትሠራው በአስማት ነው ።ብዙዎችንም ታስታለች።ትማርካለች። ራእዩ ስለ ሴቲቱ ማንነትና ስለተቀመጠችበት አውሬ 7ራሶችና 10 ቀንዶች ማብራሪያ ይሰጣል ። እስካሁን ስንመለከት በሌሎች መግለጫዎች ዘንዶው 7ራሶችና 10 ቀንዶች እንዳሉት ተመልክተን ነበር። በዚህ መግለጫ ላይ ደግሞ ስለእነዚህ ነገሮች ትርጓሜ ይሰጣል ።“መልአኩም አለኝ፦ የምትደነቅ ስለ ምንድር ነው? የሴቲቱን ምስጢርና የሚሸከማትን፥ ሰባት ራሶችና አስር ቀንዶች ያሉትን የአውሬውን ምስጢር እኔ እነግርሃለሁ።” ራእይ 17፥7።

7 ራሶችና 10 ቀንዶች ስላሉት አውሬው እንዲህ ይለናል ፦ “ያየኸው አውሬ አስቀድሞ ነበረ፥ አሁንም የለም፥ ከጥልቁም ይወጣ ዘንድ አለው፥ ወደ ጥፋትም ይሄዳል፤ ስሞቻቸውም ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ በሕይወት መጽሐፍ ያልተጻፉ በምድር የሚኖሩ አውሬው አስቀድሞ እንደነበረ አሁንም እንደሌለ፥ ነገር ግን እንዳለ ሲያዩ ያደንቃሉ።”ራእይ 17፥8። ይኸ አውሬ ከሰማይ የተጣለው ዘንዶ አይደለም። መጽሐፉ ከጥልቁ የሚወጣ ነው ይለናል ። ስለዚህም ከሰማይ የተጣለው ኮከብ በጥልቁ የታሠረውን የመፍታት ስልጣን እንደተሰጠው አይተናል “አምስተኛውም መልአክ ነፋ፤ ከሰማይም ወደ ምድር ወድቆ የነበረ ኮከብ አየሁ፥ የጥልቁም ጕድጓድ መክፈቻ ተሰጠው።”ራእይ **9፥1** ። ይኸ አውሬ "አኹን የሌለ በኋላ ግን የሚመጣ ነው"፣ "አኹን የለም" መባሉ አውሬው በጥልቁ ታስሮ መክረሙን ስገልጽ ፣ ከጥልቁ መውጣቱ "መምጣቱን ይገልጻል "። እናም ይኸ አውሬ እንዳለ ስመለከቱ ይደነቃሉ ። መገረማቸው ናፍቆታቸውን ይገልጻል ። ደግሞም የእርሱ

ማህበረሰቡ ስለኾኑ ያውቁታል ማለት ነው። የአሕዛብ ማህበረሰቦች በዚያ ልክ የሚያውቁ ከኾኑ፣ አውሬው በጥልቁ ከመኾኑ በፊት ከእነርሱ ጋር ይሰራ ነበር ማለት ነው። ስለ ጥልቁ ምን አስባችሁ ?

በመጽሐፍ ሰይጣን ከተያዘ ወደ ጥልቁ በእግዚአብሔር ሃይል እንደሚወረወሩ ያስረዳል ።ማለትም ከምጽአት በፊት ።

ሉቃስ 8፥[30]" ኢየሱስም፦ ስምህ ማን ነው? ብሎ ጠየቀው። እርሱም ብዙዎች አጋንንት ገብተውበት ነበርና፦ ሌጌዎን አለው።[31] ወደ ጥልቁም ሊሄዱ እንዳያዝቸው ለመኑት።" አውሬው አንድና ብቻና ብቻ አይደለም ። በዚህ ሰውየው ላይ የገባውን ብንመለከት በቊጥር ብዙ ናቸው ። የሰይጣን ልመናም ወደ ጥልቁ እንዳይከት ነው። ምክንያቱም አገልግሎታቸው ይቆማል ። በዚህ ክፉ መንፈስ የሚመሩም የራሳቸውን 'ጌታ' ስጠፉ ያውቃሉ ። ከጥልቁ የሚወጣውም አውሬ ወደ ጥልቁ ስለተላከ፣ ከዚህ በፊት ሕብረት ያደረጉት ማህበረሰቦች ያውቁታል ። በመጥፋቱ ሳያዝኑ አይቀሩም ። በሰማይ ስፍራ ኾኖ አማኞችን የሚከሳቸው ከሳሽ ወደ ምድር ስጣል፣ በጥልቁ በተለያየ ጊዜ የታሠሩትን ይፈታል ማለት ነው።

ስለዚህም ሴቲቱ በዚህ አውሬ ላይ የተቀመጠች ናት የሚለውን መያዝ እንችላለን ። ደግሞም አውሬው ከታሠረበት የሚፈታ ነው የሚለውን መያዝ መረዳታችንን ከፍ ያደርግልናል ።ስለ አውሬው ለማወቅ ጥበብ ያለው አዕምሮን ይጠይቃል ።“ጥበብ ያለው አእምሮ በዚህ ነው።" እንደሚል ። ራእዩ ስለ አውሬ አኹንም ሰፊ መግለጫ ይሰጠናል ፦

".. ሰባቱ ራሶች ሴቲቱ የተቀመጠችባቸው ሰባት ተራራዎች ናቸው፥” ራእይ 17፥9፤ ሰባት ተራራዎች ደግሞ ሰባት ነገስታት ናቸው። “ሰባት ነገሥታት ደግሞ ናቸው፤ አምስቱ ወድቀዋል አንዱም አለ፥ የቀረውም ገና አልመጣም፤ ሲመጣም፥ ጥቂት ጊዜ ሊቆይ ይገባዋል።” ራእይ 17፥10 ። በዚህም በዚህ ክፍል የተገለጸው 7 ቊጥር የሚሰጠው ትርጓሜ [ከሙሉነት ከፍጹምነት] አንፃር እንዳልቀረበ ያስረዳል ።

※7 ራሶች =7 ተራራዎች ናቸው ፣

※7 ተራራዎች = 7 ነገስታት ናቸው ።

ስለዚህም እነዚህ 7 ራሶች አውሬው የሚጠቀማቸው ነገስታት እንደኾኑ እንጂ በአንድ ዘመን /ጊዜ/ የሚያገለግሉ 7 ነገስታት ናቸው ማለት አይደለም ።በተለያየ ጊዜ በተለያየ ዘመን ይጠቀማቸው የነበራቸውን 7 ሃያላን ነገስታትን የሚያመላክቱ ናቸው ። ምክንያቱም 7ቱ ነገስታት አውሬው ጥበቡን የሚጠቀሙባቸው ሃያላን ነገስታት ናቸው ። ደግሞም ከሰባቱ ነገሥታት **"..** አምስቱ ወድቀዋል አንዱም አለ፥ የቀረውም ገና አልመጣም፤ ሲመጣም፥ ጥቂት ጊዜ ሊቆይ ይገባዋል።” ራእይ 17፥10። ዮሐንስ ራእዩን በሚመለከትበት ጊዜ ከ7ቱ ነገስታት አራቶቹ ነግሰው አገልግለው ውድቀው የቀሩ ናቸው ።ያገለገሉ ናቸው ።አገልግለው ያለፉ ናቸው ። ደግሞም "አንዱም አለ"እንደሚል ዮሐንስ ራእዩን በሚመለከትበት ጊዜ እያገለገለች ያለች "ራስ" አለች። በሰዓቱ የአውሬ ራስ ኾኖ የሚታገለግለው "ሮም" እንደኾነች ይታወቃል ። ደግሞም ከ7ቱ ራሶች 3ቱ ግና

የሚመጣ ነው በማለት፤ ዮሐንስ ራእዩን ከተመለከተበት ጊዜ በኋላ የሚነግሡ አውሬውን የሚያገለግል ነገስታት እንደኾኑ ያስረዳል። መጽሐፉ ይኽንን ለማወቅ ጥበብ ይጠይቃል ይለናል ። ዮሐንስ ራእዩን ከተመለከተው 95 ዓ.ም. ጀምሮ 2000 ዓመታት ብሎ 2 ሚሊኒየም ተቆጥሯል ። የቀሩትን 3 ነገስታትን ለማወቅ በውነት መጽሐፉ እንደሚል ጥበብን ይጠይቃል ። እስከዚህ ባለው ዓመታት ነገስታቱ አልተነሱም ? ስንት ቀርተው ይኹን !? በነገራችን ላይ ባቢሎን ተብላ የተመሠለችው ከስሶቱ አንደኛዋ ናት። ነገርግን የቀሩት 3 ነገስታት እንደሌሎቹ [5ቱ ነገስታት] ብዙም አይቆዩም ፤ለጥቅት ጊዜ አገልግለው ይወድቃሉ ። ይኽ ስለ አውሬው ማንነትና አሠራር አጠቃላይ መግለጫ የሚሰጥ ነው። አኹን ከጥልቁ ስለሚወጣው አውሬ መረዳታችንን እንቀጥል ፦

**"**የነበረውና የሌለውም አውሬ ራሱ ደግሞ ስምንተኛው ነው ከሰባቱም አንዱ ነው፥ ወደ ጥፋትም ይሄዳል።" ራእይ **17፥11**

ይኽ አውሬ አንደኛ ከጥልቁ የሚወጣ ነው ብለናል፤ ኹለተኛ አስቀድሞ የሚታወቅና አገልግሎ ያለፈ ነው ብለናል። ከሰባቱ ራሶች አንደኛው ነው በማለት መጽሐፍ ይገልጻል ።ማለትም ከዚህ በፊት ከወደቁት ከ4ቱ ነገስታት ጋር የሠራ ያገለገለ ነው ማለት ነው። ስለዚህም አገልግለው ወድቀው ከነበሩት ፣ጥንት ከ4ቱ ነገስታት ጋር ከሠራው አንደኛው አውሬ 8ተኛ ኾኖ በመጨረሻው ዘመን ላይ ይሠራል ማለት ነው።ስለ **8**ተኛው ራስ ስናገር **7**ተኛውን ራስ ከወደቀ በኋላ እንደሚመጣ አይገልጽም ። እንደ በፊቱ ከጥልቁ ወጥቶ የራሱን አገልጋይ ይዞ ወደውጊያ ይገባል ይለናል ።ያውም ለመጥፊያው ውጊያ ። እነዚህ አውሬ የተባሉት ጋኔኖች የየራሳቸው ጥበብ ያለባቸው ስኾኑ ለአንድ ዓላማ በተለያየ ዘዴ ባደረቧቸው ነገስታት ሥራቸውን ይፈጽማሉ ። እነዚህ ነገስታት መንግስታት ናቸው ። [ስለእነዚህ ለማወቅ የዳንኤል መጽሐፍ ያንብቡ]። ስለ አውሬው ራስ [ነገስታት] ተመለከትን ደግሞም ከብዙ ጌኔኖች የተኛው እንደኾነ ማንነቱን [ከጥልቁ የሚፈታ] መኾኑን ተገናዘብን ።አኹን ደግሞ ስለ ቀንዱ እንመለከታለን ፦

**"**ያየሃቸውም አስሩ ቀንዶች ገና መንግሥትን ያልተቀበሉ አስር ነገሥታት ናቸው፥ ዳሩ ግን ከአውሬው ጋር ለአንድ ሰዓት እንደ ነገሥታት ሥልጣንን ይቀበላሉ።" ራእይ **17፥12** ።

10ሩ ቀንዶችም መግስትን አልተቀበሉም ወይም ራስ አልኾኑም፤ "ገና" ናቸው ። እነዚህ ለጥቅት ጊዜ ራስ በመኾን ያገለግላሉ ። ከዚህ የምንረዳው ቀንዶቹም መንግስታት እንደኾኑ ነው። ነገርግን በሃይል እንደ "ራሶቹ" ያልኾኑ መንግስታት ናቸው ። ራሶቹ የወደቁና የሚነሱ የሚመጡ ብለን በተለያየ ጊዜ ያሉት ነገስታትን እንደሚያመላክቱ አይተናል ። 10 ቀንዶችን ግን እንዲያ ለማለት ራእዩ አያስደፍርም ። በመጨረሻ ዘመን ለሚያገለግለው ራስ አቅም የሚኾኑ ቀንዶች እንደኾኑ ብቻ ያስረዳል ። [በ3ተኛው መግለጫ ላይ አንደኛው "ራስ" ከራሶቹ ልወድቅ ደርሶ የሚያገግም እንደኾነ

አይተናል ። "ከራሶቹም ለሞት እንደ ታረደ ሆኖ አንዱን አየሁ፥ ለሞቱ የሆነውም ቍስል ተፈወሰ። ምድርም ሁሉ አውሬውን እየተከተለ ተደነቀ፥" ራእይ 13፥3 ። ይኽም በቃ ስልጣኗ ተገፏል ማንም አይፈራትም ጊዜዋ አብቅቷል ስባል አገግማ እንደሚታስደንቅ ያስረዳል ። ከሶስቱ ራሶች 7ተኛው ራስ የሚኾነው የሚያመላክት ነው]። ስለዚህም እነዚህ መንግስታት ከጥልቁ ከሚወጣው አውሬ ጋር አንድ ሃሳብ ስላላቸው ያላቸውን ኹሉንም አውሬው ለማገልገል ይጠቀማሉ ። ለአውሬው ይሰጣሉ። ይኽንን የሚያደርጉት የመጨረሻውን ውጊያ ከበጉ ጋር ለማድረግ ነው።

"እነዚህ በጉን ይወጋሉ፤ በጉም የጌቶች ጌታና የነገሥታት ንጉሥ ስለ ሆነ እነርሱን ድል ይነሣል፥ ከእርሱም ጋር ያሉ የተጠሩና የተመረጡ የታመኑም ደግሞ ድል ይነሣሉ።" ራእይ 17፥14 ።

አኹን ስለ ሴቲቱ ለመረዳት እንሞክራለን ። ሴቲቱ በውኃዎች [ብዙ አሕዛብ] ላይ የተቀመጠች ደግሞም በአውሬውም ላይም የተቀመጠች ናት ። በሕዝብ ላይ መቀመጧ መሰልጠኗን ስያመለክት፣ በአውሬው ላይ መቀመጧ በእርሱ ስልጣን መሥራቷን ይገልጻል፤ የሰይጣን ዙፋን ያለባት መኾኗን ያመላክታል ።ይኽቺ ሴት ታላቅ ከተማ ናት።"ያየሃትም ሴት በምድር ነገሥታት ላይ የምትነግሥ ታላቂቱ ከተማ ናት።" ራእይ 17፥18። በጉን መዋጋት ማለት ተከታዮችን ማሳደድ ማለት ነው ፤ ሐዋ 9። በመጨረሻም በዚህች ራስ ላይ ሌሎችም [ቀንዶች] ተነሳስተው እንዲጥሏት እግዚአብሔር ያደርጋል ። ስለተሸነፉ እርስበእርስ ይዋጋሉ ።የሰይጣን ዙፋን ያለባትን ማንም አይችሏትም ያሏትን ያቃጥላሉ፤ እንዳልነበረች ያደርጓታል ። "ያየኃቸውም አስር ቀንዶችና አውሬው ጋለሞታይቱን ይጣላሉ፤ ባዶዋንና ራቁትዋንም ያደርጓታል፥ ሥጋዋንም ይበላሉ፥ በእሳትም ያቃጥሉአታል።" ራእይ 17፥16። ም.18 ሙሉ ስለዚህች ታላቅ ከተማ ውድማ መኾንን ያውጃል ። ያንብቡ።

ከዚያም የብዙዎች የቅዱሳን ደም ስለፈሰሰባት በዚህች ከተማ፤ ቅዱሳን በመውደቋ ደስታቸውን ይገልፃሉ ።ራእ 19፥1-10። ከዚህ እርኩሰት ከተማ ውድቀት በኋላ ፣አምላካችን በክብር ስለነገሰ ምድር የመጨረሻውን ፍርዷን ስላገኘች፣ የደስታ የግንኙነት ታላቅ እራት ለሙሽሪት ቤተክርስቲያን ይደረጋል ፣"**ከዚህ በኋላ በሰማይ፡- ሃሌ ሉያ፤ በዝሙትዋ ምድርን ያጠፋችይቱን ታላቂቱን ጋለሞታ ስለ ፈረደባት፥ የባሪያዎቹንም ደም ከእጅዋ ስለ ተበቀለ፥ ፍርዶቹ እውነትና ጽድቅ ናቸውና ማዳንና ክብር ኃይልም የአምላካችን ነው ብሎ ሲናገር እንደ ብዙ ሕዝብ ታላቅ ድምፅ ያለ ድምፅን ሰማሁ።... የበጉ ሰርግ ስለ ደረሰ ሚስቱም ራስዋን ስላዘጋጀች ደስ ይበለን ሐሤትም እናድርግ ክብርንም ለእርሱ እናቅርብ።**" ራእ 19፥1-7 ። እንግዲህ ይህ ሰርግ ከመከራው ከመጨረሻው ፍርድ በኋላ ከ1260 ቀን ስቃይ መከራ በኋላ ለቅዱሳን እንደሚደረግ ይረዷል፤ አስተውሉ ።የሰይጣንን ሃሳብ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ከፍ ያለውን ነገር ኹሉን እናፈርሳለን ። ደግሞም ሴቲቱ

የተባለችው ከተማን መወከሏ:- የምዕራፍ 12 ሴቲቱ በግርድፉ የግድ አንዲት እንስትን ያመላክታል እንዳንል ይረዳናል ። መጽሐፉ በመጽሐፉ መንፈስ ካነበብን መረዳታችን ወደ እውነት ኹሉ መድረሳችን አይቀርም ።

### 1.2.6 ስድስተኛው መግለጫ

ከ3ኛው እስከ 5ኛው እይታ ያሉቱ የሚያሳዩት ትኩረት ያደረጉት ታላቁን መከራ ጊዜ ስኾን ከ1ኛው እስከ የ2ኛው መግለጫ ያለው ግን ዮሐንስ ራዕዩን ካየበት ጊዜ አንስቶ ያለው ክስተት የሚያሳይ ነው፤ትኩረታቸውን የተለያየ ብኾንም [ይኾን ያለውን] ዮሐንስ ራእይ ከተመለከተበት ጊዜ አንስቶ ያለውን የሚገልጹ መኾናቸውን መገንዘብ እንችላለን ። በዚህኛው እይታ ጠቅለል ያለ አጠቃላይ እይታ ስለ መጨረሻው ዘመን እንደሚሰጥ የምንመለከት ይኾናል:-

፨ሰማይ ተከፍቶ ዮሐንስ አየሁ ስል አንደኛው እይታ ጨርሶ፣ በልዩ መንገድ ሌላ ማየት እንደጀመረ እናስተውላለን ፤ደግሞም ከምስጋናዎች ከማብቅያዎች በኋላ መጀመሩ ዮሐንስ በሚያይበት እንድናይ ይረዳናል ፤“ሰማይም ተከፍቶ አየሁ፥ እነሆም አምባላይ ፈረስ፥ የተቀመጠበትም የታመነና እውነተኛ ይባላል፥ በጽድቅም ይፈርዳል ይዋጋልም።” ራእይ 19፥11። በዚህ ሰማይ መከፈት ከአጠቃላይ መግለጫ አንደኛው ስለ ክርስቶስ ነው።ስለ ማንነቱ ነው። እስካሁንም ወደፊትም ድል አድራጊ ነውና በነጭ ፈረስ ተቀምጧል ፤ በአሕዛብ ላይ ይፈርዳል ፤ ከእይታውም የተሰውረ ነገር የለም። ኹሉንም ያውቃል ። በማንነቱም ከአብ ጋር እኩል የኾነ መለኮት ነው፥“በልብሱና በጭኑም የተጻፈበት:- የነገሥታት ንጉሥና የጌታዎች ጌታ የሚል ስም አለው።”ራእይ 19፥16 ። በአምላክነቱ እርግጠኛ ኹን።

፨ ሌላኛው መልእክት ከአጠቃላዩ እይታ፣ በዘንዶው ሕብረተሰብ የተዘጋጀ እራት ነው፤“አንድም መልአክ በፀሐይ ውስጥ ቆሞ አየሁ፥ በሰማይም መካከል ለሚበሩ ወፎች ሁሉ:- መጥታችሁ የነገሥታትን ሥጋና የሻለቃዎችን ሥጋ የብርቱዎችንም ሥጋ የፈረሶችንም በእነርሱም የተቀመጡትን ሥጋ የጌታዎችንና የባሪያዎችንም የታናናሾችንና የታላላቆችንም ሁሉ ሥጋ እንድትበሉ ወደ ታላቁ ወደ **እግዚአብሔር እራት ተከማቹ ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ።”ራእይ 19፥17-18 ።** በአሰቃቂ ፍርዱ እርግጠኛ ኹን።

፨ ሌላኛው መልእክት ከአጠቃላዩ እስካሁን ካየነሁ፣ በጉን ለመውጋት በሰይጣን ሕብረተሰብ የተዘጋጀው የተሰለፈው ሰልፍ መሸነፍ ነው፣ “በፈረሱም የተቀመጠውን ጭፍራዎቹንም ይወጉ ዘንድ አውሬውና የምድር ነገሥታት ጭፍራዎቻቸውም ተከማችተው አየሁ።” ራእይ 19፥19 ።መጀመሪያ በተለይ መንገድ ያሳወቀው እንደገና የሚያሳየው መልእክት ግልጽ እንዲኾንና የተነገረው እርግጠኛነት የማጽደቅ ፤ ራዕዩን የሚያነቡት እንዲጽናኑ ነው። አውሬውም ተያዘ በእርሱም ፊት ተአምራትን እያደረገ የአውሬውን ምልክት የተቀበሉትን ለምስሉም የሰገዱትን ያሳተ ሐሰተኛው ነቢይ ከእርሱ ጋር ተያዘ፤

ሁለቱም በሕይወት ሳሉ በዲን ወደሚቃጠል ወደ እሳት ባሕር ተጣሉ። የቀሩትም በፈረስ ላይ ከተቀመጠው ከአፉ በሚወጣው ሰይፍ ተገደሉ፤ ወፎችም ሁሉ ከሥጋቸው ጠገቡ። በበጉ በአሸናፊነት እርግጠኛ ኹን።

፨ ሌላኛው መግለጫ ዮሐንስ ራእዩን ከተመለከተበት ጊዜ አንስቶ የሚኾነው ፣ የሰይጣን ታስሮ መቆየት ነው።"[1] የጥልቁንም መክፈቻና ታላቁን ሰንሰለት በእጁ የያዘ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ። የቀደመውንም እባብ ዘንዶውን እርሱም ዲያብሎስና ሰይጣን የተባለውን ያዘው፥ሺህ ዓመትም አሰረው፥ ወደ ጥልቅም ጣለው **አሕዛብንም ወደ ፊት እንዳያስት ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በእርሱ ላይ ዘግቶ ማኅተም አደረገበት**፤ ከዚያም በኋላ ለጥቂት ጊዜ ይፈታ ዘንድ ይገባዋል።" ራእ 20፥1-3።

ኢየሱስ ገና አገልግሎት ስጀምር የሰይጣን ስራ በማፍረስ ከሰዎች ልብ በማውጣት ፣በማሰር ነው የጀመረው ። " ግን በእግዚአብሔር መንፈስ አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ፥ እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ደርሳለች። ወይስ ሰው አስቀድሞ ኃይለኛውን ሳያስር ወደ ኃይለኛው ቤት ገብቶ እቃውን ሊነጥቀው እንዴት ይችላል? ከዚያም ወዲያ ቤቱን ይበዘብዛል። ማቴ 12፥28- 29።" ወንጌልም ኢየሱስ በከፈተው በርና መንገድ ለሺህ ዓመት [ለብዙ ዓመት] እስካሁን ሰይጣንን እንደፈለገ እንዳይቀሳቀስ ጠፍሮ በመያዝ የብዙዎችን ልብ ወርሷል፤በኢየሱስ ስም ስልጣን እንደፈለገ እንዳይንቀሳቀስ ስያባረር ስያሸሽ ኖሯል፤በኢየሱስ መምጣት የሰይጣን እንደፈለገ መንቀሳቀስ አለመቻል መታሰሩን ይገልጻል ፤ባይታሠር ኢየሱስ እንዴት ይገባል ? ስለታሰረ እንጂ ። ሰይጣን የታሠረው አሕዛብን እንዳያስት ነው እንደተባለው፣ የሚታተሙት ሙላት ስፈጸም ፣ ለጥቅት ጊዜ 1260 ቀናት ይፈታል፤ ይሠራል።

ሺህ ዓመት ቍጥር በሕሳብ አሃዝ ሳይኾን በምሳሌያዊ ገለጻ እንደቀረበ ከተረዳነው የመልእክቱን ጭብጥ እንይዛለን ።በመጽሐፍ ቅዱስ ሺህ ዓመት በጌታ አንድ ቀን ነው እንደሚል በመጽሐፍ ቅዱስ ፣በመጽሐፉ ሃሳብና አውድ ልንፈታ ይገባናል ። የሰይጣንን መፈታት መታሠር በአውድ ልክ ልንመለከተው ይገባናል ። መታሠሩ እንደ ፈቃዱ እንዳይሠራ በጌታችን መወለድ የጀመረ ስኾን፣ እስካሁን የሚታተሙት እስከሚሞሉ ድረስ አይሰለጠንም፤መፈታቱ ከታተሙት ቅዱሳን ሙላት በኋላ የሚጀምር የ3ዓመት ከ6ወር ዕድሜ ነው። ይኽንን በቀላሉ ከአውዱ እንረዳለን ፣ ሰይጣን እንደተፈታ በተለያየ መገለጦች የተመለከትነው ፣የመጨረሻው ጦርነት መጀመሩ አኹን ሰይጣን ታስሮ ያለ እንደኾነ እንዲንገነዘብ ያደርገናል ።ራእይ 20 … **ሺሁም ዓመት ሲፈጸም ሰይጣን ከእስራቱ ይፈታል**፥ በአራቱም በምድር ማዕዘን ያሉትን አሕዛብ፥ ጎግንና ማጎግን፥ እንዲያስታቸው ለሰልፍም እንዲያስከትታቸው ይወጣል፤ ቍጥራቸውም እንደ ባሕር አሸዋ የሚያህል ነው። ወደ ምድርም ስፋት ወጡ የቅዱሳንንም ሰፈርና የተወደደችውን ከተማ ከበቡ፤ እሳትም ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወርዳ በላቻቸው። ያሳታቸውም ዲያብሎስ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣለ፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ቀንና ሌሊት ይሣቀያሉ።

**ሰይጣን ለጥቅት ጊዜ ተፈትቶ** የመጨረሻው ውጊያ ሃይሉን አሟጦ ለማድረግ ብሰለፍም፣ እግዚአብሔር በሃይሉ አጠፋቸው የዘላለም ፍርድንም ሰጣቸው ። የሰይጣን መፈታት የሚያመለክተው 1260 ቀን፣ ከቤተክርስቲያን መሸሽግ በኋላ የሚኾነው ነው።ስለዚህም ሰይጣን አኹን ታስሮ ነው ያለው ። ኢየሱስ እያሰረው ቤቱን እየገባ ብዙዎችን ነፃ እያወጣ ነው። ሌላ ሺህ ዓመት የለምና ።ጆሮ ያለው ይስማ። ሰይጣን ታስሮ ያለው ክርስቶስ ወደ ምድር ከመጣበት አገልግሎት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ነው፤ቤተክርስቲያንንም እንደታሰረ እንዲቆይ ምክንያት የኾነች ከክርስቶስ ጋር የነገሰች የኖረች ናት፤ ይኽ ስፈጸም ሰይጣን ለጥቅት ጊዜ ይፈታል ፤ በክርስቶስ ፍርድ ይጠፋል፤ የክርስቶስ ዳግም ምጽአትም ይኾናል ።ይኽ ዕሳቤ አይደለም ።የነጠረ እውነት እንጂ። ጆሮ ያለው ይስማ ።

*አንባቢ ቤተክርስቲያን የጋነም ደጆች የማይችሏት ናት ማለት ፣ ሰይጣን ደጁን በሩን ዘግቶ "የራሴ ናቸው" ያሏቸውን ነፃ እያወጣች፣ ደጁን ሰብራ እየገባች ብዙዎችን ነፃ ማውጣቷ የሰይጣንን መታሰርን ያሳያል ደግሞም የቤተክርስቲያን መንገስንም። “እኔም እልሃለሁ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ **የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።**” ማቴዎስ 16፥18።

፨ ሌላኛው መልእክት ዮሐንስ ራእዩን ከሚያይበት ጊዜ አንስቶ ቶሎ እየኾነ ያለው ፣ የፊተኛው ትንሳኤ ነው። እነዚህ እግዚአብሔር ባዘጋጀው ዙፋን የተቀመጡ ፣በክብር ለስሙ ታምነው የሞቱ ፣ ቅዱሳን ናቸው ። “ዙፋኖችንም አየሁ፥ በእነርሱም ላይ ለተቀመጡት ዳኝነት ተሰጣቸው፤ ስለ ኢየሱስም ምስክርና ስለ እግዚአብሔር ቃል ራሶቻቸው የተቈረጡባቸውን ሰዎች ነፍሳት፥ ለአውሬውና ለምስሉም ያልሰገዱትን ምልክቱንም በግምባራቸው በእጆቻቸውም ላይ ያልተቀበሉትን አየሁ፤ ከክርስቶስም ጋር ሺህ ዓመት ኖሩና ነገሡ።”ራእ 20፥4። በዙፋኑ ላይ ከክርስቶስ ጋር መቀመጥ ብቻ ሳይኾን [ኤፌ1] ይፈርዳሉ ፣ ዳኝነት አላቸው ። ከክርስቶስ ጋር ይኖራሉ ይነግሣሉ ። እነዚህ በፊተኛው ትንሳኤ የተነሱ ናቸው ። “**በፊተኛው ትንሣኤ ዕድል ያለው ብፁዕና ቅዱስ ነው**፤ ሁለተኛው ሞት በእነርሱ ላይ ሥልጣን የለውም፥ ዳሩ ግን የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ካህናት ይሆናሉ ከእርሱም ጋር ይህን ሺህ ዓመት ይነግሣሉ።” ራእይ 20፥6 ።

እነዚህ የክርስቶስ ካህናት የተመረጡ ትውልድ ፣ ሰይጣን የማይሰልጥንባቸው፣ ፊተኛው ትንሳኤ ያገኙ ናቸው ። በዚህ አውድ ፊተኛው ትንሳኤ ማለት በክርስቶስ ከፍርድ ያመለጡ ወደ ሕይወት የገቡ፤ ራሱ ክርስቶስ ያላቸው ማለት ነው። እኔ ትንሳኤ ነኝ እንደሚል። እነዚህ ክርስቶስ ትንሳኤ ኾኖላቸው የትንሳኤ ሕይወት በምድር የሚኖሩ ፣የሚነግሱ ቅዱሳን ናቸው ። ብዙዎች ወደዚህ ሕይወት ክርስቶስን በማመን ብቻ እየተቀላቀሉ ይገኛሉ። ከብዙዎች ሰይጣን እየወጣ ክርስቶስ እየከበረ እየነገሰ ይገኛል ። የሰይጣን መታሰሩና የፊተኛው ትንሳኤ እስካሁን እየኾነ ያለ ነው።

፨ሌላኛው መልእክት የመጨረሻው የፍርድ ሁናቴ የሚገልጽ ነው፣ "ታላቅና ነጭ ዙፋንን በእርሱም ላይ የተቀመጠውን አየሁ፥ ምድርና ሰማይም ከፊቱ ሸሹ ስፍራም አልተገኘላቸውም።... ባሕርም በእርሱ ውስጥ ያሉትን ሙታን ሰጠ፥ ሞትና ሲኦልም በእነርሱ ዘንድ ያሉትን ሙታን ሰጡ፥ **እያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን ተከፈለ**።"ራእ 20፥11-13፣14፣15። በየትኛውም ሁኔታ የሞቱ ሰዎች ነፍስ መቃብር ብኖርም ባይኖርም ይነሳል። ለመጨረሻ ፍርድ። እዚህ ጋር ከሞት የሚነሱት ኃጢአንና ጻድቃን ኹሉ እንደኾኑ እንረዳለን ። ኹሉም በእግዚአብሔር ልጅ ፊት ይቆማሉ እንደ የሥራቸው ይቀበላሉ ።ልክ ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል ለፍርድ በቀኝና በግራ እንደሚቆሙ እንዳመለከተ፣“በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል።” ማቴዎስ 25፥33። ይኸም ክፍል በመጨረሻው ፍርድ ላይ እንዲያ እንደሚኾን ያሳስባል ። አጠቃላይ ጠቅለል ያለ መልእክት ነው በዚህ ቍጥር ስር የተመለከትነው ።

፨ በኹሉም ካሜራዎች በኩል የተመለከትናቸው ክስተቶች በበጉ በፍርድና በአሸናፊነት የሚጨርሱ ናቸው ።በዚህ ክፍል ላይም እስካሁን ያልታየ ነገርንም በተጨማሪ ይሰጠናል ፤ ኹሉም ዐድስ ስለመኾን።" አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርንም አየሁ፥ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና፥ ባሕርም ወደ ፊት የለም። ቅድስቲቱም ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፥ ለባልዋ እንደ ተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ፥ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ።ታላቅም ድምፅ ከሰማይ፡- እነሆ፥ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው ከእነርሱም ጋር ያድራል፥ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል፤እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል፥ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና ብሎ ሲናገር ሰማሁ። በዙፋንም የተቀመጠው፡- እነሆ፥ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ አለ። ለእኔም፡- እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነተኛዎች ናቸውና ጻፍ አለኝ። አለኝም፡- ተፈጽሞአል። አልፋና ዖሜጋ፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ። ለተጠማ ከሕይወት ውኃ ምንጭ እንዲያው እኔ እሰጣለሁ። ድል የሚነሣ ይህን ይወርሳል አምላክም እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል።ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ የርኵሳንም የነፍሰ ገዳዮችም የሴሰኛዎችም የአስማተኛዎችም ጣዖትንም የሚያመልኩ የሐሰተኛዎችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው፤ ይኸውም ሁለተኛው ሞት ነው።" ራእ 21፥1- 8።

### 1.2.7 ሰባተኛው መግለጫ

በዚህ ክፍል የምናየሁ በጥቅሉ ፀሐይ የለበሰች፣ነጭ የለበሰች፣ሙሽሪት የበጉ ሚስት ተብላ በሌሎች መግለጫዎች የተገለጠችኹን ቤተክርስቲያንን ነው፤ በዝርዝር ። ከምዕራፍ 21፥9 እስከ 22፥6 ያለው ለዚህ ዝርዝር መግለጫ ይሰጣል ። “ሰባቱም ኋለኛዎች መቅሠፍቶች የሞሉባቸውን ሰባቱን ጽዋዎች ከያዙት ከሰባቱ መላእክት አንዱ መጥቶ፡- ወደዚህ ና፥ የበጉንም ሚስት ሙሽራይቱን አሳይሃለሁ ብሎ ተናገረኝ።” ራእይ 21፥9 ። ይቺ የበጉ ሚስት ሙሽራይቱ ፣ የእግዚአብሔር

መኖሪያ የኾነችው ቤተክርስቲያን ናት፤“በመንፈስም ወደ ታላቅና ወደ ረጅም ተራራ ወሰደኝ፥ የእግዚአብሔርም ክብር ያለባትን ቅድስቲቱን ከተማ ኢየሩሳሌምን ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አሳየኝ፤ ብርሃንዋም እጅግ እንደ ከበረ ድንጋይ እንደ ኢያሰጲድ ድንጋይ ሆኖ እንደ ብርሌ የጠራ ነበረ፤”ራእይ 21፥10-11 ።

መጽሐፉን በሐዲስ ኪዳን መንፈስ ካለነበብን ልናስተውል ልንረዳ አንችልም ። እስራኤል የተባለችው በዚህ መጽሐፍ ሙሽሪት ቤተክርስቲያን ናት። በዚህ ተመስላ የተነገረችው ጌታ የመረጣት ለዚህ ስለኾነ ነው። ይቺ እስራኤል ዘሥጋ የኾኑት አትወክልም ኹሉንም የሰውን ዘር ያለ ልዩነት በደሙ የፀደቁትን የምትወክል ናት። መጽሐፉ ለእስራኤል ዘሥጋ ይናገራል ሃሰተኞች ብሉም የእውነት ቃል እንዲህ ተገልጦ ስፈርድ ማመካኛ ስያሳጣ ይኖራል ። ቅጥሯ የተጠበቀ ታላቅም የኾነ፣ ብዙዎችን ከነገድ ከቋንቋ የተዋጁትን የያዘች፣ መሠረቷም በሐዋርያት ስም ትምህርት የቆመ፤በእምነት ከኢየሱስ የተወለዱ የእግዚአብሔር እስራኤል የአብርሃም የእምነት ልጆች ናቸው ።144,000 የታተሙትም የእግዚአብሔር እስራኤሎች እኚህ ቅዱሳን ናቸው እንጂ የያዕቆብ እስራኤሎች አይደሉም ።

ከተማይቱ የተለካች የሚገብባት በእሳት ተፈትነው ድል ነስተው ያለፉት ናቸው ።“የተናገረኝም ከተማይቱንና ደጆችዋን ቅጥርዋንም ይለካ ዘንድ የወርቅ ዘንግ ነበረው።” ራእይ 21፥15 ።እነዚህ የእግዚአብሔር እስራኤሎች የእፉኝት ልጆች የተባሉት ሳይኾኑ፣ ከያዕቆብ የተወለዱ የያዕቆብ ስም መሠረት የኾናቸው ሳይኾኑ፣ በበጉ ሐዋርያት ማንነት የተተከለች ቤተክርስቲያን ናት። የእግዚአሔብር ህንጻ እኛ ነንና። [አንዳንዶቹ በሞኝነት እንደሚሉት ታቦትና መቅደስ በሰማይ የለም]። መቅደሱ ራሱ እግዚአብሔር ነው።“ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክና በጉ መቅደስዋ ናቸውና መቅደስ በእርስዋ ዘንድ አላየሁም።” ራእይ 21፥22 ። እርሱን በመካከላቸው ያለ መጋረጃ ፊት ለፊት እያዩ ያመልኩታል ፤ ለዘላለም የሕይወት ውኃ ወንዝ ከውስጣቸው እየፈለቀ ሳይጠሙ ይኖራሉ። ራእ 22፥1-5።

*የራእዩ ማጠቃላያ ከዚህ በኋላ ያለው ዮሐንስ እስካሁን ለተመለከተውና[በተለይ በዚህ በመጨረሻው መግለጫ ስለተመለከተው የሚሰጥ አጠቃላይ መልእክት ነው። ሌሎችን መልእክቶችን ስዘጉ ፍርድን ይገለጻል።በዚህ ግን ስለ ቤተክርስቲያን የተነገረ ስለኾነ ለዚህ ክብር እንዲበቁ ጥብቅ ማሳሰቢያ በምድር ለሚኖሩት ይሰጣል ። "እነሆም፥ በቶሎ እመጣለሁ። የዚህን መጽሐፍ ትንቢት ቃል የሚጠብቅ ብፁዕ ነው አለኝ። ... ወደ ሕይወት ዛፍ ለመድረስ ሥልጣን እንዲኖራቸው በደጆችዋም ወደ ከተማይቱም እንዲገቡ ልብሳቸውን የሚያጥቡ ብፁዓን ናቸው።" ራእ22፥7-14። ሰዎች ኹሉ የትንቢቱን ቃል ጠብቀው መዳንን እንዲወርሱ ያሳስባል ፤ ይኽ መጽሐፍ ሃሰተኞች እንደሚሉት ከምዕራፍ አራት ጀምሮ ያለው ቤተክርስቲያን ከተነጠቀች በኋላ ያለውን የሚናገር አይደለም ። በግልጽ እንደተመለከትነው በዚህ አመጽ

ሳይሳተፉ ታምነው ስሙን ይዘው የሚኖሩ የሚገቡባት ሕብረት ናት። በቶሎ እመጣለሁ ጌታም ያለው ምድር ላይ ላለች ቤተክርስቲያን ነው ።

" በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን የትንቢት ቃል ለሚሰማ ሁሉ እኔ እመሰክራለሁ፤ ማንም በዚህ ላይ አንዳች ቢጨምር እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ የተጻፉትን መቅሠፍቶች ይጨምርበታል፤ማንምም በዚህ በትንቢት መጽሐፍ ከተጻፉት ቃሎች አንዳች ቢያጎድል፥ በዚህ መጽሐፍ ከተጻፉት ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ እግዚአብሔር ዕድሉን ያጎድልበታል።" ራእ22፥18-19። መልእክቱ ለሚሰማ ኹሉ የተነገረ ነው፡፡

በዚህ መጽሐፍ ላይ የተጻፈውን ግልጽ መልእክት የሚጻረር እስከዛሬ የሚያስተምሩ ዋጋቸውን ይቀበላሉ። ሰዎች መዳንን ያለ ሥራ በእምነት እንዲያው በነፃ ወርሰው ሕይወትን እንዲቀበሉና፣ ለተቀበሉት እውነት እንዲታመኑ የሚያስተምረውን የእግዚአብሔርን ቃልን በመጻረር ፣ መዳንን በብዙ መንገድና በብዙዎች በኩል በቀላሉ ማግኘት እንደሚችሉ በማስተማር በጉን የሚዎጉ እነዚህ የዲያብሎስ ማህበረሰቦች ፍርድን ይቀበላሉ ። መጽሐፍ በግልጽ የሕይወት ውኃ /የዘላለም ሕይወት/ ያለ ዋጋ እንደሚቀበሉ ይመሰክራል ፣ አለኝም፡- ተፈጽሞአል። አልፋና ዖሜጋ፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ። ለተጠማ ከሕይወት ውኃ ምንጭ **እንዲያው** እኔ እሰጣለሁ። ድል የሚነሣ ይህን ይወርሳል አምላክም እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል።ራእ 21፥6-8።

※ክርስቶስ፣ መንፈስ ቅዱስም ቤተክርስቲያንም "ና" ይሉኛልና፣ አልቆይም በቶሎ እመጣለሁ ፤የተጠማም የሕይወት ውኃ ይጠጣ ይምጣ ወደራሱ በማለት ያሳስባል ።ይኽንን ናልን ጥሪ ያቀረቡት ምድር ላይ ያለች ቤተክርስቲያን እንጂ የተነጠቀችው ቤተክርስቲያን ወይም እስራኤል ዘሥጋ አይደለችም ። ዮሐንስ ከሙሽሪት ቤተክርስቲያን አንዱ ነውና ለእግዚአብሔር ቃል ፈጣን ምላሽ ይሰጣል ፣“ይህን የሚመሰክር፡- አዎን፥ በቶሎ እመጣለሁ ይላል። አሜን፥ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ና።”ራእይ 22፥20። ይላል። ስለዚህም ወንድሞቼ በመጠን እንኑሩ፤ እንዲንጠብቀው የተሰጠን ታላቅ የትንቢቱ ቃል አለንና ዐዲስ የግል የትንቢት ቃል አውጣብኝ እያልን ከሰው በሰው የኾነውን መልእክት ለመስማት ባንረባረብ መልካም ነው።አርፈን የተሰጠውን የተስፋ ቃል እንጠብቅ ። እየኾነ ያለውን እያስተዋልን በመጠን እንኑር ። “የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችን ጋር ይሁን፤ አሜን።” ራእይ 22፥21።

**መደምደሚያ**

ራእይ መጽሐፍ እንዲናነበው የተከፈተ መጽሐፍ ነው።እንዲንተረጉመው ጌታ ይፈልጋል ። ጊዜው ስለደረሰ ፡፡እንደ ዳንኤል ራእይ የተዘጋ አይደለምና ። “ዳንኤል ሆይ፥ አንተ ግን እስከ ፍጻሜ ዘመን ድረስ ቃሉን ዝጋ፥ መጽሐፉንም አትም፤ ብዙ ሰዎች ይመረምራሉ፥ እውቀትም ይበዛል።”ዳንኤል 12፥4። የራእይ መጽሐፍ ግን ጊዜው ስለቀረበ በማህተም አልተዘጋም ። “ለእኔም፦ ዘመኑ ቀርቦአልና የዚህን መጽሐፍ ትንቢት ቃል በማኅተም አትዝጋው።”ራእይ 22፥10 ። ጌታ እንዲናውቀው ይፈልጋል ። ለዮሐንስ በተገለጠው ልክ እንዲናውቀው ይፈልጋል ። ኢየሱስ ከአብ የተቀበለውን ፣ ለእኛ እንደ ወረደ አድርሷል ።ይኸንን እንደ ወረደ እንዲንረዳ ይፈልጋል ።መልእክቱ መጣመም የለበትም ። መልእክቷም አንድ ብቻ ናት። በግምት ልንደፍረው ትውልዱን ልናወዛግበው አይገባም ። ደግሞም ጌታ እራሱ መጽሐፉን ለመረዳት እውቀት "ይበዛል እንዳለው" ያደርጋል ።

ሰምተው የሚጠብቁትን ወደ ቃሉ ዘወር የሚሉትን ብዙዎችን ያስነሳል ። ያለመከልከል እውቀቱን መስጠትና ማፍሰስ ይፈልጋልና "አልተማርኩም" በማለት አንቦዝን ፤መጽሐፉን በመንፈስ ስነበብ መስማትም ይቻላልና፤ ክህሎታችንን መጽሐፉን ለመፍታት ልያግዝ አይችልም ።አለመማርህም ልያግደው አይችልም ። በባዶ የሚሠራ አምላክ ነውና፤ ምንም የሚሳነው ነገር እንደሌለው በእውነት ልብ ልናምነው ይገባናል ። ተረድተን ከኾነ በእኛ በኵል አልፏል በማለት ልንታበይ አይገባም ።ወደ አንድ መረዳት፣ ሃሳብ፣ እውቀትና መንፈስ ለመግባት እንትጋ ። ስምና ዝና የራስ ደቀመዛሙርት ለማፍራት ሳይኾን የሚታተሙት የጌታ ምርጦች እንዲበዙ እንትጋ ።ይኸንን የራእይ መጽሐፍ ለመረዳት አመቺ አከፋፈል ይዞ የቀረበው "የራእይ መጽሐፍ ጥናት መጽሐፍ" ነው፤ ለእኔ። አግኝታችሁ እንዲታነቡ በዚህ አጋጣሚ አበረታታለሁ። እናንተም በዚህ ልክ ከፋፍላችሁ ብታነቡ ትጠቀማላችሁ ብዬ አምናለሁ ። በቀላሉ ለማጥናት ፦

1ኛ. በምዕራፍ 1 የመልእክቱን ምንጭ፣ተቀባይ፣ተደራሲያንና ይዘቱን ትረዳለህ ፣

2ኛ. ከምዕራፍ 2-3 ድረስ ያለው በሰዓቱ ስለነበረች ቤተክርስቲያን በቀጥታ "አኹናዊ መልእክት" የሚናገር ስኾን፣ ሌሎችም እራስ መመልከቻ አቋም መፈተሻ ኾኖ የሚያገለግል ቀጥተኛ መልእክት ነው፣

3ኛ. ከምዕራፍ 4 ጀምሮ እስከመጨረሻው ያለው፣ ለሰባቱ በሥጋ አሕዛብ ለኾኑ አብያተክርስቲያናት [ለዛሬይቱ ቱርክ ] ግና ወደፊት ስለ ሚኾነው ስለዘመን ፍጻሜ ሰፊ ማብራሪያ የያዘ ሲኾን፣ በእነዚህ አሕዛብ አብያተክርስቲያናት ለዓለም አብያተክርስቲያናት የተሰጠ ነው። ከምዕራፍ 4 እስከ ምዕራፍ 5 ድረስ ያለው ከመልእክቱ አንፃር ስለ አምላክ ማንነት መግለጫ ይሰጣል፣

4ኛ. ከምዕራፍ 6 እስከ ምዕራፍ 8 ፥1 ድረስ ያለው፣ በዓለም የሚኾኑት ክስተቶችን ይገልጻል፣

5ኛ. ከምዕራፍ 8፥2 ጀምሮ እስከ ምዕራፍ 11፥18 ድረስ ያለው፣ በዓለም የሚኾኑ ማስጠንቀቂያዎችን ያሳያል፣

6ኛ.ከምዕራፍ 11፥19 ጀምሮ እስከ ምዕራፍ 15፥4 ያለው ጦርነቱ ከሰማይ እንደምጀምር ያሳያል፣

7ኛ. ከምዕራፍ 15፥5 ጀምሮ እስከ ምዕራፍ 16 ድረስ ያለው፣ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ቍጣ [ፍርድን ] ያሳያል፣

8ኛ. ከምዕራፍ 17 ጀምሮ እስከ ምዕራፍ 19፥10 ድረስ ያለው ፣ የሰይጣን ሥራ አስፈፃሚ ስለኾኑችው ከተማ ሰፊ ትንተና ይሰጣል፣

9ኛ. ከምዕራፍ 19፥11 ጀምሮ እስከ ምዕራፍ 21፥8 ድረስ ያለው ፣ በዓለም ግና ስለሚፈጸመው አጠቃላይ ግንዛቤ ያስጨብጣል ፣

10ኛ. ከምዕራፍ 21፥9 ጀምሮ እስከ ምዕራፍ 22፥6 ድረስ ያለው፣ ድል ነስታ ዓለምን ስለአሸነፈች ቤተክርስቲያን ስለሚጠብቃት ክብር ሰፊ መግለጫ ይሰጣል ። ይኸም በዓለም ያለች ቤተክርስቲያን የተዘጋጀላትን ክብር ስለሚጠብቃት እንዲታውቅ ነው፣

11ኛ. ከምዕራፍ 22፥7-21 ያለው፣ እስካሁን ስለተሰጠው መልእክት ማሳሰቢያ ይሰጣል ።

በዚህ ልክ እንዲታነቡ አበረታታለሁ ጠቅሞኛልና፤ በቀላሉ ለመረዳት ያስችለናል ። የራእይ መጽሐፍ ከምዕራፍ አራት ጀምሮ ያለው ቤተክርስቲያንን አያመለክትም ፤ ለእስራኤልና ላልተነጠቁ ኢ-አማኞች ነው ብሉም እንኳን ፣ የራእዩ መልእክት ስለ ታላቁ መከራ ብቻ እንደ ማያትት አይተናል ።ምክንያቱም እነሱ እንዲያ የሚሉት 'ስለተነጠቅን' ከምዕራፍ 4 ጀምሮ ያለው አያመለክተንም በማለት ነው። መልእክቱ ግን የተጻፈው የተሰጠው በሥጋ አሕዛብ ለኾኑ ለ**7**ቱ አብያተክርስቲያናት ነው፤ በእነሱ በኵል ነው እንዲሁም ለሌሎች [በሥጋ አይሁዳውያን] ለኾኑት ጭምር የሚደርሰው፤ የኹሉ ስለኾነ ።

ደግሞም በዚህ ልክ ካነበብን በዝርዝር ወደ ሙሉ መረዳት መምጣታችን አይቀርም ።አንደኛውን መግለጫ ከአንደኛው መግለጫ ጋር አስተያይተን ማንበብ ከቻልን መረዳታችን ከፍ ይላል።እያስተያይን ከተመለከትነው በይበልጥ ደግሞ ግልጽ ይኾንልናል። ለምሳሌ :- የሞቱ ሰዎች የፍትህ ጥያቄ ለኢየሱስ በማቅረብ "ፍረድልን" ይላሉ። በም.6 በተገለጠው መግለጫ ላይ። የእግዚአብሔር ፍርድ በተገለጠው መግለጫ ላይ ደግሞ የጥያቄአቸውን መልስ በዝርዝር ስሰጥ እንመለከታለን “የቅዱሳንና የነቢያትን ደም ስላፈሰሱ ደምን ደግሞ አጠጥተሃቸዋል፥ የሚገባቸው ነውና ብሎ ሲናገር ሰማሁ።” ራእይ 16፥6። ይኸም የሞቱ ሰዎች ለፍርድ ስጮኹ ጌታም ጊዜው ደርሶ መፍረዱ፣ **በታላቁ መከራው ጊዜ የቅዱሳን ሰርግ እንዳልነበረ ያሳያል ።የሞቱትም ለፍርድ እንደሚጮኹ ያረጋግጣል ።**

ሰርግም ድግስም በታላቁ መከራ ጊዜ የለም። እንዲሁም ጌታ ስለደማቸው ዓለምን ከማጥፋቱ በፊት እንደእነርሱ ያሉ እንዲታተሙ በማለት በታላቁ መከራ ጊዜ የብዙዎች መዳን ፣ወደ ጌታ ዘወር ማለት እንዳለ ይጠቁሟል ። ይኸም

<<ቅድሜ መከራ ንጥቀትና የአየር ላይ ሰርግ በመከራው አለ >> ሚባሉት የፈጠራ የሃሰት የእባቡ ትምህርት እንደኾኑ ያስታውቃል ። የራእዩን ትርጓሜ "ዕሳቤ" ብቻ ተብሎ ከውሸት ጋር ተቻችሎ መኖር አይገባንም ።ወይም የተማሩ የሚባሉ ሰዎች የዓለም እውቅና ስላላቸው ትርክቱን ስለደገፉ "ፀድቆ" የሚኖር አይምሰላችሁ ። መልእክቷም አንድ ናት፤ ወጥ ናት፤ እንመሰክር። ለነፍሳችሁ ማንም አይቆምም፤ ማንም ደግሞ አይጠየቅም፤ እወቁ አምልጡ፤ ተዘጋጁ፤ በመጠንም እንኑር ።ጌታ ልመጣ በደጅ ነው፤ጆሮ ያለው ይስማ።

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. ለንጥቀት አስተምህሮ ስባል የተጨነገፉ

### የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

መነጠቅ ማለት ወደላይ መወሰድ ማለት ስኾን በዚህ ሃሳብ ላይ ከሞት ተነስተው በትንሣኤ አካል ከመከራው በኋላ ወደላይ የሚወሰዱትን ሳይኾን፣ <<ከመከራው በፊት ከመቅጽበት እየተለወጡ ቅዱሳን ይነጠቃሉ>> የሚለውን ሃሳብ ነው የሚወክለው። ለዚህ አስተምህሮ ይኾናሉ ብለው እያጣመሙ በድፍረትና በግምት የሚጠቅሷቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በጥልቀት አንድ በአንድ እንመለከታለን ፦

*1ኛ. “እንግዲህ ሊመጣ ካለው ከዚህ ሁሉ ለማምለጥ፥ በሰው ልጅም ፊት ለመቆም እንድትችሉ ስትጸልዩ ሁል ጊዜ ትጉ።”ሉቃስ 21፥36። ማምለጥ የሚለው ቃል መነጠቅን ያመለክታል ስለሚሉት። "ሊመጣ ካለው ከዚህ ኹሉ" ማለት ሊመጣ ያለው አንድ ብቻ እንዳደለ እጅግም ብዙ ብዙ መቅሰፍት እንደኾነ እንረዳለን ። "በፀሐይና በጨረቃም በከዋክብትም ምልክት ይሆናል፤ በምድር ላይም አሕዛብ ከባሕሩና ከሞገዱም ድምፅ የተነሣ እያመነቱ ይጨነቃሉ፤ሰዎችም ከፍርሃትና በዓለም የሚመጣበትን ከመጠበቅ የተነሣ ይደክማሉ፤ የሰማያት ኃይላት ይናወጣሉና።በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ በኃይልና በብዙ ክብር በደመና ሲመጣ ያዩታል።ይህም ሊሆን ሲጀምር ቤዛችሁ ቀርቦአልና አሻቅባችሁ ራሳችሁን አንሡ።"ሉቃ 21፥25-28። አኹን አስተውሉ፦

እነዚህ ታላላቅ መቅሰፍቶች ስኾኑ ዓለማዊያን "ምን እየመጣ ነው?" ብለው በመከራ ውስጥ ኾነው ያስባሉ፤ይጨነቃሉ፤ እናንተ ግን የኢየሱስ መምጫ እንደኾነ አውቃችሁ ነቅታችሁ ጠብቁ የሚል ነው። አስተውሉ ። እየኾነ ያለውን ታላላቅ መቅሰፍቶች የእግዚአብሔር ቍጣዎችን ቅዱሳንም በዓለም ስላሉ እየተመለከቱ ይገኛሉ። ስለዚህ አትሸበሩ እየመጣ ያለው ክርስቶስ እንደኾነ አውቃችሁ በእምነት ቁሙ የሚል መልእክት ነው።ምክንያቱም እየመጣ ያለው መቅሰፍት ብቻ ሳይኾን የመጨረሻ ፍርድን ያደርጋል ።ስለዚህ በሰው ልጅ ፊት ለመቆም በክብር ለመኾን ከፈለጋችሁ ተግታችሁ ጠብቁ። የሚል ነው።

ይኽ የሚያሳየው ቅዱሳን በመላው ምድር በሚደርሰው በመጨረሻው በጌታ ፍርድ ሳይጠፉ፣ ምልክቶቹን አይተው በትጋት እንድገኙ ነው። እንጂ ከመከራው በፊት በመነጠቅ ስለ ማምለጥ አይደለም ።ከጌታ ከኢየሱስ ጽድቅ ፍርድ ስለማምለጥ እንጂ። ቅዱሳን ሊመጣ ካለው መቅሰፍቶች የሚያመልጡት በምድር ኾነው በጌታ ተጠብቀው እንጂ ወደ ሰማይ ተነጥቀው አይደለም ።ምክንያቱም ይኽንን ኹሉ የመጨረሻው የፍጻሜ መቅሰፍት ይመለከታሉ ። ቃሉ በግልጽ ይኽንን ስያስቀምጥ አንዷን ቃል ከአውዱ እያፋቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተለየ ልዩ ወንጌል ያስተምራሉ ። ጆሮ ያለው ይስማ። ተግቶ ኢየሱስ

ክርስቶስ እስከሚመጣ ድረስ መጠበቅ በግልጽ በመከራው ስለ ማለፍ ያስተምራል ። "የሰው ልጅ ፊት ለመቆም" በማለት የሰው ልጅ የሚመጣው ለፍርድ እንደኾነ ያመለክታል ።ለፍርድ የሚመጣው ከታላላቅ የምድር መናወጦችና ቊጣዎች በኋላ እንደኾነ የተገለጠ ነው።

*2ኛ. "ልባችሁ አይታወክ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፥ በእኔም ደግሞ እመኑ። በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፤ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና፤ሄጄም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ፥ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ።**"** ዮሐ 14፥1-3። "እወስዳችኋለሁ ማለቱ ከዚህ ዓለም መሄድን መነጠቅን ያመለክታል ።"[8] ይላሉ፣ ወድ አንባቢ ኾይ; ቅዱሳን በመጨረሻው ዳግም ምጽአቱ እንደሚወሰዱ እንደማምን ይህም የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት እንደኾነ መስክርያለሁ። ነገርግን መሄድን መወሰድን ኹሉንም ጠቅልሎ ለቅድሜ መከራ መነጠቅ ማስረጃ አድርጎ መጠቀም ግን ትክክል እንዳልኾነ እያሳየሁ ነው።

በዚህ ክፍል ላይ ሁለተኛ እመጣለሁ ኢየሱስ ማለቱ; መጀመሪያ በሥጋ እንደመጣ ቀጥሎም ልወስደን እንደሚመጣ የሚያረጋግጥ ስኾን፣ የክርስቶስ መምጣት ቅድሜ መከራ መምጣትና ከመከራው በኋላ መምጣት በመኾን **ሦስት መምጣት እንዳልኾነ ልንገነዘብ ይገባናል** ።የኹለተኛው መምጣት ዳግም ምጽአት የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ነው። በመምጣቱም በክፍሉ አውድ እንደተገለጸው በመኖሪያው ያኖረናል እንጂ ከመኖሪያው ወርዶ በአየር ላይ የሚያቆየን አይደለም **።አስተውሉ ።ጌታ ያዘጋጀው መኖሪያ እንጂ ማረፊያ[ለጥቅት ጊዜ ለ7ዓመት የሚያቆይ ማረፊያ] አይደለም ።ማደሪያ ቋም መኖሪያ ስኾን፣ ማረፊያ ጊዜያዊ እንደ በርን ያለ መቆያ ስፍራ ነው።** ወደ ራሱ ወደ አባቱ ይወስደና ።ጆሮ ያለው ይስማ ።

3ኛ. "ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤""እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ።" ኤፌሶን 5፥26-27 ።

"ጳውሎስ ለኤፌሶን ቅዱሳን ስጽፍ ጌታ ኢየሱስ ያለ ነውር የኾነችው ቤተክርስቲያን ለራሱ የሚያቀርበው በመነጠቅ እንደኾነ ያመለክታል።እንዲያቀርብ የሚለው ቃል በምድር ያሉትን ቅዱሳንን ወደ ሰማይ ማጓጓዝን ያመለክታል፤ይህም መነጠቅን ይጠቊማል።"[9] ይላሉ ።በዚህ ክፍል ላይ ጳውሎስ ስለመነጠቅ ያወራል ? የክፍሉ አውድ የሚለው እንደ በሪያ ሰዎች እንመለከታለን ፣

---

[8] ዝኒህ ከማሁ

[9] ዝኒህ ከማሁ

ክርስቶስ ዳግም ለኹለተኛ ጊዜ ስመጣ በሕይወት ያሉት ከመቅጽበት ይለወጣሉ ፤ የትንሳኤ አካል ይለብሳሉ ፤ የሞቱት ይነሳሉ የትንሳኤ አካልንም ይለብሳሉ ። ይኽ ክፍል ግን ስለትንሳኤ ኾነ ስለመነጠቅ አይናገርም ። ክርስቶስ የራሱን ቤተክርስቲያን እንደዋጃት፤ ከዓለም ለይቶ በቅድስና እንዲትኾን ለራሱ እንድትኖር ለዘለዓለሙ እንደለያት ይገልጻል ።ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን ቀድሶ አንጽቶ ለራሱ አቅርቧል እንጂ ገና በመነጠቅ የሚያቀርብ አይደለም ። የእርሱ የኾነች ንፅህት ቤተክርስቲያን ለርሱ ኾና ትኖራለች ። በዚህ ክፍል ላይ ቤተክርስቲያንን በመነጠቅ ለማጓጓዝ ነው ለማለት የሚያስችል ቃል የለም። ያውም ከመከራ በፊት መነጠቅ። ቤተክርስቲያን በምድር ሳለችም የእርሱ ናት።አካሉ ናት። ለእርሱ የተለየችና የቀረበች ናት።ፍጻሜው በሌለ ግንኙነት ፣ በደሙ ቀድሶ አስጀምሯታል። እንዲያቀርብ የሚለው ቃል ወደፊታዊ ብቻ አይደለም ። አኹናዊ ማቅረቧንና ቀጣይነት ያለውን ማቅረብን የሚያመለክት ነው። የሚያቀርበው ወደፊት ነው ብንል እንኳን የሚያቀርበው በመነጥቅና በማጓጓዝ ነው አውዱ አይልም፤ **በቃሉ ቀድሶ በውኃ አጥቦ ያቀርባታል ይላል**። ጆሮ ያለው ይስማ።

4ኛ. "እነሆ፥ አንድ ምሥጢር እነግራችኋለሁ፤ ሁላችን አናንቀላፋም ነገር ግን የኋለኛው መለከት ሲነፋ ሁላችን በድንገት በቅጽበተ ዓይን እንለወጣለን፤ መለከት ይነፋልና ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ እኛም እንለወጣለን።ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና።" 1ቆሮ 15፥51-53። እንለወጣለን የሚለው ቃል መነጠቅን ያመለክታል።[10] ይላሉ፡፡

በዚህ ክፍል ላይ ጳውሎስ ስለ ትንሳኤ ያስተምራል ።"የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲሁ ነው። በመበስበስ ይዘራል፥ ባለመበስበስ ይነሣል፤"1ኛ ቆሮንቶስ 15፥42 ። አስተውሉ። ትንሳኤ ከሞት ስለ መነሳት ነው። በአዲስ አካል በትንሳኤ አካል ስለመነሳታችን ጳውሎስ ያስተምራል ። የትንሳኤ አካልም የማይበሰብስ ዘላለማዊ መኾኑን ይገልጻል ። ክፍሉ ስለ ትንሳኤ ስለመኖር እንጂ ከትንሳኤው በኋላ ስለ መነጠቅ አይገልጽም ። ከትንሳኤ በኋላ መነጠቅ መኖሩ እሙን ብኾንም የክፍሉን አውድ መሠረታዊ መልእክቱን መያዝ አግባብ ነው። ጳውሎስ የኋለኛው መለከት ስነፋ፣ የሞቱ በትንሳኤ አካል የሚነሱ ከኾኑ፣ በሕይወት ሥጋ ያሉት ምን ይኾናሉ? የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል ። በሕይወት ሥጋ ያሉት ከመቅጽበት የትንሳኤ አካል ይለብሳሉ ይለወጣሉ ። በማለትም ይመልሳል ።

በዚህ ሃሳብ ላይ መያዝ ያለብን፣ እነርሱ እንደሚሉት ከመከራው በፊት በስውር መነጠቅ እንደማይኾን ነው።አንድ ጊዜ ይኾናል የመጨረሻው መለከት ስነፋ። የሞቱት ይነሳሉ በሕይወቴ ሥጋ ያሉት ይለወጣሉ። ይኽ የኢየሱስ የመጨረሻው ሁለተኛ መምጣትን እንጂ ስውር ዳግም ምጽአት አያመለክትም ። በሕይወት ሥጋ ያሉ ቅዱሳን መለወጥና የሞቱት መነሳት አንድ ላይ መኾኑ ይኽንን ያረጋግጣል ።ከንቱ ሃሳባቸውን አፈር ከድመ ያለብሳል። ሌላኛው መረዳት

[10] ዝኒህ ከማሁ

የሚገባን ነገር የኋለኛው [የመጨረሻው] መለከት ማለት ምን ማለት እንደኾነና መቼ ይነፋል የሚለውን ነው፤ የመጨረሻ መለከት ምን ማለት እንደኾነ ወደ ራእይ መጽሐፍ በመጨረሻ መለከቶች የሚኾኑት ክስተቶች የተገለጡ እውነቶችና መገለጦች፥የተሰጡ መግለጫዎች እናያለን ፡-

".. እነሆ፥ ሦስተኛው ወዮ በቶሎ ይመጣል።ሰባተኛው መልአክ ነፋ፤ በሰማይም፡- የዓለም መንግሥት ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ ሆነች፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣል የሚሉ ታላላቅ ድምፆች ሆኑ።በእግዚአብሔርም ፊት በዙፋኖቻቸው የተቀመጡ ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች በግምባራቸው ተደፍተው ለእግዚአብሔር እየሰገዱ እንዲህ አሉ፡- ያለህና የነበርህ ሁሉን የምትገዛ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ ትልቁን ኃይልህን ስለ ያዝህ ስለ ነገሥህም እናመሰግንሃለን፤ አሕዛብም ተቈጡ፥ ቍጣህም መጣ፥ በሙታንም ትፈርድ ዘንድ ዘመን መጣ፥ ለባሪያዎችህም ለነቢያትና ለቅዱሳን ስምህንም ለሚፈሩት ለታናናሾችና ለታላላቆችም ዋጋቸውን ትሰጥ ዘንድ፥ ምድርንም የሚያጠፉትን ታጠፋ ዘንድ ዘመን መጣ።በሰማይም ያለው የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ፥ የኪዳኑም ታቦት በመቅደሱ ታየ፥ መብረቅና ድምፅም ነጐድጓድም የምድርም መናወጥ ታላቅም በረዶ ሆነ።" ራእ 11፥14-18። ይኼኛውን መግለጫ በኹለተኛው መግለጫ አይተናል ። ወዮታ አለበት፤ የትልቁን ሃይል ይይዛል፤በአሕዛብ ላይ ይፈርዳል ፤ዋጋቸውን ይሰጣል፤ብቻውም ይነግሣል ። ስለዚህም የመጨረሻው መለከት የሚያመለክተው የመጨረሻውን ወዮ ፍርድን፤ የክርስቶስ መንገሥን፤ በሙታንም ላይ የሚሰጠው ፍርድን ነው። ሙታን ፍርድን የሚቀበሉት ከሞት ተነስተው በእግዚአብሔር ፊት ቆመው ነው።ቅዱሳንም የሥራቸውን የሚቀበሉት በእግዚአብሔር ፊት ቆመው ነው።ይኸ ኹሉ የሚኾነው በክርስቶስ ዳግም መምጣት ነው። የኋለኛው መለከት ስነፋ የሞቱት ቅዱሳን በትንሳኤ አካል ይነሳሉ፤ በሕይወት ያሉት ይለወጣሉ፤ ሙታንም ይነሳሉ የመጨረሻው ፍርድ ይኾናል ።ይኸ ብቸኛው ዳግም ምጽአት ነው።

5ኛ."ድንኳን የሚሆነው ምድራዊ መኖሪያችን ቢፈርስ፥ በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሠራ የዘላለም ቤት የሚሆን ከእግዚአብሔር የተሠራ ሕንጻ እንዳለን እናውቃለንና።በዚህ ውስጥ በእውነት እንቃትታለንና፥ ከሰማይም የሚሆነውን መኖሪያችንን እንድንለብስ እንናፍቃለንና ለብሰን ራቁታችንን አንገኝም።በእውነትም የሚሞተው በሕይወት ይዋጥ ዘንድ ልንለብስ እንጂ ልንገፈፍ የማንወድ ስለ ሆነ፥ በድንኳኑ ያለን እኛ ከብዶን እንቃትታለን።ነገር ግን ለዚሁ የሠራን እግዚአብሔር ነው እርሱም የመንፈሱን መያዣ ሰጠን። እንግዲህ ሁልጊዜ ታምነን፥ በእምነት እንጂ በማየት አንመላለስምና በሥጋ ስናድር ከጌታ ተለይተን በስደት እንዳለን የምናውቅ ከሆንን፥ታምነናል ይልቁንም ከሥጋ ተለይተን በስደት መኖር በጌታም ዘንድ ማደር ደስ ይለናል።ስለዚህ ደግሞ ብናድር ወይም ተለይተን ብንሆን እርሱን ደስ የምናሰኝ ልንሆን እንቀናለን። መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ፥ እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናልና። " 2ቆሮ 5፥1-10።

የሚበሰብሰው ሥጋ የማይበሰብሰውን እስከ ሚለብስ ድረስ የሚቆይ ጊዜያዊ አካል ነው፤ ስለዚህም ከዚህ ጊዜያዊ አካል በመላቀቅ ድካም የሌለበት ዘላለማዊ የትንሣኤ አካል እስከምንለብስ ድረስ በመጓጓት እንኖራለን ፤ በጊዜያዊ ደካማ ሥጋችን ስላደረግነው ሥራ ኹሉ የሚገባንን ፍርድ እንቀበላለን ። ታዲያ ይኽ ክፍል የትንሣኤ አካል ስለመልበስ ከመናገር ውጪ ከመከራው በፊት ንጥቀት እንዳለው ይገልጻል ? አይገልጽም ።እንድሁም በመቃተት ከብዶት የሚኖረው በመከራው ውስጥ መኾኑን ያሳየናል ። አዲስና ዘላለማዊ ፍጹም አካል ከለበስን በኋላ ንጥቀት አለ፤ ይኽም ከመከራው በኋላ ከመጨረሻው መለከት መንፋት በኋላ የሚፈጸም ነው። ስለዚህም ክፍሉ ለቤተክርስቲያን ቅድሜ መከራ ንጥቀትና ስለኢየሱስ [ዳግም በአየር] ላይ ስለመምጣት የሚናገር አይደለም ።

6ኛ. "የጌታ ቀን፥ ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ፥ እንዲሁ ይመጣ ዘንድ ራሳችሁ አጥብቃችሁ አውቃችኋልና።ሰላምና ደኅንነት ነው ሲሉ ያን ጊዜ ምጥ እርጉዝን እንደሚይዛት ጥፋት በድንገት ይመጣባቸዋል ከቶም አያመልጡም። እናንተ ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ቀኑ እንደ ሌባ ይደርስባችሁ ዘንድ በጨለማ አይደላችሁም፥ እግዚአብሔር ለቍጣ አልመረጠንምና፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መዳንን ለማግኘት ነው እንጂ።"1ተሰ 5፥1-9።

ጳውሎስ የተሰሎንቄ ቅዱሳንን የኢየሱስ መምጫ ቀን አውቃችኋል ይላቸዋል ። ምክንያቱም አማኞች በተደጋጋሚ የሚደረጉ መቅሰፍቶች ስመለከቱ ምን ልመጣ ነው ብለው እንደ ዓለማዊያን የሚጠብቁ ሳይኾኑ፣ ኢየሱስ ልፈርድ ይመጣ እንደኾነ ያውቃሉ፤ ደግሞም በቃልም በጽሑፍም ተምረዋል፤2ተሴ 2፥1 ። ስለዚህም ለአማኞች ተዘጋጅተው ለሚጠብቁ እንደ ሌባ ሳይኾን የሰጠው ቀን ቀጠሮ ደርሶ እንደሚመጣ ስኾን ነው ።ለአሕዛብ ግን ድንገት የወረደባቸው ዱብዳ ነው። ምክንያቱም አሕዛብ እና ሃሰተኛው አስተማሪ ሰላም ነው፣ብልጽግና ነው፣ማደግ ነው፣መንገሥ ነው፣መውረስ ነው ምድርን ስሉ፣ ዘመኑን ስለማያውቁ ኹሉንም እንዳልነበረ የሚያደርግ የጌታ ቀን ይመጣል ።

በጨለማ ስላይደልን እንደ ሌባ ሳይኾን፣ ለመጓዝ ለመሄድ እንደተዘጋጅን ሰው ስንጠብቅ መጥቶ ይወስደናል ። የጌታ ቀን ታላቅ ፍርድ የሚደረግበት ፣ዲያቢሎስ ተይዞ ከነጭፍሮቹ ወደ እሳት ባሕር የሚጣሉበት ፣ አሕዛብ ከፍርዱ የተነሳ የሚያለቅሱበት መሸሸጊያ የለሌበት ቀን ነው። ለጌታ ምርጦች ደግሞ የምስጋና የንግሥና የክብር ቀን ነው።ቍጣው በእኛ ላይ አይደለም ። በመጨረሻው መለከት ለእኛ የዘላለም ሕይወት ፤ለአሕዛብና ለሰይጣን የዘላለም ሞት ይኾናል ። ስለዚህም ለቍጣ አልመረጥንም ማለት ከታላቁ መከራ በፊት ወደ ሰማይ እንነጠቃለን ማለቱ አይደለም። የጌታ ቀን ለአሕዛብ ቍጣ የሚኾንበት ያ የመጨረሻው ፍርድ እንጂ ከመከራው ዘመን በፊት ስለመነጠቅ የሚናገር አይደለም ። አንዷን ጥቅስ ከተመለከትን እውነት ልመስል ይችላል እንጂ እውነቱ በመጻሕፍት የተገለጠ ነው።ከፍም ዝቅም ብለን ማንበብ አለብን፤መጽሐፍ ቅዱስ በግላችን ኾነኔን ይኽ ጽሑፍ ያዘጋጀውንም ጸሐፊው የሚለውንም ትተን ቃሉ የሚለው መሠረታዊ ትርጓሜ ምንድነው የሚለውን ማጥናት አለብን። መጽሐፍ "ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ፥" ማለት ጌታ በስውር ይመጣል፣

ስመጣ አይታየም ማለቱ አይደለም፤ የሚመጣበትን ቀን ሰውሮታል ማለት እንጂ፡፡ ስለዚህም አማኞችን ምልክቶቹን ስታዩ እወቁ፤ አሕዛብ ግን ሳያስተዉሉና ሰይነቁ ይመጣባቸዋል የሚል ነው፡፡

7ኛ. "በገዛ ራሱ ጊዜም ይገለጥ ዘንድ፥ የሚከለክለውን አሁን ታውቃላችሁ።የዓመፅ ምሥጢር አሁን ይሠራልና፤ ብቻ ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ አሁን የሚከለክል አለ። በዚያም ጊዜ ጌታ ኢየሱስ በአፉ መንፈስ የሚያጠፋው፥ ሲመጣም በመገለጡ የሚሽረው ዓመፀኛ ይገለጣል፤ ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ፥ የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው። ስለዚህም ምክንያት፥ በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ፥ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል። "2ተሰ 2፥6-12 ።

የክፍሉን ሃሳብ ከቁ.1 ጀምረን ብንመለከት የበለጠ ለመረዳት ይረዳናል፡፡ በቁ.1 ላይ ጳውሎስ ለተሰሎንቁ ሰዎች፣ስለ ኢየሱስ መምጣትና ወደ እርሱ ስለ ምንሄድበት ቅን የተደላደለ መረዳት እንዲኖር ለምስረዳት ይፈልጋል፤ ከዚህ በፊት በቃል ይሁን በጽፉፍ በተማሩት እውቀት ድንግዝግዝታ እንዳይኖር ለማድረግ፡፡ በዚህም የጌታቀን ደርሷል ብላችሁ አትንወጡ ይላቸዋል፡፡ በቁ.3 ላይ ኢየሱስ ክህደቱ ወይም ዓመፃ ሰው ከመገለጡ/ከመምጣቱ/ በፊት አይመጣም ይላቸዋል፡፡ በቁ.4 ዓመፃ ሰውም ስገለጥ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ በቁ.5 ይህንን እውነት ከዚህ በፍት ማስተማሩን ያሳስባል፤ እንዲያስተዉ፡፡ በቁ.6-7 አሁን የዓመፃ ሰው ጊዜ ብሆንም እንዳይገለጥ መከለከሉን ያስታውቃል፡፡ ደግሞም ጳውሎስ አሁን የሚከለክለው ምን እንደሆነ ታዉቃላችሁ በማለት ፤ በዚህ ነገር ላይ ከዚህ በፊት በማስተማሩ በስም ሳይገልጥልን ያልፋል፡፡ የዓመፃ ምስጢር አልተገለጠም እንጂ አውንም በስውር ይሰራል፤ የለም አልተባለም፡፡

አውሬው በግልጽ እንዳይሠራ የሚትከለክለው ቤተክርስቲያን ስላልተነጠቀች ነው፤ ከመንገድ እስኪትወገድ የሚለው የቤተክርስቲያን መነጠቅን ያመለክታል[11] የሚለው የመጋቢ ተኩ ሃሳብ ከመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ መልእክት ጋር ይቃረናል ።በእርግጥም በግልጽ እንዳይሠራ የምትከለክለው ቤተክርስቲያን ናት፤የሚትወገደው ደግሞ ግን ቤተክርስቲያን አይደለችም ። [በዚህ ክፍል ላይ አውረው በግልጽ እንዳይሠራ ቤተክርስቲያን መከልከሏ፤የቤተክርስቲያን ንግሥናና የሰይጣን ሺህ ዓመት መታሠር ጊዜ እንደኾነ ከላይ የተመለከትነው ሃሳብ ስያጸድቅ እናያለን ]። ክርስቶስ የአመጽ ሰው ሃሰተኛው ነቢይ ከመገለጡ በፊት አስቀድሞ አይመጣም ።አውሬውም ቤተክርስቲያን ታትማ ሙላቷ ሳይፈጸም ፤ሴቷ ጸሃይ ለብሳ ሳትገለጥ፣ ብርቱዎችን ሳይወለዱ፣ የእግዚአብሔር እስራኤሎች 144,000 ተብሎ በቊጥር አሃዝ የተመሰሉትን ተቈጥረው የማያልቁ ታትተመው ሳያልቁ፣ መለኮታዊ ሃይል ተሟልታ እንዲትበር እንዲታመልጥ በኃል ሳትሞላ፣ አውሬው

[11] ዝኒህ ከማሁ

በግልጽ አይመጣም። አውሬው በግልጽ የሚመጣው ቤተክርስቲያን ዝግጅቷን ስትጨርስ ስኾን፣ መጀመሪያ ከሰማይ ወደ ምድር ይጣላል ።ከዚያም የሰማይ መኖሪያውን ይለቃል። ከዚህ በኋላ በቀጥታ በግልጽ ይሠራል። ራዕ 12፡፡

ቤተክርስቲያን በአውሬው ላይ ነግሳ በኢየሱስ ስም ስልጣን ሥልጥናና ጠፍራ ከያዘችበት ፤ መንገዱን ከዘጋችበት ፤ ዝግጅቷን ስትጨርስ ወደ ሰማይ ሳይኾን በምድር ከእይታው ትሠወራለች ። በዚህ ክፍል ላይ ጳውሎስ የዓመፃ ሰው ከመገለጡ በፊት ቤተክርስቲያን መከልከሏን እንጂ ስትነጠቅ ወደ ሰማይ ስትሰበሰብ ለሰይጣን መግቢያ እንደሚኾን አያስረዳም።እንዲሁም የመጨረሻው የአመጻ ሰው የሚገለጠው ለ3ዓመት ከ 6ወር በታላቁ መከራ ስለኾነ ቤተክርስቲያን ነበረች። ምክንያቱም ወንድ ልጅ እንደተወለደ ነው ሰይጣን ወደ ምድር የተጣለው ። አንባቢ ያስተውል ። ከመንገድ እስኪወገድ የተባለችው ቤተክርስቲያን አይደለችም ። የሚወገደው ሰይጣን ነው።ለዘላለም እስከሚወገድ ድረስ ለጥቅት ጊዜ ከቤተክርስቲያን ሙላት በኋላ ይፈታል ።የተሰጠውን ጊዜ ስያበቃ ወደ እሳት ባሕርይ ውስጥ ይጣላል ።

8ኛ. " ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ተስፋ እንደሌላቸው እንደ ሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ፥ አንቀላፍተው ስላሉቱ ታውቁ ዘንድ እንወዳለን።ኢየሱስ እንደ ሞተና እንደ ተነሣ ካመንን፥ እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉቱን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና።በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህ ነውና፤ እኛ ሕያዋን ሆነን ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቀር ያንቀላፉቱን አንቀድምም፤ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን።ስለዚህ እርስ በርሳችሁ በዚህ ቃል ተጽናኑ።" 1ተሰ 4፥15- 18።

በዚህ ክፍል ላይ በግልጽ በሕይወት ስላሉት ቅዱሳን መነጠቅ ተጽፏል ።ሌሎች ክፍሎች ከመቅጽበት መለወጥ እንዳለ ብልጭታ ብሰጡም፣ ይኸኛው ክፍል በግልጽ በሕይወት ስላሉት መነጠቅ ያስረዳል ።የጳውሎስ ትኩረት በጌታ ኾነው ስለሞቱ ቅዱሳን መጨረሻ ማስረዳት ነው። አሕዛብ እንደሚያስቡት ስሞቱ ሕይወት መጨረሻ ሳትኾን ለአዲስ ሕይወት ጅማሮ እንደኾነ ያስረዳል ።

በዚህ ክፍል ላይ ከክፍሉ ሃሳቦች ትንሽ ጠጠር ያለች "ያንቀላፉቱን ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋል "የሚለው ይገኛል ።ይኸንን ለመረዳት የጳውሎስን ትኩረት መያዝ አለብን፤ ስለሞቱት ቅዱሳን እንደሚያስረዳ ። የሃሳቡ ቅደም ተከተል እንዲህ ነው፣

፩ኛ. ክርስቶስ ሞቷል ተነስቷል ይኸንን እወቁ የሚል ስኾን፣

፪ኛ. በክርስቶስ ኾነው የሞቱትን ጳውሎስ; "አንቀላፍተዋል" በማለት ነገሩን ለማስረዳት ያመቻቻል፣ ያንቀላፋ ይነሳል የሞተ ግን አይነሳም የሚል ዕሳቤ ስለነበራቸው ፣ በክርስቶስ ኾነው የሞቱትን አንቀላፍተዋል ይለናል ፣

፫ኛ. ክርስቶስ ዳግም ስመጣ የሞቱት ይነሳሉ፣

፬ኛ.ክርስቶስ ዳግም ስመጣ ያልሞቱት ቅዱሳን ይለወጣሉ ፣

፰ኛ. ክርስቶስ በቅዱሳን መላእክት ታጅቦ ይመጣል፣

ስለዚህ ስለሞቱት ቅዱሳን የሚሰጠው ግንዛቤ ፣አስቀድመው የትንሣኤ አካል ስለሚለብሱ አስቀድመው ከጌታ ጋር ይኾናሉ፤ማለትም ተነጥቀው አይደለም ፤ባሉበት በለበሱት አካል። ስለዚህም የሞቱት ክርስቶስ ስመጣ የሞቱትን ከነበሩበት ከተጣሉበት፣ ከወደቁበት፣ ከተቃጠሉበት፣ ከተሰጡበት ያመጣል ፤ያነሳል። በሕይወት ካሉት ቅዱሳን ቀድመው በአዲስ ማንነት ይገኛሉ ።ያንቀላፉቱን; እግዚአብሔር ክርስቶስ ስመጣ ከእርሱ ጋር በሕይወት ወዳሉት ያመጣል ፤ ያመጣል የተባለው ከሰማይ ወደምድር መጀመሪያ ከተነጠቁበት ሳይኾን በሕይወት ካሉት ቅዱሳን በሞት ከተለዩበት ስፍራ ያመጣል ማለት ነው። /ከጌታ ጋር የሚመጡት ከዚህ በፊት የተነጠቁ 24 ሽመግለዎች ናቸው የሚባለውም መሠረት የለውም/፡፡ በክርስቶስ መምጣት ያልነበሩ ቅዱሳን ወደ መኖር ይመጣሉ ።ይኸም ቀድመው መነሳታቸውን፣ ክርስቶስ በባሕር ፣በእሳት ፣ለአውሬ እራት የኾኑትን ፣የሉም ጠፍተዋል፣ሕይወታቸው አልቀዋል የተባሉትን፥ ክርስቶስ ስመጣ እግዚአብሔር ለሞቱት ሕይወትን በመስጠት ያስነሳቸዋል ፤ ያመጣቸዋል ማለት ነው። ምክንያቱም ክርስቶስ ስመጣ በቅዱሳን መላእክት እንደታጀበ ብቻ ክፍሉ ያስረዳል ። ጳውሎስም ለማስተማር የፈለገውን ሃሳብ በሚገባ አሳይቷል ። የሞቱት ወደ መኖር ይመጣሉ። እንደ ሞቱ ጠፍተው አይቀሩም ።

በዚህ ክፍል ላይ; በመጨረሻው ፍርድ በጉ ሠራዊቱን እያስከተለ በመለከት በመላእክት ድምጽ በግልጽ ታጅበው ስለመምጣቱ እንጂ ቅድሜ መከራ ይነጠቃሉ የሚል ሃሳብ የለም። ይኽ ቅድሜ መከራ መነጠቅ ከኾነ; የሞቱት የሚነሱት ስንት ግዜ ነው? በሕይወት ያሉት የሚለወጡት ስንት ግዜ ነው ? መጽሐፉን መንፈስ ቅዱስ በገለጠበት መንፈስ ማንበብ አስፈላጊ ነው። ከመሃል እየመዝግን ቃሉ ማለት የፈለገውን ትተን የራሳችን ትርጓሜ ለመስጠት መድፈር በነፍስ ላይ መቀለድ ነው። ጳውሎስ ይኽንን ስገልጽ ይመስለኛል አላለም፤ ታላቁን እውነት ከራሱ ሃሳብና ዕሳቤ ተነሳስቶ ስላልተናገረ፣ "በጌታ ቃል" እላለሁ በማለት አመላክቷል ። /ጳውሎስ ተጽናኑ ያለው ቅድሜ መከራ ንጥቀት አለ ብሎ ሳይሆን የሞቱት ቅዱሳን ሞተው ስለማይቀሩ ነው፡፡ ምክንያቱም ያዘኑት ስለሞቱት እንጂ መከራ ይመጣል ስለተባለ አይደለም፡፡ አውዱ ይህንን ያረጋግጣል/፡፡

9ኛ. "የጥፋት ውኃም መጥቶ ሁሉን እስከ ወሰደ ድረስ እንዳላወቁ፥ የሰው ልጅ መምጣት ደግሞ እንዲሁ ይሆናል።በዚያን ጊዜ ሁለት ሰዎች በእርሻ ይሆናሉ፤ አንዱ ይወሰዳል አንዱም ይቀራል፤ ሁለት ሴቶች በወፍጮ ይፈጫሉ፤ አንዲቱ ትወሰዳለች አንዲቱም ትቀራለች።" ማቴ 24፥39-41። ይኽንን ሃሳብ ኢየሱስ ስለመጨረሻው ዘመን ከተናገረበት ከምዕራፍ 24 ጀምረው ያለውን በዝርዝር እንመለከታለን ። ሙሉ መረዳት እንዲኖረን ።ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ወደ መቅደሱ ጅራፍ ይዞ የገባውን ክስተት ከም.21-23 ያለው ቃል ያስረዳል ። ከመቅደስ ወጥቶ ስሄድ በም.24 ላይ

ደቀመዛሙርቱ ጥያቄ አቀረቡ፡- "ኢየሱስም ከመቅደስ ወጥቶ ሄደ፥ ደቀ መዛሙርቱም የመቅደሱን ግንቦች ሊያሳዩት ቀረቡ። እርሱ ግን መልሶ፡- ይህን ሁሉ ታያላችሁን? እውነት እላችኋለሁ፥ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ አይቀርም አላቸው።" ማቴ 24፥1-2። የኢየሱስ መልስ አስደንጋጭ ነበር፤ ደቀመዛሙርቱ በሚያሳዩት ሕንፃ ከመደነቅ ይልቅ፣ እንዲህ እንዳማረበት እንደማይቀር እንደሚፈርስ ነገራቸው ። በዚህ ደቀመዛሙርቱ በይበልጥ ስለዚህ ነገር ስለ ቤተመቅደስ መፍረስ ማወቅ ፈልገው ጥያቄ አቀረቡ፡-

"እርሱም በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ፥ ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀርበው፡- ንገረን፥ ይህ መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድር ነው? አሉት።" ማቴ 24፥3 ። ከደቀመዛሙርቱ ጥያቄዎች ፣ ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስ ዳግም እንደሚመጣ እንደሚያምኑና እንደሚያውቁ ደግሞም በመጪው ዘመን የሚኾን ስለኾነ፣ የኢየሱስን መምጣት ከመቅደሱ መፍረስ ጋር በአንድ ጊዜ እንደሚኾን ማሰባቸውን እንረዳለን። ጥያቄአቸውን ፩ኛው. ስለ ኢየሩሳሌም መቅደስ መፍረስ መቼ እንደሚኾን ለማወቅ ስኾን፣ ፪ኛው. የኢየሱስ መምጣትና ምልክቱ ምንድነው የሚለው ነው። ኢየሱስ ለጥያቄአቸው [የቤተመቅደስ መፍረስና ስለመምጣቱ] የሰጠው ምላሽ አጠቃላይ ማስጠንቀቂያና ምልክት ነው ፡-

"ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፡- ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ።ብዙዎች፡- እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና፤ ብዙዎችንም ያስታሉ።ጦርንም የጦርንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ፤ ይህ ሊሆን ግድ ነውና ተጠበቁ፥ አትደንግጡ፤ ዳሩ ግን መጨረሻው ገና ነው።ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣልና፥ ራብም ቸነፈርም የምድርም መናወጥ በልዩ ልዩ ስፍራ ይሆናል፤እነዚህም ሁሉ የምጥ ጣር መጀመሪያ ናቸው።በዚያን ጊዜ ለመከራ አሳልፈው ይሰጡአችኋል ይገድሉአችሁማል፥ ስለ ስሜም በአሕዛብ ሁሉ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ።በዚያን ጊዜም ብዙዎች ይሰናከላሉ እርስ በርሳቸውም አሳልፈው ይሰጣጣሉ እርስ በርሳቸውም ይጣላሉ፤ብዙ ሐሰተኞች ነቢያትም ይነሣሉ ብዙዎችንም ያስታሉ፤ከዓመፃም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች።እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል።ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፥ በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል። " ቊ.4-14።

ማስጠንቀቂያው ሃሰተኞች ክርስቶሶች እንደሚነሱ፣ ጦርነት እንደሚኖር፣ የአንድ ወገንና የመንግስታት ጦርነት እንደሚካሄድ ፣ ይኽ ኹሉ ስኾንም መጨረሻ ገና እንደኾነ አስረዳቸው ። ስለዚህም አንባቢ እነኚህ ክስተቶች ከታርክና አኹን እየኾነ ያለውን በመመልከት ወደ መጨረሻ እየሄድን እንደኾነ ፣የትንቢቱ ቃሉ እየተፈጸመ እንደኾነ መረዳት እንችላለን ።ይኽ ከራእይ ምዕራፍ ስድስት ከአንደኛው እስከ አምስተኛው ማህተም ጋር ካለው ስሙም እንደኾነ አንባቢ ማስተዋል ይችላል ። በዚህ ላይ የሐሰተኛ ትምህርት ጥቃት ፣ብዙዎችንም ማሸነፍ፣ የእርስበርስ የአንድ ወገኖች ጦርነትና የዓለምአቀፋዊ ጦርነቶች

[በመንግስታት] እንደሚካሄዱ ተመልክተናል ። ይኽ የትንቢት ቃል ኢየሱስ የገለጠው ከተገለጠበት ጊዜ ጀምሮ እየኾነ ያለው ስኾን፣ መጨረሻው ገና መኾኑን ፣መምጣቱ የዓለም ፍጻሜ ገና መኾኑን ያመለክታል ።ብዙዎች ሳይረዱ በእነዚህ ክስተቶች የመጨረሻው እንደኾነ ተረድተው ስስቱና እስካሁን ጌታ አልመጣም በማለት እንደማይመጣ በማሰብ ሰነፎች ኾነዋል፤ ተኙተዋል ።እነኚህ ምልክቶች መጨረሻው ገና መኾኑን የሚገልጹ እንደኾኑ ልናስተውሉ ይገባናል ። እነዚህ የመጨረሻው እንደ ቀረቤ ጠቋሚ የምጥ ጣር መጀመሪያዎቹ ናቸው ። የምጥ ጣር መጀመሪያ የሰይጣንን ወደ ምድር መውደቅ ፣የአውሬውን መነሳት የሚያመለክት ነው። ታላቁን ምጥ መግቢያ የሚገልጽ ነው ።

የጌታ መምጣት የመጨረሻው ከመኾኑ በፊት፣ የሐሰተኞች ነቢያት መነሳት ብዙዎችንም ማሳት እስካሁን እየበዛ የመጣ ነው፤የብዙዎች ሃሰተኞች መነሳት ይኽንን ቃል አረጋግጧል ።እነዚህ የእግዚአብሔርን ቃል ቀላቅለው ሸቃቅጠው ለገዛ ፍላጎታቸው ይኾን ዘንድ አጣመው የሚሰብኩ እንደሚሉት አይደለም። አሕዛብ ይድኑ ዘንድ የወንጌል እድል ስለተሰጣቸው ፣ የመንግሥቱ ወንጌል እስካሁን እየተሰበከ ይገኛል ። ሰዎች ይድኑ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር አገዛዙ ይገቡ ዘንድ፣ ከሰይጣን እስራት ይፈቱ ዘንድ የመንግስቱ ወንጌል ክርስቶስ ዳግም ከመምጣቱ በፊት፣ ከመጨረሻው በፊት ይሰበካል ፤እየተሰበከ ይገኛል ።ሃሰተኞች እንደሚሉት ወንጌልን እንደሚሸቃቀጡት አይደለም ። የጸጋ ወንጌል እንጂ አኹን የመንግሥቱ ወንጌል የለም፤አይሰበክም በማለት ብዙዎችን እንደ አዋቂ ስያምታቱ ቆይተዋል። ጆሮ ያለው ይስማ ። አዕምሮ በሰይጣን ካልተያዘ በስተቀር የመንግሥቱን ወንጌል በክርስቶስ ሥራ እንዲያ በጸጋ በእምነት እንዲድኑ ጌታ ያዘጋጀውን የምስራች ፣ በዘንደው መንፈስ እየተመሩ [በስውር] ለዓላማቸው አልመች ስላለ እያጣመሙ በእግዚአብሔር ቃል ላይ በድፍረት ይናገራሉ ፤ያስተምራሉ ።ብዙዎችን ያስታሉ።

[1]"እንግዲህ በነቢዩ በዳንኤል የተባለውን የጥፋትን ርኩሰት በተቀደሰችው ስፍራ ቆሞ ስታዩ፥ አንባቢው ያስተውል፥ በዚያን ጊዜ በይሁዳ ያሉት ወደ ተራራዎች ይሽሹ፥ በሰገነትም ያለ በቤቱ ያለውን ሊወስድ አይውረድ፥በእርሻም ያለ ልብሱን ይወስድ ዘንድ ወደ ኋላው አይመለስ።በዚያችም ወራት ለርጉዞችና ለሚያጠቡ ወዮላቸው።ነገር ግን ሽሽታችሁ በክረምት ወይም በሰንበት እንዳይሆን ጸልዩ፤በዚያን ጊዜ ከዓለም መጀመሪያ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያልሆነ እንግዲህም ከቶ የማይሆን ታላቅ መከራ ይሆናልና።**እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም ነበር፤ ነገር ግን እነዚያ ቀኖች ስለ ተመረጡት ሰዎች ያጥራሉ።**በዚያን ጊዜ ማንም፡- እነሆ፥ ክርስቶስ ከዚህ አለ ወይም፡- ከዚያ አለ ቢላችሁ አትመኑ፤ ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፥ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ። እነሆ፥ አስቀድሜ ነገርኋችሁ። እንግዲህ፡- እነሆ፥ በበረሀ ነው ቢሉአችሁ፥ አትውጡ፤ እነሆ፥ በእልፍኝ ነው ቢሉአችሁ፥ አትመኑ፤መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ፥ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ

ይሆናልና፤በድን ወዳለበት በዚያ አሞራዎች ይሰበሰባሉ።" ቍ.15-28። ይኸንን መልስ ደቀመዛሙርቱ ካቀረቡት ከኹለቱ ጥያቄዎች አንፃር እንረዳለን ፤ስለ ኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ መፍረስና ስለ ኢየሱስ ዳግም ምጽአት ።

ስለ ኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ መፍረስ አንፃር ፣ ትንቢቱ በ70 ዓ.ም ተፈጽሟል ። የጥፋት እርኩሰት የተባለው በተቀደሰችው ስፍራ መቅድስ ላይ የቆመው ፣ መቅደሱን እንዳልነበረ ለማድረግ የመጣ የሮም ቄሳር ነው። ይኸ ጊዜያዊ ትንቢት በ70ዓ.ም የተፈጸመ ስኾን ታርክም ስለ ኢየሩሳሌም መቅደስ መፍረስ በ70 ዓ.ም እንደኾነ ይመሰክራል ። ስለዚህ መቅደሱ ከመፍረሱ በፊት ከዚያች ከተማ ሽሹ የሚል መልእክት አስቀምጧል ።ይኸ ትንቢት በኢየሩሳሌም ላይ ብቻ የሚደረግ ስለኾነ የሽሽታውን ሁኔታ ፣ እርጉዞችን የሚያጠቃ ነው።ምክንያቱም በዚህ የሚያመልጡት የሮጡት ብቻ እንጂ ያመኑቱ ብቻ አይደሉም ።ስለዚህም ያመኑትም ወደ ሌላ ከተማ መሮጥ አለባቸው ። መከራው በኢየሩሳሌም ብቻ ስለኾነ ለሽሽት አመቺ ወቅት እንዲኾን ፣ ለሞት አሳልፎ እንዳያስጥ ፤ ማምለጥ ስችሉ ወደኃላ እየተመለሱ እንዳይወሰዱ፣ ከመከራው እንዲቀሩ እንዲተርፉ ፣ በመከራው እንዳይነጠቁ ያሳስባል ። ከጥያቄዎቹ እና ከመልሱ አንፃር ስንመለከት በአንድ በኢየሩሳሌም ላይ ብቻ የተወሰነ ስለኾነ ስለ ቤተመቅደስ መፍረስ እንደተነገረ እንደኾነ እንረዳለን ።

ስለ ዓለም መጨረሻው ከመቅደስ መፍረስ ጋር ተያይዞ የተነገረውን ወቅቱን ለይተን ለመረዳት የክፍሉን አውድ በትህትናና በትዕግሥት ልንመለከተው ይገባናል ። የጥፋት እርኩሰት መቅደስ ላይ መቆም ፣የአውሬው ዋነኛው መዲና ኢየሩሳሌም መኾኑን ያመለክታል “በድናቸውም በታላቂቱ ከተማ አደባባይ ይተኛል እርስዋም በመንፈሳዊ ምሳሌ ሰዶምና ግብጽ የተባለች ደግሞ ጌታቸው የተሰቀለባት ናት።” ራእይ 11፥8 ፣ የጥፋት እርኩሰት በኢየሩሳሌም ስነግሥ በግልጽ ስመለከ፣ መሥራት ስጀምር፣ ወደ ምድር ሰይጣን ወርዷል ማለት ነው። ይኸ ስኾን ታላቁ መከራ 1260 ቀን ስቃይ በምድራዊያን ላይ ይጀመራል ማለት ነው። **እነዚህ የመከራ ቀኖች ጥቅት ናቸው ፤እንዲያ ባይኾን ብዙዎችን ያስት ነበር ማለት ነው።** መከራዎችን ዮሐንስ ስመለከት ማንስ ልድን ይችላል ብሎ እንደነበረ አይተናል ራእ ም.6። ሰዎች እንዲድኑ የመከራው ጊዜ ጥቅት ጊዜ ብቻ የሚቆይ ይኾናል ማለት ነው።

ሃሰተኛው አውሬው መገለጥ [ከምድር የወጣው አውሬ ሃሰተኛው ነቢይ ፤የጥፋት ልጅ] ክርስቶስ በሰማይ ነው፣በምድር ነው፣ በተራራ ነው፣ .ወዘተ. እያሉ በዚያ ጊዜ ልያስቱ ይሞክራሉ ።እናንተ ግን አትከተሉት ፤ እወቁ የሚል ነው። ይኸ የአውሬው መገለጥ በመቅደስ መቆም የምጥ ወቅት መኾኑን አንባቢው ያስተውል ።ስለዚህም ኢየሱስ በዚያን ጊዜ በስውር እንዳለና ፣እንደሚገኝ ብናገሩም አትመኑ።ምክንያቱም የኢየሱስ መምጣት ግልጥ ነው። መብረቅ ቦግ ብሎ በዓለም እንደሚታይ የኢየሱስ መምጫ መገኛ መኖሪያ ስመጣ በግልጥ ይታያል ። እነዚህ ሃሰተኞች የዘንዶው መንገድ ጠራጊዎች በዚያ ሰዓት ኢየሱስ በስውር እንዳለ ያስተምራሉ ፣ስርግ በስውር እንደሚኾን ያስተምራሉ ፣ እናንተ ግን እወቁ አትመኑ ፤አትከተሏቸው። ስለዚህ ከኢየሱስ መልስ የቤተመቅደስ መፍረስ እና ስለመምጣቱ የነገረው ምልክቱ ተመሳሳይ እንደኾነ

እንረዳለን ። ይኹን እንጂ **በኢየሱስ መምጣት ማንም የትም መሸሽ አይችልም** ።ምክንያቱም ሙሉ ምድር የሚያጠፉ ቀኣጣ ስለሚገለጥ ። የወቅቱ ቀረምት መኾን አለመኾን ለውጥ አያመጣም ።እንዲሁም ማንም ወደሌላው ሃገር ከተማ ተራራ በመሸሽ ልያመልጥ  አይችልም ።

ከዚያች ወራትም መከራ በኋላ ወዲያው ፀሐይ ይጨልማል፥ ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም፥ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፥ የሰማያትም ኃይላት ይናወጣሉ። በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል፥ በዚያን ጊዜም የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ይላሉ፥ የሰው ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል፤ መላእክቱንም ከታላቅ መለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፥ ከሰማያትም ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከአራቱ ነፋሳት ለእርሱ የተመረጡትን ይሰበስባሉ። ማቴ 24፥29-31 ።  ከዚያች ወራት መከራ በኋላ [አውሬው በነገሠበት ከ42 ወራት ታላቁ መከራ በኋላ ] ኢየሱስ ይመጣል ። ኢየሱስ ስመጣ ምልክት በሰማይ ይታያል ። ምድር ላይ የሚኖሩ ያዩታል ። የመላእክት መለከትም ያስተጋባል ። ጌታ በግልጽ እንዳስተማረው ፣ ከአውሬ በኢየሩሳሌም መዲናነት ፣በግልጽ በምድር ላይ ስገለጥ ታላቅ መከራ ይኾናል ።ከዚያም በኋላ የተሰጠው ጥቅት ጊዜ ስያበቃ የኢየሱስ መምጣት ይኾናል ።

ስለ መምጣትህ ንገረን ያሉት በዝርዝር አስረድቷል ።ጌታ ኹለት ጊዜ እንደሚመጣ ፣በስውርም እንደሚመጣ ፣ አልገለጸም ። የኢየሱስ መምጣት የዓለም መጨረሻ ነው። ታዲያ ስለመጨረሻው ዘመን ስያስተምር ቅዱሳን ቀድመው እንደሚነጠቁ እንዳል ለጠ ይረዷል ፤ ይኽ ትውልድ አያልፍም በማለት በመከራው ማለፋቸውን አስረድተዋል ።ደግሞም በዚያ መከራ ሰዓት  ሳይታለሉ ጸንተው እንዲቆሙ አስጠንቅቋል ። ኢየሱስ ስለ መምጣቱ ኾነ ስለ መጨረሻው ዘመን ስለ ታላቁ መከራ ስያስተምር ኹለቴ እንደሚመጣ አላስተማረም ።አንድ ጊዜ ብቻ እንደሚመጣ እንጂ ።

"ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም። የኖኅ ዘመን እንደ ነበረ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና።በዚያች ወራት ከጥፋት ውኃ በፊት፥ ኖኅ ወደ መርከብ እስከገባበት ቀን ድረስ፥ ሲበሉና ሲጠጡ ሲያገቡና ሲጋቡም እንደ ነበሩ፥ የጥፋት ውኃም መጥቶ ሁሉን እስከ ወሰደ ድረስ እንዳላወቁ፥ የሰው ልጅ መምጣት ደግሞ እንዲሁ ይሆናል። በዚያን ጊዜ ሁለት ሰዎች በእርሻ ይሆናሉ፤ አንዱ ይወሰዳል አንዱም ይቀራል፤ ሁለት ሴቶች በወፍጮ ይፈጫሉ፤ አንዲቱ ትወሰዳለች አንዲቱም ትቀራለች።" ማቴ 24፥36-41።

በዚህ ክፍል ላይ  በኢየሱስ መምጣት በዚህ ምድር ላይ በኖኅ ጊዜ እንደኾነው እንደሚኾን ተገልጿል፤ ይወሰዳል ይቀራል፤ትወሰዳለች ትቀራለች ። እነዚህ ቃላቶች ለቅድሜ መከራ መነጠቅ አስተምህሮ የሚጠቀሱ አይደሉም ። አንባቢ ያስተውል። በኖኅ ጊዜ የጥፋት ውኃ ልመጣ ስል የሰው ልጆች አላወቁም ነበር፤ ኢየሱስ ስመጣም ምድራዊያን አያውቁም ።ቤተክርስቲያን እንደ ኖኅ ስትዘጋጅ ፤ዓለማውያን ደግሞ በጥፋታቸውም ይቀጥላሉ ።ምልክቶችን ስመለከቱም አያስተውሉም ። ስለዚህም መርከቡ ተሰርቶ እንዳለቀ ፣የጥፋት ውኃ መጥቶ ይወስዳል ፤ የሚመጣው ውኃ የጥፋት ውኃ

ነው።የሚወስደውም ይኸ የጥፋት ውኃ ነው። ከዚህ ጥፋት ውኃ ሳይወሰዱ መቅረት መትረፍ ነው። ልክ እንደዚህ እንደ ጥፋት ውኃ ኢየሱስም በታላቅ ቍጣ ይመጣል ፤ በቍጣው ስገለጥ በቍጣው የምወሰዱት ምድራዊውን ናቸው ። የሚቀሩት የሚተርፉት አስተውለው ተዘጋጅተው የኖሩ ናቸው ። የጌታ መምጣት በጥፋት ውኃ መመሰሉን ካስተዋሉ ይኸን መረዳት አያስቸግርም ። ይኸ ለቅድመ መከራ መነጠቅ የሚጠቀስ ሳይኾን ከመከራው ከአውሬው ከጥፋት ልጅ ከታላቁ ስቃይ በኋላ የሚመጣውን የሚያሳስብ ነው። የኢየሱስ መምጣትም በመከራው ያለፉትን በእርሱ ኾነው የሞቱትና በሕይወት ጸንተው ቆመው ያሉትን ለመቀበል ነው። ቅድሜ መከራ መነጠቅ የሰይጣንን ስውር ሥራ ነው፤ ሃይልን ቅዱሳን እንዳይለብሱ በማድረግ በቀላሉ አውሬው ስገለጥ ለማድቀቅ የሠራው የውሸት ትርክት ነው።

ዮሐንስ ታላቁን መከራ ስመለከት "ማንስ ልድን ይችላል?" የሚል ፍርሃት ያለውን ጥያቄ አቅርቦ ነበር። የዮሐንስ ፍርሃት ሥጋዊ ብቻ አይደለም ፤ በመንፈስ ነውና መንፈስ ቅዱስ ግልጠቱን ሰጥቷል። ምክንያቱም በታላቁ መከራ ጊዜ የመከራው ቀናት ያጠሩ [ትንሽ የኾኑ፣ ለጥቅት ጊዜ ብቻ የሚቆዩ] ባይኾኑ ሰው[የዳነው ጭምር መቆም አቅቶት መውደቁ የማይቀር ይኾን ነበር፤ ወደ ክህደትም የመግባት እድልም እጅግም ሰፊ ይኾን ነበር። “እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም ነበር፤ ነገር ግን እነዚያ ቀኖች ስለ ተመረጡት ሰዎች ያጥራሉ።” ማቴ 24፥22። እነዚህ የተመረጡት በመከራው ጊዜ የሚድኑቱ ስኾኑ ከሚገባው በላይ መከራ እንዳይቀበሉ የመከራውን ቆይታ ጌታ እንዲያጥር አድርጓል ። በጥልቀት ሃሳቡን ከራእዩ ጋር ላገናኝ። የታላቁ መከራ ቆይታ 3 ዓመት ከተኩል ነው። በማቴዎስ ወንጌል "እነዚያ ቀኖች ባያጥሩ ሥጋ የለበሰ ኹሉ ባልዳነ ነበር" የሚለው በታላቁ መከራ ጊዜ እንኳን መከራ ብቻ እንዳይኾን ወይም በመከራው የተወሰነ እረፍት ጊዜ እንዳለው; መከራው ረገብ የሚልበት ጊዜ እንዳለው ይጠቍማል ። ይኸንን በ6ኛው ማህተም መፈታት በታላቁ መከራ ጊዜ፣ መከራው እያየለ ስመጣ፣ ዮሐንስ "ማንስ ልድን ይችላል?" ከሚለው ጥያቄ ጋር ስናስተያይ፣ ጌታ መከራውን ለሚታተሙት ለተመረጡት ስባል እንዳይቀጥል በማድረጉ ፣ ታላቁ መከራ; መከራ ብቻ ኾኖ እንዳይቀጥል መከራውን ማሳጠሩን እንረዳለን ። “የአምላካችንን ባሪያዎች ግምባራቸውን እስክናትማቸው ድረስ ምድርን ቢሆን ወይም ባሕርን ወይም ዛፎችን አትጕዱ አላቸው።” ራእይ 7፥3። ደግሞም ስለተመረጡት ስባል መከራው ጋብ እንዲልና በዚያ በታላቁ መከራ መሃል ወንጌል የሚሰበክበት ጊዜ እንዳለው በሌሎች መግለጫዎች በተሰጡት ፍንጮች ማየት እንችላለን። ለምሳሌ :-

ራእይ 10፥[9] ወደ መልአኩም ሄጄ፡- ታናሺቱን መጽሐፍ ስጠኝ አልሁት። እርሱም፡- ውሰድና ብላት፥ ሆድህንም መራራ ታደርገዋለች በአፍህ ግን እንደ ማር ትጣፍጣለች አለኝ።[10] ከመልአኩም እጅ ታናሺቱን መጽሐፍ ወስጄ በላኋት በአፌም

እንደ ማር ጣፋጭ ሆነች፤ ከበላኋት በኋላም ሆዴ መራራ ሆነ።[11] በብዙ ወገኖችና በአሕዛብም በቋንቋዎችም በነገሥታትም ላይ እንደ ገና ትንቢት ትናገር ዘንድ ይገባሃል ተባለልኝ።

በዚህ ክፍል ላይ ጌታ በዓለም የሚሰጣቸውን ማስጠንቀቂያዎችን የሚያሳይ ስኾን፣ ለዓለም ፍጻሜ ለመኾን የመጨረሻው የ7ኛው መለከት መነፋት ስቀረው፣ ጌታ በ6ኛው መለከት ላይ የሚያደርገውን ያትታል ፤ራእይ ም.10። 6ኛው መለከት የታላቁን መከራ ጊዜን ኩነት የሚያብራራ ስኾን፣ ሰዎች መቅሰፍቶች ስወርዱም ንስሐ መግባት ባለመቻላቸው ፣ አገልጋዮች ለዚያ ጊዜ የተጠበቁት ፣ መራራ አገልግሎት ተጋድሎ እንዲያደርጉ ያደርጋል ። ዮሐንስ ስበላ ጣፍጦ ፥በኾዱ ገብቶ ሥሠራ ግን መራራ መከራ ስቃይ ያለበት አገልግሎት እንደተሰጠው ይጠቊማል። ይኽም በዚያ ሰዓት "ትንቢት ልትናገር" ይገባሃል ተብለው አሕዛብ ወደ እርሱ ፈቀቅ እንዲሉ መከራ መሃል የሚሰብኩትን ያመለክታል ። ይኽ በመከራ ጊዜ የሚኾን በመኾኑ;መከራው መከራ ብቻ ኾኖ እንዳይቀጥል ፣ምናልባት ከተመለሱ ተብሎ የንስሐ እድል፣ መከራው ጋብ  ተደርጎ መሰጠቱን ያሳያል ። የንስሐ እድል ብሰጥም የተመረጡት እንደ ማህተሞቹ ምስጢር የሚድኑ ስኾን፣ እንደ ማስጠንቀቂያዎቹ ምስጢር ደግሞ እርኩሳን እየረከሱ በጥፋታቸው እንደሚቀጥሉ ያሳያል ። ነገርግን በታላቁ መከራ ጊዜ መከራ ብቻ እንዳይኾን ብደረግም ጊዜው ብያጥርም፣ ያጠረበት ምክንያት ሰዎች እንዲድኑ ስኾን፣ የዳኑት ድነው እንዲቀሩ ወደኋላ እንዳይመለሱ መከራው "ለተመረጡት"ስባል እንዳይቀጥል ተደርጓል ።  የክፍሉ ሃሳብ የሚያብራራ ይኽ ነው እንጂ ስለተመረጡት ስባል ያጠረው ቀን ፣ መነጠቅን የሚያመላክት አይደለም ። ጆሮ ያለው ይስማ።

※አሁን አሁን የማቴዎስ መንጌል ም.24 ስለ ቅድሜ መከራ ንጥቀት አስተምህሮ እንደማይሆን ስለተረዱ መምህራኑ አዲስ ሙግት አደራጅተዋል፡፡ ይህ ክፍል ከቤተክርስቲያን ንጥቀት በኃላ ያለውን ያመላክታል በማለት/ ያረድ ዮሐንስ፣ድንቅ ፍጻሜ፣ገጽ 71፣2014ዓ.ም ዕትም /፣ ይወሰዳል ይቀራል ትረጓመአቸው እንደማይሆን አስረድተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ጌታችን በክፍሉ የተናገረው ስለ ቤተመቅደሱ መፍረስ ጭምር ነውና አስከድም እልለሁ፡፡

***በእግረ መንገዴ ኢየሱስ ስለመምጣቱ  ቀን ኢያስተማረ "ቀኑን አላውቅም"  ማለቱ ምን ማለት እንደኾነ መረዳት ጥሩ ይመስለኛል ።** ብዙዎቻችን ስለ ኢየሱስ ሙሉእ ሰው|| መኾን ብናምንም እንኳን ቃሉ የሚለውን መቀበል ግን ይከብደናል፤ ይጎረብጠናል። በመጀሪያ ቃል [መለኮት] ብቻ ነበር። [የሐ1]። ሰውን ለማዳን; መለኮት ሰው[ም] ኾነ። መለኮት ሰውነትን ለራሱ ገንዘብ አደረገው ። እንደ መከራየት ወይም ለጊዜው እንደመጠቀም በሰው ላይ አላደረም ። ሰዎች የእግዚአብሔር ማደሪያዎች ናቸው፤ መለኮት ሰው ላይ እንዲያ አላደረገም፤ራሱ ሰው ኾነ እንጂ። በመለኮት ማንነቱ ላይ ሰውነትን ያዘ። ለዚህም ነው መጽሐፍ "እግዚአብሔር በገዛ ደሙ ዋጀ" የሚለው ።ሐዋ 20፥28። ሰውነት የራሱ ስለአደረገው።

ሰው ለማዳን መለኮት ሰው መኾን ስለ አስፈለገው ሰውነትን ማጥፋት ፣ መዋጥ ፣ መቀነስ፣ መቀላቀል አላስፈለገውም ።ምክንያቱም ሰው ስኾን; ለሥራው ንፁህ ሰው መኾን ተገብቶአልናል ። ደግሞም አምላክነቱንም አልጣለም ። ምክንያቱም

አምላክነቱን ከጣለ "የእግዚአብሔር ብቸኛ ልጅ" አይባልምና፤ ማንነትም አይጣልም አይቀየርምና፤ ቋሚ ባሕርይ ነውና። ስለዚህም መለኮት ከክብሩ እንጂ ከማንነቱ አልወረደም ። ይኸንን እንዲህ የቀደሙት አመሳጥረውታል ፡-

በክርስቶስ አንድ አካል ሁለት ባሕርያት አሉ። ሰውነት እና መለኮትነት ። ያለመጠፋፋት፤ ያለመዋዋጥ፤ በመጠባበቅ፤ያለመቀላቀል ይኖራሉ ። ምንም እንኳን ሰውነት በግዝፈት ብታይም ከመለኮት ተልቆ መለኮትን ውጦ አይኖርም፤ አይታይም ። ምንም እንኳን መለኮት አምላክ ብኾንም ሰውነትን አልቀነሰም፤አላጠፋም ። ስለዚህም ምክንያት በአንድ አካል ሙሉእ መለኮት እና ሙሉእ ሰውነት ይኖራል እንላለን ። ግሩም ነው። ምስጢርም ነው።

ይኸንን እንዲህ ካልን እንደ ሃገር በቀል እሳቤው እንደ "ካራዎች"ወገን ፥ ወልድ የራሱ መለኮት ስላለው መንፈስ ቅዱስ አላስፈለገውም፤ አልተቀባም[12] አንልም ። መንፈስ ቅዱስ ከፅንሰት[ሉቃ1] እስከ መቃብር [ሮሜ8፥11] አልፎም መስዋዕትን እስከማቅረብ ከእርሱ ጋር ነበር ። ዕብ9፥14። በምድር ስመላለስ መንፈስ ቅዱስ ያግዘው ነበር። ቃሉም በመንፈስ ቅዱስ የተቀባ [የተሞላ የተቆጣጠረው] ነው ይላልና ።[ሉቃ4፥17] ። ክርስቶስ በአምላክነቱ; ሰውነቱ ላይ ተጽዕኖ አላደረገም ፤መንፈስ ቅዱስ የሚያስፈልገውን ኹሉንም ያደርግ ነበር። ለእኛ እንዳስፈለገ ኹሉ;ለክርስቶስ ሰውነትም አስፈልጓል ።

የኢየሱስ ሰውነት አስተዳደግ ምትሀታዊ አይደለም ። እንደ እኛ ነው እንጂ ፤ የእግዚአብሔር ልዩ ግቡኝት የነበረው ። በመንፈስና በጉልበት [በዕድሜ] ከመጠንከር እስከ በጥበብ እየተሞላ እስከ ማደግ እንደኾነ ይገልጻል ። “ሕፃኑም አደገ፥ ጥበብም ሞልቶበት በመንፈስ ጠነከረ፤ የእግዚአብሔርም ጸጋ በእርሱ ላይ ነበረ።” [ሉቃ 2፥40]። ከሕፃኑ ዕድሜ መጨመር; አስተዳደግ ጋር ጥበብም እየተጨመረ እየሞላው እንዳደገ እንረዳለን ። ይኸ እውነት ነው።

እንዲህ ከኾነ; ሰውነቱ [በቃል] በአምላክነቱ ተጽዕኖ ስር ሳይኾን በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር መኾኑን እንረዳለን ። ስለዚህም ለክርስቶስ ሰውነት ጥበብ [ዕውቀትና ማስተዋል] ከአብ በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጥና የሚጨምር ነው። በመንፈስ ቅዱስ መቀባቱን ካመንን ይኸንን አለመቀበል ግማሽ እምነት ወይም ክህደት ይኾናል።

ኢየሱስ በሰውነቱ በመንፈስ ቅዱስ እገዛ [ማስተዋልና መረዳት] ለአብ በሚገባ መታዘዙ ፣ ቃሉ እንዲህ ይገልጻል “ምንም ልጅ ቢሆን፥ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ፤” [ዕብ5፥8] ፣ ይለናል ። እኛ እያመጽን ከስህተታችን ስንማር፣ ክርስቶስ ግን በመታዘዝ እየታዘዘ እየተማረ እየተማረ ሄደ፤ አገለገለ። ፈተናው እየጨመረ እየበዛ ስመጣ ፣ከእያንዳንዱ ፈተና በመታዘዝ ብቻ መማሩ የማስተዋል እድገት ተደርጎ ልቆጠር የሚችል ነው። መለኮታዊ ፈተና በራሱ አስተማሪና አሳዳጊ ነውና ። ሰውነቱ እንደተማረ ልንክደው አይገባንም ።

መንፈስ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ ሰውነቱን መርዳቱንና መቆጣጠሩን ከተረዳን፥ መላእክት እንኳን ኢየሱስን [ለሥጋው] እርዳታ አስፈልጎት እንዳገለገሉት መመልከት እይታችንን ያግዛል ። ማቴ4፤ ኢየሱስ ከሚቀበለው መከራ

12

ጭንቀት የተነሳ በፍራት ስጣጣር መጥተው ያገለግሉት ነበር። ሉቃ22፥ 43። ይኽ እውነት ነው። መራቡ፣መጠማቱ፣ ከሕመሙ የተነሳ መጮኹ፣ ማልቀሱ ፣ማዘኑ የእውነት እና ጥልቅም ነበር፤ ነው።

የመለኮት ሙሉአት በክርስቶስ ሰውነት ተገልጦ ይኖራል ማለት ፣ የአብ መለኮት በሰውነቱ ስላለው፥ የሰውነትን ባሕርይውን ውጥዋል ወይም ሰውነትን አዳፍኗል ማለት አይደለም ።ከላይ እያየን የመጣነው የወልድ መለኮት ሰውነቱን እንዳልዋጠ እና ለሰውነቱ መንፈስ ቅዱስ መሪ እንደኾነ ነው። በዚህም ይኽ ቃል የቃሉን እውነት ከላይ ያለውን ሃቅ የሚጣረስ እንዳይደለ መመልከት ተገቢ ነው። “በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራልና፤” ቆላ 2፥9። ማለት የአብ መለኮታዊ ባሕርይን የኢየሱስ ሥጋ አሳይቷል ወይም የማይታየውን የአብን ማንነት በሚሉአት ሰውነቱ ገልጿል ፤ተርኳል ማለት ነው።ይኽ "ኢየሱስ የአብ እውነተኛ ነፀብራቅ ነው" [ዕቤ1]፣ የሚለውን የሚገልጽ ነው።

የአብን ትክክለኛ ባሕርይን ሰውነቱ በመለኮት፥ ተለውጦ ወይም ተቀይጦ ወይም ተዳፍኖ ሳይኾን፣ ክርስቶስ በሰውነቱ ለሰዎች ልገባ በሚችል መልኩ አሳይቷል ማለት ነው። "ተረከው" ማለትም ሰውነቱ መለኮቱን ተረከው፤ገለጠው ፤ እንጂ መለኮት ሰውነትን አላሳየም አልተረከም። ቃል ሰው የኾነው ሰውነትን ለማሳየት ሳይኾን፣ መለኮትን ለመግለጥ ነው። [በባሪያ መልክ የአምላክን ባሕርይ ገለጠ እንጂ በመለኮት የሥጋን ባሕሪይ አላሳየም]

ስለዚህም ኢየሱስ ክርስቶስ በሰውነቱ የመምጫውን ቀኑንና ሰዓቱን አላውቅም ማለቱ እውነት ነው። “ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም።”[ማቴ 24፥36]። ምክንያቱም 1ኛ. ሰው ስለኾነ መንፈስ ቅዱስ ስላልገለጠው 2ኛ.የራሱ የቃል መለኮት ሰውነቱ ላይ ተጽዕኖ ስለማያደርግ፣ አላውቅም ማለቱ ትክክልና ልናምነው የተገባ ነው። ይኹን እንጂ ይኽ በሥጋው ወራት እንጂ አኹን የሚሠራ አይደለም ። ምክንያቱም፡-

አኹን ክርስቶስን በሥጋ በድካም ሰውነቱ [በውስንነቱ] አናውቀውም ።በትንሳኤው አካሉ በማንነቱ በክብሩ እንጂ። “..፤ ክርስቶስንም በሥጋ እንደ ሆነ ያወቅነው ብንሆን እንኳ፥ አሁን ግን ከእንግዲህ ወዲህ እንደዚህ አናውቀውም።” [2ኛ ቆሮ 5፥16]። ስለዚህም በሥጋው ወራት ስለተራበ አኹንም ሙብልን ይራባል፣ መጠጥን ይጠማል ብለን አናምንም ። ልክ እንደዚሁ በሰውነቱ በሥጋው ወራት "አላውቅም" ብልም፣ በአምላክነቱ በሥጋው ወራት እንኳን እያለ ፥ የሰው ልብን ሁሉንም መርምሮ የሚያውቅ ጌታ ነው[ዮሐ2]፤ ከእርሱ ፊት የተሠወረ ነገር አኹን የለምና ፤ በክብሩ ፊት ችሎና ቆሞ ተቋቁሞ መመልከት የሚቻለውም አኹን የለም።መጽሐፍ “ባየሁትም ጊዜ እንደ ሞተ ሰው ሆኜ ከእግሩ በታች ወደቅሁ። ቀኝ እጁንም ጫነብኝ እንዲህም አለኝ፡- አትፍራ፤ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ፥” [ራእይ 1፥17]፤ይላልና ክብር ኹሉ ለእርሱ ይኹን፤ አሜን ።

## 2.1 የክርስቶስ ስውር ዳግም መምጣትና ስውር ንጥቀት

ክርስቶስ ወደ ምድር [ሰው ኾኖ] ለማዳን ስመጣ በግልጥ ነበር የመጣው ፣ ለመፍረድ ዳግመኛ ስመጣም በግልጥ ይመጣል ። ኢየሱስ ከእርገቱ በኋላ ዳግመኛ ለፍርድ አንድ ጊዜ ብቻ ይመጣል ። ይኽ እውነት ከላይ በተመለከትናቸው ርዕሶች በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጠ በመጠኑ አይተናል ። ሃሰተኞች; ክርስቶስ በስውር ይመጣል በስውርም መጥቶ ቤተክርስቲያንን ወደ ራሱ በስውር ይወስዳል የሚሉት ውሸት እንደኾነ አንባቢ ልያስተውል ይገባል ። ቅድሜ መከራ ንጥቀት የሚያስተምሩት በሕይወት ሥጋ የነበሩ ቅዱሳን; መነጠቅና የሞቱ ሰዎች ትንሣኤ ኹለቱ በማድረግ መጽሐፍ ቅዱስ የማያውቀውን የዲያብሎስን ትምህርት ያስተምራሉ ።የትምህርቱ ዓለማም ቅዱሳንን ማኮላሸት ነው። ይገርማል ኢየሱስ ስመጣ የሞቱት ይነሳሉ ፤በሕይወት ያሉት ከመቅጽበት ተለውጠው በትንሳኤ አካል ይነጠቃሉ ።አንድ ላይ ወደ ሰማይ ያርጋሉ እንጂ ኢየሱስ ስመጣ በሕይወት ያሉት ተነስተው ፣የሞቱት ሳይነሱ ቀርተው ወይም ግማሹ ተነስተው የሚል አስተምህሮ በመጽሐፍ የለም።

አንባቢ እንደ በሪያ ሰዎች እንዲመራመሩ አበረታታለሁ ። ለራስዋ እድል ይስጡ። በዚህ እንዲያ ነው እንዲህ ነው  ከሚል ዝባዝንኬ ከፍደል ጨዋታ ከቃላት መራቀቅ ፈቀቅ  ብለው በመጽሐፍ ቅዱስ ጸሓፊያን ላይ አድሮ የገለጠው መንፈስ ቅዱስ፣ ያንኑ እንድገልጽ ይጸልዩ ። መንፈስ ቅዱስ የሰው ደቀመዛሙርት አያደርግም ። የክርስቶስ ተከታይ የቃሉ ኗር፤ ቃሉን ጠባቂ፤ የሥጋዊ አዕምሮ ለወለደው ትርክት መንፈስ ቅዱስ አሳልፎ አይሰጥም ። ስለዚህም ለራስዋ ጊዜ ይስጡ። ያሰላስሉ፤ይጸልዩ ። እግዚአብሔር በጎደለው በባዶው እንደሚሠራ የተገለጠ ነው። እግዚአብሔርን ለመሥራት የሰው ሽምግልና አይገድበውም፤ የሰው ጉብዝና አያግዘውም። እርሱ ብቻውን ይሠራል ።በባዶ ጋን ቃሉን ያሞላል።  ስለዚህም በክርስቶስ መንፈስ ይኽንን እውነት በመስማት ከሚጠፉት ጋር እንዳይጠፉ አሳስባለሁ ።ጆሮ ላለው ።

ከዚያች ወራትም መከራ በኋላ ወዲያው ፀሐይ ይጨልማል፥ ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም፥ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፥ የሰማያትም ኃይላት ይናወጣሉ። በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል፥ በዚያን ጊዜም የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ይላሉ፥ የሰው ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል፤ መላእክቱንም ከታላቅ መለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፥ ከሰማያትም ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከአራቱ ነፋሳት ለእርሱ የተመረጡትን ይሰበስባሉ። ማቴ 24፥29-31።  ይኽንን ክፍል ከፍ ባለው ክፍል የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24 ስንመለከት ለማየት ሞክረናል ። ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ጥያቄ መልስ እየሰጠ ነበር።ደቀመዛሙርቱ ስለመምጣቱ ምልክት ለጠየቁት ኢየሱስ የሰጠው መልስ ነው። አንባቢ ያስተውል ።

ኢየሱስ ስለመምጣቱ ስጠየቅ ኹሌቴ እንደሚመጣና በስውር እንደሚመጣ ሃሰተኞች እንደሚሉት አልገለጸም ። አንድ ጊዜ ብቻ የሚኾን ነውና ፤መምጣቱም አንድ ጊዜ ብቻ እንደኾነና በግልጥ እንደኾነ አመላክቷል ። የሰው ልጅ ስመጣ ፦ ፀሐይና ጨረቃ መጨለሙ ፣ከዋክብት መውደቁ ፥ የሰማይ መናወጥ ለኹሉም ግልጽ የሚታይ ክስተት ነው። የምድር ወገኖች ይኽንን ክስተት ተመልክተው ዋይ ዋይ ይላሉ።ደግሞም የሚመጣው አምላክን ያዩታል ። መጽሐፍ እንዲህ በግልጽ እየመሰከረ ደፍረው በግምት ኢአማኞች  አያዩትም በማለት ውሸትን ይናገራሉ ። ኢየሱስ ስለመምጣቱ ስጠየቅ ፣የሰጠው ምላሽ ይኽ ነው። ይኽንን እውነት በመምጣቱ እንደሚኾን ከመቀበል ውጪ ፣ በቃሉ ላይ መሰልጠን አግባብ አይደለም ። ድሮም ሰይጣን ሥራው ኢአግባቢነት ያለውን ማድረግና ማስደረግ ነው። እንዲያ ባይኾን ስለመምጣቱ ኢየሱስ በነገረው ባረፍን ነበር። ኢየሱስ ስለመምጣቱ ስናገር ለጥያቄአቸው አንድ ጊዜ ብቻና በግልጥ እንደሚመጣ ብቻ ባል ነገሬ ነበር፣ መምጣቱ ኹሌተ ብኾን እንዴት ይኽንን ሳይገልጽ ያልፋል ብላችኹ ታስባላችኹ? ያልተጻፈውን እየፈጠሩ ማንበብና ማስነበብ ስለለመዱ እንጂ የኢየሱስ መምጣት አንድ ጊዜ ብቻ የሚኾን ነው።

ኢየሱስ ዳግመኛ ስመጣ;በታላቅ መለከት መላእክት እየነፉ ታጅቦ ይመጣል፤ "መላእክቱንም ከታላቅ መለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፥ ከሰማያትም ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከአራቱ ነፋሳት ለእርሱ የተመረጡትን ይሰበስባሉ"። መላእክቱ እንዲህ በታላቅ ድምጽ እየነፉ ስመጣ እንዴት በስውር ይመጣል እንላለን ? በዚህ ክፍል ላይ ብቻ አይደለም በሌሎች ክፍሎችም ይኽ እውነት ተቀምጧል ። “ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤” 1ኛ ተሰ 4፥16 ።ኢየሱስ በእግዚአብሔር መለከት በታላቅ ድምጽ በመላእክት አለቃ ታጅበው መምጣቱ ፣ በመምጣቱ ብዙዎች እንድሸበሩ ዋይ ዋይ እንዲሉ ከሚያደርጉ ትይንቶች  አንዱ ነው።  ታዲያ ይኽ መምጣቱ ስውር ነው ለማለት ያስችላል ? ውኃውን ወተት ነው የማለት ድፈረት ካልኾነ በስተቀር ። ደግሞም በዚህ መምጣት የተመረጡት የጌታ ምርጦች ይሰበሰባሉ ፤ከሰማያትም ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከአራቱ ነፋሳት ለእርሱ የተመረጡት ይሰበስባሉ።

ሰይጣን በስውር ስሰራ ያልተነጠቀችው ቤተክርስቲያን ሰይጣን በግልጥ ስሰራ ትነጠቃለች ማለት ምን ማለት ነው? ሰይጣን የጨለማው ሃይል ይለያያል ።በታላቅ ቍጣ ወደ ምድር ከመምጣቱ ከመውረዱ በስተቀር ሌላ ነገር የለም። ዮሐንስ በራእዩ ልክ እንደ ኢየሱስ ፣መምጣቱን ኾነ የቅዱሳን ከመከራው በኋላ መነጠቅን በግልጽ ያስረዳል ። ዮሐንስ ራእዩን ካየበት ጊዜ ጀምሮ የሚኾነው የተመለከተውን በማዳፈን ከቅዱሳን መነጠቅ በኋላ ያለው ይገልጻል በማለታቸው ራእዩ ከምዕራፍ አራት ጀምሮ ያለው በ7ዓመታት ውስጥ ያለውን ያመለክታል ማለታቸው እንደኾነ ሳስተውል ይደንቀኛል ። [በራእይ ይዘት የተመለከትናቸው መገለጫዎችን ይመልከቱ ]። የደነቀኝ ግን ለዚህ ማስረጃ አለመኖራቸው‹‹

## 2.2 ከመከራው በስውር የተነጠቁ ቅዱሳን ሰርግ

ጌታ እንዴ ሌባ እመጣለሁ ያለውን ቀኑን "አላሳውቃቸውም" ለማለት እንጂ በስውር መጥቶ በስውር ቅዱሳንን ለመንጠቅ አይደለም ። ጌታ በስውር የሚወስደው ማንን ስለፈራ? ወይም በግልጥ ብመጣ ማንስ ልቋቋመኝ ይችላል ብሎ? ለእግዚአብሔር አብ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ክብር ምስጋና ይኹንና፣ አይደለም ኢየሱስ ስሙን የሚጠሩት እንኳን ሰይጣንን ጠፍረው አስረው ሰልጥነው ይይዛሉ ።

በምድር ላይ ያሉት ስሞቱ ፣ስረሸኑ፣ደማቸው ስፈስ፣ ስሰቃዩ፣ስንገላቱ ፤ ጌታ ከሌሎች ጋር ሰርግ ያደርጋል ይላሉ ፤ ሙሽሪት ሳትሰበሰብ ።ሰርግ የደስታ የድል ድግስ ነው። ሌሎች በጨካኙ አውሬ እየተገነጠሉ ስሞቱ ፣ ጌታ ከሌሎች ጋር በድግስ በደስታ በሰርግ እንደተቀመጠ ማስተማር በራሱ ፣ስበዛ ራስ ወዳድነት ነው። እግዚአብሔርንም አለማወቅ ነው።

በጉ ሰርግ የሚያደረገው ባቢሎን ወድቃ፣ አውሬው ታስሮ ፣ የእግዚአብሔር ፊትህ በአሕዛብ ላይ ከተገለጠ፣ ከፍርድ በኋላ እንጂ ግማሹ ስሰቃይ ከግማሹ ጋር ጌታ ድግስ አይደግስም ፤አያደርግም ። ሰይጣን እንዲታሰር እንዲፈረድበት የሚጮኹ ቅዱሳን፣ ፍርዱን ሳይቀበል እንዴት ይደሰታሉ ?በመጽሐፍ በግልጽ የተቀመጠው የበጉ ሠርግ ፣ ከኢየሱስ ዳግመኛ መምጣት ከፍርድ በኋላ ነው። **“የበጉ ሰርግ ስለ ደረሰ ሚስቱም ራስዋን ስላዘጋጀች ደስ ይበለን ሐሤትም እናድርግ ክብርንም ለእርሱ እናቅርብ።” ራእይ 19፥7 ።**

ሰርግ የሚደረገው የተመረጡት ኹሉ በክርስቶስ ስጠቀለሉ ፣ ቤተክርስቲያን የበጉ ሚስት ራሳቸውን ስታዘጋጅ ነው። አንደኛው ተዘጋጅቶ አንደኛው ሳይዘጋጅ፣ ኹሉም የተመረጡት ሳይታተሙ ከክፍሎቹ ጋር ጌታ ሰርግ አያደርግም ። ሰርግ ደስታ ሰላም ያለበት ነውና የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ነው፥ "መንግሥተ ሰማያት ለልጁ ሰርግ ያደረገ ንጉሥን ትመስላለች። የታደሙትንም ወደ ሰርጉ ይጠሩ ዘንድ ባሮቹን ላከ ሊመጡም አልወደዱም። ደግሞ ሌሎችን ባሮች ልኮ፡- የታደሙትን፦ እነሆ፥ ድግሴን አዘጋጀሁ፥ ኮርማዎቼና የሰቡት ከብቶቼ ታርደዋል፥ ሁሉም ተዘጋጅቶአል፤ ወደ ሰርጉ ኑ በሉአቸው አለ። እነርሱ ግን ቸል ብለው አንዱ ወደ እርሻው፥ ሌላውም ወደ ንግዱ ሄደ፤ የቀሩትም ባሮቹን ይዘው አንገላቱአቸው ገደሉአቸውም። ንጉሡም ተቈጣ፥ ጭፍሮቹንም ልኮ እነዚያን ገዳዮች አጠፋ፤ ከተማቸውንም አቃጠለ። በዚያን ጊዜ ባሮቹን፦ ሰርጉስ ተዘጋጅቶአል፥ ነገር ግን የታደሙት የማይገባቸው ሆኑ፤ እንግዲህ ወደ መንገድ መተላለፊያ ሄዳችሁ ያገኛችሁትን ሁሉ ወደ ሰርጉ ጥሩ አለ። እነዚያም ባሮች ወደ መንገድ ወጥተው ያገኙትን ሁሉ ክፉዎችንም በጎዎችንም ሰበሰቡ፤ የሰርጉንም ቤት ተቀማጮች ሞሉት። ንጉሡም የተቀመጡትን ለማየት በገባ ጊዜ በዚያ የሰርግ ልብስ ያለበሰ አንድ ሰው አየና፡- ወዳጄ ሆይ፥ የሰርግ ልብስ ሳትለብስ እንዴት ወደዚህ ገባህ? አለው እርሱም ዝም አለ።በዚያን ጊዜ ንጉሡ አገልጋዮቹን፡- እጁንና እግሩን አስራችሁ በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጡት፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል አለ።የተጠሩ ብዙዎች፥ የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸውና። ማቴ 22፥2-14።

"ሰርግ በጠላቶቹ ፊት በድል የሚገለጥ እንጂ ተደብቀው እንደ ሌባ ሕጋዊ እንዳልኾነ ግንኙነት የሚገረግ አይደለም" ። ሰርጉ ኹሉም የተመረጡት በተገኙበት የሚደረግ እንጂ እንደ ሌባ ሳይታሰብ በስውር የሚደረግ አይደለም ። በመጽሐፍ ወደፊት ሰርግ መኖሩን ዮሐንስ በራእዩ የገለጠው ፤ከባቢሎን መውደቅና መፍረስ ከበጉ ቁጣ በኋላ ነው። መጽሐፍ ይኽንን እውነት እያስተማረ ሳለ፣ ያልተጻፈውን የሚያነቡ የበጉ ሰርግ ከክፍሎቹ ጋር ብቻ እንደሚደረግ ምንዝርና ያስተምራሉ ።አያፍሩም ። አንባቢ ግን ያስተውል ።

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. በታላቁ መከራ ጊዜ ቅዱሳን እንዴት በመከራው ያልፋሉ?

ይኸንን ጥያቄ ማቅረብ አስፈላጊ ነገር ነው። ስለ ቅድሜ መከራ ንጥቀት አስተምህሮ ስሁትነት በቀላሉ እንዲናውቀው ያደርገናል ። በውነቱ ቅዱሳን ከመከራው በፊት ይነጠቃሉ ? የራእይ መጽሐፍ ከምዕራፍ አራት ጀምሮ ያለው ቤተክርስቲያንን አያመለክትም ? የሚሉት ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ ይሻሉ። አዕምሮ ያለው አንባቢ በቀላሉ መረዳቱ አይቀርም ። የራእይ መጽሐፍ ከምዕራፍ አራት ጀምሮ ያለው ቤተክርስቲያንን አያመለክትም ስሉ፣ ስለ መጽሐፉ ምንም አይነት መሠረታዊ እውቀት እንደሌላቸው ያስታውቃል ። ምክንያቱም መጽሐፉ ስለ 7 ዓመት መከራ ጊዜ ብቻ የሚያትት አይደለም ። አንባቢ ያስተውል ። በድጋሚም እላለሁ ። መጽሐፉ ከምዕራፍ አራት ጀምሮ ያለው ዮሐንስ ራእዩን ከተመለከተበት ጊዜ አንስቶ የሚፈጸሙትን ነገሮችን በዝርዝር የያዘ ነው። እንዲሁም ምዕራፍ 21 ጭራሽ ከዓለም ፍጻሜ በኋላ ስላለች ክብርት ቤተክርስቲያን ስለሚጠብቃት ክብር በስፋት የሚያትት ነው። እንዲሁም መጽሐፉ ለእስራኤላውያን [ዘሥጋ] ብቻ እንዳይደለ ፍርድ ስለሚገባት ጋለሞታይቱ ባቢሎን የሚናገርም እራሱን የቻለ ዝርዝር መግለጫ የያዘ መጽሐፍ ነው።

የራእይ መጽሐፍ ስለ ቅድሜ መከራ ንጥቀት አስተምህሮ ኑፋቄ በቂ ማስረጃ ያቀርባል ። በታላቁ መከራ ጊዜ እንኳን ቅዱሳን እንዴት እንደሚያልፉ ዝርዝር ሃሳብ በየመግለጫው ይሰጣል ። በታላቁ መከራ ጊዜ [በ42 ወራት ውስጥ ] በመከራው የሚያገለግሉ ቅዱሳን [ስለ ኹለቱ ምስክሮች፤እነዚህም ቅድሜ መከራ ያልተነጠቁ ቅዱሳን ናቸው፤ ኑፋቄውን የሚገልጥ ነው] ፥ በመከራው ሰማዕት የሚኾኑት በመከራው የሚያልፉ ቅዱሳን 144,ሺህ ቅዱሳኖች፣ ደግሞም መከራው የማያገኛቸው ቅዱሳኖች[ ሴቲቱ] በሰፊው ተብራርተው ተቀምጠዋል ። አንባቢ ኾይ እስካሁን በተመለከትናቸው ሴቲቱ መከራ እንዳያገኛት በምድር ስትሰወር ፣ ሰይጣን ከዘሮቿ ጋር ጦርነት እንደሚያደርግ አይተናል ። ዘሮቿ ቅዱሳኖች ናቸው ። ይኽም በታላቁ መከራ መሃል በእሳቱ ተፈትነው የሚያልፉ ቅዱሳኖች መኖራቸውን ያረጋግጣል ። በዚህ ርዕሰ ስር በይበልጥ ለማየት እንሞክራለን ።

### 3.1. የ144,000 ሺህ የሚታተሙ ቅዱሳኖች

ስለ ዘመን ፍጻሜ ጤናማ መረዳት የሚኖረን የሺህው ዓመት መንግስትና ቅብርጥሰ በሚል ርዕሰ ከራእይ መጽሐፍ ከመሃል ተወስዶ በተዘጋጀው ትምህርት ኾነ ዕሳቤ አይደለም ። ራእይ መጽሐፍ ሙሉውን ይዘት በመረዳት በማጥናት እንጂ። ራእዩ የሚያመራው ስለ ሰላማዊ እግዚአብሔር መንግስት ነው። ይኽም በመግለጫዎች ስያመራን አይተናል ። ለምሳሌ በታተመው መጽሐፍ ማህተሞች የተገለጠው 7ኛው ማህተም የዓለምን ፍጻሜንና የክርስቶስ መንገስን ያውጃል ፣ ደግሞም በ7ቱ ማስጠንቀቂያዎች በኩል በተገለጠው 7ኛው ማስጠንቀቂያ የሚገልጸው ክርስቶስ በአሸናፊነት ኹሉንም መቆጣጠሩንና

መንገሱን ፣ ዓለም ፍጻሜ ስለማግኘቷ ነው፣ ደግሞም ሌሎችም በመግለጫዎች የተመለከትናቸው ወደ ዓለም ፍጻሜ የሚያመሩ ናቸው ። ስለዚህም ራእይ መጽሐፍ ስለ ዓለም ፍጻሜ በተለያየ መንገድ ራእዩ ከተገለጠበት ጊዜ አንስቶ ያለውን የሚያሳይ መግለጫ እንጂ እነርሱ እንደሚሉት "ከንጥቀት" በኋላ ስላለው ታላቁ መከራ ጊዜ ብቻ የሚናገር አይደለም ። መግለጫው የመጨረሻ መጨረሻ የሰይጣን ከሰማይ መጣል ጋር ተያይዞ ያለውን አስቸኳይና ታላቅ ጦርነትን ያሳስበናል ። 3 ዓመት ከተኩል የሚኾነውን የመከራው ጣዕር ይገልጻል ። ኢየሱስ እንዳስተማረው በዮሐንስ ራእይም መከራው የምጥ ጣዕር መጀመሪያ እና ምጥ [3 ዓመት ከተኩል ያለው ] ተብሎ ተገልጿል ። ታላቁ መከራ መጀመሩ የዓለምን ታርክ ወደ ፍጻሜ መግባቱን የሚያስታውቅ ስኾን፣ ከራእይ መጽሐፍ አንፃር ስንመለከት ከሰማይ ከሰይጣን መውደቅ ጋር ተያይዞ የሚጀመር ነው። [ይኽንን በመግለጫዎች እንደተመለከትነው አንባቢ ማስተዋል ይችላል]። ለምሳሌ ፦

**የዓለምን ታርክ በመጽሐፍ በታተሙት ከተገለጸው አንፃር ብንመለከት ፣ በ6ኛው ማህተም የሰይጣን መውደቅን እና ታላቁ መከራ መጀመሩን ያበስረናል።**

" ስድስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ አየሁ፥ ታላቅም የምድር መናወጥ ሆነ፥ ፀሐይም እንደ ማቅ ጠጕር ጥቁር ሆነ፥ ጨረቃም በሞላው እንደ ደም ሆነ፥ በለስም በብርቱ ነፋስ ተናውጣ ቃርያዋን ፍሬ እንደምትጥል የሰማይ ከዋክብት ወደ ምድር ወደቁ፥ ሰማይም እንደ መጽሐፍ ተጠቅልሎ አለፈ፥ ተራራዎችና ደሴቶችም ሁሉ ከስፍራቸው ተወሰዱ።የምድርም ነገሥታትና መኳንንት ሻለቃዎችም ባለ ጠጋዎችም ኃይለኛዎችም ባሪያዎችም ጌቶችም ሁሉ በዋሾችና በተራራዎች ዓለቶች ተሰወሩ፥ ተራራዎችንና ዓለቶችንም፦ በላያችን ውደቁ በዙፋንም ከተቀመጠው ፊት ከበጉም ቍጣ ሰውሩን፤ታላቁ የቁጣው ቀን መጥቶአልና፥ ማንስ ሊቆም ይችላል? አሉአቸው።" ራእ 6፥12-17።

በእነዚህ ክስተቶች ለማሳየት የፈለኩት በታላቁ መከራ ጅማሮ ከሚከሰቱ ነገሮች አንዱ "የመላእክት ከሰማይ መውደቅን ነው" ። "**የሰማይ ከዋክብት ወደ ምድር ወደ**ቁ"ከዋክብት የሚለው ቃል ለቅዱሳን መላእክትን ብቻ ያገለግላል ማለት አንችልም ። ዲያቢሎስ "ከዋክብት" ተብሎ መጠራቱ ለሰይጣን ክብር ልጨምር አይችልም ።ምክንያቱም ሰይጣን በመጽሐፍ ቅዱስ "ኮከብ" ተብሎ ተጠርቷል ፣ “አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ፥ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ! አሕዛብንም ያዋረድህ አንተ ሆይ፥ እንዴት እስከ ምድር ድረስ ተቈረጥህ!” ኢሳ 14፥12 ።

*ዓለም ወደ ፍጻሜ ስትሄድ ሰይጣን ከሰማይ ረገፈ ይባል፣ ቅዱሳን መላእክቱም ይውድቃሉ? ብንል መልሱ "አዎ"የሚል ነው። በሌሎች መግለጫዎች ይኽ እውነት አለ፤ ራእ 12።*

ስለዚህም ስለ ሚታተሙ ቅዱሳን ለማወቅ አውዱን ጠብቀን እንዲህ መሄድ ግድ ይለናል ። እንደ ማህተሞቹ መግለጫ [1ኛው መግለጫ ] ወደ ታላቁ መከራ ያመራው በ5ኛው ማህተም እግዚአብሔርን የሞቱ ሰዎች "ፍርድልን" በማለት የፍትህ ጥያቄ በማቅረባቸው ነው። ለዚህ ጥያቄአቸው ጌታ የሰጠው መልስ፣ እንደ እናንተ በመስዋእትነት የሚሞቱ ቅዱሳን

ስላሉ ታገሱ የሚል ነው። ራእይ 6፥ [9] አምስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ፥ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ጠበቁት ምስክር የታረዱትን የሰዎች ነፍሳት ከመሠዊያ በታች አየሁ።[10] በታላቅ ድምፅም እየጮኹ፦ ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ፥ እስከ መቼ ድረስ አትፈርድም ደማችንንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከ መቼ አትበቀልም? አሉ። [11] ለእያንዳንዳቸውም ነጭ ልብስ ተሰጣቸው፥ **እንደ እነርሱም ደግሞ ይገደሉ ዘንድ ያላቸው የባሪያዎች ባልንጀራዎቻቸውና የወንድሞቻቸው ቍጥር እስኪፈጸም ድረስ፥ ገና ጥቂት ዘመን እንዲያርፉ ተባለላቸው።**

ቀድመው ከታላቁ መከራ በፊት የሞቱ ቅዱሳን ፍትህን በመጠየቃቸው፣ ጌታ የቀሩት ወንድሞቻችሁ [እንደ እነርሱ ዓለምን ድል ነስተው የሚያልፉ] ቍጥር ወይም ኹሉም ድል በመንሳት በመስዋዕትነት እስከሚያሸንፉ ድረስ ታገሱ አላቸው ። እንግዲህ ጥቅት ዘመን ነው የሚያርፉት ። ጌታም ከዚህች እረፍት በኋላ በሞቱ ቅዱሳን ጥያቄ መሠረት ታላቁን ፍርዱን ቍጣውን በዓለም ላይ ይገልጻል ። በ6ተኛው ማህተምም ታላቁ ቍጣ ስገለጥ ፣ ዮሐንስ መአቱን በማየት በቍጣው ማንስ ይቆማል በማለት ፣ በቍጣው ጊዜ እራሱን በማድረግ ለእምነቱ ከባድ መኾኑን በጥያቄ አመላክቷል። “ታላቁ የቁጣው ቀን መጥቶአልና፥ **ማንስ ሊቆም ይችላል?** አሉአቸው።” ራእይ 6፥17 ።

አንባቢ ልብ ይበሉ በዚህ መግለጫ ላይ፣

1ኛው.ስማዕት የኾኑ ቅዱሳን የፍትህን ጥያቄ አቅርበዋል፣

2ኛው.ጌታም; እንደ እነርሱ ያሉት እስከ ሚሞሉ ድረስ ታገሱ ብሎአቸዋል ፣

3ኛው. ከጥቅት ጊዜ ትዕግሥት በኋላ ጌታ ፍርዱን ቍጣውን ገለጠ፣

ዮሐንስ ቍጣውን ስመለከት ማንስ ልቆም ይችላል ያለው ፣ ወንድሞቹ በዚህ ኹኔታ እንዴት ልገኙ ይችላሉ የሚል ጥያቄ ታሳቢ ያደረገ ሃሳብ ነው፤የመጣለት ። እውነት ነው። 6ኛው ማህተም ስከፈት የተገለጠው አስፈሪ ነው። በሰማይ ኾኖ የሚያስቸግረን ሰይጣን መውደቅ ጋር ተደምሮ ። ስለዚህ አኹንም እንደ ሞቱ ሰማዕታት ሰማዕት የሚኾኑ እንዳልተገኙ ልብ ይሏል። ዮሐንስ በፍራሃት ላቀረበው ጥያቄ ምላሽ ሳያገኝ ሌላ መቅሰፍት የሚያመጣ መላእክት ተመለከተ፣“ከዚህም በኋላ በአራቱ በምድር ማዕዘን ቆመው አራት መላእክት አየሁ፥ እነርሱም ነፋስ በምድር ቢሆን ወይም በባሕር ወይም በማንም ዛፍ እንዳይነፍስ አራቱን የምድር ነፋሳት ያዙ።” ራእይ 7፥1።

ራእዩ እንደቀጠለ ነው። ነገርግን ከመሃል በዚያ ታላቁ መከራ ጊዜ ሰማዕታት እንዲገኙ መቅሰፍቱ እንዳይቀጥል ተደረገ፣ ራእይ 7፥ [3] የአምላካችንን ባሪያዎች ግምባራቸውን እስክናትማቸው ድረስ ምድርን ቢሆን ወይም ባሕርን ወይም ዛፎችን አትጕዱ አላቸው።[4] የታተሙትንም ቍጥር ሰማሁ፤ ከእስራኤል ልጆች ነገድ ሁሉ የታተሙት መቶ አርባ አራት ሺህ ነበሩ።

አንባቢ አስተዋሉ? ነገሩን ቀርቤ እየተመለከትኩ ነው። በዚህ መከራ ጊዜ የሚታተሙት ብቻ ናቸው እነዚያ ቅዱሳን ። እነዚያ ቅዱሳን ከአውዱ ውጪ በመውጣት የብሉይ ኾነ የሐዲስ ኪዳን ቅዱሳንን ኹሉንም ያጠቃልላል ካልን፣ በጭራሽ አውዱን የጠበቀ መረዳትና መልእክት አይኖረንም ። እነዚህ ቅዱሳን ክርስቶስ ልመጣ ስል በሚገለጠው በታላቁ ቍጣ ጊዜ የሚታተሙ፣ ቀድመው የሞቱ ሰማዕታት ወንድሞች የሚኾኑ ናቸው ። እነዚህ እስራኤላውያን ተብለዋል ። እስራኤል ዘሥጋ ብቻ ናቸውን?

## 3.2. እስራኤል

ወደ ሚታተሙት እስራኤላዊያን ነገድ ትርጓሜ ውስጥ ከመዝለቃችን በፊት ስለ እስራኤላውያን ዘር ሃረግ መጠነኛ ዳሰሳ ማድረግ ያስፈልጋል፥ እስራላዊነት የሚጀምረው በአብርሃም መጠራት ነው። ከዚያ በፊት አልነበረም ። አብርሃም እንደ ማነኛውም የዓለም ሕዝብ የሚኖር ነበር፤ ጣኦትን ከሚያመልኩ ማህበረሰቦች መሃከል የተገኘ ነው። በእግዚአብሔር ጥሪ ከዚያ እንዲወጣና ከሚኖርበት ማህበረሰብ በላይ ብዙ ብዙ ሊያደርገው እንደኾነ ገለጸ፤ ቃልም ገባለት፣ ወደ ሜዳም አወጣውና፦ ወደ ሰማይ ተመልከት፥ ከዋክብትንም ልትቈጥራቸው ትችል እንደ ሆነ ቍጠር አለው። ዘርህም እንደዚሁ ይሆናል አለው።አብራምም በእግዚአብሔር አመነ፥ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት። ዘፍ 15፥5-6።

ስለ እነዚህ አዲስና ልዩ ማህበረሰቦች ለአብርሃም በራእይ የሚደርሳቸውን አስታወቀ፣ "አብራምንም አለው፦ ዘርህ ለእርሱ ባልሆነች ምድር ስደተኞች እንዲሆኑ በእርግጥ እወቅ፤ ባሪያዎች አድርገውም አራት መቶ ዓመት ያስጨንቋቸዋል።ደግሞም በባርነት በሚገዙአቸው ሕዝብ ላይ እኔ እፈርዳለሁ፤ ከዚያም በኋላ በብዙ ከብት ይወጣሉ።" ዘፍ 15፥ 13-14። የአብርሃም ልጅ የይስሐቅ ልጅ የያዕቆብ ልጅ፣ የኾኑ በቍጥር የበዙ የእስራኤል ነገዶች የሚያልፉበትን ጌታ ለአብርሃም ቀድሞ በራእዩ አስታወቀ። የያዕቆብ ልጆች [የእስራኤል ነገዶች]፦

"ልያም ፀነሰች፥ ወንድ ልጅንም ወለደች፥ ስሙንም ሮቤል ብላ ጠራችው እግዚአብሔር መከራዬን አይቶአልና፥ እንግዲህም ወዲህ ባሌ ይወድደኛል ብላለችና። ደግሞም ፀነሰች፥ ወንድ ልጅንም ወለደች፤ እኔ እንደ ተጠላሁ እግዚአብሔር ስለ ሰማ ይህን ደገመኝ አለች፤ ስሙንም ስምዖን ብላ ጠራችው። ደግሞም ፀነሰች፥ ወንድ ልጅንም ወለደች፤ አሁንም ባሌ ወደ እኔ ይጠጋል፥ ሦስት ወንዶች ልጆችን ወልጄለታለሁና አለች ስለዚህም ስሙን ሌዊ ብላ ጠራችው።ደግሞም ፀነሰች፥ ወንድ ልጅንም ወለደች፤ በዚህም ጊዜ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ አለች፤ ስለዚህም ስሙን ይሁዳ ብላ ጠራችው። መውለድንም አቆመች።" ዘፍ 29 32፥35። *ያዕቆብ ከልያ የወለዳቸው ልጆች ፣ 1ኛው. ሮቤል ይባላል፣ 2ኛው. ስምዖን ይባላል፣ 3ኛው. ሌዊ ይባላል፣ 4ኛው. ይሁዳ ይባላል ፥

"ራሔልም፡- እግዚአብሔር ፈረደልኝ፥ ቃሌንም ደግሞ ሰማ፥ ወንድ ልጅንም ሰጠኝ አለች፤ ስለዚህ ስሙን ዳን ብላ ጠራችው።... ራሔልም፡- ብርቱ ትግልን ከእኅቴ ጋር ታገልሁ፥ አሸነፍሁም አለች፤ ስሙንም ንፍታሌም ብላ ጠራችው።" ዘፍ 30፥6-8 ።*ያዕቆብ ከራሔል ባሪያ [ባላ] የወለዳቸው ልጆች፣ 5ኛው.ዳን ይባላል፣ 6ኛው. ንፍታሌም ይባላል ፣

"ልያም፡- ጉድ አለች፤ ስሙንም ጋድ ብላ ጠራችው።... ልያም፡- ደስታ ሆነልኝ፤ ሴቶች ያመሰግኑኛልና አለች፤ ስሙንም አሴር ብላ ጠራችው።" ዘፍ 30፥11-13።*ያዕቆብ ከልያ ባሪያ [ዘለፋ] የወለዳቸው ልጆች፣ 7ኛው. ጋድ ይባላል ፣ 8ኛው. አሴር ይባላል፣

" ልያም፡- ባሪያዬን ለባሌ ስለ ሰጠሁ እግዚአብሔር ዋጋዬን ሰጠኝ አለች፤ ስሙንም ይሳኮር ብላ ጠራችው።... ልያም፡- እግዚአብሔር መልካም ስጦታን ሰጠኝ፤ እንግዲህስ ባሌ ከእኔ ጋር ይኖራል፥ ስድስት ልጆችን ወልጄለታለሁና አለች፤ ስሙንም ዛብሎን ብላ ጠራችው።" ዘፍ 30፥18-20።*ያዕቆብ ከልያ የወለዳቸው ልጆች፣ 9ኛው.ይሳኮር ይባላል ፣ 10ኛው.ዛብሎን ይባላል ፣

"ስሙንም፡- እግዚአብሔር ሁለተኛ ወንድ ልጅን ይጨምርልኝ ስትል ዮሴፍ ብላ ጠራችው።"ዘፍ 30፥24። *ያዕቆብ ከራሔል የወለደው ልጅ፣ 11ኛው. ዮሴፍ ይባላል ።

"ምጡም ባስጨነቃት ጊዜ አዋላጂቱ፡- አትፍሪ፥ ይኸኛው ደግሞ ወንድ ልጅ ይሆንሻልና አለቻት። እርስዋም ስትሞት ነፍስዋ በምትወጣበት ጊዜ ስሙን ቤንኦኒ ብላ ጠራችው፤ አባቱ ግን ብንያም አለው።" ዘፍ 35፥17-18። *ያዕቆብ ከራሔል የወለደው ፣ 12ኛው. ብንያም ይባላል ።

* " የያዕቆብም ልጆች አሥራ ሁለት ናቸው። የልያ ልጆች፤ የያዕቆብ በኵር ልጅ ሮቤል፥ ስምዖን፥ ሌዊ፥ ይሁዳ፥ ይሳኮር፥ ዛብሎን፤ የራሔል ልጆች፤ ዮሴፍ፥ ብንያም፤ የራሔል ባርያ የባላ ልጆችም፤ ዳን፥ ንፍታሌም፤ የልያ ባሪያ የዘለፋ ልጆችም፤ ጋድ፥ አሴር፤ እነዚህ በሁለቱ ወንዞች መካከል በሶርያ የተወለዱለት የያዕቆብ ልጆች ናቸው።" ዘፍ 35፥22-26።መጽሐፍም እንደሚል የእስራኤል [የያዕቆብ] በኵር ልጆች የልያ ልጆች ስኾኑ የመጀመሪያው ልጅ ሮቤል ነው። ዘፍ 49 ይመ.።

"እነዚህም ሁሉ አሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ናቸው፤ አባታቸው የነገራቸው ይህ ነው፥ ባረካቸውም፤ እያንዳንዳቸውን እንደ በረከታቸው ባረካቸው።" ዘፍ 49፥28 ።

እግዚአብሔር በራእይ ለአብርሃም አስታውቆ እንደነበረው እስራኤላውያን ለባርነት ተዳረጉ ፤ እግዚአብሔርም ከባርነት በማውጣት ወደታሰበላቸው ሕይወት እንዲገቡ ተከላቸው።"ከግብጽ የወይን ግንድ አመጣህ፤ አሕዛብን አባረርህ እርስዋንም ተከልህ።" መዝ 80፥8 ። የወይን ግንድ የተባለችው እስራኤል ነች። ብትተከልም; ጌታ ብንከባከባትም ግን ፍሬ አላገኘባትም።"አሁን ስለ ወዳጄና ስለ ወይን ቦታው ለወዳጄ ቅኔ እቀኛለሁ። ለወዳጄ በፍሬያማው ኮረብታ ላይ የወይን ቦታ

ነበረው። በዙሪያው ቈፈረ፥ ድንጋዮችንም ለቅሞ አወጣ፥ ምርጥ የሆነውንም አረግ ተከለበት፥ በመካከሉም ግንብ ሠራ፥ ደግሞም የመጥመቂያ ጉድጓድ ማሰበት፤ ወይንንም ያፈራ ዘንድ ተማመነ፥ ዳሩ ግን ሆምጣጣ ፍሬ አፈራ።" ኢሳ 5፥1-2። እስራኤላውያን ኵርንችት በማፍራታቸው እግዚአብሔር ሌላ ወይን ግንድ ተከለ። ኢየሱስን ።ለዚህም ነው ኢየሱስ "እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ" ያለው ።ዮሐ 15።

ለእስራኤላውያን የልጅነትና ክብር ተሰቷቸው ነበር፣ ሮሜ 9። እነርሱ ግን ከመንገድ ላይ ወድቀው ቀሩ፤ 1ቆሮ 10። በዮሐንስ መጥምቁ የተገለጠው አስደንጋጭ ዘለፋም ይኸንን ያረጋግጣል ። "የአብርሃም ልጆች ነን በማለት በሥጋ ዘር ብቻ ተመካኙ፣ የአብርሃም ልጅነት የሚያረጋግጥ ፍሬ ግን የላቸውም ።የአብርሃም ልጅነት ለዓለም ጣፋጭነት የተተከለች ልዩ ማህበረሰባዊነት ነች ። እነርሱ ግን በሥጋ ለመመካት ብቻ ተጠቀሙ። ዮሐንስ መልካም ሥራ ስላላየባቸው ፣ የአብርሃም ልጅ ነኝ በማለት የአብራም ልጅነት እንደማይረጋገጥ መሰከረ። እንዲሁም በንስሐ ካልተመለሱ ከክብራቸው ከልጅነታቸው ልቆረጡ እንደሚችሉ አስታወቀ ።

" በልባችሁም፦ አብርሃም አባት አለን እንደምትሉ አይምሰላችሁ፤ እላችኋለሁና፦ ከነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣለት እግዚአብሔር ይችላል።አሁንስ ምሳር በዛፎች ሥር ተቀምጦአል፤ እንግዲህ መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቈረጣል ወደ እሳትም ይጣላል። " ማቴ 3፥9-10። ዮሐንስ መጥምቁ የአብርሃም ልጅነት በዘር እንዳይደለ ፣በዘር የአብርሃም ልጅ ብኾኑ እንኳን የእፉኝት ልጆች በሥራቸው እንደኾኑ መሰከረ። ንስሐ ካልገቡ የአብርሃምን ልጅነት ልያጡ እንደሚችሉ ፍርድ መድረሱን አስታወቀ ።

ኢየሱስም ለሥጋ እስራኤላውያን ልዩ ቦታ አልሰጠም ። የአብርሃም ልጆች እንደኾኑ አልመሰከረም። የአብርሃም ልጅነት በመንፈስ በሥራ የሚገለጥ ነውና፣ በሥራቸው የዲያብሎስ ልጅነት እንደሚታይባቸው በነቢያት የተገለጠውን አስታወቀ ። ኢየሱስ አብራሃም ከዓለም ጠርቶ ለክብሩ እንዳቆመ፣ በእርሱ ዘር በኵል የተጠሩትን ለክብሩ እንዲኖሩ ፈልጎ ነበር። ነገርግን አልወደዱም ። እንደገና በዘር የተመሠረተውን መጠራትን ለክብሩ መለየትን በማጥፋት ከዓለም ተጠርቶ የወጡትን በራሱ መሠረተ፤ ማቴ 16። ነገርግን ክርስቶስ ከእነርሱ ከኾኑት ተውልዶ በሥጋ ብመጣም አልተቀበሉትም ። ፍጥረት ኹሉ የእርሱ ነው። በአብርሃም በኵል ያቋቋመው በዘር የተመሠረተው አንደኛው መንጋ ስኾን ይኸንን ዕድል ያላገኙ ሌሎች ማህበረሰቦች ደግሞ ሌላኛዎቹ መንጋዎች ናቸው ። “ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፤ እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል ድምፄንም ይሰማሉ፥ አንድም መንጋ ይሆናሉ እረኛውም አንድ።” ዮሐንስ 10፥16 ። ጌታ አሕዛብንም ሕዝቡ ብሎ የለያቸውንም አንድ በማድረግ ልያሠማረ ወደደ ። ልዩነት የነበረው የጥል ግድግዳ በሞቱ አስወግዶ ።አስታራቀ።

አሕዛብ ወይም የአብርሃም ልጅነት በሥጋ ሳይኾን በራሱ እንዲገኝ አደረገ። ለአብርሃም የተገባው ተስፋ ያለ ዘር ልዩነት ክርስቶስን በማመን ኹሉም እንዲቀበሉ አደረገ። ኹሉም በደለኞች ስለኾኑ የተመሠረተው አዲስ መሠረት ነው። ኹሉም

ኃጢአተኞች በመኾን እግዚአብሔርን ስለበደሉ ወደቤቱ እራሱን በመቀበል ብቻ እንዲገቡ አደረገ። በሥጋዊ ዘር የሚወረስ አንዳች ነገር የለም፤ በሥጋ ከአብርሃም ዘር ባለመኾንም የሚቀርም አንዳች ነገር የለም። ኹሉም በደሙ በኵል ስሪዬትን በመቀበል የአብርሃም ልጅነት እንዲቀበሉ አደረገ። ስለዚህ የሐዲስ ኪዳን እስራኤል ጌታን የተቀበሉ ኹሉ ናቸው ። በክርስቶስ ያሉት ከዓለም ተጠርተው የወጡ ናቸው ። በሐዲስ ኪዳን ለሥጋዊ አይሁድነት ልዩ ስፍራ የላቸውም ። የአምልኮ ማዕከል ቤተመቅደስ ከነበረበት ወደ ስሙ ቀይሯልና። ሮሜ 3፥[1] እንግዲህ የአይሁዳዊ ብልጫው ምንድር ነው? ወይስ የመገረዝ ጥቅሙ ምንድር ነው? በሁሉ ነገር ብዙ ነው።[2] አስቀድሞ የእግዚአብሔር ቃላት አደራ ተሰጡአቸው። ታዲያ ምንድር ነው?" አዎን ታዲያ ምንድነው ? እስራኤል መንፈሳዊ ትርጓሜዋ በጌታ ያሉት አማኞች ፤ ከዓለም ተጠርተው የወጡ ናቸው ።

ወደ አውዱ ዝርዝር ሃሣብ ውስጥ ስንገባ፣ የሚታተሙት የእስራኤል ነገድ ራእይ መጽሐፍ በሚሰጠው መግለጫ ከእስራኤል ዘሥጋ  ከያዕቆብ ከተወለዱ ልጆች ነገዶች ጋር ስናነፃፅር በፍጹም አይገናኝም ። ራእይ መጽሐፍ የሚታተሙትን እንዲህ ይገልጻል፣ ራእይ 7፥ [4]" የታተሙትንም ቍጥር ሰማሁ፤ ከእስራኤል ልጆች ነገድ ሁሉ የታተሙት መቶ አርባ አራት ሺህ ነበሩ።[5] ከይሁዳ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ ታተሙ፥ ከሮቤል ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ ከጋድ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥[6] ከአሴር ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ ከንፍታሌም ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥[7] ከምናሴ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ ከስምዖን ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ ከሌዊ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ ከይሳኮር ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥[8] ከዛብሎን ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ ከዮሴፍ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ ከብንያም ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ ታተሙ።" እነዚህ በታላቁ መከራ ጊዜ የሚታተሙት ወይም የሚድኑት ናቸው ። ነገዶቹን ከያዕቆብ ከተወለዱት እስራኤል ጋር ስናስተያይ አይገናኝም ። ለምሳሌ ፦

በያዕቆብ ልጆች በተመሠረተው የእስራኤል ነገዶች ላይ በኵሩ ሮቤል ነው፤ በራእይ በተገለጡት ነገዶች ግን በኵሩ ይሁዳ ነው። ምክንያቱም የሚታተሙት እስራላዊነት የተመሠረተው በክርስቶስ ነው። ክርስቶስ ደግሞ የይሁዳ አንበሳ ነው፤ ከወንድሞች በኵርም ነው። ይኸም የራእይ መጽሐፍ የእስራኤል ነገዶች ዝርዝር እስራኤል ዘሥጋ እንዳልሆነ ይጠቊማል። እንዲሁም ከያዕቆብ ልጆች[ 5ኛው ዳን ይባላል] ነገርግን በራእይ መጽሐፍ ነገዶች ዝርዝር ውስጥ አልገባም ።እርሱ ወጥቶ የዮሴፍ ልጅ ምናሴ በነገዶች ዝርዝር ውስጥ ገብቷል። ይኸም የሚታተሙቱ እስራኤል ዘሥጋ እንዳልኾኑ ይጠቊማል። እነዚህ ነገዶች በእስራኤል ዘሥጋ ተመስለው የቀረቡ መንፈሳዊ ትርጓሜ የያዙ እንጂ እስራኤል ዘሥጋ አይደሉም ። አይሁዳዊነት በክርስቶስ በመኾንና ባለመኾን ኾኖ እንደተቀየረ ፤እስራኤላዊነትም በክርስቶስ በመኾንና ባለመኾን የሚገኝ ነው። የእስራኤል ነገዶች የሚታተሙት በዚያ መከራ ጊዜ ጌታን የሚቀበሉ በደሙ የተዋጁ የጌታ አገልጋዮች ናቸው ።ለእነዚህ የነገድ የቋንቋ ልዩነት የላቸውም ። ከኹሉም ነገድ የተወጣጡ አማኞች ናቸው ።ጥቍርም ነጩም የኾኑ ኹሉ

ናቸው ። እውነተኛ እስራላዊነት በክርስቶስ የአብርሃምን በረከት መውረስ ነውና። ቃሉም ስለ ሚታተሙት ሰዎች ሥጋዊ ማንነት ስገልጽ ፡-

"ከዚህ በኋላ አየሁ፥ እነሆም፥ አንድ እንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል ከሕዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ፤ ነጭ ልብስም ለብሰው የዘንባባንም ዝንጣፊዎች በእጃቻቸው ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆሙ፤" ራእይ 7፥9። እነዚህን እስራኤል ዘሥጋ ናቸው ማለት ጭፍናምነት ካልኾነ ወይም ገማችነት ካልኾነ; ምን ልባል ይቻላል ? አንባቢ ኾይ ያስተውሉ። እነዚህ ቅዱሳን በታላቅ ደስታ ጌታን ስያመሰግኑ ፣"በታላቅም ድምፅ እየጮሁ፡- በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለአምላካችንና ለበጉ ማዳን ነው አሉ።"ራእይ 7፥10። በዙፋኑ ለተቀመጠው አብና ለበጉ እኩል ምስጋና ስያቀርቡ እንመለከታለን ። እነዚህ ቅዱሳን ጌታን ማመስገናቸው ተከትለው ሌሎችም ምስጋናቸውን; ይቀጥላሉ ፣ራእይ 7፥[11] "መላእክቱም ሁሉ በዙፋኑና በሽማግሌዎቹ በአራቱም እንስሶቹ ዙሪያ ቆመው ነበር፤ በዙፋኑም ፊት በግምባራቸው ተደፉ፥ ለእግዚአብሔርም እየሰገዱ፡-[12] አሜን፥ በረከትና ክብር ጥበብም ምስጋናም ውዳሴም ኃይልም ብርታትም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ለአምላካችን ይሁን፤ አሜን አሉ።" ከዚያም ስለእነዚህ ሰዎች አኹንም ጥያቄ ብዥታ እንዳይኖር ፣ "የታተመው 144,000 ቅዱሳኖች እነማን ናቸው?" ብሎ አንዱ ከሽማግሌዎች መሃል ዮሐንስን ይጠይቀዋል ። ዮሐንስ የጌታን ፍርድ የሚገለጠውን ስመለከት ማንስ ልድን ወይም ልቆም ይችላል ? በማለት ሰው ለመዳን እንኳን የማያስችል ታላቅ ቍጣ በመኾኑ ላቀረበው ጥያቄ መልሱን ይሰጣል ፡-

ራእይ 7፥ [13] "ከሽማግሌዎቹም አንዱ ተመልሶ፡- እነዚህ ነጩን ልብስ የለበሱ እነማን ናቸው? ከወዴትስ መጡ? አለኝ።[14] እኔም፡- ጌታ ሆይ፥ አንተ ታውቃለህ አልሁት። አለኝም፡- እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው፥ ልብሳቸውንም አጥበው በበጉ ደም አነጹ።[15] ስለዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት አሉ፥ ሌሊትና ቀንም በመቅደሱ ያመልኩታል፥ በዙፋኑም ላይ የተቀመጠው በእነርሱ ላይ ያድርባቸዋል።[16] ከእንግዲህ ወዲህ አይራቡም፥ ከእንግዲህም ወዲህ አይጠሙም፥ ፀሐይም ትኵሳትም ሁሉ ከቶ አይወርድባቸውም፤[17] በዙፋኑ መካከል ያለው በጉ እረኛቸው ይሆናልና፥ ወደ ሕይወትም ውኃ ምንጭ ይመራቸዋልና፤ እግዚአብሔርም እንባዎችን ሁሉ ከዓይናቸው ያብሳል።" አዎን እነዚህ ቅዱሳኖች ከነገድ ከቋንቋ ከሕዝብ ኹሉ የተገኙ፣ ከታላቁ መከራ በደሙ ድል ነስተው የመጡ ናቸው ።እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው። አለቀ። ደግሞም ማን ልቆም ይችላል ለሚለው ጥያቄ መልሱ፣ ማንም ልቆጥራቸው የማይችሉትን ጌታ ያቆማቸዋል ያድናቸውማል የሚል ነው ።

ዮሐንስ ልቆጠሩ የማይቻሉ እንደኾኑ መስክሯል ።ይኸም በዚያ ታላቅ መከራ ልቆጠሩ የማይችሉ ሰዎች ድል በመንሳት ዓለምን ያሸንፋሉ ማለት ነው። ለዮሐንስ ጥያቄ ተገቢ ምላሽ ተሰጥቶታል ። ማንስ ልድን ይችላል ? እስራኤል ዘሥጋ ብቻ

አይደሉም ወይም የሚቆጠሩ ጥቅቶች ብቻ አይደሉም ። ከመከራው በፊት ቀድመው የሞቱ ሰዎች ያቀረቡት ጥያቄ መልስ አግኝቷል ። ፍርደልኝ ስለማለታቸው እንደእነርሱ ታምነው የሚሞቱ ስለመኖራቸው የተሰጠው ቃል ተፈጽሟል ። የእነዚህ ቊጥር ስፈጸም እፈርዳለሁ ጠብቁ እንዳለውም በታላቁ መከራ በደሙ ሃይል ድል ነስተው የሚያልፉት አማኞች ቊጥር ተፈጽሟል ። እነዚህ ቅዱሳኖች ስለተገኙ ኹሉም ነገር ጸጥ ረጭ በማለት ያልቃል ።ጌታ ነግሷልና ሰላም ኾኗል። 6ኛው ማህተም ወደ ዓለም መጨረሻ የሚያመራ ነው። በ7ተኛው ማህተም የሚድኑት ኹሉ ከዳኑ በኋላ የእግዚአብሔር ሰላም መምጣቱን በጸጥታ ይገልጻዋል  ሌሎች መግለጫዎች በድል ዝማሬዎች ይገልጣሉ ።“ሰባተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ እኵል ሰዓት የሚያህል ዝምታ በሰማይ ሆነ።" ራእይ 8፥1። በቃ አለፈ ፤በጉ ነገሰ፤ሰላም ሰፈነ ማለት ነው።ሃሌ ሉያ።

ውድ አንባቢ ኾይ; ከታላቁ መከራው በፊት የሞቱ ሰዎች አየር ላይ ኾነው ፍረድልን አላሉም፤ እራት እየበሉም አይደሉም ፤ሰርግም የለም። እነርሱ ሞተዋል ሰማዕት ኾነዋል። ጌታን የሚለምኑት ፍርድን ነው። ልክ እንደ አበል ደም; ደማቸው ፍትህን ይጠይቃል ። አልተነጠቁም በአየር ላይም አይደሉም ። ደማቸው ከምድር ይጮሃል ። እንደእነርሱም ደግሞ በግፍ የሚሞቱት ሰማዕት ከኾኑ በኋላ ጌታ ጸጥ ረጭ አደረገ።መንግስቱን ተቆጣጠረ ። ሃሰተኛ አስተማሪዎች እንደሚሉት አይደለም ። የቃሉ እውነት ግን ስመሰክር ማመካኛ ያሳጣል ። አንድ ላይ እንደ ቀድሞቹ ሰማዕት በመከራው ጊዜ የሚሞቱ ሰማዕትም ፍትህን ያገኛሉ። ጌታ ከመከራው በኋላ ይመጣል ። ይወስደናል ። ይኽንን እንደ ቃሉ አለማመን ለሲኦል ሙሽሪነት መታጨት ነው። መከራ አያገኛችሁም ብሉም እንኳን በመከራው እንደ ቀድሞቹ ማለፋቸው የቃሉ እውነት ነው። ሃይልን እንዳትቀበሉ ተኝታችሁ እያላችሁ ከሰማይ የሚጣለው ሰይጣን እንድነጥቃችሁ፣ ከመከራው በፊት ትነጠቃላችሁ ይላሉ ። ለእግዚአብሔር በኢየሱስ ስም ክብር ይግባውና ይኽንን የተረዱ ሃይልን ለመቀበል የሚዘጋጁ እግዚአብሔር የሚሠራቸው ብርቱዎች አሉ፤ ብዙም ናቸው ።

## 3.3. ሴቲቱና ዘሯ

ይኽንን ለመረዳት ሙሉእ የራእይ መጽሐፍ ም.12 ዳሰሳ እናደርጋለን ፣ <<ታላቅ ምልክትም በሰማይ ታየ ፀሐይን ተጐናጽፋ ጨረቃ ከእግሮችዋ በታች ያላት በራስዋም ላይ የአሥራ ሁለት ከዋክብት አክሊል የሆነላት አንዲት ሴት ነበረች። እርስዋም ፀንሳ ነበር፥ ምጥም ተይዛ ልትወልድ ተጨንቃ ጮኸች። ...   አሕዛብንም ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ልጅ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ልጅዋም ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ።ሴቲቱም ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን በዚያ እንዲመግቡአት በእግዚአብሔር ተዘጋጅቶላት ወደ ነበረው ስፍራ ወደ በረሀ ሸሸች።..... ከእባቡም ፊት ርቃ አንድ ዘመን፥ ዘመናትም፥ የዘመንም እኵሌታ ወደ ምትመገብበት ወደ ስፍራዋ ወደ በረሀ እንድትበር ለሴቲቱ ሁለት የታላቁ ንሥር ክንፎች ተሰጣት። እባቡም ሴቲቱ በወንዝ እንድትወሰድ ሊያደርግ ወንዝ የሚያህልን ውኃ ከአፉ በስተ ኋላዋ አፈሰሰ።

ምድሪቱም ሴቲቱን ረዳቻት፥ ምድሪቱም አፍዋን ከፍታ ዘንዶው ከአፉ ያፈሰሰውን ወንዝ ዋጠችው።ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ ተቈጥቶ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትን የኢየሱስም ምስክር ያላቸውን ከዘርዋ የቀሩትን ሊዋጋ ሄደ፤ በባሕርም አሸዋ ላይ ቆመ።>> ራእ 12፥ 1-18።

* በዚህ ምዕራፍ ላይ ስለ ዘመን ፍጻሜ የሚሰጠው መግለጫ በአዲስ ክስተት የተመላ ነው፤ ክስተቱም ተአምሩም ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ ነው። አዲስና ልዩ ነው። ስለ ዘመን ፍጻሜ ለማሳወቅ ማብራሪያውን ከሰማይ ይጀምራል ። ወደ ፍጻሜው የሚደረገው ግስጋሴ በታላላቅ ክስተቶች የተሞላ ነው። በሴቲቱ ቷ መገለጥ ። ይህቺ ሴት ፀሃይን ለብሳ ፣ጨርቃ ረግጣ ደግሞም በ12 ከዋክብት አክሊል አሸብርቃ እንደተገለጠች በክስተቱ በመደነቅ ዮሐንስ ይገልፃል ። ፀሃይ መልበሷ ፦የብርሃን የጽድቅ ምሳሌ ነው፤ሴቲቱ በክርስቶስ ባሕርይ በጽድቅን [ክርስቶስን] በሙላት በመልበስ እንደተገለጠች ያስገነዝበናል ።እንዲሁም" ጨረቃ የራሱ ብርሃን የሌለው ከሌላው የወሰደውን የሚያበራ ስለኾነ የዲያብሎስ ምሳሌ ነው" [ታላቁ መከራ በደጅ ሐዋ. ጌታቸው ሳሉ]። ይህቺ ሴት ጨረቃን የተጫማች ወይም በክብር ያጠለቀች አይደለችም ።የረገጠች ናት [መደበኛ ትርጉም ይመ.]። ጨረቃ ከእግሮቿ በታች ያላት ናት። ይኸም ጨረቃ ብርሃን ሳይኖረው ብርሃን መስሎ ፣ እውነት ሳይኾን እውነት መስሎ የተገለጠውን መልኩን የቀየረውን የዲያብሎስ ምሳሌ ነው።

ክርስቶስ ለአማኞች የጽድቅ ልብስ ነው። ጳውሎስ ከክብር ወደ ክብር እንሻገራለን እንዳለው ወደ ክብሯ ማማዋ የደረሰች የፍጥረታትም ናፍቆት የኾነች ሴት ናት። ይህቺ አንድ ግለሰብ አይደለችም ። አንድና ወጥ ማህበረሰብ ወካይ እንጂ። ያውም ድል የነሱ ክብራን አማኞችን ።አማኝ ነኝ የሚል ኹሉ ወደዚህ አይደርስም ። የሚደርሱት የተሰጣቸውን ሃላፊነት በአግባቡ የተወጡት ናቸው ። ይህቺ ሴት 12ቱ የሐዲስ ኪዳን እየሩሳሌም ነገዶች ክብር ያላት ናት።

*ሴትቱ ስትገለጥ ጸንሳ ያለች ናት፤ ጽንስ በአንድ ቀን ተረግዞ በአንድ ቀን የሚወለድ አይደለም ። ጸንሳ እያለች ነው የተገለጠችው። በክብር ከተገለጠችው በኋላ ልትወልድ ተጨንቃለች።የተገለጠችው የመውለጃ ጊዜዋ ስለደረሰ ነው። ከምታሳልፈው መከራ የተነሳ ተጨንቃለች ። ከሕመሙ የተነሳ ጮሃለች። ይህቺ ሴት በዓለም ፍጻሜ የሚኾነውን ወክላ የተገለጠች ናት እንጂ የሚንወዳት የኢየሱስ እናት ብፅዕት ማርያም አይደለችም ።ማርያም ስንተ ነው የምትጸንሰው? ምነው ? ይኽ አዲስና ልዩ ክስተት ነውና እናስተውል። ዮሐንስ በደብዳቤው  ከዚህ በፊት የታየውን ክስተትን ታላቅ ምልክት ታይቷል በማለት አልገለጸም ።በታላቅ ፍርሃትና ደስታ ልንመለከተው የሚገባ ነው። የሴትቱ በክብር መምጣት መገለጥ ተከትሎ ፣በሰማይ አኹንም ሌላ አዲስ ክስተት ይከተላል ፣

ራእይ 12፥[3] ሌላም ምልክት በሰማይ ታየ፤ እነሆም ታላቅ ቀይ ዘንዶ፤ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶችም ነበሩት በራሶቹም ላይ ሰባት ዘውዶች ነበሩ፥[4] ጅራቱም የሰማይን ከዋክብት ሲሶ እየሳበ ወደ ምድር ጣላቸው። ዘንዶውም ሴቲቱ በወለደች ጊዜ ሕፃንዋን እንዲበላ ልትወልድ ባላት ሴት ፊት ቆመ። ... [7] በሰማይም ሰልፍ ሆነ፤ ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉ።

ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ፥ አልቻላቸውምም፥[8] ከዚያም ወዲያ በሰማይ ስፍራ አልተገኘላቸውም።[9] ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፥ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፤ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ።

የሴቲቱ በክብር በመለኮታዊ ሃይል በጽድቅ መገለጧ፣ በሰማይ ያሉትን የመናፍስቱን ጦርነት እንዲግል ያደርገዋል ። በቅዱሳንና በእርኩሳን መላእክት መካከል ትልቅ ጦርነት አለ፤የነበረ ነው፤ዳን 10። ግን ዲያቢሎስ እስካሁን ጳውሎስ እንደገለጠው በሰማይ ስፍራ ያለ ነው። “መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።” ኤፌሶን 6፥12 ። ሴቲቱ ስትገለጥ በምድር ከፍተኛው ክብር ላይ ደርሳ ስትገኝ፣ ደግሞም ከምታልፈው መከራ የተነሳ ተጨንቃለች ደግሞም ልትወልድ ደርሳ ስትገለጥ፣ በሰማይ የነበረው ጦርነት ቅዱሳኑንና እርኩሳን መላእክትን ወደ ምድር እንዲወድቁ ያደርጋል ። ዲያቢሎስ ተሸንፎ ስወድቅ፤ ከራሱ ጋር 1/3ኛ የሚያህሉትን ቅዱሳንን መላእክትን ይዞ ይወርዳል ። በዚህም ሃይል እንዳለው ሃይሉ እንዳልተወሰደ እንረዳለን ። ቅዱሳን መላእክቱ ከእርሱ ጋር ወደ ምድር ወረዱ። ለሐዲስ ኪዳን እስራኤል የሚገባትን ጥበቃ ለማድረግ ።የቆሰለ ውሻ ስናከስ መጥፎ ነውና እንዳይጎዳቸው ለመከላከል መላእክቱ ወርደዋል ። በዚህም በመጨረሻው ጦርነት የማይታዩ አካላትም በጦርነቱ ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ እንደሚያደርጉ እንረዳለን ።

*የሰይጣን ወደ ምድር መጣል የታላቁ መከራ ጅማሮ እንደኾነ አይተናል ። በሰይጣን ወደ ምድር መጣል የተሰጣትን መከራ በድል አልፋ በቅድስና እንደ ፀሃይ የበራችው የክርስቶስ አካል ሌሎችን ልጇቿን ዘሯን ለመውለድ ልትጸንስ ደርሳ ነበረች። ዲያቢሎስ በእርሷ በቅድስና በመለኮታዊ ባሕርይ መገለጥ ከሰማይ ስለወደቀ ፤ያውም ላይገኝ ከሰማይ ስፍራ ስለተጣለ ደግሞም በሽንፈት ስለተጣለ፣ እርሷን ለማጥፋት ሃይሉንና ጥበቡን ተጠቅሞ አሳደዳት። ይኽም የታላቁ መከራ ጅማሮ ነው። ምንም እንኳን ዲያቢሎስ እንዲህ በቍጣ ብያሳድዳትም ፤ቀንዱ ሃይሉ ኾነ ራሱ ጥበቡ ልይዛት ልውጣት አልቻለም ። የሰማይን ጦርነት ስለተሸነፈ በምድር በግልጽ ያወጀውን ጦርነት ለማነሸነፍ ብመጣም ፤ ልውጣት አልቻለም ።እግዚአብሔር ለሴትቱ ታላቅ ንስር ክንፍ መለኮታዊ ሃይል ሰጥቷት ስለነበር አመለጠች፤ ሴትቱን በናፍቆት ትጠብቃት የነበረችው ፍጥረታትም ኤረዷት፤ የዘንዶውን ማህበረሰብ በታላቅ መቅሰፍት በመምታት ዋጠች፤አጠፋችው። ምድርም ለቅድስት ቤተክርስቲያን ዋሻ መከለያ ኾነች።የተናፈቀችው የእግዚአብሔር ልጆች ተገልጠዋልና አገዘችው። ስለዚህም ሴትቱ አማኞች ናቸው ። ዛሬ ላይ አማኝ ነኝ የሚሉ ናቸው እያልኩ አይደለም ። ድል በመንሳት ከታላቁ መከራ እንዲሰወሩ የተደረጉ አማኞች ናቸው ።ካስተዋልን ጌታ ለፊልድልፍያ ቤተክርስቲያን የነገረው የተስፋ ቃል ፍጻሜ ያገኙት አማኞች ናቸው ።እንደ ፊልድልፍያ ቤተክርስቲያን ያለ ነቀፌታ የሚሄዱት ወደዚህ ክብር እንደሚደርሱ ጌታ አስታውቋል ፡-

“የትዕግሥቴን ቃል ስለ ጠበቅህ እኔ ደግሞ በምድር የሚኖሩትን ይፈትናቸው ዘንድ በዓለም ሁሉ ላይ ሊመጣ ካለው ከፈተናው ሰዓት እጠብቅሃለሁ።”ራእይ 3፥10።

አየ; በመከራ በጭንቅ በትዕግሥት ያለፉትን የተሰጣቸውን መስቀል የተሸከሙትን ጌታ ለእነርሱ ካልተገባ መከራ ይጠብቃል ።ይኽ ለእኛ ነው። ጆሮ ያለው ይስማ ተብለናልና ። በዓለም የሚኖሩ ኹሉ በሚፈተኑበት ፈተና ያለ ነቀፌታ የኖሩ ቅዱሳን አይፈተኑም። ጌታ ዓለም ኹሉ በመከራ ስያልፍ "ከመከራው እጠብቃለሁ" የሚልን ተስፋ ሰጥቷል። እንግዲህ ይኽ መከራ ዓለም ኹሉ የሚያልፍበት አንደኛው ታላቁ መከራ ነው። ጌታ በመከራው እጠብቃለሁ እንዳለ ይጠብቃል ።ተነጥቀው አይደለም ።ኤልያስን እንደ ጠበቀ ይጠብቃል ።እንደ ሰወረ ይሰውራል ። ይኽ የእግዚአብሔር ሥራ ነውና በሠራሃት ምድር ታላቁ መከራ እንዳያገኘን ይጠብቀናል ። ወዳጆቼ ይኽ ተስፋ አለን።ይኽ ቃል አለን። ግን ሰይጣን በመከራው እንዲትነጠቁ በድካማችሁ ተቆራምዳችሁ እንዲትኖሩ መርዙን ይግታል። ሴቲቱን ሰይጣን ልነካና ልጨፈልቅ አይችልም ።ወደዚህ እንዳትደርሱ በብዙ መንገድ ትምህርት አዕምሮን በማሳወር ላይ ነው።ሰው ይኽንን እውነት አውቆ እየተጽናና መከራውን እየታገሰ ድል እንዳይነሳ ሳይታክት ይሠራል ። ሴትቱ ማርያምም አይደለችም እስራኤል ዘሥጋም እይደለችም ። ከታላቁ መከራው በፊት በጽድቅ የተገለጡ በመምጣቱ የኖሩ፣ ያለ ነቀፌታ የተመላለሱ ፣ በክርስቶስ የኾኑት ናቸው ። አዎን ጽድቅ ልብሳቸው የኾነላቸው ሃሰተኛውን መርገጥ ክብራቸው የኾነላቸው ሃሰተኞችም አውሬውም ልውጣት ኾነ ልቋቋማት ያልቻላት መለኮታዊ ሃይልን የለበሰች በክርስቶስ ያለች ቤተክርስቲያን ናት ሴቲቱ። እነዚህ አማኞች በታላቅ መከራ አይጎዱም። መከራው ልያገኛት አይችልም ። ከሰይጣንም በላይ ስለኾኑ ተስፋ ቆርጦ ወደ ቀሩት ትኩረቱን ያዞራል። ሴትቱ በዚህ መከራ መሃል ለዓለም የተወቻቸው ልጆቿ ዘሯ እነማን ናቸው ?

*ዘሯ ሰይጣን ወደ ምድር ከወደቀ በኋላ ኹለተኛ እላማ ውስጥ የወደቁት ናቸው ።ዘሯ መኾናቸው የአካልን ከፋይነትን ያረጋግጣል ።ይኽ ከእርሷ የተወለዱ ወይም የተገኙ ልጆች መኾናቸውን ።ይኽ ከስተት በታላቁ መከራ ጊዜ የሚኾን ነው።አንባቢ ያስተውል። “ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ ተቈጥቶ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትን የኢየሱስም ምስክር ያላቸውን ከዘርዋ የቀሩትን ሊዋጋ ሄደ፤”ራእይ 12፥17 ። ከሴትቱ የቀሩት ቅሬታዎች ዘሯ የኾኑ አካሎቿን ልዋጋ ፊቱን ወደእነዚህ ያዞራል ። ከዘሯ የቀሩትም የዋዛ አይደሉም ።ሴትቱ ከሰይጣን ሃይልና አቅም በላይ ኾና ሌላ መከራ እንዳትቀበል ስትሰወር ስትበርር ፣ ለዓለም በዚያ ጊዜ እንዲያገለግሏት ለዚህ ግዜ ጳንሳ ያቆየችው ልጁ ቿ አሏት ፤ወንድ ልጆቿ።እነዚህም ከእርሷ የተገኙ እንደ እርሷ ያሉ ናቸው ። እነዚህ እነማን ናቸው ?

“አሕዛብንም ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ልጅ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ልጅዋም ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ።” ራእይ 12፥5።

ሴትቱ የራሷን አገልግሎት ጨርሳ ወደተዘጋጀላት ማረፊያ ጊዜያዊ መደበቂያ ስፍራ ላይ [ለ3ዓመት ከተኩል] ስትቆይ ፣ ጸንሳ የነበረችኹን ልጅ ወልዳ ለዓለም ዘሯን ሰጥታ ትሸሽጋለች።ለዚህም ነው ሴቲቱ ማርያም አይደለችም የምንለው ። ሴቲቱ የወለደችው ልጅ፣ በቀጥታ ኢየሱስ ነው እንዳንልም የሚያደርገን ። አዎን ይኽ ለእርሱ የተሰጠ በእጁ ያለ ስልጣን ነውና።ግን ካስተዋልን ይኽ ስልጣን የሚሰጣቸው አማኞች እንዳሉ ጌታ ተስፋ ሰጥቷል፣

"ድል ለነሣውና እስከ መጨረሻም ሥራዬን ለጠበቀው እኔ ደግሞ ከአባቴ እንደ ተቀበልሁ በአሕዛብ ላይ ሥልጣንን እሰጠዋለሁ፥ በብረትም በትር ይገዛቸዋል፥ እንደ ሸክላ ዕቃም ይቀጠቀጣሉ፤" ራእይ 2፥26-27

የተሰጠውን መስቀል በድል የተወጣ አማኝ ወደዚህ ክብር ይደርሳል ። ይኽንን ስልጣን አስቀድሞ እሰጣለሁ ብሎ የገለጠው ጌታ ነው። ከቤተክርስቲያን ለዚህ ክብር የሚበቁ አሉ። በአሕዛብ ላይ ስልጣን የሚሰጣቸው እንደ ሸክላ የሚቀጠቅጡ። ይኽንን ለመረዳት ድል የሚነሱት የሚያገኙትን ኹሉን በአግባቡ የተረዳ ሰው አይጠፋበትም። በብረት ብትር ይገዛቸዋል ስለተባለ ብቻ የተወለደው ኢየሱስ ነው ማለት አንችልም ? ቤተክርስቲያን ኾነ ማርያም ወይም እስራኤል ዘሥጋ ኢየሱስን አያስገኙም ። በዚያ ጊዜ የሚፈጸም ታላቅ ክስተት ነው። ኢየሱስም አይነጠቀም። ስለእነዚህ ወንድ ልጆች በሌላ ክፍልም ጌታ መግለጫ ይሰጣል ።በታላቁ መከራ ጊዜ ከዘሯ የቀሩት በስልጣን ያገለግላሉ ። በሃይል ያገለግላሉ ። ይኽ የፍጻሜው አገልግሎት ነው። ከቤተክርስቲያን ምስረታ ከ120ዎቹም የሚልቅ ነው። በሐዋርያት ዘመን መንፈስ ቅዱስን ያሳዘነ ድፍት ብሎ በፊታቸው ይደፋል ። ክብሩ ስላለ ውሸት ስፍራ አልነበረውም ።በእነዚህ ፍጻሜ አገልጋዮች ከዚህ በላይ ይኾናል ። የተሰጣቸው ስልጣን የዘንዶ ማህበረሰብ ልቋቋመው የማይችል ነው። በሌሎች መግለጫዎች ስለእነዚህ ቅረታ ከዘሯ ስለቀሩት ልጆች አገልግሎት እንዲህ ይነበባል ፦

ራእይ 11፥[1] "በትር የሚመስል መለኪያ ለእኔ ተሰጠኝ፥ እንዲህም ተባለልኝ፦ ተነሥተህ የእግዚአብሔርን መቅደስና መሠዊያውን በዚያም የሚሰግዱትን ለካ።[2] በመቅደሱም ውጭ ያለው እድሞ ለአሕዛብ ተሰጥቶአልና ተወው አትለካውም፤ እነርሱም አርባ ሁለት ወር የተቀደሰችውን ከተማ ይረግጡአታል።[3] ለሁለቱም ምስክሮቼ ማቅ ለብሰው ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን ትንቢት ሊናገሩ እሰጣለሁ።[4] እነዚህ በምድር ጌታ ፊት የሚቆሙ ሁለቱ ወይራዎችና ሁለቱ መቅረዞች ናቸው።[5] ማንምም ሊጐዳቸው ቢወድ እሳት ከአፋቸው ይወጣል ጠላቶቻቸውንም ይበላል፤ ማንም ሊጐዳቸው ቢወድም እንዲሁ ሊገደል ይገባዋል።[6] እነዚህ ትንቢት በሚናገሩበት ወራት ዝናብ እንዳይዘንብ ሰማይን ሊዘጉ ሥልጣን አላቸው፥ ውኃዎችንም ወደ ደም ሊለውጡ በሚፈልጉበትም ጊዜ ሁሉ በመቅሠፍት ሁሉ ምድርን ሊመቱ ሥልጣን አላቸው።"

ይኽ ክፍል ስለፍጻሜው ከቀረበው መግለጫዎች በምድር የሚፈጸሙትን" ማስጠንቀቂያዎች" የሚያትት ክፍል ስኾን፣ እስከዛሬ ዮሐንስ ራእዩን ከተመለከተበት ጊዜ አንስቶ የሚኾነውን ማስጠንቀቂያ ይይዛል ።ይኽም ጌታ ፍርድ ብቻ ሳይኾን

የቊጣ መግለጫ የኾኑ ማስጠንቀቂያም እንደሚያደርግ ያሳውቃል ።ከምዕራፍ 8 ከቊ.2 ጀምሮ እስከ 11፥18 ያለው ።በዚህ ልክ መመልከት ካልቻላችኹ አውዱን መያዝ አትችሉም ። ማስጠቀቂያዎቹ በምነፉ በ7ቱ መለከቶች የተገለጡ ስኾኑ ፣ መቅሰፍቶች ሰውን ሳይኾን የሰውን አከባቢ የሚመቱ እንደኾኑ የራእይ መጽሐፍ ይዘት ስንመለከት አይተናል ። ይኸም ወደ ፍጻውም ስገሰግስ ያለውን ክስተት ያሳየናል ።በዚህ ላይ መግለጫዎቹ የመጨረሻ የመጨረሻውን ይገልፃሉ ።ዋናው ዓላማው የተራራውን ጫፍ የክርስቶስ መምጣት ማሳየት ስለኾነ ። ሃሳቡን ለመያዝ ለ7ቱ ማስጠንቀቂያዎች ፣ 5ተኛው መለከት ምዕራፍ 9፤የሰይጣንን መውደቅ ያበሥረናል። ይኸም ታላቁን መከራ ጅማሮ ይገልጻል ።ምክንያቱም ታላቁ መከራ የሚጀምረው በሰይጣን ከሰማይ መውደቅ እንደኾነ በሌሎች መግለጫዎች አይተናል ።“አምስተኛውም መልአክ ነፋ፤ ከሰማይም ወደ ምድር ወድቆ የነበረ ኮከብ አየሁ፥ የጥልቁም ጒድጓድ መክፈቻ ተሰጠው።” ራእይ 9፥1 ።
አምስተኛው መለከት ስነፋ የታላቁ መከራ ጅማሮ የሚያበስር ስለኾነ፣ ከሰማይ ኮከብ መውደቁን ይገልጻል ።ከሰማይ የወደቀው ሰይጣንም ይኸንን ተከትሎ በምድር ታስረው ያሉትን ስፈታና ለጦርነት ለጥፋት ስያዘጋጅ እናያለን ። አንባቢ ኾይ ወደኋላ ሄጄ የማሳየው ሙሉ መረዳት እንድኖር ምናልባት ከረዳሁ ብዬ ነው።አይሰለቹ። አምስተኛው ከተነፋ የሚቀረው ኹለት ነው። እንደ ማስጠንቀቂያዎች ገለፃ ከኾነ በአምስተኛው ማህተም ታላቁ መከራ ይጀመራል ።ይኸም የመጨረሻ የመጨረሻ ትይንት የሚገልጽ ነው። በማህተሞቹ ምስጥር ስንመለከት የሚታተሙት ታትመው ሳያልቁ በታላቁ መከራ መሃል የወንጌል እድል ለሰዎች እንደተሰጠ አይተናል ።ራእ7። በዚህም በታላቁ መከራ የንስሐ እድል እንደሚሰጥ ወንጌል እንደሚሰበክ ፍጻሜ ከመደረጉ በፊት አገልጋዮች እንደሚሰብኩ አይተናል።ይኸም በታላቁ መከራ መሃል የሚደረግ እንደኾነ መገንዘብ እንችላለን ።“ወደ ፊት አይዘገይም፥ ዳሩ ግን ሰባተኛው መልአክ ሊነፋ ባለው ጊዜ ድምፁም በሚሰማበት ዘመን፥ ለባሪያዎቹ ለነቢያት የምስራች እንደ ሰበከላቸው የእግዚአብሔር ምሥጢር ይፈጸማል አለ።” ራእይ 10፥7 ። ምንም እንኳን የንስሐ እድል ብሰጥም አለማዊያን ልመለሱ ስላልወደዱ ጌታ የሚወስደውን እርምጃ የሚያትት ክፍል ነው ፤። ራእ 11።
*የእግዚአብሔርን መቅደስና በዚያ የሚሰግዱት ተለዩ። ተለኩ። በሌሎችን ላይ ጌታ ፍርዱን ስገልጽ በመቅሰፍቱም በወንጌሉም ልስተካከሉ ስላልወደዱ ፥ የተቀበሉት እንዳይጎዱ በመለየት ቀጣዩን እርምጃ ይወስዳል ። እነዚህ በመቅደሱ ያሉት አንዳች ጉዳት እንዳይደርስ ተብለው የተለዩ ስኾኑ ሴቲቷ በመባል በሌላኛው መግለጫ ተቀምጠዋል ።ሴቲቱ የወለደቻቸው ልጆች ከዘሯ የቀሩት ደግሞ የዘንዶ ኹለተኛ እላማ የኾኑት ደግሞ ኹለቱ መቅረዞች ተብለዋል ።“እነዚህ በምድር ጌታ ፊት የሚቆሙ ሁለቱ ወይራዎችና ሁለቱ መቅረዞች ናቸው።” ራእይ 11፥4 ።እነዚህ በዚህ ሰዓት የሚያገለግሉ የሴትቱ ዘር ከእርሷ የተገኙ ልጆቿ ናቸው ። አኹን አስተውል ። ኢየሱስ በአሕዛብ ላይ ስልጣን እሰጣለሁ እንዳለው

በአሕዛብ ላይ ስልጣ ኖሯቸው፣ ለዚህ አገልግሎት ከመቅደሱ ከሚሰግዱት  የተመረጡ ፣ ጌታ አሕዛብን የሚቀጣባቸው ፍርድ አስፈጻሚዎች ናቸው ። የእነዚህ የመጨረሻ ዘመን በታላቁ መከራ የሚያገለግሉት አገልጋዮች አገልግሎት ለ3ዓመት ከተኩል የተገደበ ነው።“ለሁለቱም ምስክሮቼ ማቅ ለብሰው ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን ትንቢት ሊናገሩ እሰጣለሁ።” ራእይ 11፥3።

*ወዳጄ አኹን እናገናኘው። በሴቲቱ በክብር መገለጥ ሰይጣን ከሰማይ ይወድቃል፣ መላእክቱ ይጥሉታል ።ከዚያም ሴቲቱ ልጆቿን ትወልዳለች ፤ ሴቲቱም የእነዚህ ልጆች መገኛ ስለኾነች እንዳትወልድና ከወለደችም ለሙብላት ብዙ ጣሬ ግን አልተሳካም ። የተዘጋጁትን ካሳደደ በኋላ ከእርሷ የተገኙትን ያሳድዳል። ሰይጣን እነዚህን ልጆቿን ቤተክርስቲያን እንድትወልድ ለምን ይፈራል ? ይተጋል? እነዚህ አገልግሎታቸው በስልጣን ነው። ልነካቸው ልቋቋማቸው አይችልም ። ሴቲቱ ወልዳ 1260 ቀን ብቻዋን ስትሰደዱ፣ ልጇ ደግሞ 1260 ቀን ያገለግላል ። አየህ የዘሯ የቀሩት እንደእርሷ በመለኮታዊ ሃይል የተሞሉ ስልጣን ያላቸው እንደኾኑ ። እነዚህ ኹለቱ ወረራዎች የተባሉት ብርቱዎች እንዲህ ያሉ ናቸው ፦

ራእይ 11፥5 ማንምም ሊጎዳቸው ቢወድ እሳት ከአፋቸው ይወጣል ጠላቶቻቸውንም ይበላል፤ ማንም ሊጎዳቸው ቢወድም እንዲሁ ሊገደል ይገባዋል። 6 እነዚህ ትንቢት በሚናገሩበት ወራት ዝናብ እንዳይዘንብ ሰማይን ሊዘጉ ሥልጣን አላቸው፥ ውኃዎችንም ወደ ደም ሊለውጡ በሚፈልጉበትም ጊዜ ሁሉ በመቅሠፍት ሁሉ ምድርን ሊመቱ ሥልጣን አላቸው።

እነዚህ በኤልያስ እና በሙሴ መንፈስ የሚያገለግሉ ጌታ የሰጠውን መስቀል በትዕግሥት ያለፉ ለዚህ ክብራማ አገልግሎት የተመረጡ ቅዱሳኖች ናቸው ። ይኽ ስልጣን በኢየሱስ የተሰጠ ነው። ራእዩ 12 ተወልደው መነጠቃቸውን ብቻ ይገልጻል ። እነዚህ በ1260 መከራ ቀናት የሚያገለግሉ የጌታ ብርቱ ወታደሮች አሕዛብን ረግጠው ቀጥቅጠው ከአገለገሉ በኋላ ይነጠቃሉ ።በመከራው አልፈው በመጨረሻም ነፍሳቸውን ይተወዋሉ። በሞታቸው የዘንዶ ማህበረሰብ ደስታውን ይገልፃሉ ።ግን ከሦስት ቀን በኋላ ከተሰቀሉበት ተነስተው ወደ ሰማይ አሕዛብ እያዩ ይወሰዳሉ ።

*ውድ አንባቢ ኾይ; ሴቲቱ እንደ ፊላደልፊያ ቤተክርስቲያን ያለ ነቀፌታ ያለች ቅዱሳን ስኾኑ፣ የእርሷ ዘር የኾኑት ደግሞ በክርስቶስ ያሉ ኹሉ አማኞች ናቸው ። አንድ መንፈስ ስለጠጡ። ዘመኑን ያወቀችው ሴቲቱ የሚትወልደው የሚታዘጋጀው ዘሯ ከእርሷ የተገኙት ወንዶች ልጆች ብርቱዎች ለዚህ አገልግሎት የተመረጡ እንደ ትያጥሮን ቤተክርስቲያን ድል በመንሳት በአሕዛብ ላይ ስልጣንን የተቀበሉ ናቸው ። ነገርግን በክርስቶስ ኾነውም ሳይነቁ ድል ሳይነሱ ያሉት ዘሮቿ ወይም አንድ መንፈስ ያላቸው አሉ።ምክንያቱም የተዘጋጁት ብቻ ናቸው ከመከራው የሚሸሽጉት። ያልተዘጋጁት አማኞች ደግሞ በዚያ መከራ ጊዜ በሰይጣን የመታለል እድል አላቸው ።“ቅዱሳንንም ይዋጋ ዘንድ ድልም ያደርጋቸው ዘንድ ተሰጠው፥ በነገድና

በወገንም በቋንቋም በሕዝብም ሁሉ ላይ ሥልጣን ተሰጠው።" ራእይ 13፥7። ዘሯ ኹለት ትርጓሜ ይይዛል እያልኩ ነው። አንደኛው በመከራው በስልጣን የሚያገለግሉ ስኾኑ፣ ኹለተኛው ያልነቁ አማኞች ናቸው ። ከእነዚህ ብዙዎችንም በሰይጣን ይሸነፋሉ። የቅድሜ መከራ ንጥቀት አስተምህሮ ፣ አኹን ተዘጋጅተህ መከራ ከማያገኛቸው ሴቲቱ እንዳትኾንና በመከራው መሃል ለማገልገል ከሚመረጡት ብርቱዎች እንዳትኾን ማድረግ ነው።ምክንያቱም የቀሩትን በቀላሉ ያሸንፋል ። የቅድሜ መከራ አስተምህሮ ግና ለሚገለጠው አውሬ መንገድ ከሚጠርጉ አስተምህሮዎች አንደኛው ነው። ይኽንን እወቅ። ዘሯ የተባሉት ጌታን የተቀበሉ ኹሉ ስኾኑ፣ከዘሯ ደግሞ ድል ነስተው በፍጻሜው በስልጣን የሚያገለግሉት ወንድ ልጇ ናቸው ።

*ውድ አንባቢ፣ ጌታ ድል ለሚነሱት የሚሰጠውን ለመቀበል ብንተጋ አይሻልም !? አዎን ድል ለነሳው ይላልና፤ ድል ለመንሳት እንዲያበቃን አብዝተን ይኽንን እያሰብን እንድረዳን እንጸልይ ! በውነት ሴቲቱ እስራኤል ዘሥጋ በፍጹም አይደለችም ። በሃሳባቸው በቀላሉ መመከት እንችላለን ። ሴቲቱ እስራኤላውያን ናቸው የሚሉ፣ እስራኤላውያን በታላቁ መከራ በሰማዕትነት እያለፉ ድል ይነሳሉ፤መከራውን ይቀበላሉ ይላሉ።ነገርግን ሴቲቱ ታላቁን መከራ እንዳትቀበል ተደርጋ፣ እግዚአብሔር በዚያ በታላቁ መከራ ጊዜ እንዲትሰወር ወዳዘጋጀው ስፍራ ትገባለች ።ይኽንን አላስተዋሉም ። ብያስተውሉ እንዲህ አይሉም ነበር። እናንተ ግን ንቁ።

ራእይ 11፥[7] "ምስክራቸውን ከፈጸሙ በኋላ ከጥልቁ የሚወጣው አውሬ ይዋጋቸዋል ያሸንፋቸውማል ይገድላቸውማል።[8] በድናቸውም በታላቂቱ ከተማ አደባባይ ይተኛል እርስዋም በመንፈሳዊ ምሳሌ ሰዶምና ግብጽ የተባለች ደግሞ ጌታቸው የተሰቀለባት ናት።[9] ከወገኖችና ከነገዶችም ከቋንቋዎችም ከአሕዛብም የሆኑ ሰዎች ሦስት ቀን ተኩል በድናቸውን ይመለከታሉ፥ በድናቸውም ወደ መቃብር ሊገባ አይፈቅዱም።[10] እነዚህም ሁለት ነቢያት በምድር የሚኖሩትን ስለ ሣቀዩ በምድር የሚኖሩት በእነርሱ ላይ ደስ ይላቸዋል በደስታም ይኖራሉ እርስ በርሳቸውም ስጦታ ይሰጣጣሉ።[11] ከሦስቱ ቀን ተኩልም በኋላ ከእግዚአብሔር የወጣ የሕይወት መንፈስ ገባባቸው በእግሮቻቸውም ቆሙ፥ ታላቅም ፍርሃት በሚመለከቱት ላይ ወደቀባቸው።[12] በሰማይም፦ ወደዚህ ውጡ የሚላቸውን ታላቅ ድምፅ ሰሙ፤ ጠላቶቻቸውም እየተመለከቱአቸው ወደ ሰማይ በደመና ወጡ።"

ከሴቲቱ የተወለዱት እነዚህ ሰይጣን በተፈታበት በራሱ ጥቅት ጊዜ እንኳን የሚያስጨንቁ ጦረኞች የክርስቶስ ወታደሮች ናቸው ። ሞተው ሳይቀበሩ ከ3ቀን በኋላ ይነሳሉ።አሕዛብ ደስታቸውን ሳይጨርሱ ከሞት ተነስተው ይነጠቃሉ። አገልግሎታቸው ስለተፈጸመ ወደ ጌታ ይሰበሰባሉ ። ከዚህም በኋላ ጌታ በታላቅ ፍርድ ይመጣል ።መነጠቅ ከመከራው በኋላ ብቻና ብቻ ነው።የበጉ ሰርግም ከመከራው በኋላ ብቻና ብቻ የሚኾን ነው። እንደሌሎቹ መግለጫዎች በ7ኛው

መለከት እግዚአብሔር መንግስቱን መቆጣጠሩን ያበሥራል። "ሰባተኛው መልአክ ነፋ፤ በሰማይም፦ የዓለም መንግሥት ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ ሆነች፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣል የሚሉ ታላላቅ ድምፆች ሆኑ።" ራእይ 11፥15

*ስለዚህም በአጭር ቃል ሴቲቱ ድል የነሳች ቤተክርስቲያን ስትኾን፣ መከራው ሳያገኛት ተጠብቃ ለ1260 ቀን የሚታልፈዋ ናት። ጌታ የሰጣት ተስፋ ያገኘች፣ "የትዕግሥቴን ቃል ስለ ጠበቅህ እኔ ደግሞ በምድር የሚኖሩትን ይፈትናቸው ዘንድ በዓለም ሁሉ ላይ ሊመጣ ካለው ከፈተናው ሰዓት እጠብቅሃለሁ።" ራእይ 3፥10።

*ወንዱ ልጇ ደግሞ ከዘሯ የቀሩት ቅሬታዎች ስኾኑ፣ ጌታ ለዚህ አገልግሎት ያዘጋጃቸው ናቸው፤ "ድል ለነሣውና እስከ መጨረሻም ሥራዬን ለጠበቀው እኔ ደግሞ ከአባቴ እንደ ተቀበልሁ በአሕዛብ ላይ ሥልጣንን እሰጠዋለሁ፥ በብረትም በትር ይገዛቸዋል፥ እንደ ሸክላ ዕቃም ይቀጠቀጣሉ፤"ራእይ 2፥26-27

*144,000 ቅዱሳኖች ደግሞ በታላቁ መከራ ጊዜ የሚታተሙ አማኞች ናቸው፤ በመከራው በእሳት ስለሚያልፉ በታላቁ መከራ የሚመሰክሩ ስለኾኑ፣ ኹለተኛ ሞት ላይ ልጎዱ የማይችሉ በእሳቱ የሚያልፉ አማኞች ናቸው።ልክ እንደ ሰምርሴስ ቤተክርስቲያን ። ምክንያቱም ቅድሜ መከራ አንዳች አይነት ንጥቀት የለም። ኹሉም የተሰጠውን መስቀል በትዕግስት ተቀብለው ከመከራው በኋላ የሞቱት ይነሳሉ፤ በሕይወት ያሉት [ሴቲቱ] ትለወጣለች፤ ይነጠቃሉ ። መጽሐፍ የሚመሰክረው ይኽንኑ ነው። ወስብሐት ለእግዚአብሔር ።

*ይኽንን አውቃችሁ ተዘጋጅታችሁ ጌታ ላሰበላችሁ ሕይወት እንዳትደርሱ በመከራው ለመናጠቅ፥ከፉው ይኽንን እንዲታውቁ አይፈልግም ። እናንተ የማታውቋቸው ይኽንን ተረድተው የሚኖሩ የሚዘጋጁ ብዙዎች ናቸው፤አሉ። እንነሳ ፊታችንን ወደ እርሱ እናቅና። ድል ለመንሳት ።

*****ልዩ ማብራሪያ ስለ ሴቲቱ**;** ሃይል የለበሰችው የሴቲቱን መገለጥን ጳውሎስ በምስጢር ፍጥረታት እንኳን በናፍቆት የሚጠባበቁት እንደኾና ምጥ ተይዘው እንደሚኖሩ ያስረዳል ፦ "ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ።" ሮሜ 8፥18። ሐዋርያው ጳውሎስ አኹን የሚቀበለውን መከራውን ከሚጠብቀው ክብር ጋር በማመዛዘን ሕሳብ ይሰራል ፤ አኹን የሚቀበለውን መከራውም ምንም እንዳይደለ ስሌቱን ይደመድማል ። መከራ ስቀነስ ከሚገለጠው ክብር; ነጋቲቭ ሳይመጣ አይቀርለትም ። እንዲህ ማሰብ ጥሩ ነው። በአኹኑ ተድላችን ክርስቲናችን አይመዘንምና። ጳውሎስ በክርስቶስ ለኾኑት "መከራና ስቃይ የለብንም" ለሚሉ ሃሰተኛዎች የመልስ መልስ ነው። ጳውሎስ "ለእኛ ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር" ማለቱ ይኽንን ክብር እየተጠባበቀ እንደኾነ ያስታውቃል ። ይኽንን ክብር ተስፋ ያደርጋል ።

“የፍጥረት ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃልና።” ሮሜ 8፥19 ።

ተከድነው ተሸፍነው የነበሩት እንዲታዩ ፣ ፍጥረት ይናፍቃል ፤ በናፍቆትም ይጠባበቃሉ ። የፍጥረት ናፍቆት የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው ። ምክንያቱም “ፍጥረት ለከንቱነት ተገዝቶአልና፥ በተስፋ ስላስገዛው ነው እንጂ በፈቃዱ አይደለም፤” ሮሜ 8፥20 ። በዚህ አውድ ፍጥረት የሚለው ቃል የሚወክለው ለከንቱነት ካለፈቃዱ የተገዛው ነው። የሰው ልጅ በበደሉ ስወድቅ ክብሩን ስያጣ፣ ለእርሱ የተሰጠውም ፍጥረትም ክብሩን አጥቷል ። ትክክለኛ እንደ አምላክ የኾኑ ገዥያቸው ያልወደቁ የሰው ልጆች ናቸው ።

ትክክለኛ ገዥያቸው ያጡት በምድርና በባሕር ያሉት ፍጥረታት ናቸው ማለት እንችላለን ። “እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው፦ ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም፤ የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው።” ዘፍ 1፥28 ። የሰው ልጅ ግን ከክብሩ ስወርድ የተሰጡት ፍጥረታትም በክፉ ዓለማውያን እጅ ላይ ወድቀዋል ። ነፃነታቸውን ክብራቸውን ይፈልጋሉ ፤ይጠባበቃሉ ፤ ወደ ክብራቸውም ለመመለስ ይናፍቃሉ ።“ተስፋውም ፍጥረት ራሱ ደግሞ ከጥፋት ባርነት ነፃነት ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን ክብር ነፃነት እንዲደርስ ነው።” ሮሜ 8፥21 ።

“ፍጥረት ሁሉ እስከ አሁን ድረስ አብሮ በመቃተትና በምጥ መኖሩን እናውቃለንና።” ሮሜ 8፥22 ። መግዛት ለማይገባው ርጎራጌ ለሌለው ለከንቱ ሃይል፥ ለአመጸኛው ተላልፈው የተሰጠው ፍጥረት፣ ነፃ አውጪ የኾኑ የእግዚአብሔር ልጆች እንዲገለጡ በናፍቆት ከመጠባበቅ ፣ እንድገለጡ በመቃተት በጭንቅና በስቃይ ውስጥ ኾኖ ይኖራል ። ስለ እኛ መንፈስ እንደሚቃትት ስለእነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች መገለጥ ምጥ ተይዞ በናፍቆት ይጠባበቃል ። ይኽንን ሚስጢር ከእኛ በላይ ፍጥረት ተረድተው የሚኖሩ ይመስለኛል ። የእኛ መክበር መድረስ ለፍጥረታት ጭምር እንደኾነ ማንስ አስተዋለ? ፍጥረታት በናፍቆት እየተቃታቱልን እንደሚጠብቁ ማንስ ተረዳ? ይኽ ታላቅ ነገር ምንድነው ? የዓለምን ኹኔታ የሚቀያየር ። የእግዚአብሔር ልጆች እስካሁን አልተገለጡም? እነማን ይኹኑ ?

እግዚአብሔር የሰው ልጅ ከወደቀ በኋላ አብርሃምን ጠርቶ በእርሱ በኩል አዲስ የራሱን ማህበረሰብ ለመሥራት ፈለገ። ከአብርሃምም እስራኤላውያንን አገኘ። ለእስራኤላውያንም ልጅነትንና ክብርን ሰጠ፤ ሮሜ 9። በእነርሱም ለፍጥረታት ያለውን ሃሳቡን በሥርዐት እንዲይዙ አሳሰበ፤ “ምድርም ለእኔ ናትና፥ እናንተም ከእኔ ጋር እንግዶችና መጻተኞች ናችሁና ምድርን ለዘላለም አትሽጡ።” ዘሌ 25፥23። እስራኤላውያን ግን ለራሳቸውም ኾነ በናፍቆት ለሚጠባበቁት ፍጥረታትም ነፃ አውጪ መኾን አልቻሉም ።

እግዚአብሔር በክርስቶስ ሞት የፀደቁትን በመንፈስ እየተመሩ ወደዚህ ክብር ነፃነት እንዲደርሱ እየሠራ ይገኛል ። ፍጥረታትም በተስፋ መገለጣቸውን እየተጠባበቁ ይገኛሉ ። ምክንያቱም ለእነርሱም የተነገረ ትንቢት አለ፥ " ተኵላ ከበግ ጠቦት ጋር ይቀመጣል፥ ነብርም ከፍየል ጠቦት ጋር ይተኛል፤ ጥጃና የአንበሳ ደቦል ፍሪዳም በአንድነት ያርፋሉ፤ ታናሽም ልጅ ይመራቸዋል። ላምና ድብ አብረው ይሰማራሉ፥ ግልገሎቻቸውም በአንድነት ያርፋሉ፤ አንበሳም እንደ በሬ ገለባ ይበላል። የሚጠባውም ሕፃን በእባብ ጕድጓድ ላይ ይጫወታል፥ ጡት የጣለውም ሕፃን በእፉኝት ቤት ላይ እጁን ይጭናል። በተቀደሰው ተራራዬ ሁሉ ላይ አይጐዱም አያጠፉምም፤ ውኃ ባሕርን እንደሚከድን ምድር እግዚአብሔርን በማወቅ ትሞላለችና።"ኢሳ 11፥6-11። የእግዚአብሔር ልጆች ስገለጡ እንዲህ ይኾናል።

በእግዚአብሔር ልጆች መገለጥ ተሳዳጅና አሳዳጅ አጥፊና ጠፊ የለም፤ ይጠፋል ፤ ኹሉም በሰላም ይኖራል ።አንበሳ እንኳን እንደ በሬ ሳር ይበላል ።አንዱ አንዱን በቀንዱ አይገነጠልም። ፍጹም ሰላም የኾነው የእግዚአብሔር አገዛዝ ነፃነት ይመጣል ። በእግዚአብሔር ልጆች መገለጥ ይኽ ይፈጸማል ። ይኽ ተስፋ ለፍጥረታቱ ጭምር አለ። ድንቅ ነው። ከማውቃቸው የተነሳ ስለእኛ በመቃተትና በምጥ ላይ ናቸው ። ዲያቢሎስ የአኗኗር ኹኔታውን ያበላሸው ለሰዎች ብቻ አይደለም ። የእግዚአብሔር ልጆች ወደ ክብራቸው ስመለሱ ከመጀመሪያው የሚበልጥ ክብርና ሕይወት ይጠብቃቸዋል ። ፍጥረታት ይኽንን አውቀው በምጥ ይኖራሉ ።ምጥ የዛሬ ጭንቀት ስኾን የአዲስ ብስራት አመላካች መከራ ነው፤ የሚወለዱ ልጆች አሉት፤ የሚገኙ ፤የሚገለጡ ልጆች።

የእግዚአብሔር ልጆች እነማን ናቸው ? ግና የሚገለጡ ። “በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና።” ሮሜ 8፥14 ። በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ልጆች ከኾኑ መገለጣቸው ወይም መታየታቸው ከመጀመሪያው የሚልቅ ልዩ እንደኾነ ያስታውቃል ።የፍጥረት ተስፋ በሐዋርያቱ እራሱ አልተፈጸመም፤ ተስፋን ሰጠ እንጂ። ጳውሎስ የፍጥረት ናፍቆት የሚፈጸምበት ጊዜ ግና እንደኾነ ያስገነዝበናል ። የእግዚአብሔር ልጆች እስከዛሬ አሉ፤ ግን በሙላት ጊዜው ደርሶ አልተገለጡም። የፍጥረት ተስፋም አልተፈጸመም ። ታዲያ የእግዚአብሔር ልጆች መገለጥ [መምጣት] መቼ ነው እነማን ናቸው !? ይኽ ጠንካራ ንባብ ነው።

ብዙዎች በራእይ 12 በተገለጠችው "ሴት" ትርጓሜ ቤተክርስቲያን እንደኾነች ይስማማሉ ። ባይስማሙም እውነቷን መካድ አይቻልም ። በክርስቶስ ድል ነስተው የሚያልፉ ምዕመናት "የሴቷን" ክብር ያገኛሉ ። ይህቺ ሴት ፀሃይ ለብሳ የተገለጠች ናት። በእግዚአብሔር መለኮታዊ ባሕርይ በቅድስና የተገለጠች ናት። ራእዩ "አዲስ ምልክት ታየ" ማለቱ አዲስ ክስተት ተአምር እንደኾነ ያስታውቃል ። አዲስ ክስተቱም በክብር መገለጧ ነው። የእግዚአብሔር ልጆች የኾኑ በፊትም ነበሩ፤ የእነዚህ መገለጥ ግን ሙላትን የሚገልጽ ነው። የዓለምን ታርክ የሚቀይሩ ፃድቃን ናቸው የተገለጡት። የሴቲቱ መገለጥ እንዲሁ ተነስቼ የእግዚአብሔር ልጆች መገለጥ ነው አላልሁም ። በሴቲቱ መገለጥ ምድር ሴቲቱን ስትረዳና ተስፋ የኾኑ

ልጆች በመምጣታቸው ፣ የዘንዶውን ማህበረሰብን ስትውጥ ስታጠፋቸው ስትረዳቸው ትታያለች። ምድር አስቀድሞውኑ ለሰው ልጆች የተሰጠች ናትና ፤ ወደ ክብራቸው የተመለሱ ጻድቃን መከራ የማያገኛቸው ስመጡ፣ ስገለጡ ትረዳለች። ምድር ለንፁህ ሰው ልጅ የተሰጠች ናትና፤ ዘንዶው ስያሳድዳት ትረዳለች። ለዘመናት የጠበቀችው ተስፋዋ ነውና።

ውድ አንባቢ ኾይ; በጭፍናምነት ሴቲቱ እስራኤል ዘሥጋ የኾኑ ናቸው የሚሉት ልመልሱ የማይችሉ ነጥቦች አሏቸው ። ሴቲቱ የተገለጠችው በታላቁ መከራ ሰዓት ነው፤ ሰይጣን ከሰማይ ወድቆ በታላቅ ቍጣ ለመዋጋት ለመውጋት በግልጽ በተሰለፈበት ጊዜ ነው። የሴቲቱ መገለጥ ሰይጣንን ከሰማይ እንዲወድቅ አድርጓል ። ይኽም የዓለምን ታርክ ወደ መገባደጃው ያፋጥነዋል ። ለጥቅት ጊዜ ብቻ ነውና የተፈታው ይረባረባል ። ይኽንንም ያንንም ያለውን ኹሉንም አቅም አሟጦ ይጠቀማል ። ሴቲቱ እስራኤል ዘሥጋ ናት የሚሉት፣ እስራኤላውያን በዚህ መከራ በመስዋዕትነት እንደሚያልፉ እንደሚገደሉ ያስተምራሉ ። ነገርግን ሰይጣን ከሰማይ ወድቆ ሴቲቱን ልያሳድዳት ስል፣ እግዚአብሔር ከሌላት ። በሰይጣን ሳትነካ ተጠብቃ ወደ በረሃ [መንፈሳዊ ስፍራ] ሸሸችሁ። ሰይጣን ልሰዋቸው ልደርሳቸው ስላልቻለ ከዘሯ የቀሩትን ልዋጋ ሄዷል። ስላልቻለ ተዋት ። እስራኤላውያን ብኾኑ እንደ አስተምህሮአቸው ሴቲቱ ልትሞት ሰማዕት ልትኾን ይገባት ነበር። በመከራ በስቃይ ማለፍ ይገባት ነበር። ግን ምስጢሩ ወዲህ ነውና በግምት ልደርሱ አልቻሉም ።

*በዚህ መከራ ስቃይ ጊዜ እስራኤል ዘሥጋ ኢየሱስን ይወልዳሉ ? ከዚያም ኢየሱስ ይነጠቃል ? ይኽ እውነት የሚመስል ትርጓሜ እንጂ ኢየሱስ አይወለድም ። ከቤተክርስቲያንም ከእስራኤልም አይገኝም ፤ የተወለደው ልጅ ከራእይ አውድ አንፃር ማየት መቻል አለብን ። ኢየሱስ አንዴ ብቻ ኹሉንም ለመጠቅለል ይመጣል ። ከላይ እንጂ የሚመጣው ቤተክርስቲያን ኾነ እስራኤል አምጣ አታስገኝም። የሚመጣው ታላቁ መከራ ስጀመር አይደለም ። ሴትቱ የወለደችው በሙላት ከተገለጠች በኋላ የሰይጣን ከወደ ምድር መጣል ጋር ተያይዞ ነው። ይኽም 3 ዓመት ከተኩል መከራ ጊዜ ነው። ታዲያ በዚያ መከራ ጊዜ ኢየሱስ ይመጣል ? አይመጣም ።አኹን በተለያየ መንገድ የሳትነው በቂ ነው። እዚጋር መቋጫ ማግኘት አለበት ። ራእዩ ለእኛ ነው።

ወንዱ ልጅ እስራኤል ዘሥጋ የወለዱት "ኢየሱስ ነው" ብሉም ግን ከአስተምህሮአቸው ጋር በፍጹም አይሄድም ። ምክንያቱም በመከራ ጊዜ ኢየሱስ ከተነጠቁ ቅዱስ ጋር በአየር ላይ ሠርግ ላይ ነው ይላሉ፤ የራእይ መጽሐፍ ደግሞ በመከራው ጊዜ ተገኝቶ ወይም ተወልዶ ይነጠቃል ይላል !?አይልም ።ይኽ በራሱ ቅልምድምድ የኾነ ሃሳብ እንደኾነ ያረጋግጣል ። ይመጣል የተባለው እንኳን በእነሱ ከሄድን በመከራው ጅማሮ ነው፤ ደግሞ እንደገና ይነጠቃል ? ስንተ ልነጠቅ ነው ኢየሱስ ? አንባቢ; ለራሶ ጊዜ ሰጥተው ያስቡ፤ያሰላስሉ ። መልእክቱ በግልጽ የሚታውቅበት ጊዜ አኹን ነው።

*በእግዚአብሔር ልጆች መገለጥ በሴቲቱ በጽድቅ መምጣት ፣ ከሰማይ ቅዱሳን መላእክት ሰይጣንን ይጥላሉ ። እርሱም ሴቲቱ ጸንሳ ስለነበረች መጀመሪያ ልጇን ለማጥፋት ፈለገ ፣ ነገርግን ሴቲቱ ወንድ ልጅ ወለደችው በአሕዛብ ላይ ስልጣን ያለውን ፣ ከዚያም ሰይጣን ሴቲቱን አሳደዳት ለማጥፋት የራሱን ማህበረሰብ አስነሳ ፣ ግን ጌታ ለዚህ ታላቁ መከራ ስፍራ አዘጋጅቶ ስለነበር ወደ ተዘጋጀላት ስፍራ እንድትገባ የሚያግዝ የንስር ክንፍ አስተማማኝ መለኮታዊ ሃይል ሰጣት፣ ሴቲቱም አመለጠች ምድርም ረዳች፤ የሚያሳድዷትን በመቅሰፍት ዋጠች። ሴቲቱ በታላቁ መከራ ተሰውራ ተጠብቃ 1260 ቀን ታሳልፋለች። መከራው አያገኛትም ። ሴቲቱ ክብርት ቅድስት ንፅህት ድል የነሳች ቤተክርስቲያን ናት።

ከዚህም በኋላ ሰይጣን ከዘሯ የቀሩትን ለመዋጋት ይመጣል ፤ ሴቲቱ የወለደችው ልጅ አሕዛብን በብረት ብትር የሚገዛ ነው፤ ከሴቲቱ ጋር አልተሸሸገም። አሕዛብን እየገዛ እየቀጠቀጠ ያገልግል ነበር። ለ1260 ቀን። ከዚያም በጌታ ይወሰዳል ። ነገርግን ከሴቲቱ ወይም ከወንድ ልጇ ጋር ያልኾኑ አማኞች ቅዱሳን የነበሩ ግን ያልነቁ ያልተዘጋጁ ፣ በዚያ በታላቁ መከራ ተታልለው ይወድቃሉ፤ ይጠፋሉ። “ቅዱሳንንም ይዋጋ ዘንድ ድልም ያደርጋቸው ዘንድ ተሰጠው፥ በነገድና በወገንም በቋንቋም በሕዝብም ሁሉ ላይ ሥልጣን ተሰጠው።”ራእይ13፥7።

አንባቢ ኾይ ቅድሜ መከራ ንጥቀት አስተምህሮ ከሰይጣን የመጣ ማደንዘዣ ነው የሚለው ለዚህ ነው። ሴቲቱ መለኮታዊ ፈተና ተቀብላ በድል የተወጣች ፣ ቤተክርስቲያን ስትኾን ፥ ወንድ ልጇ ደግሞ ለፍጻሜው አገልግሎት የተመረጡ አማኞች ናቸው ። ሰይጣን እነኚህን ኹለቱን ልቆጣጠራቸው አይችልም ። ወደዚህ ክብር እንዳትደርሱ "ከመከራው በፊት ትነጠቃላችሁ"፣ራእይ መጽሐፍ ም.4 ጀምሮ ቤተክርስቲያንን አያመለክትም፤ለቤተክርስቲያን የተጻፈ አይደለም በማለት፥መልእክቱን አውቃችሁ ተዘጋጅታችሁ የሰይጣንን መጥፊያ ገኸ ባለስልጣናት እንዳትኾኑና ደግሞም በመርዙ የበከላቸውን በቀላሉ ለማድቀቅ ያመጣው ትምህርት ነው። ዕሳቤ ብቻ ነው ችግር የለውም እያስባለ የድንዛዜ መርፌ በብዙዎች ላይ ወግቶ ይገኛል ። በታላቁ መከራ ጊዜ ከሚጠፉት እንዳትኾኑ ይኽንን የቅድሜ መከራ ንጥቀት አስተምህሮ በማወቅም ኾነ ባለማወቅም የተቀበላችሁት የተተባበራችሁት እንዲትጥሉ እመክራለሁ። ጆሮ ያለው ይስማ።

*ደግሜ እላለሁ ወዳጆቼ; ሴቲቱ እስራኤል ዘሥጋ የያዕቆብ ቤትን ያመላክታል የሚሉት ፣ ሴቲቱ በታላቁ መከራው እግዚአብሔር ባዘጋጀላት ስፍራ መከራው ሳይደርስባትና ሳይነዳት በጌታ ተጠብቃ እንደሚታሳልፍ ያስተዋሉ አይመስለም ። ምክንያቱም እስራኤላውያን በዚህ ታላቁ መከራ በሰማዕትነት ይድናሉ ፤መከራውን ይቀበላሉ ይላሉና። የሴቲቱ ትክክለኛው ትርጓሜ ግን እንደ ፊላደልፍያ ቤተክርስቲያን የተሰጣቸውን መለኮታዊ ፈተና በድል የተወጡ ነጭ የለበሱ፤ ማህበረ ምዕመናንን ወይም ማህበረ ቅቡዓን ቤተክርስቲያንን የምትገልጽ ናት ። ደግሞም የራእይ መጽሐፍ የትረካ መጽሐፍ; ገድል አስመስለው የሚተረጉሙት ሴቲቱ "ማርያም ናት" ይላሉ፤ደግሞም ሴቲቱን ያሳደደውም ዘንዶ "ሄሮድስ" ነው ይላሉ። ይኽም ሴቲቱን የሚያሳድደው ዘንዶ፣ ከሰማይ የወደቀና የተጣለ ዲያቢሎስ እንደኾነ አለማስተዋላቸውን ያረጋግጣል

።ምክንያቱም ሄሮድስ ከምድር ምድራዊ የኾነ ሰው ስኾን፣ የሴቲቱ አሳዳጅ ግን በሰማያዊ ስፍራ የነበረው ነገርግን በትዕቢቱ "በልኡል እመሰላለሁ" ያለው ዲያቢሎስ ነው። እግዚአብሔር ፊቱን ያብራላችሁ።

ማጠቃለያ

እነዚህ ሃሰተኞች ወደ መንግስቱ ለራሳቸውም አይገቡም፤የተመረጡትንም አያስገቡም። “እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ መንግሥተ ሰማያትን በሰው ፊት ስለምትዘጉ፥ ወዮላችሁ እናንተ አትገቡም የሚገቡትንም እንዳይገቡ ትከለክላላችሁ።” ማቴ 23፥13 ። ትውልድን እያወዛገቡ ይኖራሉ፤ ስያስቱ ይኖራሉ ። አይመለሱም ። ይኽንን የጻፍኩት ለሚሰሙት ጆሮ ላላቸው ብቻ ነው። ሰይጣን በመካከላቸው እንክርዳድ በመዝራት ስያወዛግብ በመኖሩ እንዲያመልጡ ነው፤ ከሐሰተኞች እጅ በመናጠቅ ለማትረፍ ነው።

ሰይጣን በስውር ሥሠራም ኾነ በግልጽ ሥሠራ ያው ነው። ቀድሞም የእግዚአብሔር ልጆች ስሰደዱ ስረሹኑ ነበር ። በዚህም መሃል ቤተክርስቲያን በድል አድራጊነት አልፋለች ።በግልጽ ተገልጾ ሥሠራ ደግሞም በመለኮታዊ ሃይሏ ከሃሳቡና ከአቅሙ በላይ ትኾናለች ። የሃሰተኛው መብዛት ነፃነት ማጣትና በዘንደው ማህበረሰብ መገለል፣ መሰደድ፣ መገደል፣ እንጂ ሌላ አይደለም ። ምክንያቱም በዚያ በታላቁ መከራ ሰዓት ወደዚያ የዘንደውን ማህበረሰብ የሚያስጨንቁ ብርቶዎች ወይራዎች እንደሚነሱ ተመልክተናል ።እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ በክፍል ኹለት በደንብ ስለ ሴትቷ ፣ስለ ታተሙት ቅዱሳን ፣ስለ እስራኤል መንፈሳዊ ትርጓሜ እንመለከታለን ።

በመጨረሻው ሰዓት ሰይጣን መላኩ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ዲያብሎስና ግብረአበሮቹን ከመንገድ ለማስወገድ ነው። ጌታ እንክርዳዱን ከስንዴው በመለየት ፣ እንክርዳዱን ኾነ ፍሬ ያላፈሩ ቅዱሳንን ለማስወገድ ይኽንን አድርጓል፣" ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ፥ የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው።ስለዚህም ምክንያት፥ በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ፥ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል።" 2 ተሴ 2፥9-12። ስለዚህ ባለማመናቸው ምክንያት ፍርድን እንዲቀበሉ ጌታ ይኽንን አድርጓል ።

ታዲያ የስውር ንጥቀት አስተምህሮና ትርኩቱ ዓላማው ምንድነው ? በስውር የሚሠራው አውሬ በግልጥ ለመሥራት ስመጣ አኹን ያለንበት ጊዜ በግልጽ እየመጣ መኾኑን አብስሯል፤አመላክቷል ። ታላቁ መከራ ለመጀመር ትንሽ ጊዜ ነው የሚቀረው ። ታላቁ መከራ መጀመሩን የእምነት ነፃነታችንን ስናጣ፣ የሙብት ሃገር ናት የተባለችው ባቢሎን ስታስገድድና ስትገድል ፣ሰው አባል ካልኾነ ምልክቱን ካልተቀበለ መግዛትና መሸመት ሳይችል ስቀር ፣ መጀመሩን በታላላቅ የምድር መናወጦችና መቅሰፍቶች እናውቃለን ። አኹን እርስበርስ እየተነታረክን በከንቱ መለፍለፍ ክርክር በማሳለፍ ጊዜው የሚናጠፋበት ጊዜ አይደለም ።መዳናችን ቀርቧልና ሃይልን ለመቀበል የትንቢቱን መልእክት እያስተዋልን ወደ ጎዳ የምንገባበት ሰዓት ነው። ስለዚህም የስውር ንጥቀት ኑፋቄ በስውር ለሚሠራው ደግሞም ለሚገለጠው ሃሰተኛው ነቢይ መንገድ ጠራጊ ነው።

መንገድን የሚጠርገው በዚህ በታላቁ መከራ ሰዓት ሃይልን ያልለበሱ አማኞችን ያደቅቃቸዋል፤ ያሸንፋቸዋል ፡፡ስለዚህ ከሚታተሙት መሃል እንዳትኾኑ ተግቶ ይሠራል ፡፡ በዚያ ሰዓት የተዘጋጁቱ በሙሴና በኤልያስ መንፈስ በአሕዛብ ላይ ሰልጥነው ፣በአፋቸው ቃል መቅሰፍትን እያመጡ ያገለግላሉ ፡፡ይኽን አውቃችሁ ወደዚህ እንዳትደርሱ ለእኛ የተጻፈው ራእዩ ለእስራኤል ነው በማለት አስተኝቷል፡፡ አንባቢ ሴትቱ የተባለችው የክርስቶስ እስራኤል እንደኾነች አውቃችሁ መለኮታዊ ባሕሪ ፀሐይን ጽድቅን እንዳትለብሱ በተለያየ ውሸት አስተምህሮ ጠፍሮ ይዞዋል ፡፡ አንባቢ ከተመረጡት ወገን ከኾኑ ወደ ጎዳ ይገባሉ ፡፡ከሚጠፉት መሃል ከኾኑ በእግዚአብሔር እውነት ላይ የራስዎ ኾነ የሰይጣንን ሃሳብ ስናገሩ ይውላሉ ፡፡ይኽ የመጨረሻው ዘመን ነውና አንለምን አንለማመጥም፡፡ የበጉ ፍርድ ቀን ደርሷል ፡፡ ስለዚህም መጽሐፍ “ዓመፀኛው ወደ ፊት ያምፅ፥ ርኩሱም ወደ ፊት ይርከስ፥ ጻድቁም ወደ ፊት ጽድቅ ያድርግ፥ ቅዱሱም ወደፊት ይቀደስ አለ፡፡” ራእይ 22፥11 ፣ እንደሚል እላለሁ ፡፡ ድል ነሽ ለመኾን ሃይልን ለመታጠቅ ከተያዙበት አብዘኛውን ጊዜ ከሚያጠፉበት ነገር በአስቸኳይ ይለዩ፡፡ወደ ጓዳም ይግቡ፡፡ የእግዚአብሔር ጸጋ ይብዛላችሁ ፡፡

ውድ አንባቢ ኾይ; አኹንም ቤተክርስቲያን በስውር ትነጠቃለች ብለው ያስባሉ ? አኹንም በስውር ጌታ ይመጣል፣ለሚወስዳቸው አማኞች ብቻ እየታየ ብለው ያስባሉ ? ይኽ ተራ የፈጠራና የዲያብሎስ ትምህርት ካለ አንዳች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ እውነት ነው ብለው ያምናሉ? ይኽ ተራ ትርክት እንደኾነ እስካሁን አልተረዱም ? መጽሐፍ ስለ ኢየሱስ ዳግም መምጣት ኹለቴ በማድረግ አያስተምርም ፡፡ መምጣቱ እንዴ ሌባ የተባለው ቀኑቱን ሳያሳውቅ መምጣቱን ለመግለጽ እንጂ በስውር መጥቶ በስውር ስለመውሰድ አይደለም ፡፡ መጽሐፍ አንድም ጊዜ ጌታ በስውር መጥቶ በስውር እንደሚወስደን አይናገርም ይልቁንም በግልጥ እንደሚመጣና አሕዛብ ኹሉ እንደሚመለከቱ ይገልጻል ፣“እነሆ፥ ከደመና ጋር ይመጣል፤ ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል፥ የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ፡፡ አዎን፥ አሜን፡፡” ራእይ 1፥7 ፡፡ ታዲያ እውነቱ እንዲህ ከኾነ የስህተትን ትምህርት ከማን ተማራችሁ? ማንስ ጨመረ ወይም ቀነሰ ከቃሉ? ሰይጣን አይደለምን !? ስለዚህም ወዳጆቼ ይኽንን እንዲታውቁ እወዳለሁ ፡፡ ኢየሱስ በግልጥ ዳግመኛ ይመጣል ፤ አሕዛብ ኹሉ ያለቅሳሉ ፤ፍርድ ይሰጣቸዋልና ፤ የተዘጋጀችው ሙሽሪት ግን ደስ ይላታል ፡፡ ከመከራው በኋላ በሕይወት ያሉት ይለወጣሉ ፣የሞቱትም ተነስተው አንድ ላይ ይሄዳሉ፤ ለዘንዶው እና ለማህበረሰቡ የዘላለም እሳት ይኾናል ፡፡ የመጨረሻ ይኾናል ፡፡ ለሙሽሪት ግን እርሱ ባለቤት ዙፋኑን ከበው ለዘላለም መኖርና መንገስ ይኾናታል፡፡ ለዚህ እንዲንበቃ በጌታ አብረን እንዲንሠራ አጥብቄ ከውሸት ትምህርት እንድታመልጡ እመክራችኋለሁ ፡፡

የራእይ መልእክት የተላከው ከእግዚአብሔር ለኢየሱስ ባሪያዎች እንዲደርስ እንጂ ለዮሐንስ ብቻ ወይም ለእስራኤል ብቻ የተሰጠ አይደለም ፡፡ባሪያዎቹ በደሙ የታጠቡ አገልጋዮች ናቸው ፤የዮሐንስ ወንድሞች ፡፡ ይኽንን ከመጽሐፉ ብንረዳ

በድፍረት የራእይ መጽሐፍን ለሥጋ እስራኤላውያን ብቻ አድርገን ባልተረጐምን ነበር። መልእክቱ 1ኛ. ከእግዚአብሔር ለኢየሱስ የተሰጠ ስኾን፣ ኢየሱስ ለባሪያዎቹ ለአገልጋዮቹ እንዲያደርስ የተሰጠ ነው። 2ኛ. ኢየሱስም መልእክቱን ለአገልጋዮቹ እንዲደርስ በመላአክ በኩል ወደ ዮሐንስ ላከ። 3ኛ. መላአኩም ከኢየሱስ የተቀበለውን ለዮሐንስ ሰጠው ። ይኽ እውነት ግና በምዕራፍ አንድ የተገለጠ ስኾን፣ ደኅና አንባቢ በቀላሉ ልረዳ ይችላል ፥ “ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባውን ነገር ለባሪያዎቹ ያሳይ ዘንድ እግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው በእርሱም የተገለጠው ይህ ነው፥ ኢየሱስም በመልአኩ ልኮ ለባሪያው ለዮሐንስ አመለከተ፥” ራእይ 1፥1 ። 4ኛ. ለዮሐንስንም መልእክቱ የተሰጠው ለአገልጋዮቹ ለባሪያዎቹ እንዲያደርስ ነውና ፣ ለኹሉም መሰከረ ። “እርሱም ለእግዚአብሔር ቃልና ለኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር ላየውም ሁሉ መሰከረ።” ራእይ 1፥2 ።ስለዚህም መጽሐፉ ለኹላችንም የሚያስፈልግ የእግዚአብሔርን መልእክት የያዘ እንጂ አንደኛው ተነጥቆ ለቀሩት ለሌሎች ብቻ ወይም ለእስራኤል ዘሥጋ የተጻፈ አይደለም ። ኹሉም ይጠብቁና ይሰሙ፣ ያነቡት ዘንድ ተሰጥቷል ።“ዘመኑ ቀርቦአልና የሚያነበው፥ የትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና በውስጡ የተጻፈውን የሚጠብቁት ብፁዓን ናቸው።” ራእይ 1፥3 ።

መጽሐፉ የዮሐንስን ራእዩን መቀበሉን ያመላክታል ፤ ራእይ መቀበል ብቻ ሳይኾን የተጻፈው ለእርሱም ጭምር እንደኾነ ይገልጻል ። ምክንያቱም ለዚህ እውነት መከራ ከአገልጋዮቹ ከወንድሞች ጋር የሚቀበል ነውና። ታዲያ ዮሐንስ ይኽንን ሰዎች ኹሉም ልሰሙ ልፈጽሙ ደግሞም ልያነቡት የሚገባ መጽሐፍ እንዴት መሰከረ? እንዴትስ ለባሪያዎቹ አዳረሰ? ስንል፣ የመጀመሪያ የመጽሐፉ ተደራሲያን 7ቱ አብያተክርስቲያናት እንደኾኑ እንረዳለን ። ምክንያቱም ዮሐንስ የሚመለከተውን ለ7ቱ አብያተክርስቲያናት በጽሑፍ [በጥቅልል መጽሐፍ] እንዲልክ የተሰጠ ነው። “እንዲሁም፦ የምታየውን በመጽሐፍ ጽፈህ ወደ ኤፌሶንና ወደ ሰምርኔስ ወደ ጴርጋሞንም ወደ ትያጥሮንም ወደ ሰርዴስም ወደ ፊልድልፍያም ወደ ሎዶቅያም በእስያ ወዳሉት ወደ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ላክ አለኝ።” ራእይ 1፥11 ። ስለዚህም መልእክቱ በ6ኛ. ደረጃ የደረሰው ወደእነዚህ አብያተክርስቲያናት እንደኾነ እንረዳለን ።

ከላይ እንደተመለከትነው መልእክቱ በሰዓቱ የነበረውን የቤተክርስቲያን ኹኔታ እና ግና ወደፊት በዓለም ላይ የሚኾነው የሚፈጸመውን እንደሚገልጽ አይተናል ። ዮሐንስ የሚያየውን ይጽፋል ፤የሚጽፈውንም የሚልከው ወደ እነዚህ አብያተክርስቲያናት ነው። ወደ እነዚህ አብያተክርስቲያናት የሚልከው ደግሞ አኹን ያሉበትን መንፈሳዊ ሕይወታቸውን [ኹኔታን] በጌታ ዓይን ስታይ ስመዘን ያለውን የሚገልጽ የሚያሳይ ነው፣ ደግሞም ወደፊት የሚፈጸመውን ትንቢት እየተጠባበቁ እንዲኖሩ የተላከ የተሰጠ የወደፊታዊ ትንቢት መልእክት ነው። ስለዚህም መልእክቱን ለተቀበለው ለጸሐፊው ለዮሐንስ; ከጌታ ከባሪያዎቹ የመጀመሪያ ተደራስያን የኾኑት እነዚያ አብያተክርስቲያናት ናቸው ማለት እንችላለን ።

ስለዚህም ራእዩ ሙሉውን በእስያ ላይ ለነበሩትን አሕዛብ እንደተጻፈ መረዳት እንችላለን ።በእነሱም በኩል በእግዚአብሔር ችሎታ ወደ እኛ ደረሰ ፤ የእግዚአብሔር ዓላማ መልእክቱን ለባሪዮቹ ኹሉ በማድረስ እንደተፈጸመ መረዳት እንችላለን ። እግዚአብሔር ይመስገን ።ይኸ መጽሐፍ ፤ይኸ መልእክት ፤ለዚያውም በአስቸኳይ ልንሰማው፣ ልናነበውና ልንጠብቀው የሚገባው መልእክት ወደ እኛ በመድረሱ ክብሩ ይስፋ ።

አኹንም እነዚያ ሃሰተኞች ልያስተኙን ልያጠፉን ቃሉን "የእኛ ነው ፤ለእኛ ነው" ብለን በማንበብና በመስማት ደግሞም በመጠበቅ ብፁዕ ፤የተባረከና በጌታ ሰላም ያለን እንዳንኾን ለማድረግ የሚሉትን ታምናለህ? አኹንም ልብህ መንታ ይኾንሃል? አኹንም አጥርተህ ማየት ይሳንሃል ? አኹንም ከሰይጣን እንደኾነ ትጠራጠራለህ ? መልእክቱ ከምንጩ ከአብ ወደ ኢየሱስ ከኢየሱስ ወደ መላእኩ ከመልአኩ ወደ ዮሐንስ ከዮሐንስ ወደ ባሪያዎቹ ወደ 7ቱ አብያተክርስቲያናት ከዚያም ወደ ዓለም ኹሉ ደረሰ።ስለዚህም ወደ እኛ የደረሰውን ቀጥተኛውን መልእክት እናገራለሁ፤ ዮሐንስ በጌታ መንፈስ ኾኖ እንደተናገረው ። ጆሮ ያለው ይስማ።

ውድ አንባቢ ኾይ በክርስቶስ ኾኜ እንደገናም እመክራለሁ ። ግር የሚል ወይም በክርስቶስ እውቀት ሃሳቡ ላይ የሚነሳውን የትኛውንም ሃሳብ አፈርሳለሁ ፤አንዳች ክፍተት እንዲኖር አልፈልግም፤አልሰጣቸውም ።ጌታ የሚሰጠኝን ኹሉንም እናገራለሁ ። ዮሐንስ በራእዩ ለኤፌሶን ወይም ለትያጥሮን ወዘተ. መልእክቱን ስያቀርብ የኤፌሶንን ብቻ ለኤፌሶን አልላከውም። ወይም የኤፌሶንን ለኤፌሶን ብቻ አልሰጠም። ይኸንን መረዳት መልካም ነው ። ስለዚህም በቀላሉ ለመረዳት ፣ አንደኛ ዮሐንስ ያየውን ለ7ቱ አብያተክርስቲያናት እንዲልክ መታዘዙን ማስተዋል አለብን፤ ይኸንን ከተረዳን ዮሐንስ የተመለከተው ከምዕራፍ 1 ጀምሮ እስከ 22 ያለውን ለ7ቱም አብያተክርስቲያናት እንደላከ እንረዳለን፤እንዲልክ ስለታዘዘ፣ ኹለተኛ. የእያንዳንዱ የቤተክርስቲያን መልእክቶች ሌሎችም ጭምር ለኹሉም እንደሚኾን እንረዳለን ።ምክንያቱም ለኤፌሶን አኹናዊ ኹኔታን የሚያሳየው መልእክት ፣ለኤፌሶን ብቻ የተሰጠ ሳይኾን ጆሮ ያለው ኹሉም እንዲሰማ የተሰጠ የተላከ ነው። ቀጥተኛው ለኤፌሶን ብኾንም ሌሎችም በዚህ መልእክት እራሳቸውን እንዲፈትሹ የተሰጠ መልእክት ነው፤ “መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ። ..።” [ራእይ 2፥7]፣ የሚለው ቃል ይኸንን ያረጋግጣል ። ለኤፌሶን ተናግሮ "ለአብያተክርስቲያናት የተላከውን መባሉ"ኹሉንም መልእክቶች ጆሮ ያለው እንዲሰማ መነገሩ፣ አንድም መልእክቱ ለኤፌሶን መኾኑን ስገልጽ ፣አንድም ኤፌሳናውያን የሌሎችንም አብያተክርስቲያናት መልእክት እንዲሰሙ የሚያሳስብ ነው፣ አንድም ኹሉም የዓለም አብያተክርስቲያናት ኹሉንም መልእክት የራሳቸው መልእክት አድርገው እንዲሰሙ መጋበዙ ነው፣ ራእዩ በዮሐንስ በኩል ለ7ቱ አብያተክርስቲያናት እንደተናገረው ፣ እነዚህም ለሌሎች አብያተክርስቲያናት መልእክቱን እንዲያዳርሱ እንዲያሰሙ የተሰጠ እንደኾነ ያስረዳል ።ይኸ የራእይ መጽሐፍ ;አይደለም የወደፊቱን ይቅርና [ከም.4 ጀምሮ ያለው] በሰዓቱ ለነበሩቱ አብያተክርስቲያናት የተላከው ራሱ፣ ለእነርሱ ብቻ የተጻፈ

እንዳይደለ እንድንረዳ ያደርገናል ። ስለዚህም አንድም መልእክት ሳይቀር ለእኛ ለሐዲስ ኪዳን ካህናት በበጉ ደም ለታጠብን አገልጋዮች እንዲደርስ የተሰጠ መኾኑን ልንገነዘብ ይገባናል ።

ውድ አንባቢ ኾይ ጌታ በስውር ቤተክርስቲያንን ነጥቆ ከከፍሎቹ ጋር ለጥቅት ዓመታት[ለ7 ዓመት] የበጉን ሰርግ እንደሚያደርግ የሚያስተምሩት ውሸት ፣የሰይጣን ትምህርት እንዲያስተውሉ ደግሜ ደጋግሜ እነግራለሁ ። አይታክተኝም ። ልናስተውል ከወደድን ወደ ሰርጉ የተመረጡት ኹሉ የሚገቡት እንጂ ከፍሎቹ ግማሾቹ ገብተው ሌላው ቀርቶ የሚደገስ በፍጹም አይደለም ። የሞቱት ተነስተው በስውር በሕይወት ያሉት ተለውጠው ፣ተነጥቀው ከእነርሱ ጋር ብቻ ሰርግ እንደሚደረግ ማስተማር በእግዚአብሔር ቃል ላይ በግምት ብቻ ሳይኾን በግልጽ መቃወምን የሚያሳይ ነው። አስተውሉ ።በራእይ ይዘት ጥናታችን ፣ የሞቱት ኢየሱስን እስከ መቼ በምድር ያሉት ላይ አትፈርድም ብለው ስጠይቁ፣ ጌታ እንደ እናንተ የሚሰው አሉና ታገሱ እንዳለ አይተናል ። " አምስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ፥ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ጠበቁት ምስክር የታረዱትን የሰዎች ነፍሳት ከመሠዊያ በታች አየሁ። በታላቅ ድምፅም እየጮኹ፦ ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ፥ እስከ መቼ ድረስ አትፈርድም ደማችንንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከ መቼ አትበቀልም? አሉ። ለእያንዳንዳቸውም ነጭ ልብስ ተሰጣቸው፥ እንደ እነርሱም ደግሞ ይገደሉ ዘንድ ያላቸው የባሪያዎች ባልንጀራዎቻቸውና የወንድሞቻቸው ቍጥር እስኪፈጸም ድረስ፥ ገና ጥቂት ዘመን እንዲያርፉ ተባለላቸው።" ራእ 6፥9-11። በዚህ ክፍል ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው ሰማዕታት ፍርድን ይለምናል ፣የእግዚአብሔርን ፍትህን ይጠይቃሉ፤ እግዚአብሔርም እንደ እነርሱ ሰማዕት ኾነው የሚሞቱ አሉና ትንሽ ታገሱ አላቸው ። አስተውል ይኽንን የሚለው ዝም ብዬ አይደለም ።

የሞቱ ሰዎች ፍትህን ስጠይቁ ፥ እግዚአብሔርም የፍትህ ጥያቄያቸው አግባብ እንደኾነ ተቀብሏል ።ግን ጥቅት ግዜ እንዲጠብቁ ነግሮአቸዋል። ስለዚህ የሚታተሙት ቍጥር እስኪሞላ እስኪፈጸም ድረስ እግዚአብሔር አይፈርድም ። አይፈርድም ማለት ኢየሱስ ሳይሞላ አይመጣም ማለት ነው። ጥያቄአቸውን ለመመለስ ጌታ ይሠራል ። የራሱ የኾኑትን ለመለየት የቅዱሳን ትዕግሥት የሚጠይቅ ፈተና ይለቃል ፣ በዚህ ፈተና የሚያልፉት የሚታተሙ ናቸው ።እነዚያ ታትመው ስያልቁ የፍትህ ጥያቄአቸው መልስ ያገኛል ። ስለዚህም ጌታ በራእይ መጽሐፍ እንደተገለጸው ታላቁን መከራ ይለቃል ፣ “ስድስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ አየሁ፥ ታላቅም የምድር መናወጥ ሆነ፥ ፀሐይም እንደ ማቅ ጠጕር ጥቁር ሆነ፥ ጨረቃም በሞላው እንደ ደም ሆነ፥” ራእይ 6፥12 ። ከዚያ መከራ የተነሳ ዮሐንስ ማንስ ልድን ይችላል ብሏል። “ታላቁ የቍጣው ቀን መጥቶአልና፥ ማንስ ሊቆም ይችላል? አሉአቸው።” ራእይ 6፥17። ዮሐንስ እንደፈራው ሳይኾን ታላቁን መከራ ሰማዕት የሚኾኑት እስኪታተሙ ድረስ ምድር እንዳትጠፋ ተደረገ፣ “የአምላካችንን ባሪያዎች ግምባራቸውን እስክናትማቸው ድረስ ምድርን ቢሆን ወይም ባሕርን ወይም ዛፎችን አትጕዱ አላቸው።” ራእይ 7፥3 ። እነዚህ ቅዱሳን

በዚህ ሰዓት የታተሙት ማንም ልቈጥራቸው የማይቻላቸው ናቸው ። ከታላቁ መከራ በደሙ የታጠቡ ናቸው ። ይኽንን ያነሳሁት ዝም ብዬ አይደለም ። የሞቱት ተነስተው በሕይወት ያሉት ተለውጠው ከመከራው በፊት ይነጠቃሉ ሰርግ ይደረጋል የሚባለው መርዝ በእግዚአብሔር እውቀት ለማፍረስ ነው። ምክንያቱም የሞቱት ሰማዕት እንደ አነርሱ ያሉትን ሰማዕታትን ይጠብቃሉ ፤ ጌታ ኹሉም ቅዱሳን ታትመው ስያልቁ፤ ስለዩ ይፈርዳል ። የምድር መጨረሻ ያደርጋል ። ስለዚህም ከመከራው በፊት የሞቱትን አይወስድም ፤ በሕይወት ያሉትንም አይወስድም ። በዚያ መከራ በደሙ ታጥበው ያልፋሉ ። ከዚያም ፍርዱን ያደርጋል ። መንግሥቱን ይቆጣጠራል ። እንዲህ ነው እንጂ ከታላቁ መከራ በፊት የሞቱትን በማስነሳት ፣ በሕይወት ያሉት በመለወጥ ፣ በስውር በመውሰድ ሰርግ አያደርግም ። የሞቱት ቅዱሳን ሌሎች እንደእነርሱ በታላቁ መከራ እስከሚሞቱ ጠብቁ ታገሱ አላቸው እንጂ አልወሰዳቸውም። ወይም ስለጥያቄአቸው ብሎ በሕይወት ያሉትን ለውጦ አልወሰደም ። በድሙ ታጥበው መስክረው እንደ እነርሱ እንዲያልፉ አደረገአቸው። እነዚህ ሃሰተኞች የዲያብሎስ ተላላኪዎች ይኽንን እንዳታውቁ አስቀድመው ለእናንተ አይደለም ፤ተነጥቃችኋል በማለት እንዳያነቡ ድንዛዜን ይረጫሉ። እወቁ።

ቤተክርስቲያን ከመከራው በፊት ትነጠቃለች ለማለት የሞቱት ይነሳሉ ፣በሕይወት ያሉት ይለወጣሉ የሚሉትን ስንመለከት ፣ሳይነጠቁ የቀሩትም እንደገና የሚነሱ በሕይወት ያሉትም እንደሚለወጡ ማስተማራቸው ፣ መጽሐፍ ቅዱስ አያውቅም ። ለዳነ አማኝ ትንሣኤ ኢየሱስ ነው። ሙታን ነበርን መጽሐፍ እንደሚል በኢየሱስ አዲስ ፍጥረት ኾኗልና ትንሳኤው ኢየሱስ ነው፤ ይኽ የመጀመሪያው ትንሳዔ ነው፤ ቀን ሳይኾን አካላዊ ቃል ክርስቶስ ነው። ይኽ መረዳት በፊት አልነበራቸውም፣ “ማርታም፦ በመጨረሻው ቀን በትንሣኤ እንዲነሣ አውቃለሁ አለችው።” ዮሐ 11፥24 ። ማርታ በኋለኛው [በመጨረሻ ቀን] ያለውን ትንሳኤውን ታውቃለች ።ምክንያቱም የብሉይ ቅዱሳን በመጨረሻ ትንሳኤ እንዳለ ያውቃሉ ።“በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉቱ ብዙዎች ይነቃሉ፤ እኵሌቶቹ ወደ ዘላለም ሕይወት፥ እኵሌቶቹም ወደ እፍረትና ወደ ዘላለም ጕስቍልና።” ዳንኤል 12፥2 ። እነዚህ ሃሰተኞች ግን ከ18 C ጀምረው ውሸትን አስተማሩ ብዙዎችን አሳቱ።

አንዳንዶቹ ይኽ መሠረታዊ ትምህርት አይደለምና የትኛውም እምነት ምንም ለውጥ አያመጣም ብለው ያስባሉ ።ምክንያቱም አሉ የተባሉ ባለቀለሞች ተወዛግበው አወዛግበውታል፣ ተወናብደው አወናብደውታል። የትኛዋ የእግዚአብሔር እውነት ትክክል እንደኾነች ማወቅ እንዳይቻል አድርገዋል፤ ሰይጣን በሰጣቸው ዝና እውቅና የብዙዎችን አፍ አስሯል ። እይታን ሰርቋል ፤አዕምሮ በርዘዋል።ለ7ቱ አሕዛብ ቤተክርስቲያን እንዲልክ የተጻፈውን፥ የራእዩን መልእክት ለእስራኤል ዘሥጋ እና ላልተነጠቁ አሕዛብ ነው የተጻፈው ከማለት በላይ? ራእዩ የተጻፈው እንዲልክና እንዲደርስ የተሰጠው አንደኛው ለባሪያዎቹ ለአገልጋዮቹ ስኾን፣ ኹለተኛው ለ7ቱ አብያተክርስቲያናት ነው፤እነዚህም አንድ ናቸው "አማኞች" ።

ለቤተክርስቲያን የተሰጠውን መልእክቱን ለቤተክርስቲያን አይደለም ፤ ቤተክርስቲያን ተነጥቃለች ብሎ ማታለል ፣መልእክቱ እንዳይደርስ ድንዛዜ መርጨት እንዴት እንዴ ተራ ዕሳቤ ይቈጠራል ? እንዲህ የሚሉቱን ለዘብተኛ ያደረጋቸው ፣ስለ ቃሉ እውቀት ትክክለኛ መረዳት አለማግኘታቸው ነው፤ በአግባቡ አለመብላታቸው ነው። ብበሉ ይጨክኑ ነበር። ዮሐንስ የዘላለም ወንጌል ከባለ በኋላ ውስጡ ጨካኝ ኾነ፤ እውነት ያስጨክናላ። “ከመልአኩም እጅ ታናሺቱን መጽሐፍ ወኑ ነበር። ስጇ በላኋት በአፌም እንደ ማር ጣፋጭ ሆነች፤ ከበላኋት በኋላም ሆዴ መራራ ሆነ።” ራእይ 10፥10 ።

በክርስቶስ ፍቅር በብዙ ትህትና ደጋግሜ እላለሁ ፤ ከሃሰተኛ አስተማሪዎች ፣ ነቢያት ፣ሐዋርያት ፣ወንድሞች፣ እረኞች ፣ ..ወዘተ. ራቁ። ከእግዚአብሔር የተላከው በኢየሱስ የወረደው ፣በመላአኩ የደረሰው ፣በዮሐንስ የተሠራጨው የእግዚአብሔር መልእክት በግልጽ ተጽፎ ተቀምጧል ። ይኽንን በማንበብ በመስማት በመጠበቅ እንኑር ። አዲስ መገለጥ ፣አዲስ ራእይ፣ አዲስ ትንቢት የለም። ትንቢትም ራእይም መገለጥም ይኽንኑ የሚያጸድቅ ብቻ ነው ያለው የሚኖረው ።ስለዚህም ይኽንን አውቃችሁ ለራሳችሁ ብላችሁ ጌታ የሚነግረኝ ምንድነው ብላችሁ ስሙ፣አንብቡ፣ ጠብቁ። አትቅበዘበዙ። በእግዚአብሔር ቃል እረፉ ። ዘመኑን እያወቃችሁ በማስተዋል ተጓዙ ። ካለ መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ጋር በኔትወርክ በስልክ እንገናኛለን ፣እናገናኛለን፣ ተገናኝተናል ከሚሉ ሐሰተኞች ራቁ። እግዚአብሔር የቅርብ አምላክ ነው በመንፈሱ የሚያዋራና የሚመልስ። ስለዚህ ባዶ በኾነው አዕምሮአችን ጌታ ቃሉን እንደሚያሞላና የእውቀትን ሽታ እንድኖር አዕምሮአችንን "እፍ" ብሎእንዲከፍትልን እንጸልይ ፤ የተማሩ የተባሉትም ተወዛጊበው ከማወዛገብ ሌላ ምርጫ የላቸውም ። የተኛው ትክክል እንደኾነ ግራ እስከሚገባን ድረስ አወናብደዋል። እድሜ ልካቸውን ቃሉን እያጠኑና እየመረመሩ ያልደረሱትን ያላወቁትን ጌታ ለተናቁት፣እዚህግባ ለማይባሉ እንዳሳወቅ አስተውል ።ዛሬም አንተን የሰማዩን እውቀት በግልጥ ሊያሳይ ሊሰጥህ ይችላልና መንፈሱን ጠይቅ እንጂ አታሳዝን። የእግዚአብሔር መንፈስ “የእግዚአብሔር መንፈስ፥ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ፥ የምክርና የኃይል መንፈስ፥ የእውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ..።”[ኢሳ 11፥2]፣ ነውና እንጠይቅ ። እግዚአብሔር ራሱም ያስተምራልና ከእርሱ ለመማርም እንትጋ ። በጸሎታችሁ አስቡን እንዲበረታና ክፍል ሁለትም እንዲቀጥል፡፡

ዋቢ መጻሕፍት


- መጋቢ ተኩ ከበደ፣ የቅዱሳን በአየር ላይ መነጠቅ፣የመጀመሪያው ዕትም 1999 ዓ.ም
- የራእይ ዮሐንስ ጥናት መጽሐፍ ፤አ.አ 2013 ዓ.ም
- ሐዋ ጌታቸው ታርኩ ሳህሉ ታላቁ መከራ በደጅ ነው ፤ግንቦት 3 2008 ዓ.ም አ.አ
- አዲሱ መደበኛ ትርጉም ማጥኛ፤ 2003 ዓ.ም
- ያረድ ዮሐንስ፣ድንቅ ፍጻሜ፣መስከ 2014ዓም ዕትም